አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በበና ፀማይ ወረዳ የበና ብሔረሰብ ዝርው ቃል ተረኮች ክዋኔ እና ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

ንዋይ ጌታሁን

2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በበና ፀማይ ወረዳ የበና ብሔረሰብ ዝርው ቃል ተረኮች ክዋኔ እና ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

ንዋይ ጌታሁን

2004 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በበና ፀማይ ወረዳ የበና ብሔረሰብ ዝርው ቃል ተረኮች ክዋኔ እና ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ

በ

ንዋይ ጌታሁን

2004 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

አማካሪ ዘሪሁን ገብረሥላሴ	ፊርማ .....
ፈታኝ የውስጥ	ፊርማ .....
የውጭ	.....

ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና I

የቃላት መፍቻ II

አጠቃሎ III

ካርታ የክልል V

ካርታ የዞን VI

ካርታ የወረዳ VII

1. መግቢያ 1

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2

1.2. የጥናቱ ዓላማ 2

1.3. የምርምር ጥያቄዎች 3

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ 3

1.5. የጥናቱ ወሰን 4

1.6. የአጠናን ዘዴና መረጃ አሰባሰብ 4

1.7. መረጃዎችን በፅሁፍ የመገልበጥና የመተርጎም ሂደት 6

1.8. የመስክ ገጠመኝ 6

1.9. ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎች 12

2. ክለሳ ድርሳን 14

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 14

2.2. የንድፈ ሃሳብ ቅኝት 22

2.2.1. የዝርው ቃል ተረክ ምንነት 22

2.2.2. የዝርው ቃል ተረክ ክዋኔ እና ዘዴ 24

2.2.3. የዝርው ቃል ተረክ ተግባር ቅኝት 30

3. የበና ብሔረሰብ አካባቢያዊና ማህበረ-ባህላዊ ዳራ 33

3.1. መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ 33

3.2. የበና ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ 34

3.3. ቋንቋ 36

3.4. ኢኮኖሚ 36

3.5. ጋብቻ 37

3.6. ሀገረሰባዊ ልማዶች 39

3.6.1. ባህላዊ እምነቶች 39

3.6.2. ባህላዊ ሕክምና 40

ARBA MINCH UNIVERSITY ILS LIBRARY

3.6.3. መዝናኛና ጨዋታ 41
3.7. ባህላዊ አስተዳደር 42
3.7.1. ቢታ 42
3.7.2. ቆጣ 43
3.7.3. ጉዲል 44
4. የበና ብሔረሰብ ተረኮች ክዋኔ 45
4.1. ተረኮች የሚተረኩባቸው መቼቶች 45
4.2. የትረካ (የአተራረክ) ሁነቶች 51
5. የበና ብሔረሰብ ተረኮች ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ 55
5.1. የ"ተረታ" ማህበረ - ባህላዊ ፋይዳ 55
5.2. - የ"ኤዔሪ" ማህበረ - ባህላዊ ፋይዳ 69
6. ማጠቃለያ 80
ዋቢ. መፅሀፍ 82
አባሪ 1 የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር
አባሪ 2 ለቃለ መጠይቅ የቀረቡ መነሻ ጥያቄዎች
አባሪ 3 የተረኮች ስብስብ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

የፎቶ ማውጫ

ርዕስ **ገፅ**

ፎቶ-1 ግራዝማች አድነው ጋርሾ የበና ማህበረሰብ 9ኛ ቢታ.....35

ፎቶ-2 ቢታው ከስሩ የሠፈሩበት የፔንቴ ተራራ 35

ፎቶ-3 የመኖርያ ቤት የምሽት አውድ (አባወራ ደምሴ በላቸው ከሁለት ሚስቶቹና ከአምስት ልጆቹ ጋር).....46

ፎቶ-4 ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት የትረካ መቼት.....49

ፎቶ-5 የፐርሲ መስተንግዶ ከሽምግልና አውድ በኋላ.....52

ፎቶ-6 አቶ ቡራ ሼሉ ተረክ ሲተርኩ.....53

ፎቶ-7 አቶ አልዲ ቢሮ ተረክ ሲተርኩ.....53

ፎቶ-8 ማዞች.....58

ፎቶ 9 የአፃ ስርዓት 58

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ምስጋና

መምህሬ እና አማካሪዬ የሆኑት ዘሪሁን አስፋው ውድ ጊዜያቸን ሰውተው ይህንን ጥናት መልክ እንዲይዝ ላደረጉልኝ ከፍተኛ ጥረት ምስጋናዬ የላቀ ነው። በመስክ ቆይታዬ ወቅት መረጃ በመስጠት የተባበራችሁኝ የበና ብሔረሰብ አባላት በሙሉ እና በትርጉም ስራውም ሆነ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ከመጀመርያ እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ ቀና የሆነው ትብብራችሁ ያልተለየኝ አንዱአለም ብዙነህ፣ አለኸኝ ውባለህ እና ጌቱ ጋርሾ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። ለዚህ ጥናት ለመነሻ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም ላመሰግነው እወዳለሁ።

በየትኛውም ነገር እንድበረታና ራሴን እንድችል ጠንካራ እንድሆን ከጎኔ ሆነህ ለምታበረታታኝ፣ ምን ጊዜም የኔ ሃሳብ እንዲሟላ ፈቃድህ የሆነው ውድ ባለቤቴ አበባው ስዩም(ባዬ)፣ ሁልጊዜም እኔ ትልቅ ቦታ ደርሼ ለማየት የምትመኘው አባቴ ጌታሁን ውድነህ፤ ህመምሽንና ድካምሽን ወደ ጎን ትተሽ የኔ ሃሳብ እንዲሳካ በደካማ አቅምሽ ልጁን ለማሳደግ ተቀብለሽኝ ያለሃሳብ እንድማርና የተሻለ ቦታ አንድደርስ ለምትጥሪልኝ እናቴ ሙሉአለም ሙላት እና እህቴ ፀዳለ ጌታሁን ውለታችሁ ለኔ ከባድ ነውና እግዚያብሔር እድሜና ጤና ሰጥቶ ብድሩን ይክፈላችሁ።

ሁለት አመት ሙሉ ድጋፋችሁ ሳይለየኝ ያስተማራችሁኝ ወንድሜ ምሳሌ ጌታሁን እና እህቴ መሰረት ክፍሌ (መሲሸዋ) ከአለኝታነታችሁ በተጨማሪ ከእናንተ ብዙ ነገር ተምርያለሁና ከላቀ ምስጋናዬም በላይ ውለታችሁን ለመክፈል ያብቃኝ። በተለይ መሲ ለኔ እጅግ ልዩ ሰው ነበርሽ እና እግዚያብሄር ያክብርልኝ።

ለመጀመሪያ ዲግሪዬን ለመማር ፈቃዳችሁን በጠየቅኩ ጊዜ ጀምሮ አሁንም ድረስ በሚመለከታችሁ ቦታ ሁሉ ቀና የሆነው ትብብራችሁ ያልተለየኝ ስጦታው ጋርሾ እና ወንዳፈራው ዳዊት፤ ይህንን ፕሮግራም እንድከታተል በጠየቅኩህ ሰአት በፍፁም ቀናነት እንድማር የፈቀድክልኝ ደሞ በዛብህ፣ በመስክ ቆይታ ጊዜዬ ለኔ እጅግ ጥሩ የነበራችሁ የአልዱባ ጤና ጣቢያ ሰራተኞች፣ በበና ፀማይ ወረዳ ውስጥ የምትገኙ ፅ/ቤት ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በሙሉ እጅግ አድርጌ አመሰግናችኋለሁ።

የወር ደሞዜን በመላክ ከጎኔ ያልተለየኸኝ ተስፋዬ አሰፋ(ዚጎ)፣ የዘወትር ማበረታቻችሁና ምክራችሁ ያልተለየኝ ታደሰ ተሾመ እና ተሾመ ታመነ፣ በርካታ የፅሁፍ ስራውን ጊዜሽን ሰውተሽ የረዳሽኝ ጊዜሽወርቅ ገዛኸኝ፣ እጅግ አመሰግናችኋለሁ።

የቃላት መፍቻ

በርቀንቴ በጋ በሆነ ወቅት ከብቶችን ውሃና የግጦሽ ሳር ወዳለበት አካባቢ ይዞ መሄድ።

ቦርኮታ ለመቀመጫ እና ለትራስነት የሚያገለግል ከእንጨት ተጠርቦ የሚሰራ ባህላዊ እቃ

ሾፎሮ ከቡና ገለባ ተፈልቶ የሚዘጋጅ ባህላዊ ቡና

ፐርሲ ከማሽላ፣ ከቦቆሎ እና ከዳጉሳ የሚዘጋጅ ባህላዊ መጠጥ

አፃ አንድ የበና ብሔረሰብ አባል የሆነ ወንድ ሙሉ ሰው ለመሆን ከከብት ላይ በመዝለል መፈፀም የሚገባው ባህላዊ ደንብ

ጋር በአፃ ጊዜ ከሚዘለልባቸው ከብቶች በመጀመርያ ደረጃ ላይ የምትቆምና ዘላዩ ወጣት ደንብ የሚሰራባት ጥጃ

ሞሳ የመጠሪያ ስምን ተመሳሳይ በማድረግ ዝምድና የሚፈጠርበት ባህላዊ ስርአት ለምሳሌ ደምሴ የሚባል አንድ ሰው የሚወደው ጎረቤት ጋር የበለጠ ለመቀራረብ የጎረቤቱን ልጅ ደምሴ የሚል ስም በመስጠት ዝምድና መፍጠር ነው።

ሚንጊ በቶሎ ካልተወገደ መአትን/ቁጣን የሚያመጣ ልጅ፤ አንድ የብሔረሰቡ አባል የብሔረሰቡን ባህላዊ ደንቦች እና ባህላዊ ስርአቶችን ሳይፈፀም የወለደው ልጅ

ሾርቃ አንድን የደረቀ ቅል በመስበር የሚዘጋጅ ሲሆን የበና ማህበረሰብ ሾፎሮ ለመጠጫ፣ ምግብ ለመብያ እና ለሴቶች ደግሞ እንደ ኮፍያ በመሆን ለፀሃይ መከላከያነት እና በዋነኛነት ደግሞ በበጋ ወቅት የጭሮሽ ውሃ ለመቅጃነት የሚውል በርካታ አገልግሎት ያለው ባህላዊ እቃ

ላጊ ላጊ ከሚባል እንጨት በመላጥ ለማሰርያነት የሚያገለግል ጥንካሬ ያለው የገመድ አይነት

ቢታ በናዎችን በባላባትነት የሚመራ የጎሳ መሪ

ቡኪ መንግስታዊም ሆነ አካባቢያዊ ስብሰባ

ጉዲል በበናዎች በሶስተኛ እርከን ላይ ያለ ባህላዊ አስተዳደር

ጠጲ ሚጫሬ አንድ የብሔረሰቡ አባል ብሔረሰቡ ቀይስ (ነውር) ነው የሚለውን ተግባር ሲፈፅም ቢገኝ ለምሳሌ ቢሰርቅ አቻዎቹ በሚሆኑ ጓደኞቹ በአርጩሜ የሚገረፍበት ባህላዊ የቅጣት ስርአት

አጠቃሎ

ይህ ጥናት በደቡብ ኦሞ ዞን ውስጥ በሚገኘው የበና ብሔረሰብ ዝርው ቃል ተረኮች ክዋኔ እና ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ ላይ ያተኮረ ነው። በብሔረሰቡ ባህል ነክ ጉዳይ ላይ እስካሁን ድረስ የተደረገ ጥናት አላገኘሁም። በተለይም በዝርው ቃል ተረኮች ላይ ጥናት ያለመደረጉ የጥናቱ ዋነኛ አነሳሽ ምክንያት ነው። ብሔረሰቡ እለት ተእለት በሚያደርጋቸው ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ የሚጠቀማቸው ዝርው ቃል ተረኮቹ የሚቀርቡባቸውን ክዋኔ እና እነዚህ ዝርው ቃል ተረኮቹ ለብሔረሰቡ ተወላጆች ያላቸውን ፋይዳ ማሳየት የጥናቱ ዋነኛ አላማ ነው።

በመሆኑም ክዋኔን ማእከል ያደረገ ስነ ዘዴን ከመጠቀም በተጨማሪ ተግባራዊ ስነ ዘዴን ለጥናቱ ተገልግያለሁ። መረጃዎችንም ተፈጥራዊ መቼት በመጠቀም ቃለ መጠይቅ እና የተሳትፎ ምልከታ በማድረግ በቴፕ ካሴት እና በፎቶ ካሜራ ሰብስቤያለሁ። ጥናቱንም ለመተንተን ገላጭ እና የይዘት ትንተና የጥናት ስልቶች አገልግሎት ላይ ውለዋል።

በጥናቱ መሰረትም የበና ብሔረሰብ በቃል የሚተላለፉ የተለያዩ ዝርው ተረኮች እንዳሉትና በአካባቢያዊ ምደባ መሰረት "ተረታ" እና "ኤዔሪ" ተብለው እንደሚጠሩ ታውቋል። "ተረታ" ብለው በሚተርኳቸው የተረክ ዘርፎች ውስጥ በፎክሎር ሳይንስ መሰረት እውነተኛ ታሪኮች እና የአፈታሪክ ይዘት ያላቸው ተረኮችን እናገኛለን። "ኤዔሪ" በሚሏቸው የተረት ምድቦች ውስጥ ደግሞ የፈጠራ ታሪኮች ሆነው የተረት እና የሃተታ ተፈጥሮ ይዘት ያላቸው ታሪኮች እናገኝባቸዋለን።


ብሔረሰቡ እነዚህን ተረኮች አዘውትሮ የሚተርክባቸው ውስን ማህበራዊ አጋጣሚዎች (የትረካ መቼቶች) ያሉት ሲሆን እነዚህም መቼቶች በመኖሪያ ቤታቸው ጥዋትና ማታ፣ በጉዲል የምረቃ ሥነ-ሥርዓት፣ በባህላዊ የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት ላይ፣ በበርቀንቴ ወቅት፣ በቡኪ እና የጠጲ ሚጫሬ ቦታዎች ናቸው። በነዚህ ቦታዎች እነደየአውዱ የ"ተረታ" ወይም የ"ኤዔሪ" ተረክ ዘሮች ሊተረኩ ይችላሉ።

ተረኮቹ ሲተረኩ ወይም ሲከወኑ የሚኖሩትን የክዋኔ ጉዳዮች ስንመለከት የ"ተረታ" ተረክ ዘሮች አብዛኛውን ጊዜ በእድሜ ከፍ ባሉ አባቶች እና ጎልማሳ ወንዶችና አዋቂ ሴቶች የሚተረክ ሲሆን የ"ኤዔሪ" የተረክ ዘሮች ግን ከልጅ እስከ አዋቂ ባሉ አካላት የሚተረክ ሁኖ እናገኘዋለን። የሴቶችን የተራኪነት ሚና ስንመለከት ግን ከቤት ውጭ ባሉ አውዶች ላይ ከወንዶች አንፃር

እጅግ አናሳ ሁኖ ነው የምናገኘው። ሌሎችን የክዋኔ መሰረታዊ ጉዳዮችን ስንመለከት ግን ማለትም መልእክትን፣ ታዳሚን፣ የአቀራረብ ሀሳችን፣ የታዳሚን ምላሽ፣... ወዘተ በእያንዳንዱ የተረክ መቼት ስር እና ለብቻ ተለይተው በጥናቱ ውስጥ በስፋት ተዳሰዋል።


ተረኮቹ ከማህበረ-ባህላዊ ፋይዳቸው አንፃር ሲታዩ ብሔረሰቡ ማንነቱን የሚያሳይባቸው ባህላዊ እምነቶቹን ያንፀባርቅባቸዋል። ተከታዩ ትውልድም የአባቶቹን ፈለግ ተከትሎ ሰናይ እና እኩይ የሚሏቸውን ባህርያት ለይቶ እንዲያውቅ እንዲከተል ጉልህ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ። በተጨማሪም ብሔረሰቡ በዙርያው ላሉና ከአቅመ-ና ከችሎታው በላይ ለሆኑ ተፈጥሮአዊ ጉዳዮች መልስ የሚሰጥበት፣ በድካምና በተለያየ ምክንያት የዛለ አእምሮውን የሚያዝናናበትና እግረመንገዱንም የሚያስተምርበት ቁልፍ መሳርያዎቹ መሆናቸው በጥናቱ ታይቷል።

የደቡብ ክልል ካርታ




MAP OF SNNPR STATE

የደቡብ አሞ ዞን ካርታ



የበና ፀማይ ወረዳ ካርታ



ምንጭ፡- የበና ፀማይ ወረዳ አርብቶ አደር ልማት ጽ/ቤት

1. መግቢያ

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ከሚገኙ 45 ብሔረሰቦች ውስጥ 16ቱ በደቡብ ኦሞ ዞን ስር ይገኛሉ። ከእነዚህ ከአስራ ስድስቱ አንዱ የበና ብሔረሰብ ነው። የበና ብሔረሰብ በበና ፀማይ ወረዳ ከሚገኙ የፀማይ እና የብራይሌ ብሔረሰቦች ጋር ይገኛል። በናዎች ቋንቋቸው በንኛ ሲሆን የተለያዩ ባሕላዊ ስርአቶች፣ እምነቶች፣ ደንቦችና ታሪኮች ባለቤት ናቸው። ከእነዚህም መካከል አፋዊ ዝርው ተረክ አንዱ ነው። ይህ ጥናትም የበና ብሔረሰብ አፋዊ ዝርው ተረኮች ክዋኔ እና ተረኮቹም ለተወላጆቹ ያላቸውን ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው።

ጥናቱ በጠቅላላ በስድስት ምእራፎች የተከፋፈለ ነው። ምእራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመረጃ አሰባሰብና የአጠናኑ ዘዴ፣መረጃዎችን በዕሁፍ የመገልበጥና የመተርጎም ሂደት፣ የመስክ ገጠመኝ፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ባጠቃላይ ዘጠኝ ንኡሳን ርእሶችን በቅደም ተከተል ይዟል። ምእራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን ሲሆን በዚህም የተዛማጅ ጥናቶች እና የንድፈ ሃሳብ ቅኝት ተደርጓል። በንድፈ ሃሳብ ቅኝቱ የዝርው ቃል ተረክ ምንነት፣ የዝርው ቃል ተረክ ክዋኔ እና ዘዴ እንዲሁም የዝርው ቃል ተረክ ፋይዳ ላይ የተሰጡ ብያኔዎች ተዳሰዋል።

ምእራፍ ሦስት ጥናቱ የተደረገበት የበና ብሔረሰብ አካባቢያዊና ማህበረ ባህላዊ ዳራ የተዳሰሰበት ነው። በዚህም ሰባት ንኡሳን ርዕሶች የተካተቱ ሲሆን እነሱም መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥ፣ ቋንቋ፣ ኢኮኖሚ፣ ጋብቻ፣ ማህበረሰባዊ ልማዶች እንዲሁም ባህላዊ አስተዳደር ናቸው። ምእራፍ አራት የበና ብሔረሰብ ተረኮች ክዋኔ የተቃኘበት ሲሆን ተረኮቹ የሚተረኩበት የትረካ መቼቶች እና የአተራረክ ሁኔታዎችንም አካቷል።

ምእራፍ አምስት የብሔረሰቡ ተረኮች ያላቸው ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ የተቃኘበት ነው። በዚህም በተረኮቹ አይነት ወይም ምደባ መሰረት ያላቸው ተግባር/ፋይዳ በዝርዝር ተገልጿል። የመጨረሻው ምእራፍ የጥናቱን ማጠቃለያ ሃሳብ ይዟል።

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ተወልጄ ያደግኩት ጂንካ ከተማ ሲሆን በስራ ምክንያት ግን በበና ብሔረሰብ መሀል ለ4 አመታት ያህል ቆይቻለሁ። እዚያ በነበርኩባቸው ጊዜያት ከብሔረሰቡ ተወላጆች ጋር በስራም ሆነ በማህበራዊ ህይወት ጥብቅ የሆነ ቀረቤታ ነበረኝና የብሔረሰቡን የተለያዩ ባህላዊ ስርአቶች፣ ልማዶች፣ የአኗኗር ዘይቤዎች፣... እመለከትና አደንቅ ነበር። ከዚህ ባሻገር ደግሞ በስራ ላይ በነበርኩባቸው ጊዜያት የምመለከታቸውና ይገጥሙኝ የነበሩ አንዳንድ ሁነቶች ምክንያታቸውን ለማወቅ ብችል እያልኩ እናፍቅ ነበር። እናም በወቅቱ በመጀመሪያ ዲግሪ የነበረኝ የፎክሎር እውቀት ብዙም የሚያወላዳ ስላልነበር ይህንን ለማድረግ የሚያስችል እውቀት ቢኖረኝ እል ነበርና አጋጣሚውንም አግኝቼ ወደዚህ ትምህርት ክፍል ስገባ ያንን የተመኘሁትን ነገር ለመፈፀም እድሉ እንደተፈጠረልኝ በማሰብ የጥናት ትኩረቴን በዚህ ብሔረሰብ ባህል ላይ ለማድረግ ወሰንኩ።

ነገር ግን ጊዜው ደርሶ ርእስ ለመምረጥ በተዘጋጀሁ ሰአት በየትኛው ጉዳይ ላይ መስራት እንዳለብኝ የተለያዩ መረጃዎችን ሳገላብጥና ከመምህራንም ጋር ስመካከር ከዚህ በፊት በብሔረሰቡ ላይ የተጠኑ ስራዎች እምብዛም ባለመኖራቸው ክፍተቶች እንዳሉ ተረዳሁ። እናም ለአሁኑ ብሔረሰቡ ያሉትን ቃላዊ ዝርው ተረኮች በተመለከተ ክዋኔያቸውን እና ለብሔረሰቡ አባላት ያላቸውን ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ መርምሮ ለማሳየት በማሰብ ጥናቱን በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ለማድረግ ተነሳሳሁ።

1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አበይ ዓላማ በበና ብሔረሰብ ውስጥ የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በማሰባሰብ ክዋኔያቸውን እና ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳቸውን መርምሮ ማሳየት ነው። ጥናቱ የሚከተሉት ንኡሳን አላማዎችም አሉት።

- በብሔረሰቡ ውስጥ ያሉና ብሔረሰቡ የኔ የሚላቸውን ዝርው ተረኮች ለይቶ መሰብሰብ፤
- ብሔረሰቡ ዝርው ቃል ተረኮቹን የሚተርክባቸውን ማህበራዊ ገጠመኞችን እና ሁነቶችን ገልፆ ማሳየት፤
- ተረኮቹ በሚከወኑበት ወቅት የሚኖረውን የተራኪውንና የታዳሚውን ሚና ለይቶ ማመልከት፤
- ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ለብሔረሰቡ ያላቸውን ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ ተንትኖ ማሳየት፤
- የብሔረሰቡን ዝርው ቃል ተረኮች በጥቂቱም ቢሆን ሰብስቦ በፅሁፍ ማስቀመጥ

1.3. የምርምር ጥያቄዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ መልስ የሚሰጥባቸው አበይት የምርምር ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የብሔረሰቡ ዝርው ቃል ተረኮች የሚቀርቡባቸው ዋና ዋና ማህበራዊ አጋጣሚዎች ምን ምን ናቸው?
2. ዝርው ቃል ተረኮቹ በብሔረሰቡ ውስጥ ሲከወኑ የሚኖረው ሁነት ምን ይመስላል?
3. በብሔረሰቡ የሚነገሩት ዝርው ቃል ተረኮች ለብሔረሰቡ ያላቸው የማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ ገፅታ ምን ይመስላል?
4. ተረኮቹ ለብሔረሰቡ የሚኖራቸው ግልጋሎት በምን ይገለፃል?
5. የተረኮቹ ፋይዳ (ግልጋሎት) በአሁኑ ወቅት ከምናየው የብሔረሰቡ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በቀዳሚነት ይዞት ከተነሳው አላማ አንፃር ስለ በና ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ አመለካከት፣ ማንነትና ምንነት በመግለፅ ረገድ ጠቀሜታ አለው። በተጨማሪም እንደማንኛውም ብሔረሰብ የበና ብሔረሰብ በውስጡ ያሉና ለዘመናት ሲከተሉት ለነበሩ (ለኖሩ) ችግሮቹ የመፍትሄ ሃሳብ በመጠቆም ረገድ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አምናለሁ። ማለትም ተረኮቹ ጠብቀውና አጽንተው ያቆይዋቸው የብሔረሰቡ ባህላዊ ስርአቶች እና እምነቶች ለዘመናዊው የሃገር ልማትና እድገት አስተዋፅኦ ተብለው ለሚታቀዱ ግቦች አመቺ የአፈፃፀም መንገዶችን ያመላክታሉና።

ለምሳሌ የትምህርት መፅሃፍ ዝግጅት ላይ መፅሃፎቹ የሚይዟቸው የምንባብ ፅሁፎች ብሔረሰቡ በሚያውቃቸው ባህሎች ቢዘጋጁ በትምህርቱ ዘርፍ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ማዳረስ ለሚለው አገራዊ እቅድ ስኬታማነት እንቅፋት እየሆኑ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ያስችላል። በመጨረሻም ስለ ብሔረሰቡ ለማወቅ ለሚፈልግ አካል አንድ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል።

1.5. የጥናቱ ወሰን

አፋዊ ተረኮችን የሚያጠኑ የፎክሎር ባለሙያዎች እንደየምርጫቸው የተረክን ታሪክ፣ የተረቶችን ቋንቋ፣ የአተራረክ ስልት፣ የገፀባህሪ አሳሳል፣ መዋቅር፣ ይዘት፣ የተራኪውን ሚናና ማንነት፣ የአድማጭ ተመልካችን ሚና፣ የተረትን የአደራረስ እና የአከዋወን ሂደት፣...ወዘተ በዝርዝርና በጥቅል ሊያጠኑ ይችላሉ (ፈቃደ አዘዘ 1991፡53)። እኔም በዚህ ጥናት የበናን ብሔረሰብ አፋዊ ዝርው ተረኮች ክዋኔ እና ፋይዳን ማሳየት ላይ ብቻ አላማ አድርጌ የተነሳሁ በመሆኑ ተረኮቹን በአይነት መመደብም ሆነ መዋቅራቸውን እና ሌሎችንም ነገሮች ለጊዜው አልተመለከትኩም። አፋዊ ተረኮቹ በሚከወኑባቸው መቼቶች ተገኝቶ በመሰብሰብ ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ በመፈተሽ መግለፅ ላይ ብቻ አተኩሪያለሁ።

ጥናቱ የተካሄደው ከ18ቱ የበና ቀበሌዎች በ5ቱ ብቻ ሲሆን እነዚህም የአልዱባ፣ የጉርዶ፣ የቦሪ፣ የሞርገላ እና የዲዚአማ ቀበሌዎች ናቸው። እነዚህም የተመረጡበት የየራሳቸው የሆነ ምክንያት አላቸው። በዋነኛነት የብሔረሰቡ አባላት በብዛት የሚገኙባቸው መሆኑ ተጠቃሽ ሲሆን ሌላው አፈ ታሪኮችን መሰረት ያደረገ ነው። የጉርዶ ቀበሌ በናዎች በአፈ ታሪካቸው በመጀመሪያ በበና ምድር ላይ የነበሩ (በእነሱ አባባል እዚሁ በና ምድር ላይ ከመሬት ፈለቁ) የሚሏቸው የ"ጋሲ"ሳላዎች መገኛ ታሪካዊ ስፍራ (ቦታ) በመሆኑ ነው። የቦሪ ቀበሌ ደግሞ የባላባቱ መኖርያ ከመሆኑም ባሻገር ጥንት የመጀመሪያው የበና ባላባት መጥቶ ያረፈበት የፔንቱ ተራራን የምናገኘው በዚሁ የቦሪ ቀበሌ ነው። አሁንም ቢሆን ባላባቱ እና ቤተሰቦቻቸው በዚሁ ተራራ ስር ነው የሚገኙት። ሞርገላ እና ዲዚአማም ከእነዚህ ቀበሌዎች አጠገብ የሚገኙ ሲሆን የአልዱባ ቀበሌ ደግሞ ለእነዚህ ቀበሌዎች አማካይ ስፍራ በመሆኑ ነው።

1.6. የአጠናን ዘዴና መረጃ አሰባሰብ

ይህንን ጥናት ለማድረግ የሚያግዙኝን የተለያዩ መረጃዎች ለማግኘት ካልአይና ቀዳማይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሜያለሁ። ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን በቤተመፃህፍት እና በተለያዩ ቦታዎች በመሄድ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር የሚዛመዱ ጥናታዊ ስራዎችን፣ የተለያዩ መፃህፍትን፣ ሰነዶችን፣ መፅሄቶችን፣... ወዘተ በማንበብ እና በመመርመር ሲሆን ቀዳማይ የመረጃ ምንጮችን ለማግኘት የቻልኩት ደግሞ የመስክ ጥናት በማካሄድ ነው። ከመስክ ላይ ያገኘኋቸውን መረጃዎችም በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ (Participant Observation) የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን በመጠቀም በድምፅ መቅረጫ እና በፎቶ ካሜራ አማካይነት እንዲሁም የፅሁፍ ማስታወሻ በመውሰድ ለመሰብሰብ ችያለሁ። በመቅረፀ ድምፅ አማካይነት በካሴት

የተሰበሰቡ መረጃዎችን ቅደም ተከተላቸው እንዳይዛባ እያንዳንዱ ካሴት በየገፁ ቁጥር፣ ቀን እና የመረጃውን አይነት ባጭሩ በመግፍ የተያዘ ሲሆን ባጠቃላይ 18 ካሴቶች አገልግሎት ላይ ውለዋል።

ጥናቱ የበናን ብሔረሰብ አፋዊ ተረኮች ክዋኔ እና ተረኮቹ ያላቸውን ወይም የሚያበረክቱትን ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ መርምሮ ማሳየት ቁልፍ ጉዳዩ በመሆኑ ተፈጥሮአዊ መቼቶችን ተጠቅሜያለሁ። በተጨማሪም ሰው ሰራሽ መቼቶችን በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። ባጠቃላይ ዝርው ተረኮችን ግለሰቦችን በመኖሪያ ቤታቸው በማግኘት፣ ሽምግልና ላይ በመገኘት፣ ቡኪ በመሳተፍ፣ የአፃ እና የጎሪ ስርዓቶችን በመታደምና መሰል ዘዴዎችን በመጠቀም አሰባስቤያለሁ።

በጥናቴ ወቅት በምገኝባቸው መቼቶች ሁሉ የተረኮቹን ክዋኔ እና ተግባርን በተመለከተ በተለያዩ ነጥቦች ላይ ጥያቄዎችን አቀርብ ነበር። በመሆኑም በወቅቱ መደበኛ የሆነ እና መደበኛ ያልሆነ የቃለ መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተግባር ላይ ውለዋል። በእነዚህ እና በሌሎችም የመረጃ አሰባሰብ መንገዶች የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ለጥናቴ ቁልፍ ምንጮች ይሆናሉ ብዬ ከመረጥኳቸው ሰዎች ጋር በመነጋገር በተለይም እኔ ከተመለከትኳቸው ነጥቦች በመነሳት ድምዳሜ ላይ የደረስኩባቸውን ጉዳዮች ደግሞ የእኔ አመለካከት ብቻ ሁነው የተሳሳተ አቅጣጫ እንዳይዙብኝ በማለት "በእርግጥም በብሔረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ላይ ይንፀባረቃሉ ወይ?" የሚለውን ተመልክተው ማስረጃ ሆነዉ እንዲያረጋግጡልኝ አልያም እንዲያርሙኝ እና በአንድ ጉዳይ ላይ የተሰጡ የተለያዩ ምላሾችን ተነጋግረው ወደ አንድ አቅጣጫ እንዲያመጡልኝ በሚል የቡድን ውይይት ዘዴን በጥናቴ ወቅት ተገልግየበታለሁ። በቡድን ውይይት የተሳተፉት 9 ሰዎች ናቸው። እነዚህም በአከባቢው ነዋሪ የሆኑ፣ በተለያየ ደረጃ ላይ ያሉ የብሔረሰቡ ተወላጆች እና በፖለቲካ አመራርነት በብሔረሰቡ መሃል ለረጅም አመታት ያገለገሉ ሲሆኑ በእድሜም ከ30 እስከ 90 ዓመት ባለ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

የተግባራዊ ንድፈ-ሃሳብ (Functionalism theory) አቀንቃኝ ምሁራን አንድ ፎክሎር ባለው ጠቀሜታ መመዘን አለበት ሲሉ ይመክራሉ። እናም ጥናቱ የቃል ተረኮችን ክዋኔ ከማሳየት በተጨማሪ ለብሔረሰቡ ያላቸውን ተግባር (ፋይዳ) ማመልከት በመሆኑ ክዋኔን ማእከል ያደረገን ስነዘዴ *(performance centered approach)* ከመጠቀም በተጨማሪ የተግባራዊ ስነዘዴን (Functionalism theory) መሰረት ባደረገ መልኩ የተሰራ ነው።

በተጨማሪም የጥናት ዘዴውን ስንመለከት ከላይ በጠቀስኳቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች የተሰበሰቡትን መረጃዎች በገለፃና በትንተና ዘዴ ቀርቧል።

1.7. መረጃዎችን በፅሁፍ የመገልበጥና የመተርጎም ሂደት

የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተርጎምና ለመገልበጥ የተከተልኩት መንገድ የሚከተለውን ይመስላል። የተጠኚ ብሔረሰቡ የመግባቢያ ቋንቋ በንኛ ሲሆን ይህ ቋንቋ በአካባቢያዊ ዳራ ላይ እንደገለፅኩት በፅሁፍ ተቀርፆ የዋለ የፅሁፍ ቋንቋ የለውም። ስለሆነም ተረኮቹ የሚተረኩት በበንኛ ቋንቋ በመሆኑ መረጃውን በመቅረፀ ድምፅ እና ማስታወሻ በመያዝ ስሰበስብ ቋንቋውን በሚገባ በሚያውቁ ሰዎች ወድያው ቃል በቃል እንደወረደ እና በነፃ ትርጉም እንዲተረጎም አድርጌያለሁ።

መረጃውን ስብስቤ እንደጨረስኩ ቃል በቃል እንደወረደ እና በነፃ ትርጉም ወደ አማርኛ የተተረጎሙትን የብሔረሰቡን ተረኮች ወደ ወረቀት በመገልበጥ ስራውን ጀመርኩ። በመቀጠልም በአማርኛ ተተርጉመው የተገለበጡትን ተረኮች እንደገና በማረም የሃሳብ ፍሰታቸውን ጠብቀው መነበብ እንዲችሉ ለማድረግ ዳግመኛ በመፃፍ ትንተና አድርጌያለሁ።

በዚህ ሂደት ግን የተረኮቹ ትርጉም እንዳይዛባ ሆነ ተፈጥሮአዊ ቀለማቸውን እንዳይለቁ ቋንቋውን በሚገባ በሚያውቁ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቼ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ የተደረገ ሲሆን ለተረጎመ የማይችሉትን አንዳንድ ቃላትና ሃረጎች ደግሞ በብሔረሰቡ ቋንቋ እንዳለ በማስቀመጥ ከጎኑ በቅንፍ ውስጥ በአማርኛ ሃሳቡ ተገልጿል።

1.8. የመስክ ገጠመኝ

ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ ለማዘጋጀት መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት በምሄድበት ቦታ ሁሉ ትብብር እንዲደረግልኝ በትምህርት ክፍሉ የተፃፈልኝን ደብዳቤ በ25/5/04 ዓ/ም ከትምህርት ክፍሉ ተቀበልኩኝ። በ6/6/04 ዓ.ም ከሁለት ቀን ጉዞ በኋላ ጂንካ ደረስኩኝ። በ12/6/04 ዓ.ም ሰኞ እለት ከትምህርት ክፍሉ የተፃፈልኝን ደብዳቤ ይገፍ ወደ ዞኑ አስተዳደር ጽ/ቤት ሄድኩኝ። በወቅቱም በስብሰባ ጉዳይ የምፈልጋቸው የስራ ሃላፊዎች እንደማይገቡ እና ሃሙስ በ15/6/04 ዓ.ም እንድመለስ ነግረውኝ ወደ ቤቱ ተመለስኩ።

በ15/6/04 ዓ.ም ጠዋት ላይ በቀጠሮዬ መሰረት ደብዳቤዬን ይዤ ወደ ዞኑ ምክትል አስተዳዳሪ ቢሮ ገባሁ። የዞኑ ምክትል አስተዳዳሪ የነበሩትም አቶ ስጦታው ጋርሾ ፍፁም ቀና በሆነ አቀባበል ተቀብለውኝ ጉዳዬን በጥሞና ካደመጡኝ በኋላ በሚችሉት ሁሉ ሊረዱኝ ሙሉ ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልፀውልኝ እና ለምሄድበት ወረዳ ጉዳዬን በመጥቀስ አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግልኝ ደብዳቤ ሰጡኝ።

ቀጠሮ ቀን ከዞኑ 42 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ወደምትገኘው የበና ፀማይ ወረዳ ርእሰ ከተማ ቀይ አፈር በወቅቱ በነበረው የበና እና የማሌ ብሄረሰብ የእርስ በርስ ግጭት ምክንያት የፀጥታ ችግር ነበርና አብዛኛው አመራሮች በወቅታዊው ጉዳይ ላይ ውይይት ላይ በመሆናቸው የወረዳው አስተዳዳሪንም ሆነ የወረዳው ባህል ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙንኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሃላፊዎችን ማግኘት አልቻልኩም ነበር።

በ22/06/04 ዓ.ም በወረዳው ርእሰ ከተማ የገበያ ቀን በመሆኑና በዙርያው ያሉ አርብቶ አደሮች ብዙዎቹ ወደ ቀይ አፈር ከተማ የሚመጡበት እና አብዛኛውን ጊዜ ባለጉዳይ የሚበዛበት እለት በመሆኑ ሁሉም ባይሆኑ አብዛኞቹ አመራሮች በተለይም አስተዳዳሪው በቢሮው መገኘት የተለመደ ተግባር ነበርና በዚያን እለት የምፈልጋቸው አካላት ስለነበሩ ከዞን የተሰጠኝን ደብዳቤ ይዤ ቀረብኩ። የመጣሁበትንም ጉዳይ አስረድቼ ወረዳው የተቻለውን ያህል እንዲተባበረኝ ጥያቄ አቀረብኩ። በዋነኝነት ለጥናቴ ወደመረጥኳቸው ቀበሌዎች ለመሄድ ለየቀበሌዎቹ የትብብር ደብዳቤ እና በውሰት መልኩ መቅረፀ ድምፅ፣ ካሜራና ሌሎችንም ነገሮች እንዲሰጡኝ ጠየቅሁ።

ነገር ግን በወቅቱ ሁሉም የወረዳው አመራሮች ትኩረት የሁለቱ ብሔረሰቦች ግጭት ተባብሶ ወደ ከፋ ደረጃ ሳይሻገር ባጭሩ የሚቀጭበትን መንገድ ከሚመለከታቸው ጋር ተቀናጅቶ ማስቆም ነበር፤ እኔም ተረጋግቼ ስራዬን ማከናወን የምችለው ሰላም ሲኖር በመሆኑ አሁን ትኩረታቸው ለፀጥታው ስራ እንደሆነ ተነግሮኝ ስራ መጀመር እችል ዘንድ ግን ለየቀበሌዎቹ የድጋፍ ደብዳቤ ከመሥጠት ውጪ ያሉ ሌሎች ድጋፎችን ወደፊት ባሉት የጥናቴ ጊዜዎች እንደሚያደርጉልኝ ገለፁልኝ።

ጂንካም ለሶስት ቀናት ያህል በመስክ ላይ እንደልብ ለመንቀሳቀስ የሚከራይ ሞተር ብስክሌት ሳፈላልግና ከቀለብ ጀምሮ አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮችን ሳዘጋጅ ቆየሁ። ወደ አልዱባ የመኪና ትራንስፖርት እንደልብ ለማለት በማያስችል መልኩ ያለ ሲሆን እኔ ግን

ለትራንስፖርት የመረጥኩት አማራጭ ሞተር ሳይክልን ነበር። ይህንንም ያደረግኩበት ምክንያት ደግሞ በጥናቴ የተካተቱት እንደ ዲዚ አማ፣ ሞርገላ፣ ጉርዶ እና ቦሪ የሚባሉ ቀበሌያት ከዋናው የመኪና መንገድ ወደውስጥ ከ10 ኪ.ሜትር በላይ መራቃቸውና መኪና በቀጥታ የሚያቋርጣት የአልዱባ ቀበሌ እንኳን በውስጧ የያዘቻቸው አራት ንኡስ ቀበሌያት መካከል ያለውን ርቀት ከአከባቢው ቆላማነት ጋር ተዳምሮ በእግር ለማዳረስ አስቸጋሪ በመሆኑ የሞተር ሳይክልን እገዛ በአማራጭነት መጠቀም የተሻለ ስለነበር ነው፤ የኪራይ ሞተር ሳይክል ማፈላለግ ግድ የሆነብኝ።

ለጭ በ26/6/04 ዓ.ም ጠዋት ላይ የብሔረሰቡን ቋንቋ በተወሰነ መጠን መናገር የሚችል ሞተረኛ ይገፎ ከጂንካ 63 ኪ.ሜትር ከቀይ አፈር ደግሞ 21 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ወደዳለችውና ለጥናቴ ከመረጥኳቸው የበና ቀበሌዎች አማካይ ስፍራ ላይ ወደምትገኘው አልዱባ ቀበሌ ጉዞ አደረግኩ። እንደደረስኩም በቀጥታ ከዚህ በፊት ቀይ አፈር በስራ ላይ እያለሁ የምግባባቸውና ብሔረሰቡን በሰለጠነበት የጤና ሙያ እያገለገሉ ወዳሉ የጤና ባለሙያዎች መኖርያ ቤት አመራሁ።

የምሳ ሰአት ነበርና የቤቱን ሙቀት ሸሽተው ከበራቸው ካለ ትልቅ የዛፍ ጥላ ስር ሰብሰብ ብለው ተቀምጠው ሲጨዋወቱ በመድረሴ ሲያዩኝ ሁሉም ከተቀመጡበት በመነሳት ተቀበሉኝ። ለድካም ማስረሻ ሆነ ሙቀቱን ለመቋቋም ጥሩ መሆኑን ነግረውኝ ሾፎሮ በሾርቃ ተሰጥቶኝ እየጠጣሁ እረፍት አደረግኩ፤ ከእረፍት በተጨማሪም ተንቀሳቅሶ ለመስራት ፀሃዩ በረድ እስኪል መጠበቅም ግድ ይል ነበርና እስከ 10:00 ሰአት ድረስበዛፉ ጥላ ስር ቆየሁ።

በእረፍት ሳለን ስለመጣሁበት ጉዳይ አንዳንድ ሃሳብ ከጤና ባለሙያዎቹ ጋር ተወያየሁ። የምፈልጋቸውን መረጃዎች የማገኝባቸውና መረጃውን የሚሰጡኝ አካላት ደግሞ ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚያስችል ሁኔታ አማርኛ መናገር ስለማይችሉ (አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ባለመሆናቸው) የምፈልገውን ጉዳይ ለነሱ በቋንቋቸው አስረድቶ ከእነሱ የማገኛቸውን መረጃዎች ደግሞ ወደ አማርኛ በሚገባ መተርጎም የሚችል፤ ወግ ባህላቸውን፣ ህይወታቸውን እንዲሁም አካባቢያቸውን ጠንቅቆ የሚያውቅ በእነሱም ዘንድ እውቅናና ጥሩ ተቀባይነት ያለው ሰው ፈልጎ የማግኘት የመጀመሪያውና ትልቁ ተግባሬ ነበር።

እናም ለዚህም ተግባር የሚስማማ ሰው ከዚህ ቀደም ከመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ጀምሮ አብሮኝ የተማረና ቀይ አፈር ተመድቤ ስሰራ በነበርኩባቸው ሁለት አመታት በደንብ የማውቀው

አንዱአለም ብዙነህ የተባለ ወጣት አልዱባ ጤና ጣቢያ ነርስ ሁኖ ያገለግል ነበርና እሱን አገኘሁት። አንዱአለም የ29 አመት ወጣት ሲሆን ቀይ አፈር ከተማ ተወልዶ ከማደጉም ባሻገር በተለያዩ ምክንያቶች ከልጅነቱ ጀምሮ ከብሔረሰቡ ጋር ከፍተኛ ቀረቤታ፣ እውቅናና ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ብሔረሰቡ በባህላቸው መሰረት የሞሳ ስም ሰጥተውት ዝምድና ፈጥሮ እንደራሳቸው ልጅ የሚያዩት ነው።

አንዱአለም በየቀበሌው መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ወሳኝ የሆኑ ሰዎችን ከመምረጥ ጀምሮ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት እንድችል የማግባባት፣ ቀጠሮ የማስያዝ እንዲሁም የሚገኙ መረጃዎችን አንድም ሳይቀር በጥራት ቃል በቃል ወደ አማርኛ የመተርጎሙን ስራ መስራት የሚችል ነበር። ከሱ ጋር ከተገናኘሁ በኋላ ፀሀይዋ በረድ ስላለች 10:30 ላይ ከወረዳው የፃፈልኝን ደብዳቤ ይዤ የአልዱባ ቀበሌ ሊቀመንበር ወደ ሆኑት አቶ ሳራ አይታ ጋ ሄድኩኝ። እሳቸውም በምን አግባብ መንቀሳቀስ እንዳለብኝ ከብሔረሰቡ ልማድ ጋር እያገናኙ ከነገሩኝ በኋላ ከአላማዬ አንባር ትክክለኛ የመረጃ ምንጮች ይሆናሉ ያሏቸውን ግለሰቦች ራሳቸውን ጨምረው ከነሰፈራቸው ለይተው ዘረዘሩልኝ። ሊቀመንበሩ አማርኛ በደንብ ይናገሩ ስለነበር ከሳቸው ጋር እንደልብ ለመነጋገር ችዬ ነበር።

የአቶ ሳራ አይታን ጥቆማ መነሻ በማድረግና ባለሙያዎቹም ካላቸው ቆይታ አንባር ሊረዱኝ የሚችሉ ሰዎች ናቸው ያሏቸውን ግለሰቦች በመተዋወቁ መረጃ መሰብሰብ ጀመርኩ። ብሔረሰቡ አርብቶ አደር በመሆኑ አሰፋፈሩ የተበታተነ ስለነበር ከአንዱ ግለሰብ ቤት ወደ ሌላው ግለሰብ ቤት ለመድረስ ረጅም ደቂቃዎችን በቀጭን የእግር መንገድ መጓዝ ግድ ይላል። ታድያ ለመረጃ ምንጭነት ከተጠቆምኩት መካከል አንዳንድ ታዋቂ ሽማግሌዎችን ማግኘት ባለመቻሌ ምክንያቱን ሳጣራ በማሌ እና በበና ብሔረሰብ መካከል በተፈጠረ ግጭት ቢታውን (ባላባቱን) ጨምሮ ከየቀበሌያቱ ሽማግሌዎች ተመርጠው ለእርቅ ግጭቱ ወደተፈጠረበት አከባቢ ከመንግስት አካላት ጋር ተቀናጅተው መሄዳቸውን ተነገረኝ።

አንዳንድ የመረጃ ምንጮቼ ከቦታው እስኪመለሱ ጉርዶ፣ዲዚ አማ፣ ቦሪ እና ሞርገላ ቀበሌያት በመሄድ እንደ አልዱባው መረጃ የማገኝበትን መንገዶች እያመቻቸሁና ወደ ግጭቱ ቦታ ካልሄዱ ግለሰቦች መረጃዬን እያደራጀሁ ቆየሁ።

እንዳገኛቸው ከተጠቆምኩት ግለሰቦች መካከል የብሔረሰቡ ቢታ ግራዝማች አድነው ጋርሾ ናቸው። ቢታውን ለማግኘት አስቀድሞ መተዋወቅና ቀድሞ ቀጠሮ መያዝ ግድ ነበርና ይህንን የማሳካበትን ዘዴ ማሰላሰል ነበረብኝ። ከቢታው ጋር ሊያቀራርቡኝ ይችላሉ ያልኳቸውን ሃሳቦች ሳወጣና ሳወርድ ቆይቼ ከቤተሰቤ ጋር የቅርብ ዝምድና የነበራቸውን አቶ ምንዬ ግዛውን ማግኘትና በእርሳቸው በኩል ቢታውን መቅረብ የሚለው ሃሳቤ ሚዛን በመድፋቱ በአካልም ይሁን በስልክ እሳቸውን የማገኝበት አማራጮች ላይ አተኮርኩ።

አቶ ምንዬ ግዛው ነዋሪነታቸው ጂንካ ከተማ ሲሆን እኔ ጥናቴን በማደርግባቸው ቀበሌያት ከሁለት አሰርት አመታት በላይ በክብት ንግድ በመቆየታቸው ከማህበረሰቡ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አላቸው። ከህፃን እስከ አዋቂ ባሉ የማህበረሰቡ አባላት ይታወቃሉ። ሞጎ* በሚባለው የማህበረሰቡ የስም አወጣጥ ልምድ ምንዬ በሚል ስም የሚጠሩ ወጣቶችና ህፃናት ይገኛሉ። ታድያ ረቡዕ በ28/6/04 ዓ.ም በበነጋው ሐሙስ ቀይ አፈር ላለው ሰፊ ገበያ እንደመሸጋገርያ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ ግብይት አልዱባ ይካሄድ ነበርና አቶ ምንዬ ግዛውን ብዙም ሳልቸገር ገበያ ላይ አፈላልጌ አገኘኋቸው። እሳቸውም ሃሳቤን በደስታ ተቀብለው ጊዜ ሳያጠፉ ፈጥነው ወደ ትንሿ የአልዱባ ገበያ የመጡ የቢታው ልጆችን አፈላልገው በማግኘት በሳምንቱ ረቡዕ እንግዳ ይዘው ወደ መኖርያ ቤታቸው እንደሚመጡ መልእክት በመላክ ቀጠሮ አስያዙልኝ።

ከተያዘልኝ የአንድ ሳምንት ቀጠሮ በኋላ ካለሁበት አልዱባ 9 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ የቢታው መኖርያ ወደሆነችው ቦሪ ቀበሌ ከአቶ ምንዬ ግዛው ጋር በሞተር ሳይክል አመራን። ቢታውና የቤተሰቦቻቸው መኖርያ ጥንት አያት ቅድመ አያቶቻቸው ወደ በና ምድር በመጡ ጊዜ ከሰፈሩበት የፔንቴ ተራራ ስር ሲሆን ከዚያ ለመድረስ ሞተር ሳይክል አቁሞ በእግር የአንድ ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ መንገድ መጓዝ ነበረብንና አቀበታማውን መንገድ በእግር ተጉዘን ነበር ከመኖርያቸው የደረስነው። እድሜያቸውን እሳቸው በውል ባያውቁትም ማህበረሰቡ ግን ከ90 ዓመት በላይ እንደሆናቸው የሚገመቱት ቢታ ግራዝማች አድነው ጋርሾ በበራቸው ካለ ዛፍ ጥላ ስር ቆዳ ጣል ተደርጎላቸው ተቀምጠው በቀጠሮአችን መሰረት የኛን መምጣት እየተጠባበቁ ነበር።

አቶ ምንዬ ግዛው ጉዳዬን አስረድተው ካስተዋወቁኝ በኋላ እኔም እንደደንቡ ለቢታ ከሚቀርብ ስጦታ መካከል ነጭ አረቄ ስጦታ አቀረብኩላቸሁ፤ ሁለት እጆቼንም ዘርግተው ከአረቄው ላይ ፉት በማለት ፈፂ (ምርቃት) ሰጡኝ። በዚህ መልክ ከሳቸው ጋር ከተዋወኩኝ በኋላ በተደጋጋሚ ጊዜ ከቤታቸው እየተመላለስኩ የምፈልጋቸውን መረጃዎች አገኘሁ።

በተመሳሳይ መልኩ የመረጃ ምንጮቼ የሆኑ ሌሎች ግለሰቦችንም ለማግኘት ከንጋት 12:00 ሰአት በፊት ከብቶቻቸውን ይዘው ወደ ግጦሽ ለመውጣት ካላቸው መጣደፍ አንጻር በተረጋጋ ሁኔታ መረጃ ማግኘት ስለማይቻል ምሽት ከብቶቻቸውን በረት ካስገቡ በኋላ ማግኘት ዋነኛው አማራጭ በመሆኑ ምሽት ከ 1:00 ሰአት በኋላ ወደ መኖርያ ቤታቸው በማምራት እስከ ምሽቱ አምስትና ስድስት ሰአት እየቆየሁ አንዳንዴም እያደርኩ መረጃ አሰባስብ ነበር። ለዚህ ደግሞ አስተርጓሚዬ ከእነሱ ዘንድ የነበረው ቀረቤታ ለኔ ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር ባሻገር ከማህበረሰቡ ጋር በቀላሉ እንድግባባ ረድቶኛል። ይህ የምሽት ቆይታዬ እና አዳሬ መረጃዎችን ከማሰባሰብ ጎን ለጎን በብሔረሰቡ የሚከወኑ የተለያዩ ባህላዊ ስርአቶችን እንድመለከት ረድቶኛል። የአፃ ስርአት፣ ጠጲ ሚጫሬ፣ ጎሪና ኢቫንጋዲ ከተመለከትኳቸው ስርአቶች መካከል ይገኙበታል።

በቀበሌያቱም ጠቅላላ የነበረኝ የ41 ቀን ቆይታ አብሮ በማምሸትና በአዳር መታገዙ ከማህበረሰቡ ጋር ይበልጥ እንድቀራረብ ስለረዳኝ አንዳንዶች ከስራዬ ጋር ተያያዥ የሆነ ስም አውጥተውልኝ ገና ሲያዩኝ "ተረታ" መጣች ይሉኝ ነበር። ተረታ የማህበረሰቡ አንድ የተረክ አይነት ሲሆን ከዚህ ጋር አያይዘውም ነበር ተረታ የሚል ስም ያወጡልኝ። በምሽት ወጣ ገባውን ተከትሎ በእግር ጉዞ ከመውጣት መውረድ በተጨማሪ ከቀጭኗ የእግር መንገድ ዳርና ዳር ያሉትን የበረሃ እሾህ መጠንቀቅና አንዳንዴም መወጋት ነበርና ይህንን ትዕግስት ፈታኝ ሂደት በጥንካሬ አልፌ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ።

በግለሰቦች መኖሪያ ቤት በመዟዟር መረጃዎችን ከማሰባሰብ በተጨማሪ አውዶችን በመጠቀም መረጃ ማግኘት ሌላው ተግባሬ ነበር። ከተመለከትኳቸው የተለያዩ አውዶች በቦሪ ቀበሌ የነበረውን ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት በዚህ ገጠመኜ አነሳለሁ። በ 24/7/04 ዓ.ም 10:00 ሰዓት ላይ ነበር ወደዚህ ቦታ የተጓዝኩት። ዳኝነቱን የሚመሩ 13 ሽማግሌዎችና በርካታ ወጣቶች የነበሩበት ይህ አውድ አጥፊንና ተጎጂን በተረኮች አጋዥነት ገስጾው፣ መክረውና ቀጥተው ሲያበቁ እኔ በፍጥነት ወደ ሽማግሌዎች ቀርቤ በአስተርጓሚዬ አግባቢነት አላማዬን

ስገልጽላቸው ቤት ለቤት ተሟዙሬ መረጃ ሳሰባስብ ያወቁኝ ነበሩና ሀሳቤን ወድያው ተቀብለው ወጣቶቹ ባሉበት ስርዓት ይዘው እንዲቀመጡና እንዳይበታተኑ ሸማግሌዎች አዘዙ።

ከሸማግሌዎች ዕድሜያቸው 70 ዓመት እንደሆነ የሚገምቱት የዕድሜ ባለጸጋው አቶ አርባ ቱርኬ ቀጠል አድርገው የማህበረሰቡ አንዳንድ ወጣቶች ታሪክ አንጠይቅም፣ አንሰማም ብለው ባሉበት እኔ ጆሮዬን ሰጥቼ እነሱን ለማዳመጥ ካሉበት ድረስ መምጣቴን አወድሰው በባህላዊ ምረቃ ማለትም እኔን ወደፊት በማስቀደም ሁላችንም ተነስተን ፊታችንን ወደ ምስራቅ አዙረን እንድንቆም ተደርጎ ሸማግሌዎች ፊጹ ሰጥተውኝ ውይይታችንን አስጀመሩት። እዚህ ላይ ወደ ምስራቅ ፊታችንን ማዞራችን የፀሐይ መውጫ በመሆኑ ፀሐይ በወጣች ቁጥር መልካሙን ሁሉ ይዛልኝ እንድትወጣና ስራዬም የተቃና እንዲሆን፤ እና ጀርባችንን ለምዕራብ መስጠታችን ደግሞ ክፉውንና የስራዬ እንቅፋቶችን ፀሐይ ከኔ በማራቅ ይዛ እንድትጠልቅ የሚል ትርጓሜን የያዘ ነበር።

ይህ መረጃ የማግኛ ዘዴ የአውዱ ታዳሚዎች አማካይ በሆነ ዛፍ ጥላ ስር የሚገኙ በመሆኑ እንደቤት ለቤቱ ድካምን የማይጠይቅ ቢሆንም ከአከባቢው ቆላማነት አንፃር የቀትሩን ፀሐይ መቋቋምና ማህበረሰቡም በባህሪው ነገሮችን በእርጋታ ስለሚመለከታቸው እስከፍፃሜው ረጅም ሰዓታትን ታግሶ መቆየት አስፈላጊ ነበር።

1.9. ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎች

በጥናቴ ሂደት የተለያዩ ችግሮች ቢገጥሙኝም እንደየ ችግሮቹ አይነትና ስፋት መፍትሄ በማፈላለግ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ችያለሁ። ካጋጠሙኝ ችግሮችና ከመፍትሄ ተግባሮቼ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፦

- ተጠራጣሪነት በመጀመሪያው ደረጃ ይቅሳል፤ ለምሳሌ አደንና ሌሎችም በዚህ ወቅት በህግ የተከለከሉ ተግባራትን የያዙ ተረኮችን ብንነግራት በኋላ ለበላይ አሳውቃ ሌላ ችግር ትፈጥርብናለች በሚል ፍራቻ አንዳንድ ተረኮችን ለመተረክ ፈቃደኛ አለመሆን የነበረ ሲሆን በአስተርጓሚዬ አማካይነት የፈጠርኩት መቀራረብ ትክክለኛውን ዓላማዬን እንዳሰርጽ ስለረዳኝና መተማመንም ስለፈጠረልኝ ይህን መሰል ይዘት ያላቸው ተረኮችን ማሰባሰብ ችያለሁ፤
- ተረኮች በባዶ አፍ አይነገሩም ስለሚባል በግለሰብ ደረጃ መረጃ ሳሰባስብ ለግለሰቡ፣ በቡድን አውድ ላይ ከሆነ ደግሞ ለአውዱ ታዳሚዎች የፐርሲ መግጥ ገንዘብ መስጠት ነበረብኝ።

ይህ ደግሞ ከነበረኝ የገንዘብ አቅም አንፃር አስቸጋሪ ነበር። እዚህ ላይም አስተርጓሚዬ የነበረው ሰፊ ተቀባይነት እኔም በማህበረሰቡ ውስጥ ለበርካታ ቀናት ውዬ ሳድር ያዳበርኩት መግባባት በቀላሉ በሩን ስለከፈተልኝ ለደንቡ ያህል አድርጋለች እንዲባል ለፐርሰ. መግጥ መክፈል ከነበረብኝ ጥቂት ገንዘብ ብቻ በመክፈል መረጃዎችን አሰባስቤያለሁ፤

- የበናና የማሌ ብሔረሰብም የእርቅ ሁኔታ ቀጠሮዎች እየተያዙለት እዚያ እስከቆየሁባቸው ቀናት ባለመቋጨቱ ምክንያት መረጃ ሊሰጡኝ ቀጠሮ ያስያዙኝ አንዳንድ ግለሰቦች መኖርያ ቤት በቀጠሮዬ መሰረት ረጅም ርቀት በእግር ገዞ አቋርጬ ስደርስ ግለሰቦቹ ወደ ግጭቱ ቦታ ለእርቅ ተጠርተው እንደሄዱ ተነግሮኝ እመለስ ነበር። ሆኖም የእግር ገዞው አድካሚ ቢሆንብኝም አላማዬ ብርታት ሆኖኝ የማገኛቸውን ቀን ጠብቄ በተደጋጋሚ ወደ መኖርያ ቤታቸው በመሄድ አላማዬን አሳክቻለሁ፤
- በጠዋት ለግጦሽ ይዘው የወጡትን ከብቶቻቸውን ምሽት ይዘው ስለሚመለሱ በቀን መረጃ ማሰባሰብ ብዙም ውጤታማ ባለመሆኑ ምሽት ከ1፡00 ሰዓት በኋላ ወደ መረጃ ምንጮቼ መኖርያ ቤት ማምራት ግድ ይለኝ ነበር። ታድያ አስፈላጊውን መረጃ ወስጄ ሳበቃ የምሽቱ ሰዓት ወደ 5፡00 እና 6፡00 ሰዓት ስለሚደርስ ወደ ማደርያዬ ለመመለስ የማደርያ ቦታዬ ርቀት፣ የምሽቱ ሰዓት መግፋት እንዲሁም ገዞው በእግር መሆኑ ከሴትነትጋር ተዳምረው እንቅስቃሴዬን አክብደውብኛል። ሆኖም ምሽቱ በጣም የገፋና ድቅድቅ ጨለማ በሆነ ቀናት እዚያው በማደር፣ ቢመሽም ጨረቃ በደመቀባቸው ቀናት ደግሞ ወደ ማደርያዬ በመመለስ ተግባሬን ተወጥቻለሁ።

2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምእራፍ በመጀመሪያ በርእሰ ጉዳዩ ላይ የተደረጉ ተዛማጅ ጥናቶችን ቅኝት የማደርግ ሲሆን /የማጠናውን ርእሰ ጉዳይ በተመለከተ ሊነሱ የሚገባቸውን ንድፈ ሃሳባዊ እስቦችን እዳስሳለሁ።

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ጥናት በአቢይነት የሚያተኩረው በበና ብሔረሰብ ዝርው ቃል ተረኮች ክዋኔ እና ተረኮቹ ለብሔረሰቡ ተወላጆች ያላቸውን ፋይዳ ማሳየት ላይ እንደሆነ በቀዳሚዎቹ የጥናቱ ክፍሎች ላይ ገልጫለሁ። ዝርው ተረኮችን በተመለከተ በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ላይ በመጀመሪያ ዲግሪም ሆነ በሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች የተደረጉ ጥናቶችን እናገኛለን። ይሁን እንጂ በበናዎች ዝርው ተረኮች ክዋኔ እና ማህበራዊ ፋይዳ ላይ እኔ እስከማውቀው ድረስ የተሰራ አካዳሚያዊ ጥናት የለም። ነገር ግን በብሔረሰቡ ላይ ከተረክ ውጭ የተሰራ አንድ ጥናት ያገኘሁ ሲሆን እሱም በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በ2003 ዓ.ም. ላይ በዘላለም ፋንቱ "የለቅሶ ስነ ስርአት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ" በሚል ርእስ የቀረበ ነው።

ስለሆነም በዚህ ክፍል በዝርው ተረኮች ላይ በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ በውጭ ቋንቋዎች እና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል እንዲሁም በታዋቂ ጆርናል ላይ ከቀረቡ ስራዎች ውስጥ ከእኔ ስራ ጋር በውል የሚዛመዱትን ብቻ መርጨ እቃኛለሁ።

ማንያለው አባተ ባየህ በ1999 ዓ.ም ላይ የሠራው ጥናት በዝርው ቃል ተረኮች ላይ ከክፍለ ትምህርቱ ከተሰሩ ጥናቶች አንዱ ነው።ጥናቱ "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው" የሚል ርዕስ ያለው ነው። የጥናቱ ትኩረት በቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ገላጭ ትንተና ማድረግና የብሔረሰቡ አባላት የእኛ ናቸው ብለው የሚጠቅሷቸውን የቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች ለይቶ መግለጽ ነው። ትረካ ለቤንቾች ምንድን ነው? በተለያዩ አውዶች ዝርው ተረኮች ሲቀርቡ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? እና የብሔረሰቡ አባላት ዝርው ተረኮቻቸው በአሁኑ ወቅት በምን ይዞታ ላይ እንደሚገኙ ያውቁ ይሆን? ለሚሉ መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ እንደሚሰጥ ይገልፃል።

ማንያለው በጥናቱ ከመስክ የሰበሰባቸውን 97 ተረኮች ተጠቅሞ በቤንቾች "ቤንችቶስ" እና "ኤሸሸ" የሚባሉ ዝርው ቃል ተረኮች እንዳላቸውና "ቶስ" አብዛኛውን ጊዜ በቀን የሚከወን ሆኖ በአዋቂዎች የሚቀርብ እውነተኛ ወይም እውነታነታቸው ሊረጋገጥ የሚችሉ ታሪኮች የሚቀረቡበት እንደሆነና "ኤሸሸ" ግን የፈጠራ ሆኖ በአብዛኛው በምሽት ወቅት በአዋቂዎች ለህፃናት የሚቀርብ የተረክ ዘር እንደሆነ ይገልፃል።

ማህበራዊ ፋይዳቸውን በተመለከተ ማንያለው በጥናቱ ሲገልጽ ባህልን ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ፣ የባህላዊና የማህበራዊ ተቋማትንንና እሴቶቻቸውን ጠቀሜታ ከፍ ማድረግ፣ ማስተማርና ማዝናናት እንዲሁም ታሪክን መቅረስና ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ የመሳሰሉ እንደሆኑ ሲገልጽ "ኤሸሸ" የሚባለው የተረክ ዘር እየጠፋ መሆኑን ጠቅሷል። አጥኚው ጥናቱን ሲያደርግ የዝርው ተረኮቹን የክወና አውድ፣ተራኪ እና ታዳሚዎችን በተመለከተ በጥልቀት ባይገባም በጥቂቱ በዳሰሰበት ክፍል ሴቶችና ልጆች በተራኪነት እንደማይሳተፉ ይገልፃል። እዚህ ላይ ግን በተረቶቹም ውስጥ እንኳ ሴቶች በትዳር ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እንዳላቸው ሲገልጽ ሴቶች በትረካ አውድ ውስጥ በተራኪነት የማይሳተፉበት ምክንያት ምን እንደሆነ እና ሌላው ደግሞ አውድን ባነሳበት በዚሁ ክፍል የቤንች ዝርው ተረኮች ራሱን የቻለ የመተረኪያ ሥፍራ መኖር አለመኖሩን አለመግለፁ ክፍተት ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

በተጨማሪም የማንያለው ጥናት ከዚህ ጥናት በተወሰነ ለየት የሚያደርገው"ቶስ" እና "ኤሸሸ" ብሎ የከፈላቸውን የማህበረሰቡን ዝርው ተረኮች፤ ፋይዳቸውን ሲገልፅ ባንድ ላይ ደባልቆ የገለፃቸው መሆኑ ነው።

አማረ ሞላ በ1999 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበውን የጥናት ፅሁፍ ነው። የጥናቱ ርዕስም "የሸክኞ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ የአከዋወን ስልትና የይዘተ ትንተና" የሚል ጥናት አቅርቧል። በጥናቱ ያተኮረው የሸክኞን ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች በመሰብሰብ መድቦ ከአከዋወን ስልትና ከይዘት አንፃር መተንተን ላይ ሲሆን። 74 ያህል ተረቶችን ሰብስቧል።

አማረ የሸክኞ ተረቶች "ኬሞ" እና “ኤንጌሞ” ተብለው እንደሚመደቡ ገልጿል። “ኬሞ” አፈ ታሪክ ሊባሉ የሚችሉ ይዘቶች ያላቸው ተረቶች እንደሆኑና "ኤንጌሞ" ልዩ ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን የሚያመላክቱ ይዘቶች ያላቸውና በአንዳንድ ተመራማሪዎች ዘንድ "ፋቡላ" የሚባሉት አይነት እንደሆኑ አመልክቷል። በተጨማሪም እንደ ሥነ-ቃል ተመራማሪዎች

አከፋፈል ደግሞ የሸክኞ ብሔረሰብ ተረቶች አፈ ታሪክ (legend)፣ ገላጭ (Explanatory) እና ፋቡላ (Fable) ናቸው ብሏል።

አማረ የሸክኞ ሀገረሰብ ተረቶች የራሳቸው የሆነ የአከዋወን ስልት እንዳላቸውና "ኬሞ" በአቀራረብ ከ"ኤንጌሞ" እንደሚለይ በመግለጽ አፈ ታሪኮቹ የመሪዎቹን ስም፣የመኖሪያ አካባቢ....ወዘተ ጠቅሰው ሲጀምሩ ተረቶቹ ግን የገፀ-ባህሪያቱን ስም፣ ተግባር፣ ባህሪ፣...ወዘተ ጠቅሰው እንደሚጀምሩ ገልጿል። በተጨማሪም በመሪዎች ወይም በታላላቆች ፊት የሚነገር ተረት ወይም አፈ ታሪክ በተመሣሣይ የዕድሜ ክልልና በተገኘው ማህበራዊ አጋጣሚ ከሚነገረው ተረት በመግቢያው በመጠኑ እንደሚለይ አመልክቷል።

አጥኝው የሸክኞ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች የራሳቸው የሆነ መግቢያ የአጀማመር ሂደትና አጨራረስ ፣መዝጊያ፣...ወዘተ አላቸው ካለ በኋላ የመግቢያውንና የአጀማመሩን ሁኔታ ጽፎ የተረቶቹን መዝጊያ ግን እንዴት እንደሆነ አላመላከተም፤ ይህም የተወሰነ ክፍተት ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

ለማ ንጋቱ /1999 ዓ.ም/ *"በየም ብሔረሰብ ዖታ ተኮር ተረኮች የወንድና የሴት ምስል ጉንተና"* በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት በትምህርት ክፍሉ ከተሠሩ ጥናቶች አንዱ ነው። በዚህ ጥናት የአጥኚው የትኩረት ነጥብ በየም ወረዳ የሚተረኩ ተረቶችን ሰብስቦ በተረቶቹ ወንዶችና ሴቶች እንዴት እንደተገለፁ መተንተን ነው። ለዚህም ተግባር አንድ መቶ አራት ተረቶችን ከመስክ ሰብስቦ ዖታዊ ስዕል ጎልቶ የሚታይባቸውን 66 ተረቶች ለትንተና የመረጠ መሆኑን ገልጿል።

ለማ ከመስክ በሰበሰባቸው ተረቶች አማካይነትም የየም ብሔረሰብ ተረቶች በአካባቢው አጠራር መሠረት "ቶኞ" እና "ኤሻ" ተብለው እንደሚመደቡ፣ "ቶኞ" እውነት ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ታሪኮች የሚተረቱባቸው፣ "ኤሻ" ደግሞ ፈጠራ ተብለው የሚታመንባቸውና በአብዛኛው ለተዝናኖት የሚተረኩ ተረቶች እንደሆኑ ገልጿል። በተጨማሪም "ቶኞ" የሚባለው በምሁራኑ የተረት መመደቢያ ስልት መሠረት ሲታይ ታሪካዊ አፈ ታሪክ፣ ሚታዊ አፈ ታሪክና ገላጭ ተረቶች በሚል በሶስት ምድቦች ሊከፈል እንደሚችልና "ኤሻ" ግን ንዑስ ምድቦች እንደሌሉት አመልክቷል።

አጥኝው በብሔረሰቡ ተረቶች ውስጥ ሁለቱም ዖታዎች በአሉታዊና በአዎንታዊ ገጽታ የተሳሉ ቢሆኑም በአፈ ታሪክና ገላጭ በሆኑ ተረቶች ውስጥ ከወንዶች በባሰ ሁኔታ ሴቶች

የጎደፉና የበታች ተደርገው የተሳሉ መሆናቸውን ይህንንም አመለካከት ለማስረጽ እምነትን ክለላ ያደረጉ ተረቶች መኖራቸውን ጠቁሟል። በመጨረሻም በብሔረሰቡ ውስጥ በሥነ-ፆታ ላይ የሚሠሩ ማህበራትና ድርጅቶች እነዚህን በሴቶች ላይ ጫና የሚያሣድሩ ተረቶችን በመለየት ሐይማኖታዊ መሠረት እንደሌላቸው ቢያጋልጡ በሴቶች ላይ የሚፈጠረውን ጫና ለመቀነስና እኩልነትን ለማምጣት ለሚደረገው ጥረት ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት አስተያየቱን ሰጥቷል።

ለማ በጥናቱ በምዕራፍ ሦስት ላይ የተመለከተው ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ከሚያተኩርበት ርዕሰ ጉዳይ አንፃር በቂ ነው ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም ፆታዊ ጉዳይ የሚመረምር ከመሆኑ አንፃር ቢያንስ የማንነት /Identity/ ንድፈ ሀሳቦችን ቢመለከት ጥሩ ነበር።

ምንዳ ገብሬ /2000 ዓ.ም./ *"የጌዴኦ ልማዳዊ ሥርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው"* በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናቱ ዓላማው በጌዴኦ ማህበረሰብ ልማዳዊ ሥርዓቶችና በዝርው ቃል ተረኮቻቸው መሐል ምን አይነት ግንኙነት እንዳለ መመርመር፣ የዝርው ቃል ተረኮቻቸውን ጎሳዊ ምደባ እና አካባቢያዊ ስያሜ (መጠሪያ) እንዲሁም ዝርው ቃል ተረኮቹ የሚያበረክቷቸውን ማህበራዊ ግልጋሎት በመመርመር ይዘቶቻቸው በምን በምን ላይ እንደሚያተኩሩ ማሳየት ነው።

ምንዳ በጥናቱ የጌዴኦን ማህበረሰብ ባህላዊ ሥርዓቶች ቁጠላ (አምልኮታዊ ጭፈራ)፣ ፋጩ (ጥፋትን አምኖ መናዘዝ)፣ ጎንደሮ (ሥርዓተ-እርቅ) እንዲሁም የጋብቻና ጉንታዊ የሀዘን ሥርዓት ክዋኔዎችን በመጠነ ዳሷል። በተጨማሪም የጌዴኦ ዝርው ቃል ተረኮች በሁለት ጎሳዊ ምድቦች እንደሚከፈሉና በአካባቢያዊ መጠሪያዎቻቸውም መማሳ /mammassa/ እና ጢንጎ /xingo/ እንደሚባሉ ገልጿል። እነዚህ የማህበረሰቡ ዝርው ቃል ተረኮች ደግሞ እያንዳንዳቸው በአወቃቀር፣ በአቀራረብ፣ በታዳሚዎች እድሜና በመቼት... ወዘተ እንደሚለያዩ አሳይቷል፤ ሸማግሌዎችና አዛውንቱ ለወጣቱ ትውልድ ልምዶቻቸውንና ገጠመኞቻቸውን በልዩ ልዩ ሥነ-ቃሎቻቸው አማካይነት የሚነግሩበት አማካይ ሥፍራም "ሶንጎ" እንደሚባል ገልጿል።

አጥኝው በጥናቱ ባገኘው መረጃ መሠረትም ዝርው ቃል ተረኮቹ ከሚያበረክቱት ማህበራዊ ግልጋሎት አንፃር በተለይም ወጣቱን ትውልድ እነርሱ (ህበረተሰቡ) ሠናይ በሚሏቸው ሥርዓተ-አምልኮታዊ፣ ሥነ-ምግባራዊ እንዲሁም ግብረ-ገባዊ /moral/ ይዘቶች

ይኼነው ጀንበሬ እምሩ /1996/ላይ በምዕራብ ጎጃም ቃላዊ ተረኮች ላይ "A Generic Classification of Oral Prose Narratives of West Gojjam" በሚል ርዕስ ጥናት ያቀረበ ሲሆን የጥናቱ ትኩረት በምዕራብ ጎጃም ዝርው ቃል ተረኮችን መሰብሰብና በአይነታቸው መመደብ ላይ ነው።

ይኼነው በጥናቱ አማካይነት የምዕራብ ጎጃም ዝርው ቃል ተረኮችን በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች መድቧቸዋል። እነሱም folktale /ሀገረሰብ ተረቶች/፣ Legends /አፈ ታሪኮች/ እና Genealogy /የዘር ሐረግ ወይም ትውልድ ቆጠራ/ የሚሉት ናቸው። አጥኝው ስለዝርው ተረኮች ምደባ ይዞ በተነሳው ክፍል ለሁሉም የሚሆን አንድ አይነት የመመደቢያ ስልት እንደሌለ አመልክቷል። ነገር ግን በማጠቃለያው ለዚህ ጥናት ከመስክ የሰበሰባቸውን አንድ መቶ አርባ ተረኮችን የተራኪና ታዳሚን ዓይነት፣ የተረኩን ዓላማ፣ ርዕሰ ጉዳዩን፣ የአተራረክ ስልቱን እና የገፀ-ባህሪያትን አሳሳል መሠረት በማድረግ እንደመደበ ገልጿል።

የሀገረሰብ ተረቶችን፡- እንሰሴ (fable)፣ አስቂኝ ተረቶች (humorous tales) እና proverbal tale (ምሳሌያዊ ንግግራዊ ተረት) ሲል በሶስት ይከፍላቸዋል። አፈ ታሪኮችን ደግሞ የጎሳ አመጣጥና የእንስሳትን ባህሪ አመጣጥ የሚተርኩ፣ ታሪካዊ እና ሐይማኖታዊ በሚል በሶስት ከፍሏቸዋል። በተጨማሪም የሀገረሰብ ተረቶች ብዙውን ጊዜ የፈጠራ ታሪኮች እንደሆኑና በሁሉም የእድሜ ክልል ባሉ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እንደሚቀርቡ ገልጿል። አፈታሪክና ትውልድ ቆጠራዎች እውነተኛ ተደርገው የሚታሰቡ ታሪኮች የሚቀርቡባቸውና አብዛኛውን ጊዜም በዕድሜ ትልቅ በሆኑ ወንዶች የሚቀርቡ ወይም የሚሳተፉባቸው የተረክ አይነቶች እንደሆኑ አመልክቷል።

ሣህሉ ኪዳኔ (1996 እ.ኤ.አ) ላይ "Borana Oromo Prose Narratives A Contextual Study" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርቧል። በዚህ ጥናት ውስጥ የአጥኚው የትኩረት አጥብ የቦረና ኦሮሞን ዝርው ቃል ተረኮች አውድ እና አይነታዊ ክፍፍል /Ethnic Genre/ ማሳየት ነው። በጥናቱም የቦረና ኦሮሞ ዝርው ቃል ተረኮች በሶስት እንደሚከፈሉና እነሱም ዱሪ-ዱሪ /duri-duri/፣ መማክሳ /mamaksa/ እና አርጋጌቲ /arga-ageti/ እንደሚባሉ ገልጿል። ዱሪ-ዱሪ" የሕፃናት ተረቶች ሲሆኑ "ማማክሳ" እና "አረጋጌቲ" በአዋቂዎች የሚቀርቡና አርጋጌቲ የሚባለው ክፍል ሚትና አፈ ታሪክ በሚል በሁለት የሚከፈል እንደሆነ በዝርዝር አትቷል።

ሳህሉ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ከመስክ የሰበሰባቸውን 76 ተረቶች በገላጭ የጥናት ዘዴ በመጠቀም የሠራ ሲሆን የሕፃናት ተረቶች ላይ ጭብጥን የገፀ-ባህሪ ዓይነትን፣ አቀራረብ፣ ቋንቋ፣ እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን በዝርዝር ተመልክቷል። ከዚህ በተጨማሪም ከሶስቱ የተረክ ዓይነቶች "መማክሳ" በሚለው ላይ የአቀራረብ ሀሳችን፣የተራኪን ማንነት፣ የተረኩን ፋይዳ ወይም አገልግሎት ወይም ጠቀሜታ... ወዘተ ጉዳዮችን ያነሳ ሲሆን በክዋኔው ላይም የጎልማሳ ወንዶች ተጽእኖ እንዳለበት ጠቁሟል።

አብርሃም ዓለሙ (2000) *"Jimma Oromo Oral Prose Narratives: A Preliminary Descriptive Analysis* "ከሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ባቀረበው ጥናቱ ዋና ዓላማው የነበረው የጅማ ኦሮሞ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በመለየት መግለጽ ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መረጃዎችን በተሣትፎ ምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት በመሳሰሉት የምርምር መሣሪያዎች እንደሰበሰበ ይገልፃል።

አብርሃም ጥናቱን ለተረኮቹ አውዳዊ ገጽታ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ያቀረበ መሆኑን ከጥናቱ እንረዳለን። በተጨማሪ የተረኮቹን ጎሳዊ አከፋፈል ምክንያት መመርመር የተረኮቹን መክፈቻና መዝጊያ ደንቦች፣ በተረኮቹ የሚተላለፉ መሠረታዊ ጉዳዮች፣ የተራኪዎቹን እና የታዳሚዎቹን አይነትና ተግባር መለየት፣...ወዘተ የሚሉ ዋና ዋና ጉዳዮች የጥናቱ ማጠንጠኛ ሀሳቦች ሆነው እናገኛቸዋለን።

አጥኝው በጥናቱ ግኝትም የጅማ ኦሮሞ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሶስት አይነት የሚመደቡ መሆናቸውንና የመጀመሪያው ታሪክ (seenaa or taarika - historical narratives) ቀጥሎ የድሮ ወሬ/ወግ (Oddu drill-falk tales (fictional narrative) እና ሶስተኛው ቀልድ (Qoosaa-Jokes) በማለት እንደሚጠሯቸው ገልጿል። እነዚህ ተረኮች ደግሞ ሆን ተብሎ የተዘጋጀላቸው የመተረኪያ አጋጣሚ እንደሌላቸውና በየትኛውም ቦታና ጊዜ ሊከወኑ እንደሚችሉ ጠቅሷል። ይሁን እንጂ መከወኛ አውዶችን በተመለከተ ብዙውን ጊዜ ምቹ የሚሆኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች እንዳሉና እነሱም ጎረቤቶች ተገናኝተው ቡና የሚጠጡበት ሰዓት፣ የቁመሀ ሰዓቶች (የጫት መቃሚያ ሰዓቶች)፣ የገበያ ቀኖች እና የለቅሶ ሥርዓቶች ተጠቃሽ ስፍራዎች እንደሆኑ አመልክቷል።

አብርሃም ከሰበሰባቸው አንድ መቶ አራት ዝርው ተረኮች መካከል 53.8% ያህሉ eenaa (ታሪክ) የሚባለው የተረክ አይነት ሲሆን ከሌሎቹ በአንባራዊነት ከፍተኛ ቦታ ሚሰጠውና በትረካዉ ላይ የወንዶች ተጽእኖ ያለበት መሆኑን ገልጿል።

በታዋቂ "ጆርናል" Journal of African Cultural Studies ላይ ቀርቦ ያገኘሁት ሥራ Abraham Alemu ነው። ጥናቱም "Oral Narratives as Ideological Weapon for ubordinating Women: The Case of Jimma Oromo" በሚል ርእስ 2007 ላይ ታትሞ ወጣ ነው። ጥናቱ በርእሱ እንደተመለከተው የጂማ ኦሮሞዎችን ቃላዊ ተረኮች ከስርአተ ፆታ ንባታ ሚናቸው አንፃር በስፋት የዳሰሰበት ነው። ጥናቱም ሁለት መሰረታዊ ክፍሎች ያሉት ሆን የመጀመሪያው የጥናቱን ዳራ በመያዝ በውስጡ የጂማ ኦሮሞ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ላቸውን ደረጃ እና ሚና ያሳየ ነው። በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከማህበረሰቡ ዘንድ በተሰበሰቡ ረኮች አማካይነት ስርአተ ፆታ ተኮር ታሪኮች ያላቸውን ርእዮተ አለማዊ አስፈላጊነት ማሳየት ይ ያተኮረ ነው። አብርሃም በዚህ ጥናቱ የጂማ ኦሮሞዎች ዝርው ቃል ተረኮቻቸውን eenaa /historical narrative/, Oduu durii /folktales/ እና qoosaa /Jokes/ ብለው ሰሰት እንደሚከፍሏቸው ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በሰራው ጥናቱ ላይ መግለጹን ጠቁሞ በዚህ ይ ግን ሆነ ብሎ በሁለት እንደሚመድባቸው ገልጿል።

አብረሃም በዚህ ጥናቱ በጂማ ኦሮሞዎች ዘንድ በተረኮቻቸው አማካይነት ሴት እና ንድ በመሆን የሚፈጠርን የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት እንዲሁም ለሴቶች የሚሰጠውን ዝቅተኛ ታ በስፋት ጠቁሟል። ይህንንም ሃሳብ ሲያጠናክር ከቋንቋቸው ሁለንተናዊ ተፈጥሮ በመነሳት ጂማ ኦሮሞ የቋንቋ ተፈጥሮ ውስጥ queen/prince (በአማርኛው ንግስት እንደማለት ነው) ሚል ስያሜ በጭራሽ አለመኖሩን አመልክቷል።

ከላይ የተመለከትኳቸውን ጥናቶች ጠቅለል አድርጌ ስገልጻቸው የማንያለው፣ የአማረ ኛ የምንዳ ጥናቶች በተለያዩ ማህበረሰቦች ላይ የተሰሩ ቢሆኑም የየማህበረሰቡን አፋዊ ዝርው ረኮች በአውዳዊ አገባባቸውና በአይነታቸው በመመደብ ያጠኑ በመሆናቸው በከፊል ሚመሳሰሉ ሲሆን የለማ ጥናት ግን ፆታ ተኮር ተረኮች ላይ የሚያጠነጥን በመሆኑ ከሌሎቹ ልቅ በጆርናል ላይ ከቀረበው የአብርሃም ጥናት ጋር በከፊል ይመሳሰላል። ለውጭ ቋንቋዎች ተሰሩት ደግሞ ከተስፋዬ ጥናት በስተቀር ሌሎቹ ማለትም ሳህሉ፣ ይሄነው፣ ባይለየኝና በርሃም በተረኮች አውዳዊ አገባብ ላይ በማተኮር ተረኮቹን በአይታቸው በመመደብ ያጠኑ መሆናቸው ይመሳሰላሉ። የተስፋዬ ጥናት ግን የተረኮቹ ጭብጥ ላይ በመመስረት ለማህበረሰቡ

ላህሉ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ከመስክ የሰበሰባቸውን 76 ተረቶች በገላጭ የጥናት ዘዴ በመጠቀም የሠራ ሲሆን የሕፃናት ተረቶች ላይ ጭብጥን የገፀ-ባህሪ ዓይነትን፣ አቀራረብ፣ ቋንቋ፣ እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን በዝርዝር ተመልክቷል። ከዚህ በተጨማሪም ከሶስቱ የተረክ ዓይነቶች "መማክሳ" በሚለው ላይ የአቀራረብ ህጎችን፣የተራኪን ማንነት፣ የተረኩን ፋይዳ ወይም አገልግሎት ወይም ጠቀሜታ... ወዘተ ጉዳዮችን ያነሳ ሲሆን በክዋኔው ላይም የጎልማሳ ወንዶች ተጽእኖ እንዳለበት ጠቁሟል።

አብርሃም ዓለሙ (2000) *"Jimma Oromo Oral Prose Narratives: A Preliminary Descriptive Analysis* "ከሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ባቀረበው ጥናቱ ዋና ዓላማው የነበረው የጅማ ኦሮሞ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በመለየት መግለጽ ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መረጃዎችን በተሣትፎ ምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት በመሳሰሉት የምርምር መሣሪያዎች እንደሰበሰበ ይገልፃል።

አብርሃም ጥናቱን ለተረኮቹ አውዳዊ ገጽታ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ያቀረበ መሆኑን ከጥናቱ እንረዳለን። በተጨማሪ የተረኮቹን ጎሳዊ አከፋፈል ምክንያት መመርመር የተረኮቹን መክፈቻና መዝጊያ ደንቦች፣ በተረኮቹ የሚተላለፉ መሠረታዊ ጉዳዮች፣ የተራኪዎቹን እና የታዳሚዎቹን አይነትና ተግባር መለየት፣...ወዘተ የሚሉ ዋና ዋና ጉዳዮች የጥናቱ ማጠንጠኛ ሀሳቦች ሆነው እናገኛቸዋለን።

አጥኝው በጥናቱ ግኝትም የጅማ ኦሮሞ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሶስት አይነት የሚመደቡ መሆናቸውንና የመጀመሪያው ታሪክ (seenaa or taarika - historical narratives) ቀጥሎ የድሮ ወሬ/ወግ (Oddu drill-falk tales (fictional narrative) እና ሶስተኛው ቀልድ (Qoosaa-Jokes) በማለት እንደሚጠሯቸው ገልጿል። እነዚህ ተረኮች ደግሞ ሆን ተብሎ የተዘጋጀላቸው የመተረኪያ አጋጣሚ እንደሌላቸውና በየትኛውም ቦታና ጊዜ ሊከወኑ እንደሚችሉ ጠቅሷል። ይሁን እንጂ መከወኛ አውዶችን በተመለከተ ብዙውን ጊዜ ምቹ የሚሆኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች እንዳሉና እነሱም ጎረቤቶች ተገናኝተው ቡና የሚጠጡበት ሰዓት፣ የቂመሀ ሰዓቶች (የጫት መቃሚያ ሰዓቶች)፣ የገበያ ቀኖች እና የለቅሶ ሥርዓቶች ተጠቃሽ ስፍራዎች እንደሆኑ አመልክቷል።

አብርሃም ከሰበሰባቸው አንድ መቶ አራት ዝርው ተረኮች መካከል 53.8% ያህሉ seenaa (ታሪክ) የሚባለው የተረክ አይነት ሲሆን ከሌሎቹ በአንባራዊነት ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠውና በትረካዉ ላይ የወንዶች ተጽእኖ ያለበት መሆኑን ገልጿል።

በታዋቂ "ጆርናል" Journal of African Cultural Studies ላይ ቀርቦ ያገኘሁት ሥራ የAbraham Alemu ነው። ጥናቱም "Oral Narratives as Ideological Weapon for Subordinating Women: The Case of Jimma Oromo" በሚል ርእስ 2007 ላይ ታትሞ የወጣ ነው። ጥናቱ በርእሱ እንደተመለከተው የጂማ ኦሮሞዎችን ቃላዊ ተረኮች ከስርአተ ፆታ ግንባታ ሚናቸው አንፃር በስፋት የዳሰሰበት ነው። ጥናቱም ሁለት መሰረታዊ ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው የጥናቱን ዳራ በመያዝ በውስጡ የጂማ ኦሮሞ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ደረጃ እና ሚና ያሳየ ነው። በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከማህበረሰቡ ዘንድ በተሰበሰቡ ተረኮች አማካይነት ስርአተ ፆታ ተኮር ታሪኮች ያላቸውን ርእዮተ አለማዊ አስፈላጊነት ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው። አብርሃም በዚህ ጥናቱ የጂማ ኦሮሞዎች ዝርው ቃል ተረኮቻቸውን Seenaa /historical narrative/, Oduu durii /folktales/ እና qoosaa /Jokes/ ብለው በሶስት እንደሚከፍሏቸው ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በሰራው ጥናቱ ላይ መግለጹን ጠቁሞ በዚህ ላይ ግን ሆነ ብሎ በሁለት እንደሚመድባቸው ገልጿል።

አብረሃም በዚህ ጥናቱ በጂማ ኦሮሞዎች ዘንድ በተረኮቻቸው አማካይነት ሴት እና ወንድ በመሆን የሚፈጠርን የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት እንዲሁም ለሴቶች የሚሰጠውን ዝቅተኛ ቦታ በስፋት ጠቁሟል። ይህንንም ሃሳብ ሲያጠናክር ከቋንቋቸው ሁለንተናዊ ተፈጥሮ በመነሳት በጂማ ኦሮሞ የቋንቋ ተፈጥሮ ውስጥ queen/prince (በአማርኛው ንግስት እንደማለት ነው) የሚል ስያሜ በጭራሽ አለመኖሩን አመልክቷል።

ከላይ የተመለከትኳቸውን ጥናቶች ጠቅለል አድርጌ ስገልጻቸው የማንያለው፣ የአማረ እና የምንዳ ጥናቶች በተለያዩ ማህበረሰቦች ላይ የተሰሩ ቢሆኑም የየማህበረሰቡን አፋዊ ዝርው ተረኮች በአውዳዊ አገባባቸውና በአይነታቸው በመመደብ ያጠኑ በመሆናቸው በከፊል የሚመሳሰሉ ሲሆን የለማ ጥናት ግን ፆታ ተኮር ተረኮች ላይ የሚያጠነጥን በመሆኑ ከሌሎቹ ይልቅ በጆርናል ላይ ከቀረበው የአብርሃም ጥናት ጋር በከፊል ይመሳሰላል። ለውጭ ቋንቋዎች ከተሰሩት ደግሞ ከተስፋዬ ጥናት በስተቀር ሌሎቹ ማለትም ሳህሉ፣ ይሄነው፣ ባይለየኝና አብርሃም በተረኮች አውዳዊ አገባብ ላይ በማተኮር ተረኮቹን በአይታቸው በመመደብ ያጠኑ በመሆናቸው ይመሳሰላሉ። የተስፋዬ ጥናት ግን የተረኮቹ ጭብጥ ላይ በመመስረት ለማህበረሰቡ

የሚሰጡትን ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ የሚመረምር በመሆኑ በተወሰነ ከማንያለው እና ከዚህ ጥናት ጋር በከፊል ይመሳሰላል።

ከዚህ ቀጥሎ ባለው ንዑስ ክፍል ደግሞ ንድፈ ሃሳባዊ ፅንሰ ሃሳቦችን እንመለከታለን።

2.2. የንድፈ ሃሳብ ቅኝት

በፎክሎር የጥናት መስክ ውስጥ ከሚጠኑት ጉዳዮች አንዱ ስነቃል መሆኑን አብዛኛው የዘርፉ ምሁራን ይጠቅሳሉ። ይህ የስነቃል ዘርፍ ደግሞ በውስጡ እንቆቅልሾችን፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ተረቶች ፣ ሌጀንዶች፣...ወዘተ የሚጠኑበት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ይህ ጥናት በዝርው ቅርፅ የሚቀርቡት ላይ ማለትም ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በዚህ ንኡስ ክፍል ስለ ዝርው ተረኮች ምንነት እና በማህበረሰብ ውስጥ እንዴት እንደሚገለው (እንደሚከወኑ) እንዲሁም ለተፈጠሩበት ማህበረሰብ የሚኖራቸውን ፋይዳ የተመለከቱ አንዳንድ ሃሳቦች ይቃኛሉ።

2.2.1. የዝርው ቃል ተረክ ምንነት

የተረክ ምንነትን በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን የተፃፉ እና ዝርው ተረኮችን የተመለከቱ ስራዎችን ስንመለከት በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ስለጽንሰ ሃሳቡ የሚሰጡት ገለፃ እና የሚሰነዝሩት አስተያየት የተለያየ ሁኖ እናገኘዋለን። ለምሁራኑ ገለፃ እና አቋም መለያየትም የተለያዩ የዘርፉ ሊቃውንትም የየራሳቸውን ሃሳብ ያስቀምጣሉ።

በ Dorson (1972፤55) ውስጥ ዝርው ትረካዎችን በተመለከተ የሚሰጠው አስተያየት የተለያየ የመሆኑ ምክንያት ሁለት መሆኑ ይገለፃል። የመጀመሪያው ምክንያት ጥናቱን የሚያካሂዱት አጥኚዎች ተተኳሪውን ርእሰ ጉዳይ የሚመለከቱበት መንገድ የትኩረት ነጥባቸውን የሚያሳርፉበት ጉዳይ የልዩነቱ አንድ ሰበብ ነው ይላሉ። ይህም ማለት አንደኛውን ተመራማሪ የዝርው ቃላዊ ተረኮች ምንነት ዋና ጉዳይ ሲሆንበት ለሌላኛው አጥኚ ደግሞ የተረኮቹ መዋቅር ሊብስበት ይችላል እንደማለት ነው።

ሁለተኛው የመለያያው ምክንያት አጥኚው ይዞት የሚነሳው አላማ እና ያንን አላማ ይዞ ካጠና በኋላ የሚደርስበትም ግብ የተለያየ የመሆኑ ነገር ነው። እንደ Linda ገለፃ አጥኚዎች ሁሉ ይዘውት የሚነሱት አላማ ተመሳሳይ ባለመሆኑ ከጥናታቸው መጨረሻ ላይም የሚደርሱበት ግብ የተለያየ የመሆኑ ነገር የጥናቱ ተፈጥሮም ጭምር እንደሆነ እንረዳለን።

ህም በመሆኑ በተለያዩ ሰዎች ለተለያየ አላማ የሚደረግ እና የተለያየ ግብ ላይ የሚደርስ ይነት አካሄድ መኖሩ የጥናት ተፈጥሯዊ ጉዳይ መሆኑ ካስማማን በቃላዊ ዝርው ተረኮች ንባር የሚሰጡ ገለፃዎች መለያየትም ያን ያህል የሚያሳስብ ጉዳይ መሆን የለበትም የሚል ምነት አለኝ። ይልቁንም ዋናው ቁምነገር አስተያየቶቹን እንደ አስተያየት ወስዶ ማጥናት ነመርመር እና ለአካዳሚው ዓለም አንዳች እሴት እንዲጨምሩ ማድረግ ከዘርፉ ባለሙያዎች ሚጠበቅ ተግባር ነው።

ቃል ትረካዎችን /Prose Narratives/ የተለያዩ የጎንድፈ ሐሳቡ ምሁራን ስመ አጠራርን ጋቀር በተለያየ መልክ ይጠሯቸዋል። በዚህም መሰረት 'oral tradition, 'oral literature, al narrative, 'oral testimony' የሚሉትን እና የመሳሰሉ ቃላት እንደ ሁኔታው እና እንደ ሰረታዊ አላማቸው ተክተው ሲጠቀሙባቸው ይስተዋላል። መሰረታዊው አገልግሎታቸው እና ነሳታቸው ቃላዊ ያሉትን ነገር ጽሑፋዊ ከሆኑት ተመሳሳይ ጉዳዮች ነጥሎ ማሳየትና ስረዳት ነው። በሌላም አረዳድ Finnegan, (1992፡5) ላይ ቃላዊ ብለን የምናነሳው የባህል ል ከጽሑፋዊው ለመለየት ብቻ ሳይሆን እንደ ተረክ፣ ዝማሬ፣ አባባል እንቆቅልሽ ወዘተ ትን ከቁሳዊ ባህል ጋር ያላቸውንና ድንበር ለማበጀት እንደሚያስችል ያስረዳሉ። ዘሪሁን ፋውም ቃል ተረክን ስነቃል ሲሉ ያነሱታል። ለቃሉም ፍቺ፡-

> ስነቃል በመናገር በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችና የህይወት መልኮችን መግለጫ ኪነ ጥበብ ነው። ይህ ኪነ ጥበብ ማህበረሰቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያጠራቀሙትና የሚያጠራቅሙት ቅርስ ከመሆኑም በላይ ለህልውናቸው ሲሉ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት የሚከሰት ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሮ ጋር ካላቸው መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥርቅምና የገጠመኞቹ ማንጸባረቂያ ነው። (1996፣20)

ሉ። ዘሪሁን በመሰረታዊነት ለመግለጽ ከሞከሯቸው ትልልቅ ቁም ነገሮች መሀከል አንዱ ነቅረቢያ መንገዱ ሲሆን "በመተረት ወይም በመዜም" ሲሉ የገለፁት ነጥብ ነው። ከዚህም ጨማሪ የመከወኛ ስፍራ እና ሁኔታን ለማስረዳትም "ማህበራዊ አጋጣሚዎች"ን በአስረጂነት ቶምጠዋል።

በዚሁ ቃል ተረክ ውስጥ የሚወድቁ በርካታ ቃላዊ የባህል አካሎች ያሉ ሲሆን እንደየ ሪያቸው አገልግሎታቸው እና ሁኔታዎቻቸው ተነጣጥለው ወይም ተቧድነው ይመደባሉ።

ሀተታ ተፈጥሮ (Myth)፣ ገድል (Legend)፣ ተረታ ተረት (folktale)፣ ተረኮች፣ ኤፒኮች (Epic)፣ እንቆቅልሾች (Riddles)፣ አባባሎች (proverbs) ወዘተ የተለመዱ የመክፈያ መንገዶች ናቸው (Finnegan 138-142)።

እንደ Bascom ገለፃ ደግሞ እጅግ ሰፊ ስርጭት ያላቸውን ሚት፣ ሌጀንድ እና ተረኮችን በአንድ ምድብ በማምጣት ዝርው ተረክ ብለው እንደሚጠሯቸውና ይህም ተገቢ መሆኑን ያስረዳሉ።

> Prose narrative, I propose, is an appropriate term for the widespread and important category of verbal art which includes myths, legends, and folktales. These three forms are related to each other in that they are narratives in prose, and this fact distinguishes them from proverbs, riddles, ballads, poems, tonguetwisters, and other forms of verbal art on the basis of strictly formal characteristics (Bascom 1996:3)

በተጨማሪም አፋዊ ዝርው ተረክ የሌለው ማህበረሰብ በየትኛውም የአለም ክፍል ብንሄድ ማግኘት እንደማንችል ግልጽ ነው። ይህንን በተመለከተ ፈቃደ አዘዘ "ትረካ በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ያለ፣ በእለታዊ ህይወት በተለያየ መልክ የሚከወን ጉዳይ ነው።" (1991፡52) ይላሉ። አንድ ማህበረሰብ መነሻውን (የት መጣነቱን) አሊያም የመጨረሻውን መዳረሻ እንደራሱ የእውቀትና የአረዳድ ደረጃ መግለጹ አይቀርም። እንዲሁም አለምን የሚመለከትበት፣ የሚረዳበትና የሚያስረዳበት የራሱ መንገድ ይኖረዋል። እኒህ ነገሮች ሁሉ ቃል ተረኮች እንዲፈጠሩ ምክንያት ይሆናሉ። ከዚህም አንጻር ነው ተረክ የሌለው ማህበረሰብ የለም የምንለው።

2.2.2. የዝርው ቃል ተረክ ክዋኔ እና ዘዴ

በፎክሎር ጥናት ከሚተኮርባቸው አበይት ገፅታዎች መካከል ክዋኔ አንዱ ነው። ይህ ጉዳዩ ሲነሳ አብረውት የሚነሱ ተያያዥ ነጥቦች በመኖራቸው ስለ ክዋኔ ባነሳን ቁጥር አብረን የምናነሳቸው ወሳኝ ጉዳዮች ብዙ ናቸው። በመሆኑም አንድን የፎክሎር ዘውግ ማጥናት የሚፈልግ ማንኛውም ፎክሎሪስት ለጥናት የመረጠውን ማንኛውም ፎክሎራዊ ቅርፅ ሲመረምር ያ ቅርፅ ህያው ሁኖ የሚኖርበትንና ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍበትን ክዋኔው ታሳቢ ማድረግ እንዳለበት የዘርፉ ምሁራን ይመክራሉ። ታድያ በዚህ ፅንሰ ሃሳብ ውስጥ ወደሚነሱት

መሰረታዊ ነጥቦች ከመግባቴ በፊት በፅንሰ ሃሳቡ ምንነት ላይ ከዘርፉ ምሁራን የተነሱ ነጥቦችን አስቀድማለሁ።

Sims, and Martine (2005:128) ስለ ክዋኔ ባነሱት ክፍል Performance is an expressive activity that requires participation heightens our enjoyment of experience and invites response. ሲሉ ያስቀምጣሉ። ከጥቅሱ መገንዘብ የምንችለውም ክዋኔ ገላጭ የሆነ እንቅስቃሴ ሁኖ ተሳትፎን የሚሻ በልማድ መደሰትን የሚያሳድግና ምላሽን የሚጋብዝ መሆኑን ነው። ነገር ግን ይህ ክዋኔ በርግጥም ተከስቷል ወይም ተከውኗል ለማለት በዋነኛነት የጊዜ፣ የቦታ እና የተሳታፊዎች ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ እንዲሁም የመከወኛ አጋጣሚው ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው።

Bauman (1986) ስለ ክዋኔ ምንነት ሲገልፁ ክዋኔ የተግባቦት ዘዴ እና የንግግር ስልት ሲሆን ከክዋኙ አንፃር ክወናውን የሚያቀርብበትን ስልት የሚያገኝበት እና ከታዳሚው አንፃር ደግሞ የክዋኙን ችሎታ የሚለካበትን እውቀት ይፈጥርለታል ይላሉ።

እናም እንደ Bauman አባባል ክዋኔ የንግግር ስልት ከመሆኑም በተጨማሪ በክዋኝ ሆነ በታዳሚ በኩል የሚፈጥራቸው የራሱ የሆኑ አስተዋፆዎች እንዳሉ እንረዳለን። እነዚህም ለምሳሌ አንድ ስነቃል ባልተገባ ጊዜና ቦታ ቢቀርብ ከታዳሚ የሚኖረው ምላሽ ለስነቃሉ አቅራቢ ተገቢ ሁነት አለማቅረቡን ሲያመላክተው ለታዳሚው ደግሞ የክዋኙን ችሎታ የክወና ብቃት እና ግብ መቺነቱን በተመለከተ እንዲፈትሽ ያደርገዋል።

የስነቃል ክዋኔን በተመለከተ ዘሪሁን አስፋው (1996፡ 22) የሚከተለውን አስፍረዋል

> ስነ-ቃል ያለክዋኔ ህልውና የለውም። አፈጣጠሩም ሆነ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍያው ከክዋኔ የተነጠለ አይደለም።... ስነ-ቃል ሙሉ ህልውናውን የሚያገኘው ኪነጥበባዊ ሞገሱን የሚጎናፀፈው እና የተሳታፊዎቹን ልብ ነክቶ ግቡን የሚመታው በፊታቸው ሲከወን ነው።... በተጨማሪም ስነቃል ከክዋኔውና ከድባቡ ተነጥሎ ቢገኝ ፍዝ ነው

ከዚህ በመነሳት ክዋኔ ለስነቃል ዋነኛ የመታያ ጉዳይ እንዲሁም ጉዳዩን የመግለጫ እንቅስቃሴ መሆኑን እንገነዘባለን። እዚህ ላይ ይህን ጉዳይ በስነቃል ብቻ ሳንወስነው ለፎክሎር ዘርፎች በሙሉ የሚሰራ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። በመሆኑም እንቅስቃሴን (ድርጊትን)፣

ለድባቡ ድምቀት የሚሰጡ አልባሳትና ቁሳቁሶችን፣ ማህበራዊ አጋጣሚውን እና ተሳታፊውን ባንድነት የሚያካትት ነው። ባጠቃላይ ጉዳዩ (text)እና ማህበራዊ ድባቡ (context) በክዋኔ ውስጥ የማይቀሩ ወሳኝ ነገሮች ናቸው።

የክዋኔን ጉዳይ ስናነሳ አብረው የሚነሱ መሰረታዊ ነጥቦች እንዳሉ ከላይ ጠቅሼ ነበር። ከጠቀምኳቸው ነጥቦች የፎክሎሩ መከወኛ አውድ (context) አንዱ ነው። በዚህ ፅንሰ ሃሳብ ውስጥ የምናገኛቸው በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም በዋነኛነት ልብ ልንላቸው የሚገቡ መሰረታዊ ነጥቦች አሉ። ከነዚህም መቼት፣ ከዋኝ እና ታዳሚ ዋነኞቹ ሲሆኑ እነዚህን ነጥቦች ከማንሳቴ በፊት ግን ከዘርፉ ምሁራን ስለ አውድ (context) የተሰጡ ፅንሰ ሃሳቦችን አነሳለሁ።

እነ Sims ይህንን ጉዳይ ሲገልፁ፡-

> The physical setting and social situations in which members of folk groups share folklore, as well as the relationship among audience members and performers, make up the context of the performance.(Sims and Martine; 2005፡ 137)

እናም አውድ የምንለው ነገር የአንድ ፎክ ምድብ አባላት ፎክሎሩን የሚቋደሱበት አካላዊ መቼትና ማህበራዊ ሁነት ነው። ከዚህም ጋር በአብሮነት በታዳሚውና በሰዎች መካከል ያለውንም ግንኙነት ይመለከታል። ስለሆነም ስነቃሉ ሲቀርብ ወይም ሲከወን የሚኖረውን አለባበሱን፣ አቀራረቡን፣ አሰራሩን፣ እንቅስቃሴውን እንዲሁም የሚኖረውን አጋንታዊም ሆነ አሉታዊ ምላሽ፣ በዚህ ምላሽ የተነሳ የሚፈጠር ለውጥን ጨምሮ ያካትታል ማለት ነው። ከዚህ በመነሳትም አውድ የምንለው ነገር በቴክስቱና በክዋኔው ዙርያ የሚገኙትን፣ የሚከሰቱትን ሁነቶች እንደሚጠቀልል እንገነዘባለን።

Dundes (1978፤ 27) The context of an item of folklore is the specific social situation in which that particular item is actually employed. በማለት አውድን የአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ፣ ቅጥ ተግባራዊ ክንውን መፈፀምያ ውስን ማህበራዊ ሁነት እንደሆነ ይገልፃሉ። በመሆኑም አንድን ስነቃል ከበቀለበት ማህበራዊ አውድ አውጥተን በሌላ ማህበራዊ አውድ ቢከወን ተከወነ ለማለት አያስችልም። ምክንያቱም እንደ መደበኛው ማህበራዊ አውድ ሊሆን አይችልም።

Sims and Martine ስለ አውድ ሲያነሱ ከጠቀሷቸው ምሁራን ውስጥ አንዱ ምሁር Ben Amos አውድን በሁለት ወገን በመክፈል የባህል አውድ (cultural context) እና የሁኔት አውድ (situational context) ይሏቸዋል።

የባህል አውድ (cultural context) የሚለው ሰፊና አጠቃላይ ክብ ሲሆን ሊጠቃለሉ የሚችሉ አውዶችን በሙሉ የሚያቅፍ ነው። የሚቋደሱት እውቀት ለማን ዋቢ እንደሚሆንና ምን እንደሚወክል በማጠቃለል የተናጋሪውን እውቀትና የታዳሚውን የጋራ ስምምነት፣ እምነት፣ ስልት፣ ቋንቋ፣ ዘይቤ፣ የንግግር ዘውግ፣ ታሪካዊ ንቃት፣ ስነምግባራዊና ህጋዊ መመሪያዎችን ሁሉ ይጠቀልላል።

የሁኔት አውድ (situational context) ደግሞ ጠባብ ሲሆን በቀጥታ ፎክሎሩ የሚነገርበትን አውድ የሚመለከት ነው። መቼቱን፣ ጉዳዩን፣ ግንኙነቱን እና ሁነቱን (Sims, Martha 2005፡ 137)።

እነ Sims, የአውድን ምንነት የገለፁ የተለያዩ ምሁራንን ከጠቀሱ በኋላ እነሱ አውድን በሁለት ይከፍሉታል። አካላዊ አውድ (Physical context) እና ማህበራዊ አውድ (Social context) በማለት። አካላዊ አውድ (Physical context) ስነቃሉ የሚቀርብበትን መልክአምድራዊ ሁኔታ እና የአቅራቢውንና የአዳማጩን አካላዊ ሁኔታ ያካትታል። በዚህም አካላዊ አውድ ላይ የፊት ገፅታ ገለፃ፣ የድምፅ ከፍታ እና ዝቅታ፣ ዜማው፣ የሰውነት እንቅስቃሴውንና ምትን ያጠቃልላል።

ማህበራዊ አውድ (Social context) ላይ ደግሞ በፎክ ቡድኑ ውስጥ የከዋኙን እና የታዳሚውን ጎሳዊ ቅርርቦሽ፣ ትስስሮሽ፣ ሃይማኖታዊ ግንኙነት፣ የስራ እና ክልላዊ ግንኙነቶችን ያጠቃልላል። እነዚህ ጉዳዮች በሚቀርበው ቴክስት ላይ ተፅእኖ እንዳላቸው ይጠቁማሉ። በተጨማሪም ከአካላዊው መቼት በአንፃራዊነት ሰፋ እንደሚል ይጠቁማሉ (Sims, Martha C. 2005፡ 138-140)።

እናም ባጠቃላይ እነዚህን የአውድ ጉዳዮች በአንድ ስነቃል ክዋኔ ላይ ከባድ ተፅእኖ መፍጠር የሚችሉ መሆናቸውን መረዳት አያዳግትም። ደግሞም የተለያዩ ፎክሎራዊ ዘውጎች የተባሉበትን፣ ስነቃሎቹ የተከወኑበትን ፣ የተፎከሩበትን ፣ የተቅራሩበትን ፣ የተተረቱበትን ... ወዘተ አውድ መረዳት ማለት ስነቃሉን በምልአት ማጣጣም ማለት ብቻ ሳይሆን በመከወናቸው ያላቸውን ተግባር ወይም ሙያ መገንዘብ ማለት እንደሆነ እንገነዘባለን። እንግዲህ አውድን

በተመለከተ እስካሁን ያነሳናቸውን ንድፈ ሃሳባዊ እውቀቶች የሚነግሩን ሃሳብ በሙሉ የሚያስረዳን አውድ በየትኛውም የፎክሎር ዘውግ ውስጥ የፎክሎሩ ህይወት መሆኑን ነው። ታድያ ከላይ ባነሳነው ክፍል አውድ ውስጥ ትኩረት ልናደርግባቸው የሚገቡ መሰረታዊ ነጥቦች ብለን የዘረዘርናቸው የመቼትን፣ የከዋኝን እና የታዳሚ ጉዳይ ቀጥሎ በጥቂቱ እንመለከታለን።

መቼት፣ ከዋኝ እና ታዳሚ በአንድ የስነቃል ዘርፍ መከወኛ አውድ ወቅት በዋነኛነት የምንመለከታቸው ጉዳዮች ናቸው። ከዋኝ ሳይኖር ክዋኔ አይኖርም። የትኛውም ክዋኔ ደግሞ ከጊዜ እና ከስፍራ ውጪ ሊሆን አይችልም ዛፍ ስር፣ ጥላ ባለበት፣ ቤት ውስጥ፣ እሳት ዳር፣ ድንኳን ውስጥ፣...ወዘተ በምሽት፣ ጠዋት ላይ ወይም ደግሞ እንደሚከወነው የስነቃል ዘርፍ ቀትር ላይም ሊከወን ይችላል፤ ብቻ ባንዳች ምክንያት ተመራጭ በሆነው ስፍራና ጊዜ ይከወናል። በነዚህ ደግሞ ታዳሚ የግድ መኖር አለበት። ታዳሚ በሌለበት አንድን ስነቃል ተከወነ ለማለት አይቻልም። ቢያንስ ከከዋኙ ውጪ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቁጥር ያላቸው ታዳሚዎች ሊኖሩ ይገባል። ታዳሚዎቹ ልጆች፣ ወጣቶች፣ አዋቂዎች፣ ሴቶች ወይም ወንዶች አንዳንዱም በጥምረት ሊሆኑና ሊገኙ ይችላሉ። ይህንንም የሚከወነው ጉዳይ ይወስነዋል። ለምሳሌ የሚከወነው ጉዳይ ሙሾ ቢሆን በሙሾ አውራጁ ዙርያ ህጻናትን አንጠብቅም ታዳሚ ሊሆኑ የሚችሉት አንዳንድ ጊዜ ወጣቶች ብዙውን ጊዜ ግን አዋቂ ሴቶችና ወንዶች ናቸው።

ታዳሚዎች በክዋኔ ላይ የራሳቸው የሆነ ሚና አላቸው። በመሆኑም ይህ የታዳሚ ምላሽ በክዋኔ ውስጥ በፎክሎሪስቱ መታየት የሚኖርበት ወይም ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ አንዱ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ታድያ ይህ የታዳሚ ምላሽ ክዋኔውን እንደነበረ እንዲቀይ የማድረግ አልያም የመለወጥ ሃይል አለው። ይህም ሊሆን የሚችለው በከዋኙ የአከዋወን ብቃት፣ ስለሚከወነው ነገር ያለው ችሎታ፣ ከታዳሚው ጋር ያለው ማህበራዊም ሆነ ሌሎች ደረጃዎች፣...ወዘተ አማካይነት ነው። ነገር ግን ይህንን ጉዳይ የተረዳ ወይም የተገነዘበ ከዋኝ የክዋኔውን ድባብ በተለያዩ ዘዴዎች እንደነበረ ማስቀጠል ይችላል። ካልሆነ ግን ድባቡ መቀየር ይኖርበታል።

ይህ የታዳሚ ምላሽ የሚታየው በክዋኔው ጣልቃ በመግባት ማስቆም እና እንደገና መጀመር፤ አንዳንዱ ደግሞ አስተያየት ወይም እርምት በመስጠት ማስቀጠል ሌላም ሌላም ይሆናል። ይህንን ሁኔታ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የተረት አውድን በምሳሌነት እንውሰድና እንመልከተው። በተረት አውድ ላይ ጥሩ ተራች ሲተርት ታዳሚው በፀጥታ እንዲከታተለው የተረቱን ታሪክ በድምፅም ይሁን በድርጊት በተቻለው መጠን በመግለፅ ታሪኩን መሳጭ አድርጎ

ለማቅረብ መሞከር አለበት። ከዚያ በተጨማሪ የተረቱን ታሪክ በደንብ ማወቅ አለበት ይህ ሲሆን ታድያ በዙርያው ያለ ታዳሚ የሚያሳዝን ታሪክ ሲገጥመው እያዘነ የሚያስቅ ታሪክ ሲገጥመው ደግሞ እየሳቀ አብሮት ይቀጥላል። ካልሆነ ግን ታዳሚው ሌላ ነገር በማድረግ (በመሃል ተነስቶ መሄድ ወይም ሌላ ጉዳይ ማውራትን ይጨምራል) ፣ ጣልቃ ገብቶ በማስቆም አስተያየት በመስጠት ድባቡን መቀየሩ አይቀሬ ይሆናል።

ከነዚህ ጉዳዮች በተጨማሪ በክዋኔ ላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ በክዋኔው ወቅት የሚተላለፈው መልእክት ነው። በአንድ ክዋኔ ላይ ከማዝናናት እና ጊዜን ለማሳለፍ ከሚደረጉት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ውጪ አብዛኛዎቹ ክዋኔዎች ማህበረሰቡ ሆነ ብሎ የተለያዩ መልእክቶችን ለማስተላለፍ የሚከውናቸው ናቸው። ይህንን በተመለከተ ዘሪሁን አስፋው ፣(1996፡ 20)

> በስነቃል ህዝቦች ማንነታቸውን ያሳዉቁበታል የዝርያቸውን አመጣጥ ይተርኩበታል። ስለአካባቢያቸውና ባጠቃላይ ስለአለማቸው ያላቸውን ፍልስፍና ይቀርፁበታል። ወግና ልማዳቸውን አጠንክረው የሚያቆዩበት ዋነኛ መሳርያቸውም ነው። ... ሰናይ የሚሏቸውን ማህበራዊ እሴቶችና ልማዶች ተጠብቀውና ተከብረው እንዲቆዩ እኩይ የሚሏቸው ደግሞ እንዲወገዱ ያደርጉበታል።...

ይላሉ። ታድያ ይህ ጥቂት የማይባል ተግባር የሚኖረው ህብረተሰቡ በስነቃሉ አማካይነት ለትውልዱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚያስተላልፋቸው በርካታ መልእክቶች አማካይነት መሆኑን በግልባጭ የምንረዳው ነገር ነው። እዚህ ላይ በተጓዳኝ የምንመለከተው ነገር የአንድን ፎክሎር ተግባር ለማወቅ የተባለበትን አውድ ማወቁ የግድ የሆነ ተግባር መሆኑን ነው። ለምሳሌ ምሳሌያዊ አባባሎችን ከአውድ ለይተን በምናይበት ጊዜ የሚኖረው ፍቺና ከነአውዱ ሲሆን የሚሰጠው ፍቺ የተለያየ ስለሚሆን ተግባራዊነቱ ይበልጥ የሚከሰተው የተነገረበት አውድ በውል ሲታወቅ እንደሆነ እንረዳለን። እዚህ ላይ የፎክሎርን ተግባር ማውሳቱ አስፈላጊ በመሆኑ በዚሁ ወደ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ቅኝት እገባለሁ።

2.2.3. የዝርው ቃል ተረክ ተግባር ቅኝት

የአንድን ማህበረሰብ ፎክሎር ለመግለፅ ከሚያገለግሉ መሰረታዊ ንድፈ ሃሳቦች መሀከል አንዱ የፎክሎሩን ተግባር ለመፈተሽ የሚውለው የተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ነው። ይህ ንድፈ ሃሳብ በዋነኛነት ፎክሎሩ ለተፈጠረበትና ለሚከወንበት ማህበረሰብ የሚኖረው ተግባር ወይም ፋይዳ መፈተሽ ላይ የሚያተኩር ነው። በዚህ የተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ላይ ያቀነቀኑ የተለያዩ ምሁራንን የምናገኝ ሲሆን ከነዚህም Martha and Martine ፣ William R. Bascom፣ Richard M. Ddorson እና ከሀገራችን ምሁራን መሀከል ደግሞ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘን ልንጠቅስ እንችላለን። Sims and Martine (2005: 174) As Folklorists, we examine the verbal, customary and material texts of folk groups to discover why and how it is important to the people sharing it. በማለት ቃላዊም ሆኑ ቁሳዊ ሃብቶቻችን መፈተሽ እና መመዘን ያለባቸው ባለቤታቸው በሆነው የፎክ ቡድን ውስጥ ለምን እና እንዴት አስፈላጊ እንደሆኑ እና እንደሚጋሯቸው በመጠየቅ እንደሆነ ይገልፃሉ።

የፎክሎር ተግባራትን በተመለከተ እነ Sims ሲያነሱ ከጠቀሷቸው መካከል Bascom (1965፣ 293) የፎክሎር ተግባራት ብለው የሚከተሉትን አራት ነጥቦችን አስፍረዋል።

- Education, particularly, but not exclusively, in non-literate societies
- To escape from limits or impositions the culture places on us.
- Maintaining conformity to the accepted patterns of behavior
- Folklore validates culture. (Sims, Martha 2005፡ 174-175)።

ይህ ሃሳብ በንድፈ ሃሳቡ አቀንቃኝ ምሁራን ዘንድ ትችት ያስነሳባቸው ሲሆን የትችቶቹ መነሻ የሆኑ ነጥቦችን ((Sims, Martha 2005፡ 176-177) ጠቅሰዋል። ከነዚህም ነጥቦች የመጀመሪያው በፎክሎር ተግባርነት የተጠቀሱ ነጥቦች ሲዘረዘሩ መዘርዘር የነበረባቸው አይቀሬ የሆኑ ነጥቦች ማለትም ፎክሎር የሚጠየቅበትን፣ የሚተችበትን ... ወዘተ በተግባር ውስጥ ምንም ያልተባለባቸው ጉዳዮች መሆናቸው።

ሌላው የሚጠቀሰው ነጥብ ፎክሎር በሁሉም አንድ አይነት እንደሆነ እና ሁሉም የፎክሎር ዘውጎች አንድ አይነት ፋይዳ እንዳላቸው አድርጎ በመግለፅ በተጠቃለለና በተወሰነ መጠነ ስፋት ውስጥ የተቀነበበ የተግባር ነጥብ ማስቀመጥ ፎክሎርን ለሚያክል ፅንሰ ሃሳብ እጅግ አስቸጋሪ መሆኑ ነው።

ምክንያቱም ይህ ሀሳብ በፎክሎር የለውጥ ሂደት ውስጥ የሚከሰቱ ለውጦችን ለማስተናገድ እድል የሌለው ከመሆኑም ባሻገር የማህበረሰብን ለውጥ የዘነጋ በመሆኑ ወደተሳሳተ አቅጣጫ ይመራል። ይህም ብቻ ሳይሆን ንድፈ ሃሳቡ በራሱ ችግር እንዳለበት ነው የሚጠቁሙን። ይህንን ሃሳባቸውን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ከመፅሃፋቸው ውስጥ ቃል በቃል ወስጀ አቀርበዋለሁ።

> And of course if the function never changes, that implies the groups never change. In addition to assuming that all groups work in the same way, functionalism implies that groups stay the same across time and that societies are unchanging. Working with this methodology, the functional approach is always conservative and static; the functions themselves are conservative. /2005; 176/

እነ Sims, በዚህ ሳያበቁ በሌሎች ምሁራን የተባሉትንም (የተሰጡትንም) ንድፈ ሃሳቦች አንስተው ያሉባቸውን ክፍተቶች ከጠቋቆሙ በኋላ በዋነኛነት ተግባር /function/ ስለሚለው ቃል ምንነት the role or purpose of some thing or someone play in a given setting-(177) በማለት አጠቃላይ ፍቺ ሰጥተዋል። ይህንን መሰረት አድርጎ የአንድን ፎክሎር ተግባር (ሚና) መመርመር ሚናውን የበለጠ ለመረዳት ያስችላል። እዚህ ላይ ግን በዋነኛነት ማስተዋል ያለብን ነገር ንድፈ ሃሳቡ ማለትም "Functionalism theory" የራሱ የሆኑ ችግሮች ቢኖሩበትም አሁን ላይም ቢሆን እየተሰራበት ያለ መሆኑ ነው።

Dorson /1972፡ 25/ ስለተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ "Functionalism theory" ባነሱበት ክፍል ውስጥ ቴክስትን ሲገልጹ "In the functional theory, the text itself is meaningless apart from its living presentation or performance to responding audience." ይላሉ። እናም አንድ ቴክስት በአንድ አውድ ላይ ከዋኝና ታዳሚ ባለበት ካልተከወነ በስተቀር ቴክስቱ ብቻውን በራሱ ምንም ማለት እንዳልሆነ ያስገነዝባል።

ይህንን ሀሳብ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የአንድ ፎክ ቡድን ስነ-ቃልን ለንሳሌ ብንወስድ የስነ-ቃሉን ተግባር (ፋይዳ) ለመረዳት ስነ-ቃሉን ብቻ ይዘን ይዜ ነው ብለን እርግጠኛ የሆነ ነገር ለመናገር አንችልም። ምክንያቱም አንድም አውዱን ካላወቅነው በስተቀር ፍፁም ልንረዳው አማንችለው ስነ-ቃል ሊገጥመን ይችላል። አንድም ደግሞ አንድ ስነ-ቃል በተለያየ አውድ ቀርቦ

የተለያየ ተግባር ሊኖረው ይችላልና። ስለሆነም ስነ-ቃሉ ባለቤቱ በሆነው ማህበረሰብ ውስጥ ሲከወን አውዱን እና በዙርያው ያሉ ሌሎችንም ነገሮች መመልከት መቻል አለብን።

ይህንን የአውድ (context) ጉዳይ በተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ውስጥ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ መሰረታዊ ነገር ነው። ለምሳሌ የሚት ጥቅም ቅድስናን ማዝለቅ ሲሆን የምሳሌያዊ አባባል ጥቅም ሰላማዊ ሁኔታን ለመፍጠር (ለማረጋጋት) ነው። /Dundes፡ 1978: 27/ እናም ተግባር ወይም ሙያ ከተለያዩ ሁነቶች /አውዶች/ ተነስቶ ተንታኙ የሚደርስበት የፎክሎሩ አቅም ወይም አገልግሎት መሆኑን በመግለፅ በተለይም ቃላዊ ለሆነው የፎክሎር ዘውግ ተግባሩን ለመረዳት አውዱን ማወቅ መሰረታዊ ጉዳይ እንደሆነ በመጥቀስ ከላይ የገለፅኩትን ሃሳብ ያጠናክሩልናል።

ፈቃደ አዘዘ /1991፡17/ አጠቃላይ የስነ-ቃል ተግባራት ብለው አምስት ዓበይት ነጥቦችን ዘርዝረዋል። ተግባራቱም፡- የመግለጥ ተግባር፣ የማጠናከርና የመትከል ተግባር፣ የማምለጭ ተግባር፣ የማስተማር ተግባር፣ የመግታት- የመቆጣጠር ተግባር ሲሆኑ እነዚህን አምስት ተግባራት ደግሞ አንድ በአንድ ምን ማለት እንደሆኑ በዝርዝር በምሳሌ አስደግፈው ይገልጿቸዋል። ተግባራቱም በዝርዝር ተለያይተው ይጠቀሱ እንጂ በመሀከላቸው ከፍተኛ የሆነ ቁርኝት አላቸው።

በአጠቃላይ እነዚህ የተመለከትናቸው ተግባርን የተመለከቱ ንድፈ ሀሳባዊ ነጥቦች በፎክሎር ጥናት ውስጥ የንድፈ ሀሳቡን ጠቀሜታ የሚገልፁ ናቸው። ይህ ጥናት ደግሞ በበና ማህበረሰብ ውስጥ በዝርው ቅርፅ የሚገኙትን የስነ-ቃል ዘርፎች ተግባር የሚመረምር በመሆኑ እነዚህን ነጥቦች ከግምት አስገብቶ የቀረበ ነው።

3. የበና ብሔረሰብ አካባቢያዊና ማህበረ-ባህላዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ስለ በና ብሔረሰብ አጠቃላይ ገለጻ ይቀርባል። በተለይ ስለአካባቢው መልክዓምድር፣ ስለብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥ፣ ቋንቋ፣ ኢኮኖሚ፣ ጋብቻ፣ ማህበራዊ ልማዶችና ባህላዊ አስተዳደር ላይ ትኩረት ይደረጋል።

3.1. መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ

የደቡብ ኦሞ ዞን በደቡብ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ዞኖች አንዱ ሲሆን በውስጡም ስምንት ወረዳዎች ይገኛሉ። በዞኑ ከሚገኙ 8 ወረዳዎች መካከል የበና ፀማይ ወረዳ አንዱ ነው። ወረዳው እንደ አሁኑ በወረዳነት ከመደራጀቱ ከ1993 ዓ.ም በፊት ከሐመር ወረዳ ጋር አንድ በመሆኑ የሐመር በና ወረዳ በመባል ይታወቅ ነበር። በውስጡ የበና የፀማይና የብራይሌ ብሄረሰቦች ይገኛሉ። ወረዳው ከክልሉ በደቡብ ክፍል 0.5-40^0 471 ሰሜናዊ ኬንትሮስ 0.36-59^0 436 በስተምስራቅ ኬክሮስ መስመር ክልል ውስጥ ሲገኝ ከፍታውም ከባህር ጠለል በላይ ከ526—1645 ሜትር እንደሚደርስ የወረዳው ፋይ/ኢ/ል/ጽ/ቤት በ2003 ዓ/ም ሐምሌ ወር ላይ ያዘጋጀው የአምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሰነድ ያሳያል።

በና ፀማይ በስተሰሜን ከደቡብ አሪና ከማሌ ወረዳ፣ በስተደቡብ ከሐመር ወረዳ፣ በስተምዕራብ ከሳላማሳ ወረዳ፣ በስተምስራቅ ከኮንሶ ልዩ ወረዳዎች ይዋሰናል። አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱም 2549.07 ስኩየር ኪ.ሜ ሲሸፍን በዉስጡም 18 የበና ቀበሌዎች እና 13 የፀማይ ቀበሌዎች በድምሩ 31 ቀበሌዎችንና አንድ ታዳጊ ማዘጋጃ ቤት ይዟል። ዋና ከተማዋ ቀይ አፈርን ከክልሉ ርዕሰ ከተማ አዋሳ በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ 457 ኪሎ ሜትር ስንጓዝ እናገኛታለን። የበና፣ የፀማይ እና የብራይሌ ብሔረሰቦች በዋናነት በወረዳው ሲኖሩ ጥቂት ቁጥር ያላቸዉ የተለያዩ ብሔረሰብ አባላትም በተጨማሪነት ይገኛሉ። በንኛ እና ፀማይኛ በወረዳው የሚነገሩ ዋነኛ ቋንቋዎች ናቸው። በወረዳዋ ከሚገኙ ብሔረሰቦች እንጨቱ ተብሎ በሚጠራዉ ቀበሌ የወይጦ ወንዝ ዳርቻን ተከትለው የሰፈሩት ብዛታቸው 5002 አባላትን የያዘው የኦንጎታ ቋንቋ ተናጋሪዎቹ የብራይሌ ብሔረሰቦች ቋንቋ በመጥፋት ላይ እንደሚገኝና ትክለኛው የቋንቋው ተናጋሪ ሰዎችም 5 ብቻ መቅረታቸውን መረጃዎች ያሳያሉ (ዩኒክ ኢት.ቁ.1፤ ህዳር 2004፤ ገጽ 70)።

የወረዳዉ ጠቅላላ ህዝብ ብዛት ወንድ-33,595፣ ሴት-31,034 በድምሩ-64,629 መሆኑን በ2004 ዓ/ም በወረዳው ፋ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት የሥነ-ህዝብ ክፍል የተዘጋጀው መረጃ ይገልጻል። ወረዳው በሦስት ስነ-ምህዳሮች /Agro Ecology Zone/ የተከፋፈለ ሲሆን ቆላ 81.3 በመቶ፣

ደረቅ ወይናደጋ 13.7 በመቶ እና በረሃ 5 በመቶ ሽፋን አላቸው። አማካይ የዝናብ መጠኑም ከ206—570.5 ሚሊ ሜትር ይደርሳል። በተጨማሪም ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴንቲ ግሬድ 47^0C፣ ዝቅተኛዉ 16^0C፣ ሲሆን አማካይ የሙቀት መጠኑም 35^0Cመሆኑን በወረዳው ፋ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት በ2003 ዓ/ም ነሐሴ ወር የተዘጋጀው የአምስት ዓመት /ከ2003-2007/ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሰነድ ይገልጻል (ገጽ 2 እና 3)።

ከወረዳዉ ጠቅላላ ህዝብ ቁጥር ጥናቱን የማደርግባቸዉ የበና ብሄረሰብ ብዛት ወንዶች- 15,861፣ ሴቶች- 15,548 በድምሩ- 31,409 ሲሆን ከወረዳዉ ጠቅላላ የህዝብ ቁጥር ሰፊዉን ድርሻ ይይዛሉ። ለጥናቱም የአልዱባ ቀበሌን ዋነኛ ማዕከሌ በማድረግ የጉርዶ፣ የቦሪ፣ የዲዚ አማና የሞርገላ ቀበሌዎችን አካትቻለሁ።

3.2. የበና ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ

የበና ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥን በተመለከተ የማህበረሰቡ ዕድሜ ጠገብ ሽማግሌ በታሪክ የሰሙትን ሲገልጹ፤

> የበና ብሔረሰብ ከየት መጣ? ብለን የድሮ አመጣጥ ታሪክን ስናይ ሁለት ይዘት አለዉ። አንደኛዉ እዚሁ ከበና ምድር የፈለቁና ሁለተኛዉ ከየአቅጣጫዉ ወደዚህች ምድር ፈልሰዉ የመጡ ናቸዉ ይላሉ። (ግራዝማች አድነዉ ጋርሾ፣ የብሄረሰቡ ጎሳ መሪ)።


ከበና ጎሳዎች ውስጥ ጥንት በበና ምድር ላይ የነበሩ (በእነሱ አባባልም በመጀመርያ የበና ምድር ላይ ከመሬት የፈለቁ) የሚባሉት የ"ጋሲ" ጎሳዎች ሲሆኑ ታሪካዊው ቦታም አሁን ላይ "ጉርዶ" ተብሎ የሚጠራዉ የበና ቀበሌ ነዉ። ሌሎቹ ጎሳዎች ግን ከአራቱም ማዕዘናት ፈልሰዉ ወደ በና ምድር የገቡ ናቸዉ። ግራዝማች አድነዉ ጋርሾ የበና ቢታ ስለዚህም ጉዳይ አያይዘው ሲያብራሩ፡-

> እዚህ በና ምድር ላይ የፈለቁት የጋሲ ጎሳዎች ናቸዉ። ሌሎቻችን ከየአቅጣጫዉ ነዉ የመጣነዉ። እኔ አሁን ከገታ ጎሳ ነኝ። የኛ ጎሳ ወደ በና ምድር የመጣው ከአሪ ህዝብ ባኮ ተብሎ ከሚጠራ ቦታ ነዉ። ፕሬንና ዱማ በመባል የሚታወቀዉ ጎሳ ከቦረና መስመር ነዉ የመጣዉ፣ በነት የሚባለዉ ጎሳ ከገዋዳ ህዝብ አሌ ከሚባል ቦታ ነዉ የመጣዉ፣ ወልመክ ከካሮ ሲሆን ገርሺማ ከማሌ ነዉ የመጣዉ" በማለት የብሄረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ ይገልጹና አያይዘዉም "የእኔ ጎሳ ገታ ወደ በና ምድር እንደ መጣ የሰፈረዉ እዚህ አሁን አንቺም የምታይው ፔንቴ ተራራ ስር ነው። (አሁንም ቢታና ቤተሰቦቻቸው ከተራራዉ ስር ናቸዉ)

ከዚሁ አቅራቢያ በዚሁ ምድር የፊለቁት ጋሲዎች ጉርዶ የሚባል ቦታ ላይ ነበሩ (ጉርዶ ከፔንቴ ተራራ ከ5 -7 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ቀበሌ ናት) ሰዎች ቢታ የሰፈረበትን ቦታ እየተጠጉ መስፈር ጀመሩ። በዚህ መልክ ተባዝተን ለዚህ በቃን (ግራዝማች አድነዉ ጋርሾ፣ 6/07/2004 ዓ/ም፣ የካሴት ቁ.15/ሀ)።



ፎቶ-1 ግራዝማች አድነው ጋርሾ የበና ማህበረሰብ 9ኛ ቢታ



ፎቶ-2 ቢታው ከስሩ የሠፈሩበት የፔንቴ ተራራ

የበና ብሄረሰብ የሚኖርበት የበና ፀማይ ወረዳ ካሉት 31 ቀበሌዎች መካከል ዉሩሪ፣ አንሶንዳ፣ በፎ፣ ስሌ፣ ሞርገላ፣ ቦሪ፣ አልዱባ፣ ጉርዶ፣ ዲዚ አማ፣ ሻባ መሮ፣ ሻባ አርገመንዳ፣ አልካ ኪቦ፣ አርጎ፣ መቀጫ፣ ቃቆ፣ ጎልድያ፣ ይርጋና ጫሊ ተብለዉ በሚጠሩ 18 ቀበሌዎች ነው። ግራዝማች አድነዉ ጋርሾ የበና ምድር ወሰን ከየት ተነስቶ የት እንደሚደርስና ቢታው (የጎሳ መሪው) እያስተዳደሩ ያለውን ቦታ ሲያካልሉም እንዲህ ይላሉ፤

> በአሪ በኩል ድንበራችን ቃቆ ተብሎ የሚጠራዉ ወንዝን መነሻ አድርጎ የጫሊ ተራራን ያካትታል፣ በማሌ በኩል ጫሊ ሰሌ ተብላ የምትጠራውን ቦታ ይዞ እስከ ፀማይ ይቀጥላል። በመርሲ በኩል የማጎ ፓርክ የኔ ድንበር ነው፣ በሐመር በኩል ፐርዳንባይኖ ተብሎ የሚጠራ ደራሽ ውሃ አለ፤ ሰፊ አሸዋ ነው እዚያ ድረስ የኔ ህዝብ ነው። እናም የኔ ህዝብ ሰፊ ህዝብ ነው። አሁንም ድረስ የነሱ ቤት (የጎሳ መሪ) እኔ ነኝ (የበና ዘጠነኛ ቢታ ግራዝማች አድነው ጋርሾ፤ ቦሪ ቀበሌ፤ 6/7/04 ዓ/ም)።

የወረዳው ካርታም የበና ብሔረሰብ በዙሪያው ካሉ የተለያዩ ብሔረሰቦች ጋር ማለትም በስተሰሜን ከአሪ ብሔረሰብ፣ በስተደቡብ ከሐመር ብሔረሰብ፣ በስተምዕራብ ከካራና ከመርሲ ብሔረሰብ፣ በስተምስራቅ ከጸማይ ብሔረሰብና በሰሜን ምስራቅ ከማሌ ብሔረሰብ ጋር እንደሚዋሰን ያሳያል።

3.3. ቋንቋ

የበና ብሔረሰብ የአፍ መፍቻ ቋንቋው "በንኛ" የሚባል ሲሆን ቋንቋው በደቡብ ምስራቅ ኦሞአዊ የዘር ግንድ ስር እንደሚመደብ፣ Bender (1976:47) ይገልፃል። ከዚህ በተጨማሪ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የብሔረሰቦች ምክር ቤት አማካይነት በተዘጋጀው "ዩኒክ ኢትዮጵያ" የደቡብ ፈርጦች መጽሔት ላይ ቋንቋው ከመግባቢያነት ባለፈ የስራና የትምህርት መስጫ ቋንቋ እንዳልሆነና ለዚህ ደግሞ በዋናነት የተማረ የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት እንደሆነ ይገለፃል (ቁ.1፣ ህዳር 2004፣ 66)።

ይህ ዩኒክ መጽሔት በተመሳሳይ ገጹ ላይ በቋንቋው በ1987 ዓ/ም የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም እና በ1994 ዓ/ም ደግሞ የመሰረተ ትምህርት ማስተማርያ መጽሐፍ እንደተዘጋጀ ይገልጻል። ከዚህ በተጨማሪ ግን በ2001ዓ/ም በአልዱባ ኤስ.አይ.ኤም የትርጉም ስራ ፕሮጀክት አማካይነት በቋንቋው "በና-አማርኛ-እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት"፣ የተለያዩ በራሪ ወረቀቶች እንዲሁም መጽሄቶች ተዘጋጅተው ለማግኘት ችያለሁ። ብሔረሰቡ ከበንኛ ቋንቋ ባሻገር ሐመርኛን አቀላጥፎ መናገር ከመቻሉ በተጨማሪ በዙርያው ከሚያጎራብቱት ሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ካለው ቀረቤታ አንጻርም ፀማይኛን፣ አሪኛን፣ ማሌኛን እንዲሁም አማርኛን በተወሰነ መልኩ መናገር ይችላል።

3.4. ኢኮኖሚ

የበና ፀማይ ወረዳ በደቡብ ኦሞ ዞን አርብቶ አደር ወረዳዎች በመባል ከሚታወቁ 6 ወረዳዎች መካከል አንዱ ነዉ። ወረዳው አርብቶአደር በመባል የተለየበት ምክንያትም የብሔረሰቡ ኢኮኖሚያዊ መሰረት የተገነባዉ የእንስሳት እርባታ ላይ በመሆኑ ነዉ። የዳልጋ ከብት (ላምና በሬ)፣ ፍየሎች ዋነኛ የሚያረቧቸዉ እንስሳት ሲሆኑ በግ፣ ዶሮና ግመልም ተጠቃሾች ናቸዉ። ባህላዊ ቀፎ በመስቀል ንብ ማነብ ሌላው የኢኮኖሚ መሰረታቸው ነው።

በናዎች የእንስሳታቸዉን ቁጥር መጨመር የሀብታቸዉ መገለጫ በማድረጋቸዉ ከራሳቸዉ ምቾትና ተስማሚ አኗኗር ይልቅ ለከብቶቻቸዉ ምቾትና ተስማሚ ቦታን በመፈለግ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ዘመናትን አሳልፈዋል። ይህም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ የእንስሳት ሀብት ባለቤት እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። በቁጥርም፡-የዳልጋ ከብት (ላምና በሬ)- 201,145፣ ፍየል-263,300፣ በግ-79,380፣ ዶሮ-21,945፣ የጋማ እንስሳት- 20,005፣ ግመል-123 መሆኑን የ2004ዓ/ም የወረዳዉ አርብቶ አደር ልማት ጽ/ቤት መረጃ ያሳያል።

ከእርባታዉና ንብ ከማነብ ጎን ለጎን ከተረጂነት ተላቀዉ እራሳቸዉን እንዲችሉ መንግስት በዘረጋዉ እስትራቴጂ የእርሻ ስራ እንዲጀምሩ በመደረጉና ለአከባቢዉ አየር ተስማሚ ምርት እንድዲያመርቱ እየተደረገ ባለዉ ጥረት ወደ ከፊል አርሶ አደርነት በመቀየር ላይ ካሉ ቀበሌያትም ጎልድያ፣ ቃቆ፣ ይርጋና ጫሊ ተጠቃሽ ናቸው። በቆሎ፣ ማሽላና ዳጉሳ ዋና ምርቶች ሲሆኑ ጤፍና አደንጓሬ በከፊል ያመርታሉ።

ከወረዳዉ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት ሊለማ የሚችል መሬት 38,380 ሄክታር ሲሆን የለማ 29,888.4 ሄ/ር፣ ለግጦሽ አገልግሎት የዋለ 77,134 ሄክታር፣ በደን የተሸፈነ 4,017.8 ሄክታር፣ ሊለማ የማይችል ገደላማና ድንጋያማ 30,170.23 ሄክታር መሆኑን የወረዳዉ አርብቶ አደር ልማት ጽ/ቤት መረጃ ያሳያል። ይህም ሰፊ ድርሻ ይዞ ያለዉ ለግጦሽ የዋለ መሬት መሆኑ የማህበረሰቡ አኗኗር እርባታ ላይ ትልቅ መሰረት እንዳለዉ የሚያረጋግጥ ነዉ።

3.5. ጋብቻ

በበናዎች ውስጥ ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ተግባራት አንዱ ጋብቻ ነው። በብሔረሰቡ ውስጥ አመኔታ ተሰጥቶት እንደ ሙሉ ሰው መቆጠር የፈለገ አባል እድሜው ለጋብቻ በደረሰ ጊዜ በጋብቻ መወሰንና ዘሩን መተካት ይኖርበታል። በብሔረሰቡ ሁለት አይነት ጋብቻዎች ያሉ ሲሆን የአፃ ሥርዓትን ፈፅሞ የሚደረግ ጋብቻና የውርስ ጋብቻ ናቸው።

ሀ/ በአፃ ሥርዓት የሚፈጸም ጋብቻ፡- አንድ ወጣት የሚፈልጋትን ሴት ለማግባት ከፈለገ በብሔረሰቡ የሚከናወነውን ታላቁን የአፃ ሥነ-ሥርዓት ማከናወን ይጠበቅበታል። ይህንን ሥርዓት ሳይፈፅሙ መጋባት በበናዎች ዘንድ የተወገዘ ሲሆን ያገባ እንኳ ቢኖር የሚወልደው ልጅ "ሚንጊ" የሚባል ከመሆኑ በተጨማሪ ባልም ሆነ ሚስት የብሔረሰቡን ሥርዓት በመጣሳቸው በአጠቃላይ ማህበራዊ ጉዳዮች የተገለሉና የተናቁ ይሆናሉ።

አፃ ማለት የበና ወጣት ለጋብቻ የሚፈልጋትን ሴት ለማጨት ይችል ዘንድ የሚፈፅመው ከከብቶች ላይ የመዝለል ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት ለጋብቻ ከማጨት በተጨማሪ ሙሉ በና ነኝ ብሎ ለመናገርም ጭምር የሚፈፀም ሥርዓት ነው። እድሜው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነው ወጣት ከቤተሰቦቹ ጋር ከብት የሚዘልበትን ቀን ይወስናል። ከዝግጅቱ ሁለትና ሶስት ወር ቀድሞ እሩቅና ቅርብ ላሉ ዘመድ አዝማዶችና ለአከባቢው ጥሪ ይተላለፋል። የጥሪ ሂደቱ ማህበረሰቡ ማንበብና መፃፍ ባለመቻሉ የራሱ የጥሪ ማስተላለፊያ መንገድ እንዲከተል አድርጎታል። ጥሪ የሚተላለፈው ገመድ ቋጥሮ በመላክ ነው። አንድ ቋጠሮ

የአንድ ሣምንት ጊዜ የያዘ ሲሆን መነሻውንም ሐሙስ ያደርጋል። ምክንያቱ ደግሞ በሁሉም በናዎች ዘንድ የሚታወቀው የወረዳቸው ርዕሰ ከተማ ቀይ አፈር የገበያ ቀን ሐሙስ በመሆኑ ነው።

ለምሣሌ፦ ከሁለት ወር በኋላ አዓ ወይም የከብት ዝላይ ሥርዓቱን ለመፈፀም የፈለገ ገመዱን ስምንት ቦታ ቋጥሮ ከስምንት ሐሙስ በኋላ ቀጥሎ ባለው ቀን ብሎ ይልካል ማለት ነው። አንዷ ቋጠሮ አንድ ሣምንት በውስጧ ስለምትይዝ ታላቁ ሐሙስ ገበያ በደረሰ ቁጥር አንዷ ቋጠሮ ትፈታለች። በዚህ መልኩ ይቀጥልና የመጨረሻው ቋጠሮ በተፈታች ማግስት ሁሉም ታዳሚዎች ሥርዓቱ በሚፈፀምበት ቦታ ይሰባሰባሉ። ስለዚህ ብዙውን ጊዜ በበናዎች ከብት የሚዘለልበት ቀን አርብ ላይ ይውላል ማለት ነው።

በዚህም ቀን በርካታዎች ከየአቅጣጫው ይሰባሰባሉ። ከብት ታርዶ ይበላል፣ የአከባቢው ባህላዊ መጠጥ ፕርሲ/ከማሽላና ከበቆሎ ዱቄት የሚዘጋጅ ባህላዊ መጠጥ/ ይጠጣል ይጨፈራል። እስከ እሁድ በዚህ መልኩ ቀጥሎ በሶስተኛው ቀን እሁድ አመሻሹ ላይ ሁሉም ወደየመጣበት ይበተናል። በዚህ የአዓ ሥርዓት ላይ ከሚፈፀሙና ሥርዓቱን ከሚያስፈጽሙ አካላት ዋናዎቹ ከብት መዝለል እና ማዝ ናቸው፦

ከከብት መዝለል፣ ቁጥራቸው ስድስትና ከዚያ በላይ የሚሆኑ ከብቶች ፊታቸውን ወደ ፀሐይ መውጫ ማለትም ወደ ምሥራቅ እንዲያዞሩ ይደረግና በተመረጡት ሰዎች ቀንዳቸውና ከኋላ ደግሞ ጭራቸው ተወጥሮ እንዲያዙ ይደረጋል። ዘላዩ መነሻውን ከደቡብ ያደርግና ወደ ሰሜን ከተደረደሩት ከብቶች መጀመሪያ ላይ ከቆመችው ዘሎ በመውጣት ሌሎችን እየረገጠ በሩጫ ያልፋል። ቀጥሎም በዚህ መልክ ከሰሜን ወደ ደቡብ ይመለሳል። በዚህ ሁኔታ አራት ጊዜ ያለምንም መውደቅ ይመላለሳል። በዝላይ ሂደት ላይ እያለ ከከብቶች ከወደቀ ከፍተኛ ስድብና ዱላ ከሚገረፉለት ሴቶች ስለሚገጥመው በጥንቃቄ መፈፀም አለበት።

ከብቶቹ ወደ ምስራቅ የመዞራቸው ምክንያት የአገር ሽማግሌ የሆኑት የአቶ ጋርሾ ውካ ሲገልፁ ምስራቅ የፀሐይ መውጫ ስለሆነና ሁልጊዜ መልካም ነገርን ይዛ እንድትወጣ መልካምን የመመኘት ምሳሌ መሆኑን በማሰብ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ቦረና በምሥራቅ አቅጣጫ ስለሆነ ከዚህ አቅጣጫ የመጡ መኖራቸውን ለማመላከት ነው ይላሉ። ዘላዩ መነሻውንም ከደቡብ መድረሻውንም ከደቡብ አቅጣጫ ማድረጉ ከቀኝ ጀምሮ ቀኝ ላይ የሚያበቃ በመሆኑ፣ በብሔረሰቡ ዘንድ ደግሞ ብዙ ጥሩ ነገሮች የሚመሰሉት በቀኝ ስለሆነ ሕይወቱ በጥሩ ነገሮች የተሞላ እንዲሆን በማሰብ ነው።

ማዝ፣ ማለት የአፃ ሥርዓትን የፈፀመ ከክብት የዘለለ ወጣት የሚሰጠው ስያሜ ነው። አንድ የበና ወጣት ክብት ከዘለለበት ቀን አንስቶ ለጋብቻ የመረጣትን ሴት እስከሚያጭበት ጊዜ ይዞ የሚቆየው መጠሪያው ነው። ታዲያ የአፃው ሥርዓት ላይ የሚዘለልባቸው ክብቶች እንዲያዙ ማዘዝ፣ ሴቶችን መግረፍና የመሳሰሉ ተግባራትን በመፈጸም ሂደቱን በዋናነት የሚመሩት ማዞች ናቸው። የማዞች ቁጥር ይህንን ያህል ተብሎ የሚገደብ ሣይሆን በዝግጅቱ ላይ የተገኙ ማዞች ብዙም ይሆኑ ጥቂት ሥርዓቱን ይመሩታል።

ለ/ የውርስ ጋብቻ፣ በበናዎች ዘንድ የሚፈፀም ሌላው የጋብቻ አይነት የውርስ ጋብቻ ነው። የአፃ ሥርዓትን ፈፅሞ ያገባ አንድ አባወራ ቢሞት የሚች የመጀመሪያ ታናሽ ወንድሙም ሚስቱንና ሀብቱን ወርሶ ያስተዳድራል። ታናሹ አግብቶ የሚኖር ቢሆን እንኳ ሁለተኛ ሚስቱ ትሆናለች ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ አባወራው ወንድሞች ከሌሉት፣ ሚስትና ልጆቹንም ወራሽ ከሌለው ልጆችን በማሳደግ ሂደትና በኑሮ ውጣ ውረድ ያሉ ችግሮችን መቋቋም ትችል ዘንድ ለሴቷ ረዳት ስለሚያስፈልጋት "ምንይደረግ?" የሚለውን የአካባቢው ሽማግሌዎች ይመክሩና ይረዳዱ ዘንድ ለመረጡት የአካባቢው ወንድ "በስኪ" (ውሽማ) ትሁንህ ወይም በእነሱ አባባል "አንተ ውለዳት" ብለው ይሰጡታል (እዚህ ላይ ውሽምነቱ ህጋዊነት እንዳለው ልብ ይሏል)። እሱም እንደ ሚስቱ ቆጥሮ በተገቢው ያስተዳድራታል። ይህም የተመረጠው ወንድ ያገባ ቢሆን እንኳን ሁለተኛ ሚስቱ ትሆናለች። ይሁንና የመጀመሪያው ባሏ ከሞተባት በኋላ ከወረሳት ባል የሚወለዱ ልጆች ሁሉ የሚጠሩት በመጀመሪያ ሚች ባለቤቷ ስም ነው።

3.6. ሀገረሰባዊ ልማዶች

በዚህ ክፍል በሀገረሰባዊ ልማዶች ስር የሚጠኑ ጉዳዮች በሚል ፈቃደ አዘዘ (1991፡13) ላይ የጠቀሷቸው ፌስቲቫልና ክብረ በዓል፣ መዝናኛዎችና ጨዋታዎች፣ ሀገረሰባዊ መድሀኒት እና ሀገረሰባዊ ሀይማኖት ጥናቱ ከተሰራባቸው ብሄረሰቦች ባህል አንፃር ተቃኝተዋል።

3.6.1. ባህላዊ እምነቶች

በወረዳው ካለው ህዝብ መካከል፡- የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች 4102፤ የእስልምና እምነት ተከታዮች ብዛት 235፤ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ብዛት 5758፤ የካቶሊክ እምነት ተከታዮች 243 በጠቅላላ ድምሩ 10,338 ሲሆኑ ብዙ ቁጥር ያላቸው ቀሪዎቹ 39,459 (በመቶኛ 61 በመቶ) የራሳቸውን ባህላዊ እምነት ያራምዳሉ (Part1 Statistical Report on

Population Size and Characteristics. August 2010 Addis Ababa፣205) ማህበረሰቡ ከሚያምናቸውና ከሚያራምዳቸው ባህላዊ እምነቶች መካከል በርጆ፣ ጫማ ጣይዎችና ሰፊውን ድርሻ ይይዛሉ።

በርጆ፣ ቀጥታ የቃሉ ትርጉም እግዚአብሔር ማለት ነው። ታዲያ የክርስትና እምነት ተከታዮች መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን አይነት ይዘት ያለው አምልኮ አይደለም። "እኛንና ከብቶቻችንን የፈጠረ በርጆ ዳኬ /እግዚአብሔር አለ/ ብለው ያምናሉ። በርጆ አካባቢውን እንዲባርክ፣ ድርቅን እንዲያርቅ፣ ዝናብ እንዲያዘንብ፣ ከብቶቻቸውን እንዲያረባላቸውና በአጠቃላይ መጥፎ ነገርን ከአካባቢያቸው እንዲያርቅ በርጆን የመለመን ትልቅ ድርሻ ያለው ቢታ ነው። ከዚያ ባሻገር ቆግ፣ ጉዲል እና የአካባቢ ሽማግሌዎች በርጆ ጥሩ ነገርን እንዲያቀርብላቸውና ክፉውን ከነሱ እንዲያርቅ ይማፀናሉ። መስዋዕት ይሆንም ዘንድ በርጆን ለሚማፀኑት አካላት የፍዬል ወይም የበግ ጠቦት እንዲሁም ማር ይቀርብላቸዋል።

ጫማ ጣዮች፣ እነዚህ ደግሞ በብሔረሰቡ ዘንድ የተከሰተንና ወደፊት የሚከሰትን ነገር ያውቃሉ ተብለው የተለዩ ሰዎች ናቸው። በአካባቢው ዝናብ ጠፍቶ ድርቅ ሲሆን መንስኤውን ለመለየትና መፍትሔውን ለማወቅ፣ ቀዬው ያለምንም ችግር በሰላም እንዲኖር እንዲሁም ቤተሰባዊም ሆነ የግል ችግር ሲገጥም መፍትሔ ለመሻት ወደ ጫማ ጣዮች መሄድ የተለመደ ነው። ከከብት ቆዳ በስሱ የተሠራን ጫማ እያንጠባጠቡ መሬት ላይ በመጣል የጫማውን አወዳደቅና የያዘውን አቅጣጫ በማየት ትክክለኛ የሆነውን ነገር ይናገራሉ፣ የወደፊቱንም ይተነብያሉ፤ ለችግሩ መፍቻ የሚሉትን መፍትሔም ይዘረዝራሉ ጫማ ጣይዎቹ። መፍትሄው እውን ይሆን ዘንድ በሚያዙት መሠረት መሰዋዕት ይሰዋል። ችግሮችም ተወግደው ነገሮች ሁሉ ጥሩ ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል።

3.6.2. ባህላዊ ሕክምና

በበና ብሔረሰብ ዘንድ ከተለያዩ ቅጠላቅጠልና ሣር እየተቀመመ የሚሰጡ ባህላዊ መድሐኒቶች ያሉ ሲሆን ሰፊ ቦታ ይዞ የሚገኘው ግን የአራ ህክምና ነው። በዘመናዊው የህክምና ሣይንስ የተለያየ ስያሜ የሚሰጣቸው በሽታዎች እንደየአይነታቸው ህክምና እንዳላቸው ሁሉ በናዎችም አራ እና ባህላዊ ህክምናውን በሰፊው ይጠቀሙታል።

የአራ ህክምና የእንስሳትን አንጀት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሰውነትን በማልበስ የሚፈፀም የሕክምና ዘዴ ነው። አይንን ገለጥ አድርገው ሲያዩና ጥፍርን ሲያዩ ቢጫ

ለሚያደርጉ በሽታዎች የሚሰጥ ህክምና ነው። ይህንን ያውቃሉ ተብለው የሚገመቱ ግለሰቦች በሽተኛውን አይተው የፍዬል አራ ነው፣ የበግ አራ ነው፣ የዶሮ አራ ነው ብለው ይናገራሉ። ይህ ማለት መልበስ ያለበት የፍየል፣ የበግ ወይም የዶሮ አንጀት ነው ማለት ሲሆን የዶሮ አንጀት የሚታዘዘው ብዙውን ጊዜ ለህጻናት ነው። ከህጻን ውጭ ለሆኑ ግን የፍየል ወይም የበግ አንጀት ይታዘዝላቸዋል። ለህክምናውም አገልግሎት ላይ የሚውለው የነዚህ ሶስት እንስሳት አንጀት ነው።

በሽተኛው ተንጋሎ እንዲተኛ ይደረግና ፊታቸውን ሙሉ በሙሉ እና ሰውነታቸውን በከፊል የፍዬል አራ ከሆነ የፍዬል አንጀት፣ የበግ አራ ከሆነ ደግሞ የበግ አንጀት ያለብሱታል። በሽተኛውም ሙሉ በሙሉ ከበሽታው ይድናል። ይህንን ባህላዊ የህክምና ዜዴ ብሔረሰቡ ወደ ጤና ተቋማት ከመምጣቱ በፊት በሰፊው የሚጠቀመው ነው። ከዚህ ቀደም ብሔረሰቡ ውስጥ በነበርኩ ጊዜና ጥናቴን በማካሂደበት ወቅትም ይህንን የህክምና ዘዴ በተግባር የማየት ዕድሉ አጋጥሞኛል። ፈዋሽነቱንም የብሔረሰቡ አባላት ሙሉ ለሙሉ ያምኑበታል።

3.6.3. መዝናኛና ጨዋታ

ኢቫንጋዲ (የምሽት ጭፈራ)፣ በናዎች ቀኑን ከብት በመጠበቅ ውጭ የተለያዩ ሥራዎችን በመስራት ውለው ድካማቸውን የሚረሱበትና መንፈሳቸውን የሚያድሱበት ኢቫንጋዲ የተሰኘ መዝናኛ አላቸው። ኢቫንጋዲ የሚለው ቃል ከሁለት የበና ቃሎች የተመሠረተ ሲሆን ትርጉሙ ኢቫን፡-ምሽት፣ ጋዲ፡-ጭፈራ ሲሆን በጋራ የምሽት ጭፈራ የሚል ትርጓሜ አለው። የበናዎች ቀዬ ለኢቫንጋዲ ለጥ ያለ ሜዳ፣ ድንጋይና እሾህ የማይበዛበት፣ ለመንደሩ አማካይ ላይ ያለ ምቹ ቦታ ይመረጣል። ምሽት ጀንበር ካዘቀዘቀች ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት ጀምሮ ከየአቅጣጫው ወደ ተመረጠው መደበኛ ቦታ የኢቫንጋዲ ታዳሚዎች መምጣት ይጀምራሉ። ካገቡ የበና ሴቶችና ዕድሜያቸው ከ10 ዓመት በታች ከሆኑ ህፃናት በስተቀር ልጃገረዶች፣ ወጣቶች ያገቡና ያላገቡ ጎልማሳ ወንዶች ታዳሚዎች ናቸው።

ምሽቱ እየገፋ ሲሄድ ድምቀቱ እየጨመረ የሚሄደው ይህ ጭፈራ የተለያዩ አይነት የጭፈራ ስልቶች አሉት። ስልቶቹም በቅደም ተከተል ካውዴ፣ ጨራ፣ ወይሳ፣ ጉራ፣ ገለፋቆሌ፣ ቆሌ ፋራ፣ ሀሌማና ጋር ተብለው በ8 ስልቶች ይከፈላሉ። ስልቱን "በካውዴ" (ሴቶች ብቻቸውን የሚጨፍሩበት ስልት ነው) የሚጀምረው ኢቫንጋዲ በአማካይ እስከ ሌሊቱ 9 ሰዓት በድምቀት ሲጨፈር ቆይቶ ማሳረጊያውን "ጋር" (ሴትና ወንድ ተቃቅፈው በእርጋታ የሚጨፍሩበት ስልት)

በማድረግ ተጠናቆ ታዳሚዎቹ (እድምተኞቹ) ይበተናሉ። በኢቫንጋዲ ከሚከለከሉ ነገሮች መካከል የታጠቁትን የጦር መሣሪያ ወይም ስለት ይዞ መምጣትና የዝምድና ሐረግ ካላቸው ዘመዳሞች ጋር ወንድና ሴት እየሆኑ መጨፈር (መደነስ) በጥብቅ የተከለከለ ነው።

3.7. ባህላዊ አስተዳደር

የበና ብሔረሰብ የአካባቢውን ሰላም የሚጠብቅበትና ቀዬውን ለነሮ ምቹ የሚያደርግበት ባህላዊ የአስተዳደር እርከኖች አሉት። ይህ ባህላዊ መዋቅር አሁንም ጠንካራ መሰረት ያለዉና ዘመናዊው የአስተዳደር መዋቅርም አንዳንድ የመንግስት እስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም በቅንጅት እየሰራበት ያለ ነዉ። ይህ ባህላዊ አስተዳደር ቢታ፣ ቆግ እና ጉዲል በሚባሉ ሶስት ተዋረዳዊ እርከኖች የተከፋፈለ ነው።

3.7.1. ቢታ

ቢታ መሾም የተጀመረበት ወቅቱ ባይታወቅም የበናዎች የመጀመሪያዉ ቢታ አቶ አሎ የሚባሉ ነበሩ። የዘር ግንዳቸው ከገታ ጎሳ ሲሆን ወደ በና ምድርም የመጡት ከአሪ ብሄረሰብ ባኮ ከሚባል ቦታ ነዉ። የበና ቢታ መሆን የሚችለዉ ከዚሁ ገታ ጎሳ ሲሆን ንግስናዉን የሚወርሰዉም የቢታው የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ነዉ። በዚህ ቢታ ቅብብሎሽ መሰረት የመጀመሪያው ቢታ አሎ፣ ሁለተኛዉ ቢታ የአሎ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ቡኬ፣ ሶስተኛው ቢታ ጋርሾ፣ አራተኛው ቢታ ቴሶ፣ አምስተኛው ቢታ ሳራ፣ ስድስተኛው ቢታ ዶዩ፣ ሰባተኛው ቢታ ቃራ፣ ስምንተኛው ቢታ ጋርሾ፣ ዘጠነኛዉ አድነዉ ናቸዉ።

አሁን ላይ ቢታ ሆነው እየመሩ ያሉት ዘጠነኛው ቢታ ግራዝማች አድነዉ ጋርሾ ሲሆኑ በእርጅና ምክንያት ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው መስራት ስላልቻሉ የመጀመሪያ ልጃቸው ቆጻ አድነዉ የቢታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። የቆጻ ወራሽ የመጀመሪያው ወንድ ልጅ ላሌ ቆጻ ሲሆን ከላሌ በመቀጠልም የመጀመሪያው ወንድ ልጅ ጋርሾ ላሌ ቢታ በመሆን በቢታ የመተዳደር ባህላዊ የመዋቅር ቅብብሎሹ እንደሚቀጥል የብሄረሰቡ ቢታ ግራዝማች አድነዉ ጋርሾ ያስረዳሉ።

የቢታ ዋና ዋና ተግባራት፣ ይሄንን በተመለከተ አሁን ላይ በቢታነት እየመሩ ያሉት ግራዝማች አድነው ጋርሾ ሲያብራሩ የብሄረሰቡ አባላት ከሌሎች አጎራባች ብሄረሰቦች ማለትም ከማሌ፣ ከመርሲ፣ ከሐመር፣ ከካራ፣ ከኤርቦሬ ጋር እርስ በርስ ተስማምተዉ

እንዲኖሩ ህዝቦችን ማስተማር፣ የብሄረሰቡ አባላት በዕለት ተእለት ኑሮአቸዉ በሚፈጠሩ አለመግባባት ግዲያ ቢፈጸም መዳኘትና ማስታረቅ ናቸው። አንድ በና አውቆም ይሁን ሳያዉቅ የራሱን ብሄረሰብ አባል ቢገድል የሚች ወገን ሳያየዉ ገስግሶ ከቢታ ግቢ ይገባል። ከቢታው ግቢ ከገባ ማንም ለበቀል እጁን አያነሳበትም። ቢታም ጉዳዩን አጣርተዉ ሁለቱን ወገኖች በማግባባት አስፈላጊዉ የደም ካሳ እንዲከፈል አድርገው እርቅ ያወርዳሉ። ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር ግጭት ቢፈጠር ደግሞ ግጭቱ ከተፈጠረባቸዉ ብሄረሰብ የጎሳ መሪ ጋር በመገናኘት ግጭቱ የሚወገድበትን መፍትሄ በመፈለግ ሁለቱን ህዝቦች ያስማማሉ።

3.7.2. ቆግ

ይህ ባህላዊ የአስተዳደር እርከን በዘመናዊ መዋቅር ምክትል አስተዳዳሪ የሚባለዉ አይነት ነዉ። የዘር ግንዳቸዉ ከቢታ የዘር ግንድ ጋር ተመሳሳይ ከሆነው ከገታ ጎሳ ነዉ። አመጣጣቸዉና ቆግ የሚል ስያሜ ያገኙበት ታሪክ፤

> "የመጀመሪያዉ ቢታ ከገታ ጎሳ ከባኮ ምድር ወደ እኛ እንደ መጣ ህዝቡ ስለ ወደደዉ የኛ ቢታ ሁን ብሎ ሾመዉ። ከዝያ በኋላ ቆይተዉ ከዚያ አከባቢ ከገታ ጎሳ ሌሎች መጥተዉ ሰፈሩ። ይህን ጊዜ ህዝቡ እኛ አንድ ጊዜ ቢታ ሹመናል። ስለዚህ ሌላ ሁለተኛ አንሾምም እናም እናንተ ምክትል ሆናችሁ መቀጠል ትችላላችሁ አሏቸዉ። በህዝቡ ቃል መሰረት እነሱም ቀጠሉ። ቆግ የሚል ስያሜ ተሰጣቸው።" (አቶ ደሞ በዛብህ፤ የአ/ምንጭ ዩኒቨርስቲ ተማሪ፤ የብሄረሰቡ ተወላጅ)

በአሁኑ ወቅት በበና ሶስት ቆግዎች ያሉ ሲሆን በአርጎ "ቀልደዋ ዘሌ" /የቀልደዋ ቤተሰብ/ በቆግነት እየመራ ያለውም ማይሊያር ቀልደዋ፣ በሻባ "ኪሎ ዘሌ" በቆግነት እየመራ ያለውም በኒ ኪሎ ሲሆን በቢዘንዳ "ኩቲ ዘሌ" በቆግነት እየመራ ያለውም ጋያ ኩቲ ናቸው።

የቆግ ተግባራት የቢታ የቅርብ አማካሪ ሆኖ መስራትና በየአካባቢያቸዉ የቢታን ዉሳኔ ማስፈጸም፤ ዝናብ እንዲዘንብ፣ ከብቶች እንዲረቡ፣ ድርቅ እንዲጠፋ ...ወዘተ በርጆን መለመን፤ አከባቢያዊ ግጭቶችን መዳኘትና መፍታት (ከግድያ ዉጭ፤ ግድያ በቢታ ነዉ የሚዳኘዉ) በቆግ የሚፈጸሙ ናቸዉ።

3.7.3. ጉዲል

ይህ በባህላዊው መዋቅር የመጨረሻዉ የአስተዳደር እርከን ሲሆን ጉዲል ህብረተሰቡን በአቅራቢያ ማገልገል ይችል ዘንድ በየመንደሩ የሚዋቀር ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር ነዉ። በአንድ ቀበሌ ዉስጥ እንደ ቀበሌዉ ስፋትና ጥበት አንድ፣ ሁለትና ከዚያም በላይ ጉዲሎች ሊኖሩ ይችላሉ። ጉዲል በአካባቢዉ ህዝብ ከየትኛውም ጎሳ ተመርጦ የሚያገለግል ሲሆን ስነ-ምግባር መኖርና የሰዉ ደም ያላፈሰሰ መሆን ለመመረጥ የሚያበቁ መስፈርቶች ናቸዉ።

የጉዲል ተግባራት ለአዲስ አመት አዲስ እሳት ማከፋፈል፤ የዘር ወቅት ላይ ጉዲል የራሱን ዘር ቅድሚያ ዘርቶ ሌሎችም እንዲከተሉት ማድረግ፤ ምርት ከደረሰ በኋላም መመገብ ከመጀመሩ በፊት እያንዳንዱ ካመረተው የምርት አይነት ትንሽ ትንሽ ይዘው እንዲመጡ በማድረግ ያመረቱትን እንዲመገቡ መርቆ መፍቀድ ናቸዉ።

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው እነዚህ ሦስት ባህላዊ የአስተዳደር እርከኖች በበናዎች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸውና አሁንም አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ናቸው። ባህላዊ አስተዳደሮች ከመንግስታዊ መዋቅሮች ጋር ተቀናጅተው በመስራት ላይ ይገኛሉ።

4. የበና ብሔረሰብ ተረኮች ክዋኔ

ይህ ክፍል የበና ብሔረሰብ አፋዊ ዝርው ተረኮች የሚተረኩባቸውን ማህበራዊ አጋጣሚዎች (የትረካ መቼቶችን) መሰረት በማድረግ ተሳታፊውን፣ ማህበራዊ ድባቡን እና ባጠቃላይ በክዋኔ ውስጥ የማይቀሩ ወሳኝ ነገሮች ላይ ያተኩራል።

ብሔረሰቡ "ተረታ" እና "ኤዓሪ" በሚል መጠሪያ ተረኮችን በሁለት ይመድባቸዋል። "ተረታ" የሚባለው "ድሮ አባቴ እንዲህ አለኝ"፣ "ድሮ አባቴ ይህን አስተማረኝ"፣ "ድሮ አባቴ ይህን አሳዬኝ" በሚል ተጀምሮ እውነት የሚሏውን ታሪኮች የሚተርኩበትና ሲያልቅም "ከአባቴ የተማርኩት የኔ ታሪክ ይህ ነው።" በማለት የሚቋጭ የትረካ ዓይነት ነው። "ኤዓሪ" ደግሞ "ኤና ኤና ጊዜ /በድሮ ጊዜ/" በማለት ተጀምረው "እኔ የምለው በአጭሩ ይሄ ነው" በማለት ይጠናቀቃል። "ኤዓሪ" በውስጡ ሀተታ ተፈጥሮ እና ተረት (የፈጠራ ታሪክ) ይዘት ያላቸው ተረኮችን ይይዛል።

4.1. ተረኮች የሚተረኩባቸው መቼቶች

በበና ብሔረሰብ ተረኮች የሚተረኩባቸው ስድስት ዋና ዋና መቼቶች (የመተረኪያ አጋጣሚዎች) አሉ። እነርሱም፡- በመኖሪያ ቤታቸው ጠዋትና ማታ፣ በጉዲል የምረቃ ሥነ-ሥርዓት፣ በባህላዊ የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት፣ በበርቀንቴ ወቅት (በበጋ ወቅት ሳርና ውሀ ወዳለበት አካባቢ ከብቶችን ይዞ መንዝ፣ በቡኪ /በመንግስታዊና አከባቢያዊ ስብሰባዎች/ እና ጠጲ ሚጫሬ (አንድ የማህበረሰቡ አባል ጥፋት አጥፍቶ በምክር አልመለስ ሲል በአርጩሜ በመግረፍ የሚፈፀም ባህላዊ ቅጣት) ናቸው። በዚህ ክፍል እነዚህን የተረክ መቼቶች ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን።

በመኖሪያ ቤታቸው ጠዋትና ምሽት፣ ጠዋት የከብቶች መሠማርያ ሰዓት ከመድረሱ በፊት ማለትም ከንጋቱ 11:00 ሰዓት እስከ 12:00 ሰዓት ሾፎሮ (ከቡና ገለባ የሚፈላ ባህላዊ ቡና) አፍልተው የቤተሰቡ አባላት ከቤታቸው ጣሪያ ሥር ተሰባስበው እየጠጡ ይተርካሉ ምሽት ላይ ደግሞ ከብቶች ወደ በረት፣ ፍዬሎችና በጎች ወደ ጉረናአቸው ከገቡ በኋላ እራት ደርሶ እስኪመገቡ ድረስ የቤተሰቡ አባላት በመኖሪያ ቤታቸው ቅጥር ግቢ ምቹ በሚሉት ዛፍ ስር ወይም ከቤታቸው ታዛ ስር ቆዳ አንጥፈው አንዳንዴም ቦርኮታቸው ላይ ቁጭ ብለው ተረኮች ይተረካሉ።

በእነዚህ ቦታዎችና ጊዜያት በዋናነት የሚነገረው "ተረታ" ሲሆን የመተረኩም ሚና የአባወራዎች ሆኖ አልፎ አልፎም እናቶች ይተርካሉ። የቤተሰቡ አባላት በተለይ ልጆች ዋነኛ ታዳሚዎች ናቸው።

ወይዘሮ ኬሮ በላቸው የዲዚ አማ ቀበሌ ነዋሪ ሲሆኑ በአካባቢው ነዋሪም ተረኮችን ያውቃሉ ከሚባሉ ሴቶች መካከል አንዷ ናቸው። እሳቸው፤

> "ድሮ ልጅ እያለሁ አባቴ ጠዋት ከብቶችን ይዞ ከመውጣቱ በፊት ሽፎሮ ተፊልቶ እየጠጣንና ማታ ከብቶችን መልሶ ወደ በረት ካስገባ በኋላ እራት እስኪደርስ ቁጭ አድርጎ ተረታ ይነግረኝ ነበር። የአባቶችን ታሪክ እያጣቀሰ ሴት ልጅ ሊኖራት ስለሚገባት ሥነ-ሥርዓት ይተርክልኛለ። ታዲያ ለዛሬው እኔነቴ ትልቅ መሠረት ሆኖልኛል። ዛሬ ታዲያ እኔም ከአባቴ የሰማሁትን ለልጆቼ እየተረኩላቸው ነው። በዚህ ብቻ ሳላበቃ በአከባቢዬ ያሉ እናቶች ጋር ስንገናኝ የሰማሁትን ለልጆቻቸው እንዲነግሩአቸው አተርክላቸዋለሁ። "(ወ/ሮ ኬሮ በላቸው፤ ዲዚ አማ ቀበሌ፤ 3/7/04 ዓ/ም)

በማለት ጥዋትና ማታ ተረኮች የሚተረኩበትን ሂደትና የሚተረኩባቸውን ዓላማ ይገልጻሉ።



ፎቶ-3 የመኖርያ ቤት የምሽት አውድ (አባወራ ደምሴ በላቸው ከሁለት ሚስቶቹና ከአምስት ልጆቹ ጋር)

በጉዲል የምረቃ ሥነ-ሥርዓት፤ ጉዲል በማህበረሰቡ ባህላዊ አስተደደር እርከን ሶስተኛ ደረጃ ላይ ያለ የመንደር መሪ ነው። የአመቱ ምርት ተመርቶ ከማሳ እሸት ከመበላቱ

በፊት ሁሉም ካመረተው ምርት ትንሽ ትንሽ እሸት ይዞ አቅራቢያው ወደሚገኝ ጉዲል ቤት ተሰባስበው እሸቱን መብላት ይቻል ዘንድ በየዓመቱ የሚከናወን የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ነው። ይህ ስርዓት "ማሮ" (የበና ህዝብ የምስጋና በዓል) በመባል የሚታወቅ ሲሆን በጥር ወር ለሚቀበሉት አዲስ ዓመት በታህሳስ ወር መጨረሻ የሚያከብሩት የምረቃ ስርዓት ነው። በዚህ የምረቃ ሥርዓትም እሸቱ የሚበላበትን አዲስ እሳት ሰብቆ በማውጣት ጉዲሉ ለአካባቢው ነዋሪዎች ያከፋፍላል።

በዚህ ዓመታዊ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተረኮችን በደንብ ያውቃሉ የተባሉ ሽማግሌዎች ተለይተው ይመረጡና የአካባቢው ህብረተሰብ ጉዲሉ ቤት ለምስጋናው በዓል ተሰብስቦ ባለበት ለስርዓቱ ማድመቅያ የተዘጋጀውን ድግስ እየተቋደሱ ተረኮችን ይተርካሉ። በዕለቱም በጉዲሉ ቤት በዋናነት የሚተረኩት ተረኮች ትውልዱ ከአባቶቹ ሥርዓትና ደንብ ሣይወጣ በአባቶቹ መንገድ እንዲጓዝ የሚመክሩ፣ የማህበረሰቡን አመጣጥ የሚያስተምሩ፣ ትውልዱ የአባቶቹን ባህልና ወግ እንዲጠብቅ የሚያስጠነቅቁ፣ የመከባበርና የመቻቻል ልምድ እንዲዳብር የሚመክሩ "ተረታዎች" በዋናነት የሚተረኩ ሆኖ አልፎ አልፎ "ኤዔሪ"ም ይነገራል።

በባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ላይ፣ ይህ ሥነ-ሥርዓት የአካባቢው ብሔረሰብ ሰፊ የዛፍ ጥላ ስር ተሰባስበው በሽማግሌዎች መሪነት በዳይና ተበዳይ ቀርበው ፍትህ የሚሰጥበት ባህላዊ የዳኝነት ሂደት ነው። በአውዱ ወጣቶች፣ ከወጣትነት የዕድሜ ክልል ያለፉ ጎልማሶችና ሽማግሌዎች (ወንዶችም ሴቶችም) ይታደማሉ።

በዚህ አውድ የሚተረኩ ተረኮች ጠንከር ያሉ መልዕክቶችን የያዙ ከመሆናቸው በተጨማሪ ተግሳጽም ስለሆኑ በአካባቢው የሚፈሩና የሚከበሩ ሽማግሌዎች የትረካው መሪ ተዋንያን ናቸው። በጥናቱ ወቅትም በዲዚአማ ቀበሌ በቀን 3/7/04 ያየሁት በባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ላይ የነበረው ሂደት ለዚህ ዋነኛ እማኝ ይሆናል። በወቅቱ የነበረውን ሂደት በአጭሩ እንመልከት፡-

ባህላዊ ዳኝነትን ጨምሮ የተለያዩ ጉዳዮችን በሚመክሩባት የዛፍ ጥላ ስር የቀበሌዋ ነዋሪዎች ተሰባስበዋል። ሽማግሌዎች ለብቻ ከህዝቡ ትይዩ፣ ወጣቶችና ጎልማሶች ለብቻቸው፣ ሴቶችም ለብቻቸው ከሽማግሌዎች ትንሽ ወረድ ብለው ፊታቸውን ወደ ሽማግሌዎች አዙረው ተቀምጠዋል። "ያለጥፋቴ ተደብድቤ ደሜ ስለፈሰሰ ደሜ ሊካስ፣ እንባዬም ሊታበስ ይገባዋል"

በሚል ተበዳይ ነኝ ባይና "ሚስቴን በማማገጡ ነው የደበደብኩት" በሚል ደብዳቢው ሃሳባቸውን አቀረቡ።።

አቤቱታውን የሰሙ ሽማግሌዎች ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት በየተራ የተለያዩ ሀሳቦችን በማንሸራሸር ትክክለኛ ጥፋተኛውን ለመለየት የሚያስችል ሃሳቦችን ካወጡና ካወረዱ በኋላ በዛፏ ጥላ ስር ለተሰባሰቡ ታዳሚዎች በተረክ እያዋዙ መልዕክት ማስተላለፍ ጀመሩ።። መጀመሪያ የተናገሩት ሽማግሌ አቶ አልዲ ቢሮ "በእኛ በበናዎች ዘንድ የሰው ሚስት ማማገጥ "ቀይስ" /ነውር/ እንደሆነ ድሮ አባቶቻችን ያስተማሩንን ታሪክ አልሰማህም? አባትህስ ይህንን ተረታ አልነገረህም? ከአካባቢህ ሰዎችስ አልተማርክም? አንተን ጨምሮ ሌሎችም ያልሰማችሁ ካላችሁ ይህን ተረታ ስሙ፤ድሮ አባቴ የሰው ሚስት አትንካ፣ የራስህን ሚስት በባህላችን የሚፈፀመውን ሁሉ ፈጽመህ አግባ ብሎኛል።።" ብለው ሃሳባቸውን አጠቃለሉ።። ሁለተኛውም አቶ በርጊ በዛብህ ቀጥለው "ሁላችሁም ስሙ! አባቶቻችን ያስተማሩን ታማኝነትን ሆኖ ሳለ ይህንን ቃል መጣላችሁ ከየት የመጣ ነው? እኛ የምንናገረው ለማን ነው? ለሰማዩ ነው? ወይስ እኛ የምንናገረው ለምድሩ ነው? እኛን የሚሰማን ማንነው? በደንብ ስሙ! "ቀይስ" (ነውር) ከሆነ ነገር ሸሹ! አለበለዚያ ግን መጥፋታችን አይቀርም።። ..." ብለው ቁጣ በተሞላው አገላለጽ ተናገሩ።።

ሌሎችም ሽማግሌዎች በየተራቸው የሰው ሚስት እንዳይነኩ አባቶቻቸው ያዘሏቸውን ትዕዛዝ መጣስ የሚያስነቅፍ ተግባር መሆኑንና ወላጆች ተረታን ለልጆቻቸው ባለመንገራቸው የሚከሰት ጥፋት በመሆኑ ወላጆች ትኩረት እንዲሰጡ መልዕክት አስተላለፉ።። በመጨረሻም ተደብዳቢው የሰው ሚስት በማማገጡ፣ ደብዳቢው ደግሞ ለሽማግሌዎች ጉዳዩን ማቅረብ ሲገባው በራሱ እርምጃ መውሰዱ ተገቢ ስላልሆነ ሁለቱንም በባህሉ መሰረት ቀጣቸው፤ የተቀጡትንም ለሽማግሌዎች ካቀረቡ በኋላ በባህላዊ ስርዓቱ እጃቸውን ሱረት (የትንባሆ ዱቄት) ቀብተው በማጨባበጥ አስታረቋቸው።። በመጨረሻም ከቅጣቱ በተገኘው ገንዘብም ፐርሰ. (ባህላዊ መጠጥ (ጠላ)) ተገዝቶ ታዳሚው በተሟላበት ተጠጣበት።። እኔም ታዳሚ ነበርኩና ቦታዬ ከሴቶች ጋር በመሆኑ እነሱን ተቀላቅዬ ፐርሰ. ጠጣሁ።።



ፎቶ-4 ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት የትረካ መቼት (በዲዚአማ ቀበሌ)

በበርቀንቴ ወቅት፣ በርቀንቴ ማለት ለተወሰነ ጊዜ አካባቢን ለቆ ወደ ሌላ አካባቢ መሄድ ማለት ሲሆን ብሔረሰቡ አርብቶ አደር በመሆኑ የቀየው ሣር ደርቆ ከብቶቹ የሚግጡት ሲያጡና የሚጠጡት ውሃዎች ሲደርቁ በበጋ ወቅቶች ለከብቶቹ ሣርና ውሃ ፍለጋ ከአካባቢው ርቆ በወንዞች ዳርቻ ለወራት የሚቆይበት ጊዜ ነው። ወደነዚህ ቦታዎች በቅርብም በሩቅም ካሉ አካባቢዎች በርካታ ቁጥር ያላቸው ከብቶች የሚሰባሰቡ ሲሆን ወጣቶችም ከብቶችን ይዘው ይንቀሳቀሳሉ። ዝናብ ዘንቦና ሣር በቅሎ ሁሉም ወደየቀየው እስኪመለስ በዚህ ቦታ አንድ ላይ መቆየት ግድ ነው።

ታዲያ ከብቶችን ወደ ግጦሽ ሥፍራ አሠማርተው በአቅራቢያ ባለው ወንዝ ዳርቻ ካለው አሸዋ ላይ ቦርኮታ /ከእንጨት የሚሰራ ባህላዊ መቀመጫና በመኝታ ሰአትም እንደ ትራስ በመሆን የሚያገለግል/ ተንተርሶ "ተረታ" እና "ኤዔሪ" ማውራት የተለመደ ነው። በዚህ ቦታ የሚነገሩ ተረኮች በዋናነት ለልምድ ልውውጥ የሚረዱና ወቅቱን አስደሳች አድርጎ ለማሳለፍ የሚያግዙ አዝናኝ ይዘት ያላቸው ተረኮች ናቸው። ከብቶችንም ይዘው ከዚያ ቦታ የሚቆዩት ወጣቶችና ጎልማሶች በመሆናቸው ተረኮቹ የሚተረኩት በነዚሁ አካላት ነው። በጎልማሳ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት አቶ ውካ ዶይማ ነዋሪነታቸው በቦሪ ቀበሌ ሲሆን ይህንን አውድ፡-

> እኛ በርቀንቴ ስንል ከብቶቻችንን ይዘን ቃቆ ወደሚባል ወንዝ ነው የምንሄደው። ታድያ እዚያ ቦታ የኛን ጨምሮ ከሐመርና ከፀማይ አከባቢዎችም ቁጥራቸው በርካታ ከብቶች ይሰባሰባሉ። እኛም በዚህ አጋጣሚ ከብቶችን ይዘው ከመጡ የሐመርና የፀማይ ሰዎች ጋር እንገናኛለን። ብዙዎቻችን ለወላጆቻችን የመጀመርያ ወንድ ልጆች የሆንን ጎረምሶች ወይም ልጆቻችን

ለክብት ጥበቃ ስላልደረሱልን ክብቶችን ይዘን የምንወጣ ጎልማሶች ነን። ከወንዙ ዳር ቦርኮታችንን ተንተርሰን አሸዋ ላይ እንንጋለልና የሚያስቁ ኤዔሪዎችንና ከቤተሰቦቻችን የሰማናቸውን የተለያዩ ታሪኮች እያነሳን እናወራለን።(አቶ ውካ ዶይማ፤ቦሪ ቀበሌ፤16/7/04 ዓ/ም)

በማለት ይገልጹታል። በመሆኑም ይህ ጊዜ ለወራት ከቤተሰብና ከአካባቢያቸው እርቀው የሚቆዩበት በመሆኑ የቆይታ ጊዜያቸው አሰልቺ እንዳይሆን በተረኮች እየተዝናኑና እየተማማሩ የሚቆዩበት አውድ ነው።

በቡኪ /በመንግስታዊና አከባቢያዊ ስብሰባዎች/ ቦታዎች፣ ብሔረሰቡ ስለአካባቢውና መንግስታዊ አሠራሮች ለመምከር በየደረጃው ካሉ የቀበሌ፣ የወረዳ፣ የዞንና የክልል አመራሮች ጋር ሲሰባሰብ የሚወያዩበት ሀሳብ ጠቃሚና ወደ ህብረተሰቡ በፍጥነት እንዲሰርፅ የሚፈለግ ከሆነ ህብረተሰቡ ሃሳ ቡን እንዲቀበል የሚገፋፉና የሚያነሳሱ ተረኮች በነዚህ ስፍራዎች ይተረካሉ። የማይቀበሉት ሀሳብም ከሆነ የሚወያዩበት ሀሳብ ተቀባይነት እንደሌለው ሽማግሌዎች ተረክ በመተረክ ያብራራሉ።

አቶ አበባው ስዩም ትውልድና እድገታቸው ቃቆ በምትባል የበና ቀበሌ ሲሆን ለአምስት አመታትም በወረዳ አመራርነት ሰርተዋል። የስብሰባ ቦታዎችን ሁኔታ ሲገልጹ፦

> ብዙውን ጊዜ መንግስት ከህዝብ ጋር ተቀራርቦ ስለሚሰራ ለህዝቡ የሚጠቅሙ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ይዘን በተደጋጋሚ ከህዝቡ ጋር እንገናኛለን። ታድያ አንዳንድ ፕሮግራሞች አዳዲስና በህዝቡ ስላልተለመዱ ውጤታማነታቸው ላይ በአንዳንዶች ላይ ጥርጣሬን ያጭራሉ። ይህንን ያስተዋሉ በእድሜ በሳል የሆኑ ሰዎች ለመንግስትና ለበላይ መታዘዝን የሚያስረዱ ተረቶችን በመተረት መንግስት ህዝብን የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ነገር እንደማያመጣ በማሳመን ለፕሮግራሞቹ መሳካት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። በተቃራኒው በፕሮግራሙ ካላመኑበትም እንደዚሁ ከአባቶቻቸው አሰራር ውጭ መሆን አለመፈለጋቸውን የሚገልጹ ተረቶችን ይተርካሉ። ይሄኔ ግን ከመግባባት ለመድረስ በቀላሉ ስለማይቻል ከፍተኛ የሀሳብ ትግል ማድረግ ግድ ይላል። እናም አንዳንዴ ቀናትንና ወራትን የሚፈጅ ሀሳብን የማስቀየር ትግል ማድረግ ሊጠይቅ ይችላል። በዚህም ካልተሳካ ለየት ያለ የማሳመኛ ስልት ቀይሰን እንገባለን። (አቶ አበባው ስዩም፤የበና ፀማይ ወረዳ ትም/ጽ/ቤት ኃላፊ፤)

በማለት በተግባር እየገጠማቸው ያለውን ሂደት ገልጸዋል። ስለሆነም ይህ አውድ ማህበረሰቡ በሚቀርቡለት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ድጋፉን ወይም ተቃውሞውን አስረግጦ ለመግለጽ ተረኮችን በሰፊው የሚጠቀምበት ሆኖ እናገኘዋለን።

ጠጲ ሚጫሬ፣ ጠጲ ሚጫሬ ከባድ ጥፋት ያጠፋ ሰው በዕድሜ እኩዮቹ በአርጩሜ እንዲገረፍ የሚያዝ የቅጣት አይነት ሲሆን ስርቆት፣ አለመታዘዝ፣ ከብት ያለ አሳማኝ ምክንያት በተደጋጋሚ እያወጡ መሸጥ...ወዘተ ደግሞ ከሚያስቀጡ ጥፋቶች ይጠቀሳሉ። የቀዬው ሽማግሌዎችና የተገራፊው የእድሜ አቻዎች በተመረጠ ዛፍ ጥላ ስር ይሰባሰባሉ፤ ብዙውን ጊዜ የዚህ አውድ ዋነኛ ታዳሚዎች ሆነው የሚታዩት ወጣቶችና ጎልማሶች ናቸው። ለምሳሌ የሚገረፈው የ23 ዓመት ወጣት ከሆነ በቀዬው ያሉ በተለይ ደግሞ ጓደኞቹ የሆኑ በሙሉ በዚህ ቦታ መገኘት ግዴታ አለባቸው።

የሚገረፈው ግለሰብ በቦታው ከሌለ ካለበት ቦታ ፈልጎ ማምጣት፣ ከቦታው ሮጦ ቢያመልጥ አሳዶ መያዝ፤ አርጩሜ ማዘጋጀትና ሽማግሌዎች ባዘዙት መጠን መግረፍ የእድሜ አቻዎቹ የስራ ድርሻ ነው። አጥፊው እጅና እግሩ ታስሮ በሆዱ እንዲተኛ ይደረግና የእድሜ እኩዮቹ አርጩሜ ይዘው ዙርያውን ከበው ይቆማሉ። ቁጥራቸው ከ10 እስከ 20 ሊደርስ ይችላል (ቁጥራቸው የሚወሰነው በአካባቢው ባሉ በእድሜ እኩዮቹ ብዛት ስለሆነ ቁጥሩ ከዚህ ሊበልጥም ሊያንስም ይችላል)። ሽማግሌዎች ትንሽ ፈንጠር ብለው ይቀመጡና የግርፍያውን መጠን ይወስናሉ። ታድያ አንድ ግርፍያ የሚባለው ዙርያውን የከበቡት አቻዎቹ 20 ከሆኑ ሁሉም በአንድ ጊዜ እኩል አርጩሜያቸውን ጀርባው ላይ ሲያሳርፉ ነው። ሽማግሌዎቹ 10 ግረፉት ብለው ካዘዙ 10 ጊዜ በዚህ መልኩ ይገረፋል።

ሂደቱን የሚመሩት ሽማግሌዎች ጥፋተኛውን ለመገረፍ ካበቃው ጥፋት ጋር የተያያዙ ተረኮችን በየተራ በመተረክ ጥፋተኛውን ይኮንናሉ፣ አቻዎቹም ወደ ጥፋት ከመግባቱ በፊት በምክር መመለስ አለመቻላቸውን ያወግዛሉ፣ ሌሎችንም ያስጠነቅቃሉ።

4.2. የትረካ (የአተራረክ) ሁነቶች

በማህበረሰቡ ልማድ መሰረት "ተረታ" እና "ኤዔሪ" ሾፎሮ ወይም ፐርሲ እየተጎነጩ መተረክ የተለመደ በመሆኑ አንዳንዶች ተረክ እንዲተርኩ ሲጠየቁ "ተረታ" እና "ኤዔሪ" በደረቅ አፍ አይነገርም" ይላሉ። እኔም "ተረታ" እና "ኤዔሪ" ሳሰባስብ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ሾፎሮ ሌሎች ጋ ደግሞ ፐርሲ እየተጎነጨሁ ነበር። ከላይ ከተገለጹ አውዶች አንጻርም ስንመለከት የቡኪና የበርቀንቱ አውዶች የሚጠጣ ሳይኖር ወይም በደረቁ የሚከወኑባቸው ሲሆኑ ባህላዊ የዳኝነት አውድ ግን ከሂደቱ በስተመጨረሻ የሚጠጣው ነገር መኖሩ አይቀሬ ነው።



ፎቶ-5 የፐርሲ መስተንግዶ ከሽምግልና አውድ በኋላ

የ"ተረታም" ሆነ የ"ኤዔሪ" ዋነኛ ተራኪዎች ሽማግሌዎች ሲሆኑ ሌሎች ታዳሚዎች የሚያውቁ ቢሆን እንኳን ሽማግሌዎች በየተራ ተናግረው ሳይጨርሱና እነሱ እንዲናገሩ ላይፈቀድላቸው ማውራት ክልክል ነው። ከማህበረሰቡ አንዳንድ ጎልማሶች ተረክ እንዲተርኩ ሲጠየቁ "እኛ እኮ ልጅ ነን" የሚል ምላሽ ያላቸው ሲሆን ይህም "ከእኛ የተሻለ እውቀትና ልምድ ያላቸው ሽማግሌዎች ስላሉ እነሱ እያሉ እኛ አንተርክም" በማለት ለሽማግሌዎች ቅድሚያ የመስጠቱ ባህል በተረኮችም ትረካ ላይ ሽማግሌዎች ያላቸውን ጉልህ ሚና ያሳያል። ሌቶችም ከማድመጥ በዘለለ የትረካ ሚናቸው አናሳ ሲሆን አባቶቻቸው ተረኮችን የሚያውቁ ከሆነ ግን ከአባቶቻቸው ተምረው ይሆናል ተብሎ የሚመደቡ በጣት የሚቆጠሩ ሌቶች ሲተርኩ ይስተዋላል።

በበና ብሔረሰብ ተረኮች አተራረክ ላይ መሳጭ ክዋኔ የተራኪው የአተራረክ ስልት ነው። ተራኪው በአፉ የሚተርከው ተረክን በእጅና እግሩ፣ በፊቱ፣ በድምፁና በመላ ሰውነቱ የሚያደርገው እንቅስቃሴ አድማጩ ሳይሰለች ትረካውን እንዲያደምጥ ያድርጋል። ንዴትን፣ ሣቅን፣ ሩጫን፣ ድብደባን፣ ለቅሶንና መሰል በተረኩ ያሉ ድርጊቶችን ለመግለጽ የተለያዩ የሰውነት እንቅስቃሴዎችና ድምጽ ይጠቀማሉ። የተወሰኑትን ለምሳሌ ያህል እንመልከት፦

ሩጫን፣ የግራ እጃቸውን ወደ ፊት ይወጥሩና /ይዘረጉና/ የቀኝ እጃቸውን አጠፍ አድርገው ወደኋላ በመውሰድ አውራና የመሀል ጣታቸውን አገናኝተው በሚፈጥሩት ክብ ላይ ጠቋሚ ጣታቸውን እያጋጨ በሚፈጠር ድምጽ በትረካው ያለውን ድርጊት በአካላዊ እንቅስቃሴ


ያጅቡታል። ታድያ ቋንቋውን የማያውቅ አድማጭ እንኳ በትረካው ይህን እንቅስቃሴ ካየ ሩጫ መሆኑን ሊያውቅ ይችላል።

ድብደባን/ምትን/፣ የግራ እጃቸውን አይበሉቤ በቀኝ እጅ ጣቶቻቸው ደጋግመው በመጠብጠብ ሲሆን ሁሉቱንም እያቀያየሩ ከጠበጠቡ ግን አሸነፈ ወይም ገደለ የሚል መልዕክት ይይዛል።

ሐዘንን፣ የእጆቻቸውን መዳፍ ጉንጫቸው ላይ በመጫን አንገታቸውን እያወዛወዙ የሚያወጡትን ድምጽ አሳዛኝ ቅላፄ እንዲኖረው በማድረግ ያጅቡታል። በተጨማሪ በሚተርኩት ታሪክ የሚጮህ ገፀ-ባህሪ ካለ መጮሁን በአፍ ከመናገር ይልቅ በታሪኩ የተሳለው ገፀ-ባህሪ የሚያወጣውን ትክክለኛ ድምጽ አስመስሎ በማሰማት ማለትም ሰው ከሆነ "ኦ...ኦ....ኦ..." ፣ውሻ ከሆነ "ው...ው...ው..." የሚል የጩኸት ድምጽ በማውጣት ጮኸው ይገልፁታል። በዚህ ብቻ ሳያበቃም ድምጽን እያቀያየሩ ማስመሰል ሌላው የተራኪው ውበት ሆኖ እናገኛለን። የተቆጣ፣ የደነገጠ፣ የልመናና ሌሎችንም የሚገልፁ ከሚተረኩት ታሪክ ጋር የሚዛመዱ ድምጾችን አቀናጅቶ መተረክ የተለመደ ነው። በመሆኑም ታዳሚው የሚሰማው ታሪክ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች የታጀቡ በመሆናቸው በበናዎች ዘንድ ተረክ ሲተረክ የሚሰለች የለም።

ታዳሚውም ተረኩ የሚፈጥረውን ድባብ የተከተለ ስሜት የሚያንጸባርቅ ሲሆን ለዚህ ስሜት መፈጠር የተራኪው የአተራረክ ስልት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል። ነገር ግን ተራኪው በአተራረክ ስልቱ ይህንን ስሜት መፍጠር ካልቻለ ታሪኩን የሚያውቁ ታዳሚዎች ድባቡን ሊቀይሩት ይችላሉ።

በትረካ ክዋኔ ወቅት አካላዊ የአገላለፅ ስልቶች



ፎቶ-6 አቶ ቡራ ሼሎ ተረክ ሲተርኩ



ፎቶ-7 አቶ አልዲ ቢሮ ተረክ ሲተርኩ

በብሔረሰቡ ተረኮች ሲተረኩ የትረካ ህግጋቶችን መጠበቅ የተለመደ ነው። የሚተረከው "ተረታ" ከሆነ ተራኪው "ከአባቴ የሰማሁት ወይም በዕድሜዬ ያየሁት" ብሎ በመጀመር ትረካውን የሚቀጥል ሲሆን ሁሉም ታዳሚዎች ምንም ድምጽ ሳያሰሙ እስከፍጻሜው ይከታተሉታል። በመሀል ትረካውን የሚያውክ ድምጽ ማሰማትም ሆነ ተራኪውን ጣልቃ ገብቶ ማስቆም አጥብቆ የተከለከለ ነው። ተራኪውም ትረካውን ሲጨርስ "ከአባቴ የተማርኩት የኔ ታሪክ ይህ ነው" ብሎ ይቋጫል። ጣልቃ መግባት የማይቻለው የሚቀርበው ተረክ የማህበረሰቡ አባላት በአንድ አባትና ልጅ መካከል የተፈጸመ ታሪክ በማስመሰል አጠቃላዩን የበና ማህበረሰብ የሚወክል ታሪክ የሚናገሩበት ክፍል በመሆኑ ነዉ።

"ኤዓሪ" ሲተረክ ግን ተራኪው "ኤና ኤና ጊዜ" /በጥንት ጊዜ/ ብሎ ትረካውን የሚጀምር ሲሆን ታዳሚዎችም በፀጥታ የሚከታተሉት ይሆናል። ትረካውን ሲጨርስም "እኔ የምለው ይሄ ነው" ብሎ ትረካውን ይቋጫል። ነገር ግን የትረካውን ታሪክ ሲሳሳትና ትረካው ሲጠፋበት ፀጥታው ይደፈርስና ከየአቅጣጫው የእርምት ድምፆች ይሰነዘራሉ። ተራኪው ታሪኩን ከተሳሳተ ማለትም በትረካው መሀል ትክክለኛ የትረካው ክፍል ያልሆነ ታሪክ ከጨመረ ወይም ከዘለለ ታሪኩን ከሚያውቁ ታዳሚዎች ማስተካከያ ይደረጋል። ተራኪውም ማስተካከያውን ተቀብሎ ትረካውን አስተካክሎ ይቀጥላል እንጂ በትረካው ትክክለኛ ያልሆነ ታሪክ ማስተላለፍ አይችልም።

በሌላ በኩል ተራኪው በትረካው መሀል ታሪኩ ቢጠፋበትና ማስተካከያ እየተደረገለትም በተደጋጋሚ የሚሳሳት ከሆነ ከታዳሚዎች ታሪኩን በትክክል የሚያውቅ አስቁሞት ተራኪው ካቆመበት ወይም ከመጀመሪያ ጀምሮ ትረካውን ይቀጥላል። በትክክል እየተረከ መጥቶ ጠፍቶት ከሆነ ካቆመበት ተቀብሎት ትረካውን የሚቀጥል ሲሆን በተደጋጋሚ እየተሳሳተ መጥቶ ከሆነ ግን መልዕክቱን ከጅማሬው እየሸራረፈ በመምጣቱና ትክክለኛ መልዕክቱንም ስለሚያዛንፈው ታሪኩን ከመጀመሪያው በመጀመር ይተርካል። ይህንንም የተረኮች አውድ በሆኑት ቡኪና ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ላይ መመልከት ችያለሁ። አቶ ኤኮ ኡሊ የአንበሳና ሽለምጥማጥን ታሪክ በትክክል እየተረኩ በመሀል ስለጠፋባቸው አቶ አልዲ ቢሮ ካቆሙበት በመቀጠል ታሪኩን ጨርሰውታል። ከዚህም ተረኮች በማህበረሰቡ መልዕክት የማስተላለፍና ያላቸው ተቀባይነት ከፍተኛ በመሆኑ በትረካ አውዶች የሚተላለፉ መልዕክቶች ትክክለኛ የሆኑና ስህተትን ወይም የታሪኩ ክፍል ያልሆኑ ነገሮችን በመጨመርና በመቀነስ የተዛባ ታሪክ መተረክ ተገቢ አለመሆኑን እንረዳለን። አውዶቹም ያልተዛቡ ሙሉና ትክክለኛ ታሪኮች ብቻ የሚተረኩባቸው አውዶች እንዲሆኑ ጥንቃቄ ይደረጋል። ለዚህም ነው ሽማግሌዎችና ተረኮችን ያውቃሉ ተብለው የሚታመንባቸው ግለሰቦች የአውዶቹ መሪ ተዋንያን እንዲሆኑ የሚፈለገው።

5. የበና ብሔረሰብ ተረኮች ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ

የበና ብሔረሰብ ዝርው ቃል ተረኮች በጎላዊ አመዳደባቸው መሰረት "ተረታ" እና "ኤዓሪ" ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ ቀደም ባሉ የጥናቱ ምዕራፎች ተጠቅሷል። ይህ ሆኖ ሳለ በዚህ ክፍል በድጋሚ መነሳቱ እነዚህ ክፍሎች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚተረኩባቸው መሰረታዊ ተግባራት የተለያዩ ከመሆናቸው አንፃር ነው። ይህም ተረኮቹ ካላቸው ይዘት አንፃር ለምሳሌ "ተረታ" አብዛኛውን ጊዜ እውነትነት አላቸው ብለው የሚሏቸውን ታሪኮች የሚይዝ ሲሆን "ኤዓሪ" ግን የፈጠራ ይዘት ያላቸውን ታሪኮችን የሚይዝ ክፍል በመሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት የማህበረሰቡን ዝርው ቃል ተረኮች ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ በእያንዳንዳቸው ስር ለየብቻ ቀጥየ አቀርባለሁ።

5.1. የ"ተረታ" ማህበረ - ባህላዊ ፋይዳ

ይህ የተረክ ክፍል በናዎች ስለዛሬ ማንነታቸዉ ያለፉ ታሪኮችን መነሻ በማድረግ የዛሬ መሰረቶቻቸዉን እንዴ ት እንደያዙ፣ ማንነታቸዉን ማለትም ባህልና ወጋ ቸዉን ጠብቀዉ ዘመናትን እንዴት እንደተሻገሩ፣ ቀጣዩ ትዉልድም በምን መልኩ መቀጠል እንዳለበት ትክክለኛና እዉነተኛ ታሪኮቻቸዉን ማለትም ስለአኗኗራቸው፣ ስለሚያከናዉኑት ባህልና ደንብ፣ ስለታሪካዊ አመጣጣቸው የሚተርኩበት ነው። ከበርካታ አመታት በፊት የተከወነን ተግባር ከዚያ ጀምሮ "ድሮ የእኔ አባት" ተብሎ እየተተረከ ከትዉልድ ትዉልድ ዘመናትን ተሸጋግሮ ዛሬ ላይ ለመድረሱና ወደፊትም ቀጣይነት እንዲኖረዉ "ተረታ" ጉልህ ሚና ይጫወታል። የ"ተረታ" ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳዎችን እንደሚከተለው በአምስት ክፍሎች በመከፋፈል አቀርባለሁ።

- **የማንነት መለያ የሆኑ ባህላዊ ሥርዓቶችን ማጠናከርና ለትውልድ ማስተላለፍ**

የአፃ ስርአት፣ በበና ብሔረሰብ አንድ ወንድ ልጅ ሚስት ከማጨቱና ልጅ ከመውለዱ በፊት በከብት ጀርባ ላይ በመዝለል ባህላዊ የአፃን ስርአትና ደንብ መፈፀም አለበት። ዕድሜው ለዝላይ ደርሶ እያለ ይህንን ባህላዊ ስርአት ሳይፈጽምና ደንብ ሳይሰራለት ሚስት ማጨትም ሆነ ልጅ መውለድ አይፈቀድለትም። ነገር ግን ይህንን ሳያደርግ ድንገት ልጅ ቢወልድ ልጁ እንደ "ሚንጊ" ነው የሚቆጠርበት። ከዚህ በተጨማሪ በተለያየ ምክንያት ባጋጣሚ ቢሞት ያፈራው ንብረት ለምሳሌ የሰቀለው ቀፎ፣ ያረባቸው ፍዬሎች ወይም ከብቶች ካሉ የነጭ ገንዘብ ነው በሚል ቀፎውም ተገፈትሮ ወደ መሬት ይጣላል፣ ፍዬሎቹም ሆኑ ከብቶቹ ወደ ገበያ ወጥተው

እንዲሸጡ ይደረግና በገንዘቡ ይጠጣበታል እንጂ ተመልሶ ወደ ቤት አይገባም። ስለሆነም ይህንን ባህላዊ ስርአት መፈጸም የበና ብሔረሰብ አባል የሆነ ሁሉ ባህላዊ ግዴታው ነው።

ይህ ጥንታዊ ስርአት ጥንት የነበረውን ይዘት ሳይለቅ ዛሬም ድረስ እየተተገበረ ይገኛል። ይህ እንዲሆን ያስቻለውና ለቀጣይነቱ ጠንካራ መሰረት የሆነው ደግሞ ብሔረሰቡ ጥንት የስርዓቱን አጀማመር መሰረታዊ አላማ በተመለከተ በተረታ አማካይነት ለተተኪው ትውልድ እያስተላለፉ መሆኑ እንደሆነ እንረዳለን።

ተረታ 1 ጥንት በድሮ ጊዜ እኛ በናዎች ከብት ላይ አንዘልም ነበር። እስከዚያ ድረስ ግን ሲፈፀም የነበረው ሥርዓት እንቧይ ደርድሮ አንገት ላይ በማጥለቅ በከብት ሥር በማለፍ ነበር የሚፈፀመው። በመሃል ግን አንድ ሀሳብ የእኛ አያቶች አሰቡ። ሃሳባቸዉም "ሌሎች ብዜረሰቦች ያገባሉ እኛም እናገባለን፣ ሌሎች ያጫሉ እኛም እንዲሁ እናደርጋለን፣ ሌሎች ኩይታ (ጥሎሽ) ይሰጣሉ እኛም እንሰጣለን እናም ከሌሎች ብዜረሰቦች የሚለየን ነገር ምን አለ? እኛ ከሌሎች የምንለይበት የራሳችን የሆነ የእኛ የበኖች መለያ ሊኖረን ይገባል።" የሚል ነበር። ይህንን ሀሳባቸዉን ይዘዉ ለቢታና ለሀገር ሽማግሌዎች አቀረቡ በሀሳቡ የተስማሙት ቢታ "እኛ በኖች ከሌሎች እንለይ ዘንድ ማንኛዉም ወጣት የትዳር አቻዉን ከማጨቱና ከማግባቱ በፊት በከብት ጀርባ ላይ ይዝለል።" ብሎ የጎሳ መሪው በመጀመሪያ በከብት ጀርባ ላይ በመዝለል ደንቡን ከሠራ በኋላ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በከብት ጀርባ ላይ መዝለል ተጀመረ የእኛ መለያም ሆነ። ይህንን ሳይፈጽም የሚያገባ ካለ ጋብቻዉ በእኛ በበኖች ተቀባይነት የለዉም። (አቶ ሳራ አይታ፣ የአልዱባ ቀበሌ ሊቀመንበር፣ 28/06/2004 ዓ/ም፣ የካሴት ቁ.16/ሀ)

እናም በዚህ ተረክ አማካይነት ማህበረሰቡ ይህንን ባህላዊ ስርዓት የማንነቱ መለያ አድርጎ አምኖና ተቀብሎ ከዘመን ዘመን በማሻገር ዛሬም እየፈጸመ እንዲኖር አድርጎታል።

የማዝነት ስርአት፣ በማህበረሰቡ ዘንድ የአፃ ስርዓት ከተፈፀመ በኋላ የሚቀጥለው ስርአት የማዝነት ስርአት ወይም ማዝ የመሆን ስርአት ነው። ማዝ መሆን ማለት አንድ ወንድ ከብት የመዝለሉን ስርአት ከፈፀመ ከአንድ ቀን በኋላ የሚጀምረው ስርአት ነው። ይህ ስርአት ባንድ ጎኑ ለወደፊት ህይወቱ ለትዳር አጋር የምትሆነውን የሴት ጓደኛ ለማጨት የሚፈልግበት ጊዜ ሲሆን የቆይታ ጊዜውም ከሶስት ወር እስከ አንድ አመት ሊረዝም ይችላል። በሌላ ጎኑ ደግሞ የአፃን ስርአት ደንብ አሸጋጋሪ በመሆን የሚያገለግልበት ነው። የአፃ ስርአት ሲፈፀም የሚሰሩ የተለያዩ በርካታ ባህላዊ ደንቦች አሉ፤ እናም እነዚህን ደንቦች በስርአቱ ላይ በመገኘት

የሚፈፅሙ ማዞች ናቸው። ስለዚህ የትዳር አቻቸውን በጥቂት ቀናት ቢያገኙ እንኳን ተተኪ ማዝ የማፍራት ሃላፊነት ስላለባቸው ቢያንስ ለአንድና ሁለት ወር ማዝ ሁኖ የመቆየት ግዴታ አለባቸው።

በማዝነት ጊዜ ከተለመደው የአኗኗር ስርአት ለየት የሚል ህይወት ነው የሚኖራቸው። ከአመጋገብ ጀምሮ ብናይ ደም፣ ማር፣ ወተት፣ እና ስጋ ብቻ ነው የሚመገቡት። አዳራቸው በከብቶች በረት ይሆናል፣ በየትኛውም አይነት የመዝናኛ ጭፈራ ላይ መሳተፍ አይችሉም፣ ሽንታቸውን ሲሸኑም እንደወንድ ልጅ ቁመው ሳይሆን እንደ ሴቶች ተቀምጠው ነው። ታድያ ይህም ስርአት እንደ አዛ ስርአት ጥንታዊነቱን ሳይለቅ እስከዛሬ ድረስ መቀጠሉን፣ ጥንተ አፈጣጠሩን እና የማዞችን ለየት ያለ አኗኗርን በተመለከተ ለምን? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሻቸውን በተረታ አማካይነት ያስተላልፋሉ፤

ተረታ 2 አዛ ስንጆምር ማዝ የዝያን ጊዜ የለም። ማዝን ያወጣው እሱ (ቢታው) ከዘለለ በኋላ የእሱ ልጅ ቴሶ የሚባለው ነው። የዚያን ሰዓት የዝላዩን ስርዓት ለማስፈጸም አረቻ (የጭሪወፍ) ነበር የተመረጠችው። ምክንያቱም ወፏ ከሌሎች ወፎች በተለየ ወተት እና ከከብቶች ላይ መዥገር እየነቀለች ነው የምትበላው፤ ሌላ ምንም አትበላም። እናም አንድ ሰው ወፏን ይዞ ከከብቶቹ ላይ አዘለላቸው። ከዚያም ንጉሱ 'ይህች ወፍ እህል አትበላም ስለዚህ ይሄም ሰው እህል የማይበላ ማዝ ይሁን' ብሎ አለ። እናም ልጁ ሚስት አግኝቶ ደንብ እስከሚሰራ ድረስ እህል እንዳይበላ ተብሎ ተወሰነ። እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማዝ የሚሆነው ሰው የማዝነት ጊዜውን እስኪጨርስ ድረስ ወፏ ወተት እንደምትጠጣው ወተት፣ ወፏ መዥገር እንደምትበላው እሱም ሥጋ እየበላ እና በተጨማሪም ማር እየበላ ይኖራል። ከዚህ ውጭም ወፏ ዛፍ ላይ ሆና ሽንቷን የማትሸና መሬት ላይ ቁጭ ብላ የምትሸና በመሆኗ ማዝም መሬት ላይ ቁጭ ብሎ ነው የሚሸናው። አዳሩም በቤቱ ውስጥ ሣይሆን በበረት ውስጥ ማደሪያ ሠርቶ ነው። የዚህም ምክንያት እቤት ውስጥ እህል ስለሚኖር ማዙ ድንገት ወደ ቤቱ ውስጥ ሲገባ ልጃገረድ ወይም ማንኛዋም ሴት እህል ይዛ ስትወጣ ቢገናኙ እህሉም ይበላሻል፣ የልጁ ሆድም ያብጣል፣ ተነፍቶም ይታመማል። ስለዚህ ቢያንስ እስከ አንድ ዓመት እና ልጃገረድ አግኝቶ እስኪያገባ ድረስ ማዝነቱን በዚህ መልኩ እየተገበረ ይኖራል። ምናልባት ወቅቱ ፀሐይ ሆኖ የዘለለ ከሆነ ደግሞ ወተት እንደልብ ስለማያገኝ ብዙ ጊዜ ከሶስት ወር በላይ መቆየት አይፈልግም። (አቶ ቆጳ ሼሎ፤ ቦሪ ቀበሌ፤24/7/04 ዓ/ም፤የካሴት ቁ.10/ሀ)



ፎቶ-8 ማዞች



ፎቶ-9 የአፃ ስርዓት

የጎሪ ስርዓት፣ በናዎች ለዘመናት ከፍተኛ ዝግጅት እያደረጉ ከሚያከብሯቸው በርካታ ባህላዊ ስርዓቶች ውስጥ የ"ጎሪ" ስርዓት አንዱ ነው።"ጎሪ" አንድ ህፃን ተወልዶ ስድስት ወር ሲሞላው ከእናት ጡት በተጨማሪ እህል መቅመስ ይችል ዘንድ በስድስተኛው ወር ላይ የሚፈጸም ደንብ የመስራት ልዩ ስርዓት ነው። ስርዓቱ ሲፈጸም ቤተሰቡ ፕርሲ እና እንደየአቅሙ ፍየል ወይም ከብት በማረድ ድግስ ደግሶ ዘመድ ጎረቤት በመጥራት የሚከውነው ነው። በዕለቱም በህፃኑ አምባርሚያ፣ ክንድ፣ አንገትና ወገብ ላይ የላጊ ገመድ በማሰር የሚፈጸም ደንብ ሲሆን ይህንን ደንብ የሚሰራው ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ በዚሁ ጉዳይ ተለይቶ የሚታወቅ ሰው ነው።

ይህ ስርአት ህፃኑን ተጨማሪ ምግብ እንዲያገኝ ከማድረጉ በተጨማሪም ልክ እንደ አፃ ስርአት አንድን በና ሙሉ ሰው እንዲሰኝ የሚያስችል ነው። ስርአቱ በሁለቱም ፆታዎች ላይ የሚፈፀም ሲሆን የወንዶችን ለየት የሚያደርገው ይህን ሳይፈፅሙ ከብት መዝለል አለመቻላቸው ነው። ይህን ባህላዊ ስርዓት ማህበረሰቡ አምኖበትና ትኩረት ሰጥቶ እንዲፈፅመው እና ለትውልድ እንዲያስተላልፍ ተረኮችን የሚጠቀም ሲሆን ከተረኮቹም ተረታ 23 ተጠቃሽ ነው።

ተረታ 23 ድሮ አባቴ አንድ ነገር አስተማረኝ "ልጅ ወልደህ ስድስት ወር ሲሞላዉ ከእናቱ ጡት ውጪ ሌላ እህል ከመቅመሱ በፊት ደንብ የሚሰራ ሰው ጠርተህ ደንብ አሰራለትና እህል አቅምሰው ይህ የኛ ደንብ ነው። ካልሆነ ግን ልጁ በስብሶ ሳይፈለፈል እንደቀረ እንቁላል ነው፤ ሰው አይደለም። ደንቡን በወቅቱ ለማድረግ ባትችል እንኳ እህል ሲደርስ ጠብቀህ ደንቡን አሰራለት፤ አለበለዝያ ከብትም አይዝለል" ብሎ አለኝ። እና በእኛ ሀገር ሰው ሁሉ

ይህንን ደንብ በግዴታ መፈፀም አለበት። (አቶ ዱባር አይኬ፣ሞርገላ ቀበሌ፣14/7/04 ዓ/ም፣ ምሽት 1:35)

በዚህ ተረክም ባህላዊ ደንቡ እስከዛሬ ተጠብቆ እንዲቆይ ያደርገበታል። በዘመናዊው ላይንስ ሕፃናት እስከ ስድስት ወር ከእናት ጡት በቀር ሌላ ተጨማሪ ነገር እንዳይሰጣቸውና ስድስት ወር ሲሞላቸው ግን ተጨማሪ ምግብ መመገብ ለጤናቸውም ሆነ ለአካላዊ እድገታቸው ወሳኝ መሆኑ ይታመንበታል። ብሔረሰቡ ግን ይህ የዘመናዊ ሳይንስ እውቀት ሳይኖረው ይህንን ላይንላዊ አመለካከት በአኗኗር ዘይቤው በልማድ ከውኖ የህፃናቱን ጤንነት ጠብቆ ዘመናትን እንዲሻገር የተረኮቹ ሚና የላቀ እንደነበር ጥርጥር የለውም።

- **የባህላዊ እምነቶችን ጠቀሜታ ማጉላት**

"አባቴ በመራኝ መንገድ፣ በባህሌ መሰረት" እያለ ብሔረሰቡ የሚገልፃቸውና እስከዛሬም በእምነቶቹ ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ ሳይገባው የሚያምናቸው የተለያዩ እምነቶች አሉት። ከነዚህም ኮከብ ቆጠራና አንጀት ማንበብ ይጠቀሳሉ። ይህንን ተግባር የሚያከናውኑ ግለሰቦች ደግሞ ኮከብ ቆጣሪዎችና አንጀት አንባቢዎች ይባላሉ። ኮከብ ቆጣሪዎች ወደ ሰማይ አንጋጠው ኮከቦችን በመመልከት ትክክለኛውን ነገር ይተነብያሉ ተብለው የሚታመንባቸው ሲሆኑ አንጀት አንባቢዎች ደግሞ በተመስጦ የፍየል አንጀትን (ብዙውን ጊዜ አገልግሎት ላይ የሚውል ነው) እንቅስቃሴ በመመልከት ትክክለኛውን ነገር የሚናገሩ በህበረተሰቡም የሚታመኑ ናቸው።

እነዚህ አካላት በተሰጠአቸው ተጠቅመው የሚያስተላልፉትን ትዕዛዝ ማዳመጥና መተግበር ከብዙ መከራ እንደሚታደጋቸው በናዎች ይናገራሉ። ካላቸው ጠቀሜታ አንፃርም በሌሎች እምነቶች እንዳይዋጡና እንዳይተኩ ጠቀሜታቸውን አጉልተው የሚያሳዩ ተረኮች ይተረካሉ። የአልዱባ ቀበሌ ሊቀመንበር ከሆኑት ከአቶ ሳራ አይታጋር ስወያይ ኮከብ ቆጣሪዎችን በተመለከተ ኮከብ ቆጠራን ከሂደቱ ጀምረው እንደሚከተለው ተረኩልኝ፤

> በእኛ በበናዎች ሁሉም ሰው ስለ ኮከብ ቆጠራ አያውቅም። አንዳንድ ሰዎች ናቸው መቁጠር የሚችሉት። እነዚህ ሰዎች ኮከብ ቆጣሪዎች በሚል መጠርያ የሚታወቁ ሲሆን ኮኮቦችን በማየት ስለወቅቶች የሚሆነውን ነገር ሁሉ የሚያውቁበት የራሳቸው የሆነ ጥበብ አላቸው። በእኛ ሀገር ያሉ ኮኮብ የሚቆጥሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚያዩት "ጽዮ" እና "ዚክሳ" የሚባሉ ተራሮችን ነው። እነሱን በማየትም ስለወቅቶች ማወቅና መናገር ይችላሉ። ይህም እንዴት ነው? ብንል በእነዚህ ተራሮች መሀል ባለ የተፈጥሮ ክፍተት ውስጥ እነሱ በተለየ ሁኔታ የሚመለከቷቸው ኮኮቦች

በቀጥታ ሲወርዱ እና በጎን ሲያልፉ በማየት ነው ሁልጊዜ የሚተነብዩት። ለምሣሌ በዚህ ዓመት ከብቶች ይረባሉ፣ በሽታም አይኖርም፣ ዝናቡም የበረከት ነው፣ ፀሐይ አይበዛም፣... እያሉ ሊተነብዩ ይችላሉ። (አቶ ሳራ አይታ፤ አልዱባ ቀበሌ፤ 28/6/04 ዓ/ም፤ ምሽት 2፡15)

ኮከብ ቆጣሪዎች ከዋክብትን በማየት ያላቸውን የመተንበይ ችሎታና የሚተነብዩት ስለምን እንደሆነ ከገለጻው እንረዳለን። ታድያ ይህ የኮከብ ቆጣሪዎቹ ቃል ትክክለኛ ነው ተብሎ ስለሚመን ሁሉም ሰው ቃላቸውን ያከብራል። ሆኖም የቃላቸውን ትክክለኛነት የሚጠራጠሩና የማያምኑ ብሎም የማይተገብሩ ቢኖሩ የመጨረሻ እጣ ፈንታቸው ሞት መሆኑን ያረጋግጣሉ። ይህንንም አስመልክቶ በተረታ 3 አንድ ወቅት ተፈፅሟል ብለው የሚሉትን ታሪክ ይተርካሉ፤

ተረታ 3 አንድ ወቅት ላይ በናዎች "ኮከብ መጥፎ ነገር እየተናገረች ነውና ሽሹ!" ተብለው ግማሹ ህዝብ ሸሽቶ ወደ አሪ ሀገር፣ የተወሰነው ደግሞ ወደ ካሮ ሀገር ሸሽቶ ገብቶ ነበር። ከብዙ ጊዜ በኋላ ኮከቧ ወደ ቦታዋ ተመለሰችና ወደ ተለያዩ ሀገር የሸሹት ሰዎች መመለስ ጀመሩ። ወደ ካሮ ሸሽተው ከነበሩት አራት ወንዶች ብቻ ሲተርፉ፣ ወደ አሪ ከሸሹት ደግሞ አሥር ሴቶችና አንድ ወንድ ብቻ ነበር የተረፉት። ነገር ግን ሀገራቸው ላይ ቀርተው ከነበሩት አንድም ሰው የተረፈ አልነበረም። ኮከቧ ወደ ቦታዋ ተመልሳ ሀገሯ የተረጋጋች ስትሆን ወደ ካሮ ሸሽተው ከነበሩት የተረፉ አራቱ ወንዶች ወደ ሀገራቸው በመመለስ ዳገት ላይ ሆነው እንጨት ሰብቀው እሳት በማውጣት ሁልጊዜ ምሽት ላይ ያነዱ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ "ምናልባት ይህን እሳት የተመለከቱና የተረፉት ሌሎች የኛ ሰዎች ካሉ አቅጣጫችንን እየፈለጉ ይመጣሉ።" በሚል ሀሳብ ነበር።...(አቶ ደምሴ በላቸው፤ ዲዚ አማ ቀበሌ፤23/7/04 ዓ/ም፤የካሴት ቁ.1/ሀ)

በተረኩ የኮከብ ቆጣሪውን ትንቢት አምነው የተሰደዱ አከባቢያቸውን ከመታው መአት አምልጠውና በህይወት ቆይተው ወደ ቀድሞ ቀዬአቸው በመመለስ በመአቱ የጠፋውን ዘራቸውን የመተካት ሀላፊነት ሲወጡ እንመለከታለን። የኮከብ ቆጣሪውን ቃል ችላ ብለው የቀሩት ግን ሙሉ በሙሉ በመአቱ ማለቃቸውን ስንመለከት የብሔረሰቡ አባላት በኮከብ ቆጣሪዎች ላይ ያላቸው እምነት የፀና እንዲሆንና ለቃሎቻቸውም ታዛገሮች እንዲሆኑ ካልሆነ ግን በሞት እንደሚጠፉ እንዲያምኑ ተረኩ አስተዋጽኦ እንዳለው እንረዳለን።

አንጀት አንባቢዎች ብዙውን ጊዜ የሚፈለጉት ለታመመና በተለያዩ ምክንያቶች ለአደን፣ ለጦርነት፣ ለንግድና ለመሳሰሉ ጉዳዮች ሩቅ ቦታ ለመሄድ የተነሳ በከንቱ እንዳይለፋ የሚሄድበት ጉዳይ ውጤቱ ያማረ ይሁን ያላማረ እንዲተነበይለት በፈለገ ጊዜ ነው። ቀጥሎ የሰፈረው ተረት ይህንን የሚያሳይ ነው።

ተረታ 4 አባቴ ድሮ "ልጄ በደንብ ስማ" አለኝ። "ምን ማድረግ ትፈልጋለህ? አደን መሄድ ወይስ ጦርነት መግጠም? ጦርነት ለመግጠም ስትነሳ ማሸነፍ ወይስ መሸነፍህን አውቀህል? እንደዚህ አይነት ነገር ከማድረግህ በፊት የምልህን በደንብ አዳምጥ፤ አንጀት አንብበው ሁሉን የሚያውቁ አሉና ቀድመህ ወደ እነሱ ሂድ፣ ጉዞህ ከንቱ እንዳይሆን ቀድመህ ጠይቅ። ውጤትህ ምን እንደሆነ ይነግሩሀል፣ ታድያ የሚሉህን ፈጽም። አትሂድ ካሉህ ቅር፣ ሂድ ካሉህ ደግሞ ሂድ። ይህን አልሰማ ብለህ ካዘዙህ ውጭ ከሆንክ ግን መጨረሻህ በሄድክበት መቅረት ነው የሚሆነው።" አለኝ።(አቶ ቡልኮ ጋርሾ፤ሞርገላ ቀበሌ የሀገር ሽማግሌ፤14/7/04 ዓ/ም፤)

በአጠቃላይ ተረታ 3 እና 4 ማህበረሰቡ የእምነቶቹን ጠቀሜታ አጉልቶ ያሳያል። የብሔረሰቡ አባቶችም የጥንት አባቶቻቸውን እምነት እየተረኩ በማሸጋገር ለዛሬው ትውልድ አስረክበዋል። የዛሬው ትውልድም እምነቶቹን በመከተል ወደፊት ለማስቀጠልና ጠቀሜታቸውንም ለማጉላት ተረኮቹን በጥንቃቄ ዛሬም ይተርካል። እናም የእምነቶቹን ጠቀሜታ ለማጉላትና ትውልዳዊ ቅብብሎሹን ለማስቀጠል የተረታ ተረኮች ያላቸው ፋይዳ ተተኪ የሌላቸው ናቸው።

- ***ሥነ-ምግባርንና ግብረ-ገብነትን ማስተማር***

የልመና አስከፊነት፤ በተዘዋወርኩበት የበና ቀበሌያት በተፈጥሮም ችግር ይሁን ራሱ ባመጣዉ የስንፍና መዘዝ የኑሮ ውጣ ውረድን ማሸነፍ ተስኖት ሲለምን አንድም ግለሰብ አላየሁም። ማህበረሰቡም የህይወት ዘመኑን በልመና የሚያሳልፍ ግለሰብ እንደሌለ አረጋግጠውልኛል። ሀብት ባይኖረዉ እንኳን ክብት ካላቸዉ ክብት፣ ፍዬል ካላቸዉ ደግሞ ፍዬል ተዉሶ ወስዶ እያረባ የራሱን ሀብት ማፍራት አለበት እንጂ ልመና "ቀይስ" (የተወገዘ) ተግባር ነዉ። ለዚህም ወደ ልመና እንዳይገቡ ያደርጋቸዉን ታሪክ በተረታ ሲገልጹ፤

ተረታ 7 ድሮ አባቴ "ከብቶችህን በደንብ ካልጠበቅክ በጅቦች እንደሚበሉ ሁሉ በርትተህ ካልሰራህ አንተን ችግር ይበላሀል። የሰዉ እጅ ታያለህ! ለማኝም ትሆናለህ። ስለዚህ አንተ እንደዚህ ሆነህ እኔ አባትህ ከማዝንብህ በርትተህ ስራ! በላብህ እንጂ ሳትሰራ ከማንም ለምነህ እንዳታገኝ! ማንንም እንዳትለምን።" ብሎኝ ነበር። (አቶ አልዲ ቢሮ፤3/7/04ዓ/ም፤የካሴ ቁ.17/ሀ)

ታማኝነት፣ አስመልክቶ የሚተርኩት ተረታ

ተረታ 5 ድሮ አባቴ አንድ ነገር አለኝ። አባቴ ድሮ ያለኝ "የሰዉ ገንዘብ አትመኝ፣ ጫካ ሄደህ ቀፎ ስቀል፣ ከብቶችን ጠብቅ፣ ፍየሎችን ጠብቅ፣ እናትህን አታሳዝን.፣ እህቶችህንም በክብር አጋባቸው፣ እኔ ላንተ የነገርኩህን ለልጆችህ ንገር።" አለኝ።(አቶ ኤኮ ኡሊ፣ዲዚ አማ ቀበሌ፣3/7/04 ዓ/ም፣የካሴት ቁ.17/ሀ)

ተራኪው ይህንን ተረታ ተርከው ሲያበቁ በተረታው መነሻነት ዛሬ ላይ ያላቸውን የህይወት ልምድ እንደሚከተለው ይገልፁታል፣

እኔም አባቴ በመከረኝ መሰረት ቃሉን አክብሬ ቀፎ እየሰቀልኩ፣ እናቴንም እያከበርኩኝ ኖርኩኝ። አባቴንም ክፉ ነገር ብዬ አላሳዘንኩትም። ሲሞትም ቀበርኩት፣ እናቴም ስትሞት በሰላም ቀበርኳት። ታናናሾቼንም በአባቴ አደራ መሰረት አጋብቼያቸዋለሁ። ልጆቼንም ጠዋት ጠዋት ሁልጊዜ ሾፎሮ ስጠጣ የሰዉ ገንዘብ እንዳይመኙና እጃቸዉን በሰው ገንዘብ እንዳያስገቡ በራሳቸዉ ጥረት እንዲለወጡ አባቴ ለእኔ የመከረኝን እየመከርኳቸዉ ነዉ። (አቶ ኤኮ ኡሊ፣)

ይህ ተረታ በበናዎች ዘንድ የሰዉን ንብረት መንካት አስፀያፊ ተግባር እንደሆነና የራሳቸዉ ከሆነ ነገር ዉጭ እርስ በርስ የማንንም ማንም እንዳይነካ ትዉልዱን "አባቴ ያወረሰኝ ታማኝነትን ነዉ" በማለት ታማኝነትን የሚያስተምሩበት ነዉ። ታድያ ዛሬ ላይ በበና ምድር የሰዉ ንብረት የሚያጭበረብር ሌባ፣ ቃሉን የማያከብር አታላይ እንደሌለ በልበሙሉነት ሁሉም ይናገራሉ። ይህንና መሰል ተረታዎችን መተረክ ዛሬ ላይ በማህበረሰቡ ውስጥ ዳብሮ ለሚታየው የመታመን ባህርይ አስተዋጽኦ እንዳላቸው እንረዳለን።

ድህነትን ስለመጸየፍ፣ የሚተርኩት ተረታ

ተረታ 6 ድሮ አባቴ "የሰዉ እጅ እንዳታይ! ደሃ እንዳትባል! ደሃ ከምትባል የእኔ ልጅ ባትሆን ይሻላልና ቀፎ ስቀል፣ ከብትና ፍየል አርባ፣ በቀን አታንቀላፋ! በቀን ካንቀላፋህ ድህነት ይውጥሀል" አለኝ። (አቶ አልዲ ቢሮ፣ ዲዚ አማ ቀበሌ፣ 3/7/04 ዓ/ም፣ የካሴት ቁ.17/ሀ)

ይህ ተረታ የበና ማህበረሰብ ድህነትን እንዲታገሉ ብርታት ከሆናቸዉ ነገሮች መካከል የሚጠቅሱት ነው። በበና ማህበረሰብ "ድሀ አለ ወይ?" ተብሎ ቢጠየቁ ሁሉም" የበና ደሃ የለም" የሚል ምላሽ ይሰጣሉ። በና ሆኖ ደሃ መባልን የሚፈልግ የለምና። "ከብት፣ ፍየል፣ ቀፎ እስካለኝ ድረስ ሀብታም ነኝ" ይላሉ እንጂ ደሃ መባልን ይፀየፋታል። በታሪክ አባቱ ያለዉን ቃል ባለመፈጸሙ ደሃ መባሉ ዉርደት ነዉ። እናም ይህ ተረክ ድህነትን በመጸየፍ የሚችሉትን

ለርተው እራሳቸውን መለወጥ እንዲችሉና በማህበረሰቡ ውስጥ የስራ ተነሳሽነት የሌላቸው ወገኖቻቸውን ለማስተማርና ለመገሰፅ አዘውትረው የሚጠቀሙት የተረክ አይነት ነው።

ታድያ በሀገራችን አሉ ከሚባሉ በርካታ ችግሮች ድህነት አብሮን የተፈጠረ እስኪመስለን ድረስ ለዘመናት አብሮን የኖረ ግንባር ቀደም ችግራችን ነው። ዛሬ ላይ ድህነትን ለመቀነስና ብሎም ለማስወገድ መንግስት፣ ጉዳዩ የጋራ ስለሆነ ድህነት ቅነሳ ይመለከተናል የሚሉ የተለያዩ አለም አቀፍና ሀገር በቀል ድርጅቶች ማህበረሰቡን ድህነት ላይ በማዝመት ከስሩ መንግሎ ለመጣል እያደረጉ ላለው ጥረት በማህበረሰቡ ውስጥ ዘመናትን ተሻግረው ዛሬ ላይ የደረሱ የዚህ አይነት ይዘት ያላቸው ተረኮች በቀላሉ ማህበረሰቡን የማነሳሳትና ዘመቻውን በማፋፋም ወደሚፈለገው ምዕራፍ በፍጥነት ማድረስ የሚያስችል ትልቅ አቅም ስላላቸው እየተደረገ ላለው የድህነት ቅነሳ ትግል እንደአንድ የትግሉ ማሸነፍያ መሳርያ አድርጎ መጠቀም ጠቀሜታው የጎላ ነው እላለሁ።

- **የባህላዊና ማህበራዊ ተቋማት የበላይነትና ጠቀሜታን ማጉላት**

በበና ብሄረሰብ ውስጥ ያሉ ባህላዊ አስተዳደሮች የተለያየ የስልጣን ደረጃ እና የተለያየ ሚና ያላቸው ናቸው። (የባህላዊ አስተዳደሮችን አይነትና ሚና አስመልክቶ በጥናቱ ዳራ ክፍል ተተንትኗል) ህብረተሰቡም እንደየደረጃቸው የሚሰጣቸውን ክበሬታ እየሰጠ፣ ባላቸው ሚናም እየተገለገለ ለዘመናት አብረው በመኖር ዛሬ ላይ ደርሰዋል። ድርቅ በጥጋብ፣ ጦርነት በሰላም፣ በሽታ በፈውስ፣ እንዲለወጥ ከልመና እስከ መስዋእት በመሰዋት ፈጣሪያቸውን በርጅን በመለመን ለማህበረሰባቸው የተመቻቸ ህይወትን የሚያሰጡ ናቸው።

የተናገሩት ሁሉ ይፈፀማል፣ የመረቁትም ሆነ የረገሙት በፍጥነት ይደርሳል፣ ከተርታው ህዝብ የተለየ ሃይል አላቸው ተብለውም ይታሰባሉ። ስለሆነም ህብረተሰቡ ሁሉ ያከብራቸዋል፣ ያወጧቸውንም ደንቦች ሆኑ ትእዛዞች አክብረው ይፈጽማሉ። ያንን ባያደርጉ ደግሞ ከፍተኛ ችግር እንደሚደርስባቸው ያምናሉ። ይህንን አይነትም ጽኑ አመለካከት በውስጣቸው እንዲኖር ያደረጋቸው ነገር ምን እንደሆነ ሲጠየቁ ደግሞ ጥንት የተፈፀመ አባቶቻችን የነገሩን ተረታ አለ ብለው የሚሏቸው ተረኮችን ያቀርባሉ።

"ቢታ"ን (የጎሳ መሪን) ስለማክበር የሚያቀርቡት ተረታ

ተረታ 8 ድሮ አባቴ "አባትህንና እናትህን አክብር፣ ቢታን (የጎሳ መሪዉን) አክብር፣ ትዕዛዙን ፈጽም፣ የሀገር ሽማግሌዎችንና ካንተ ትልቅ የሆኑትን ሁሉ አክብር፣ ይህንን ስታደርግ ከብትህና ቤተሰብህ ይባረካሉ፣ አከባቢህ ሰላም ይሆናል፣ ዝናብም ይዘንባል፣ ድርቅም አይነካህም፣ ይህን ባታደርግ ግን ትረገማለህ፣ ድርቅም ይሆናል፣ ከብቶችህ ያልቃሉ" ብሎኛል።"(አቶ አሮምባ ጊሊያር፣አልዱባ ቀበሌ፣30/6/04 ዓ/ም፣የካሌት ቁ.14/ሀ)

ተራኪው ከዚህ ተረታ ጋር አያይዘው የሚከተለውን ገልፀውልኛል፣

እኛ በናዎች ለታላላቆቻችን፣ ለሀገር ሽማግሌዎች ልዩ ክብር አለን። ለጎሳ መሪያችንም ታዛገሮች ነን። ይህንን እንድናደርግ አባቶቻችን የነገሩንን ተረታ አንረሳውም። አሁን ላይ ግን ቁጥራችን በጣም እየጨመረ በመምጣቱ ሽማግሌዎችን የማያከብሩና ለጎሳ መሪያችንም የማይታዘዙ አንዳንዶች በአከባቢያችን ብቅ ማለት ጀምረዋል። ይህ መሆኑ ደግሞ ድሮ በአባቶቻችን የተፈጸመው ክስተት ዳግም በኛ ጊዜም እንዳይደገም የሚል ስጋትን ይፈጥርብኛል።"

ቀጥለውም ይህንን ተረታ (ተረታ 9) በከፍተኛ ስሜት ተርከውልኛል፣

ተረታ 9 "ዛሬ የምንኖርባት ይህች ምድር እኛ ከመምጣታችን በፊት በሰዎች የተሞላች ነበር አሉ። ታድያ ልክ እንደ አሁኑ ቁጥራቸዉ ሲበዛ ለጎሳ መሪዉ አለመገዛትና ሽማግሌዎችን መናቅ በመጀመራቸዉ ተረገሙ። ሙሉ በሙሉ ከምድርም ጠፉ፣ በየአቅጣጫውም ተበተኑ፣ ከዚያ በኋላ ነዉ የተበታተነዉ ዘራችን ከየአቅጣጫዉ ተሰባስቦ እንደገና ዘራችን በምድር የሞላዉ። (አቶ አሮምባ ጊሊያር፣አልዱባ ቀበሌ፣30/07/2004 ዓ/ም፣የካሌት ቁ.14/ሀ)

ታድያ ትውልዱ የአባቶቹን ትዕዛዝ ችላ ብሎ በዚሁ ከቀጠለና በጊዜ መስመር ካልያዘ የጎሳ መሪዎችና ሽማግሌዎች ማዘናቸዉና መራገማቸዉ ስለማይቀር ድጋሚ ከምድር ላይ ጠፍተን እንዳንቀር የሚል ስጋታቸውን በተረታ ከሰሙት ታሪክ ጋር አያይዘው ይገልጻሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ ለአስተዳደር ካለመታዘዝ ጋር የሚተርኩት ተረክ 10 ከ"ቆግ" ባህላዊ አስተዳደር ጋር በተያያዘ ተከስቶ ነበር የሚሉትን የአንድ ወቅት ታሪክ ነው። አቶ ጋርሾ ቡቃር ሲተርኩ፣

ተረኩም በብሔረሰቡ አባላት ህይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ ገጠመኝን የሚተርክ ነው። እናም የቆግ ስልጣን ያላቸው ትልልቅ ሰዎች የሚሉትን አለመስማት ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን አስረግጠው ያሳስባል።

ሽማግሌዎች እና ሽምግልና፣ በበና ብሔረሰብ አባላት ማህበራዊ ህይወት ውስጥ በእድሜ የገፉ ሽማግሌዎችን ቃል ማክበር በስፋት የሚታይ ጠንካራ ባህል ነው። ብሔረሰቡ የሃገር ሽማግሌዎችን ቃል አለመስማት ከፍተኛ ጥፋት እንደሚያመጣባቸው አጥብቀው ያምናሉ። ስለሆነም የብሄረሰቡ አባላት ሽማግሌዎች የሚሏቸውን ሁሉ ይሰማሉ፣ ለትእዛዞቻቸውም ይገዛሉ። ሽማግሌዎችም ከባህል የሚያፈነግጡ፣ ከአባቶቻቸው ስርአትና ደንብ ውጪ የሚሆኑ፣ እነሱ "ቀይስ" (ነውር) ናቸው ብለው የፈረጇቸውን ተግባራት የሚፈጽሙትን እየለዩ ምክር በመስጠት ከጥፋት እንዲመለሱና እንዲታረሙ ያደርጋሉ። "ተው ወደ ገደል አትሂድ! ትጠፋለህ፣ ጥይትህ ይጎድልብሃል፣ ከብቶችህ ያልቃሉ፣..."እያሉ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይመክራሉ። አልመለስ ያለን ግን በጓደኞቹ አማካይነት የተወሰነ የአርጩሜ ቅጣት (ጠጺ ሚጫሬ) እንዲቀጣ ያደርጋሉ። በዚህም አልመለስ ያለን ከዚህ ከፍ ያለ ቅጣት እየሰጡ በተደጋጋሚ ወደ ስርአት እንዲመለስ ጥረት ያደርጋሉ። ነገር ግን ይህ ሁሉ ሁኖ አልመለስ ያለን አካል ይረግማሉ። ዕርግማናቸው ይፈራል፣ የተረገመው ሰው እድሜ አይኖረውም፣ባጭሩ ይቀጫል፣ በወጣበትም ይቀራል፤ ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ ከፍተኛ ክበሬታ ይሰጣቸዋል፣ ቃላቸውም ይደመጣል። ይህ እንዲሆን ደግሞ የተለያዩ ተረታዎችን እያነሱ፣ ምሳሌ እየጠቀሱ ነገራቸውን ያጠናክራሉ። ለዚህ ተግባር ከሚጠቀሟቸው ተረታዎች ደግሞ ተረተ 11 ተጠቃሽ ነው።

ተረታ-11 አንድ ወቅት ላይ ነው አሉ በየቀኑ ከቤቱ በወጣ ቁጥር አደን ውሎ ሲመለስ አውሬ ገድሎ የሚገባ ሰው ነበር። እናም በኛ በበና ማህበረሰብ ዘንድ ደግሞ አደን ማደን፣ አውሬ መግደል የጀግንነት ተግባር ተደርጎ ቢወሰድም አዘውትሮ መግደል ደግሞ በጥብቅ የሚወገዝ ተግባር ነው። ይህ በሆነበት የዚህ ሰው አዘውትሮ ማደን እና በገባ በወጣ ቁጥር መሳሪያ ማጮሁ ጥሩ እንዳይደለ የአከባቢ ሽማግሌዎችና የሚቀርቡት ሰዎች በተደጋጋሚ ይነግሩት ነበር። ነገር ግን ይህ ሰው የሽማግሌዎችን ተግሳፅ ወደ ጎን ትቶ በተግባሩ ይቀጥልበታል። ታዲያ አንድ ቀን እንደለመደው ወደ ጫካ ሂዶ እያደነ እያለ ... የገደለው ነገር የተመለከተውን ድኩላ ሳይሆን ከዚህ በፊት አይቶት የማያውቀውን የተለየ ፍጡር ሆኖ ያገኘዋል። ባጋጠመው ክስተትም እጅግ በመደንገጡ እሱም እዚያው ሞተ።(አቶ ጪሽኮ ገሌ፤አልዱባ ቀበሌ፤29/7/04 ዓ/ም፤ምሽት 4:20)

ይህ ተረታ በብሔረሰቡ ዘንድ አደን የጀግንነት ተግባር ተደርጎ ቢወሰድም በተከታታይ ማደን ደግሞ የሚወገዝ በመሆኑ ይህንን የሸማግሌዎች ቃል አልሰማ ብሎ የሄደን የማህበረሰባቸው አባል እንደመቀጣጫ በመውሰድ ለማስተማርያነት የሚጠቀሙበት ነው።

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ በተረታ 8፣9፣10 እና 11 የጠቃቀስናቸው ተረኮች በብሔረሰቡ ውስጥ ለምናገኛቸው ባህላዊ አስተዳደሮች ህብረተሰቡ ያለውን ታዛዥነት፣ከበሬታ እንዲሁም የተቋማቱን ጠቀሜታ ከማጉላት ባሻገር ዛሬም በብሔረሰቡ ውስጥ ባላዊ አስተዳደሮቹ ጽኑ መሰረታቸውን ይዘው እንዲቀጥሉ ተረኮቹ ጉልህ ድርሻ እንዳበረከቱ እንረዳለን።

እንዲሁም አሁን አሁን በወንጀል እንደሚያስጠይቁ የህግ አንቀጽ የተጠቀሰላቸው ነገር ግን በብሔረሰቡ አባላት የሚከወኑ አንዳንድ ተግባራት ለምሳሌ ሚንጊ በሚል ህፃናትን በማፈንና ወደ ገደል በመጣል መግደል፤ የዘመናዊው ህግ ምሁራንና የአስተዳደር አካላት ለህጉ ተግባራዊነት የብቻቸው ጥረት የሚፈለገውን ውጤት ሊያመጣላቸው እንዳልቻለ በመገንዘብ በማህበረሰቡ ሙሉ ለሙሉ ተቀባይነት ካላቸው ከላይ ከተጠቀሱ ባህላዊ ተቋማት ጋር በመቀናጀት መንቀሳቀስ ጀምረዋል። በአጭር ጊዜም በርካታ ስኬቶችን ማስመዝገብ እንደቻሉ ከወረዳው ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ጽ/ቤት ባገኘሁት መረጃ መሰረት ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ ሚንጊ በሚል ይገደሉ የነበሩ 78 ህፃናት ከመጣል ተርፈው ማደጋቸውን ተረድቻለሁ በመሆኑም ባህላዊ ተቋማቱ በተረኮች አጋዥነት ታሪካዊ ቅርጻቸውን ሳይለውጡ ከዘመን ዘመን መሻገር በመቻላቸው ዛሬ ላይ የዘመናዊው አሰራር አጋዥ ሆነው እናገኛቸዋለን።

- **ታሪክን መቅረስና ለትውልድ ማስተላለፍ**

ባለ ሶስት ጡት ብቸኛዋ የበኖች የሴት ቢታ፣ በበናዎች ሶስት ጡት አላት ተብሎ የሚነገርላት ሴት አሁን ዘጠነኛው የበና ቢታ ሆነዉ የሚያስተዳድሩት የግራዝማች አድነዉ ጋርሾ አያት እንደነበረች ይታመናል፤ ስለዚህ ጉዳይ አቶ ሳራ አይታ አልዱባ ቀበሌ ሲገልፁ "ከቢታ የዘር ሀረግ ግንድ ዉስጥ ሶስት ጡት ያላት ሴት ነበረች። ይህ ደግሞ ለየት ያለ አፈጣጠር ነዉ። ቢታችን በእኛ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሄርም ዘንድ ተወዳጅ ስለሆነ ነዉ የዚህ አይነት የተለየ አፈጣጠር የተከሰተዉ" በማለት የዚህች ሴት በቢታዉ የዘር ሀረግ ዉስጥ መፈጠር ማህበረሰቡ ንግስናዉን ሳይጠራጠር እንዲቀበል የታዬ ተአምር መሆኑን ይናገራሉ። አሁን ላይ በናን በቢታነት እየመሩ ያሉትም ግራዝማች አድነዉ ጋርሾ ይህንን የብሄረሰቡን ሀሳብ ሊያጠናክሩ፤

ተረታ-12 እኔ ሶስት ጡት ያላት አያት ነበረችኝ። የተናገረችው ሁሉ ስለሚደርስ በእኛ ብሔረሰብ እሷ ያለችውን ችላ የሚል አልነበረም። እንደውም አንድ ወቅት ላይ አንድ ሰውዬ ከእሷ ጋር ተጣልቶ ስላዘነችበት ሳምንት እንኳን ሳይቀይ ሞቷል። እሷ አንድን ሰው ፊት ለፊት ተመልክታ ትሞታለህ ብላ ካለች ይህ ቃሏ በትክክል ይደርሳል። እናም አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን አይታ መጨረሻቸውን እንደትንቢት ትናገር ነበር።

የሴትየዋ ታሪክ በዚህ ብቻ አያበቃም በበና ንግስናዉን የሚረከበዉ የንጉስ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ በመሆኑ ሴት ቢታ አይታሰብም። ሆኖም እስካሁን ባለዉ የብሄረሰቡ ታሪክ ባለ ሶስት ጡት ሴት የመጀመሪያዋ ሴት ቢታ እንደ ነበረች ግራዝማች አድነዉ ጋርሾ በተረታ 12 ከገለጹት ታሪክ ጋር አያይዘው እንዲህ ብለዋል፤

> በማህበረሰቡ ዘንድም ተቀባይነት ስለነበራት የእኔ አያት ቃራ ሲሞት ንግስናዉን የመጀመሪያ ልጁ የእኔ አባት ጋርሾ መረከብ ነበረበት። በወቅቱ ግን ጋርሾ እድሜዉ ገና ስለነበር ጋርሾ ንግስናዉን እስኪረከብ ባለ ሶስት ጡት አያቴ ለሶስት ዓመት በቢታነት ህዝቡን አስተዳድራለች። በእኛ በቢታ የብዙ ዘመናት ቆይታ ሴት ቢታ ሆና አታውቅም፤ ግን የመጀመሪያዋ ሴት የበና ቢታ እሷ ብቻ ነበረች። (አቶ አድነው ጋርሾ፤ ቦሪ ቀበሌ፤ 16/7/04፤ የካሴት ቁ.13/ሀ)

እናም ባለ ሶስት ጡት ሴት ማን እንደነበረችና በህብረተሰቡ ስለነበራት ክብር በተረታ ይተርካሉ። እስካሁን ድረስ ባለው የማህበረሰቡ የቢታ ታሪክም ብቸኛዋ የሴት ቢታ በመሆኗ ታሪካ ለትውልዱ ይተረካል።

ጀግንነት፣ የበና ብሔረሰብ በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ ምክንያቶች በዙርያው ካሉ ሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ግጭት ውስጥ ይገባ እንደነበረ ታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ። ታድያ እነዚህን ታሪኮች ሲተርኩ ከግጭቱ ባሻገር ጀግንነትን በተመለከተ አርአያ አድርገው የሚያነሷቸው ግለሰቦችን ታሪክ ይተርካሉ፤ ከሚተረክላቸው ጀግኖችም ሳቤ፣ ሉሞገር እና አይታ ተጠቃሽ ናቸው። ከነዚህም የአይታ ታሪክ እንዲህ ይተረካል፦

ተረታ-13 ድሮ እናቴ የነገረችኝ አንድ ወቅት የእኛ በኖች ሐመር ውስጥ ካሉ በሸዳዎች ጋር ጥሰኛ ነበሩ። በዚያን ሰዓት አይታ የሚባል የበና ጀግና ነበር። የበሸዳ ደግሞ ሱሚ የሚባል። እናም በወቅቱ በሸዳዎች ከበና አገር አልተ የሚባል አከባቢ እየመጡ ሰዎችን ይጨርሱ ነበር። ከዚያ አይታ የሚባለው የበና ጀግና በሸዳ እየሄደ በአንድ ምሽት ብቻ እስከ አሥር ሰው ድረስ ይገድል ነበር። በዚያም ወቅት የበሸዳ እናቶች ልክ ህፃናትን አሁን ‹ጅብ መጣ!

ጅብ መጣ!› ብለው እንደሚያስፈራሩት ‹ኦይታ መጣ! ኦይታ መጣ!› እያሉ ልጆችን እያስፈራሩ ወደ ቤት ያስገቡ ነበር። ኦይታ... (አቶ ቆጳ ሼሎ፤ቦሪ ቀበሌ፤24/7/04 ዓ/ም፤የካሴት ቁ.10/ሀ)

በተረታ 12 እና 13 የምናገኛቸው ተረኮች ብሔረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የነበሩና በጊዜያቸውም በሁሉም የብሔረሰቡ አባላት እንዲታወቁ የሚያደርግ የተለየ ተግባር የነበራቸው ለዎችን ታሪክ የቃል መረጃ በመሆን ለትውልድ የሚያስተላልፉና ትውልዱ የኋላ ታሪክ ያለው መሆኑንም የሚያሳውቁት ናቸው። በተጨማሪ ለትውልዱ የዛሬ ማንነት ያለፉ አባቶቹ ወቅቱ በሚጠይቀው አግባብ የከፈሉትን መስዋእትነት በመዘከር ትውልዱ ልክ እንደአባቶቹ በህይወት ዘመኑ አሁን ካለው የጊዜው አስተሳሰብ ጋር አብሮ የሚሄድና ለትውልድ የሚተላለፍ ታሪክ በሚችለው አቅሙ ሰርቶ እንዲያልፍ የሚያበረታቱና የሚያነሳሱ ሁነው እናገኛቸዋለን።

ኢኮኖሚ፤ የብሔረሰቡ ኢኮኖሚ የተገነባው በእንስሳት እርባታ ላይ በመሆኑ የንግድ ልውውጡም በእንስሳቱ ላይ የተመሰረተ ነው። የእንስሳቱን ቁጥር እየጨመሩ መሄድ እንጂ ወደ ገንዘብ መቀየር አይቻልም። ህመም፤ እህል ሽመታና መሰል ችግሮች ካላጋጠሙ በቀር መሸጥ በጥብቅ ይወገዛል። በተረፈ የጦር መሳርያ ገዝተው ለመታጠቅ ግን ከብትን በመሳርያ መቀየር ይቻላል። የከብት እርባታና የጦር መሣሪያ መታጠቅ አጀማመርን አስመልክቶ ከሚተረኩ ተረታዎች መካከል አንዱ የሚከተለው ነው።

ተረታ-14 አባቴ ድሮ ወጥመድ አጠማመድን ካሳየኝ በኋላ እኔም ማጥመዴን ቀጠልኩ። ነብርም በወጥመዴ ተይዞ ገደልኩ። ለአባቴ ስነግረውም" እስካሁን ራሴ የሰራሁትን ጦር ይገፍ ነበር ያለሁት፤ አሁን ግን የነብሩን ቆዳ ሸጬ ዘመናዊ የጦር መሳርያ ገዝቼ አነግታለሁ (እታጠቃለሁ)" ብሎ ቆዳውን ተቀብሎኝ በሸጠዉ ብር መሳርያ ገዛ። ለእኔም ጦሩን አወረሰኝ ለሁለተኛ ጊዜ በወጥመዴ ነብር ገደልን። ይህን ጊዜ አባቴ" አሁን ቆዳውን ሸጬ ለልጄ ከብቶች ነዉ የምገዛዉ" አለና ስድስት ከብቶች ገዝቶ ሰጠኝ። ሲሰጠኝም" እንግዲህ እነዚህን ከብቶች አርብተህ ሲበዙልህ በእነሱ መሳሪያ ግዛ"› አለኝ። "ታናሽህም እንዲሁ ያደርጋል ልጅም ስትወልድ እኔ እንዳደረኩልህ አድርግ" አለኝ።(አቶ አልዳ ቢሮ፤ ዲዚ አማ ቀበሌ፤ 3/7/04 ዓ/ም፤የካሴት ቁ.17/ሀ)

በዚህ መነሻነት ብሔረሰቡ ከብት ማርባት እንዴት እንደጀመረ? እስከዛሬም ድረስ የህይወቱ መሰረቶች እንዴት እንደሆኑ? ዘመናዊ የጦር መሳሪያም በከብት ለውጠው የሚታጠቁት ከአባቶቻቸዉ በዚህ መልኩ የወረሱት ስለሆነ መሆኑን ተረታው ምላሽ ይሰጣል። በተመሳሳይ ሁኔታም ስለ አደን አጀማመራቸው ይተርካሉ፦

ተረታ-15 ድሮ አባቴ አዉሬ ለመግደል ፈልጎ ጦር ሰራ በጦሩም እህል የሚበሉ ትንንሽ አዉሬዎችን መግደል ጀመረ። ቀጥሎም በገመድ ወጥመድ ሰራና ማጥመድ ጀመረ። አንድ ቀን ትንሽ አዉሬ በወጥመዱ ተያዘች ወድያዉ ጦሩን ሰጠኝና "ግደል" አለኝ። አከታትሎም "ገደልክ ምንድነዉ የገደልከዉ?" ብሎ ጠየቀኝ ስሟን እኔ አላዉቅምና "ጃርት" ናት አለኝ። "መግፈፍት ችላለህ?" አለኝ። አለመቻሌን ስነግረዉ ቢላዋ አንስቶ ከላይ ከላይ እየፋቀ ገፎ አሳየኝና ሲጨርስም ስጋ ነዉ እንዴ? አልኩት፤ ለመብላትም ፍቃደኛ አልነበርኩም። አባቴም "እኔ በልቻለሁ ልጄ አንተም ብላ" አለኝ። እኔም ተቀቅሎ ነዉ ወይስ ጥሬዉን? ብዬ ስጠይቀዉ እንስራ አነሳና ቀቅሎ አሳየኝ። "ሲቀዘቅዝ ነዉ የሚበላዉ" ብሎ በሾርቃ (ከቅል ክፋይ የሚሰራ ባህላዊ ቁሳቁስ) አቀዝቅዞ አበላኝ። በሌላ ጊዜ ሚዳቋ በወጥመድ ተይዛ ስለነበር በጦር ገደልኳትና በላናት። ቀጥሎ ዱኩላ ተያዘ እንዲሁ አደረግን። በመጨረሻም አባቴ "እስካሁን እኔ ባጠመድኩት ወጥመድ ስትገድልና ስትበላ ነበረ አሁን ግን ልጄ ተመልከት" አለኝና ወጥመድ አሰራርና የአጠማመዱን ዜዴ አሳየኝ። (አቶ አልዳ ቢሮ፤ ዲዚ አማ ቀበሌ፤ 3/7/04 ዓ/ም፤ የካሴት ቁ.17/ሀ)

ይህ ተረታ በናዎች ዛሬም ድረስ የሚያከናውኑትን አደን እንዴት እንደ ጀመሩ? ምግብን ማብሰል ከማን እንደተማሩ? ለመመገብያነትና ለማብሰያነት የሚጠቀሟቸዉን ቁሳቁሶች መጠቀምን ከማን እንደ ተማሩ? የሚተርኩበት ነዉ።

5.2. - የ"ኤዔሪ" ማህበረ - ባህላዊ ፋይዳ

ከተረታ በመቀጠል በበናዎች የተለመደው የተረክ ዘርፍ "ኤዔሪ" ይባላል። በዚህ የተረክ ክፍል የምናገኛቸውን ተረኮች ከጭብጣቸው በመነሳት በስድስት ዋና ዋና ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳዎች ላይ የሚያጠነጥኑ ሆነው እናገኛቸዋለን። እነሱም ብልጠትን ወይም አስተዋይነትን መስበክ፣ ማስተማርና ማዝናናት፣ ለጥቅም ብሎ የራስን ማንነት አሳልፎ መስጠት እንደማይገባ፣ ስለታማኝነት እና አካባቢንና ተፈጥሮን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ናቸው። እነዚህንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን።

- **ብልጠትን ወይም አስተዋይነትን መስበክ**

በኤዔሪ ትረካ ውስጥ ተተኪው የአሁኑ ትውልድ እንቅስቃሴውን ማስተዋል በተሞላበት መንገድ እንዲያደርግ የሚተረኩ ተረኮች ከሌሎች ጋር በንጽጽር ሲታዩ በቁጥራቸው ብዙ ናቸው። ካሰባሰብኳቸው አጠቃላይ 72 ተረኮች 43 ያህሉ ኤዔሪ ሲሆኑ ከነዚህም 11 የሚያክሉት ጭብጣቸው ብልጠት ወይም ማስተዋል ነው። የዕለት ተዕለት ኑሮአችን በማስተዋል የተሞላ መሆን ይኖርበታል።

ማስተዋል ወይም ብልህነት በርካታ ፋይዳዎች አሉትና። ከሚፈለግ ግብ ላይ ለመድረስ፣ በአታላዮች ላለመቀማት፣ የመፍትሄ ሰዎች ለመሆን፣ ድንገት ከተጋረጠ አደጋ ለማምለጥ፣ ... ወዘተ አስተዋይነት የግድ ይላል።

ይህ ታድያ ዝም ብሎ የሚመጣ ባለመሆኑ ነገ የማህበረሰቡን እሴት ተረካቢ ህፃናትና ወጣቶች በማስተዋል የተሞሉ እንዲሆኑ በእድገታቸው ወቅት የማስተዋልን ወይም የብልህነትን ችሎታ እንዲያዳብሩ ተረኮች ይነገሯቸዋል። በበና ብሄረሰብ የኤፌሪ ተረኮች ሰዎ ብልጥና አስተዋይ እንዲሆኑ ጉልህ ድርሻ ያላቸው ሲሆኑ የብልህ ወይም የአስተዋይ ተምሳሌት ተደርጋ የምትቆጠረውን የሽለምጥማጥ (ድመት የምትመስል የዱር አውሬ) ታሪክን መተረክ በሰፊው የተለመደ ነው።

የመፍትሄ ሰዎች ለመሆን

ኤፌሪ- 24 ከዕለታት አንድ ቀን ዝሆን ማር ተሸክሞ ወደ ገበያ ተነሳ። በመንገድ ሲሄድ ከአንድ ሽለምጥማጥ ጋር ተገናኘ "አንተ ዝሆን ሆይ! እኔን ደክሞኛል ተሸከመኝ?" አለችው። ዝሆኑም አወርዷት ማሩን ሲያይ ቅሉ(የማሩ መያዣ ነው) ባዶ ሆኖ አገኘው። "ማሩ እንዴት አድርገሽ ጨረሽ?" ብሎ ጠየቃትና ወድያውም ይዞ አሰራት። አርጩሜም ሰብሮ ሊገርፋት ሲል ሽለምጥማጧ ፈጥና "ይህ አርጩሜ ስለማያሳምም በእሱ አትምታኝ ይልቅስ በበረሃ አርጩሜ ምታኝ" አለችው። ዝሆኑም አርጩሜ ለመስበር በረሃ ወረደ ሽለምጥማጧ በታሰረችው ቦታ ጅብ ሲያልፍ አያትና መጣ። "ለምን ታሰርሽ?" ሲል ጠየቃት። "ጮማ ስጋ ብይ ተብዬ እምቢ በማሉቴ ነው የታሰርኩት" አለችው። ጅቡም እባክሽን ባንቺ ቦታ እኔ ልታሰር?" ብሎ ለመናት። "እንዲህ ከሆነ እኔን ፍታኝና አንተ ልሰርህ" አለችው። በሀሳቡም ስለተስማሙ ጅቡ እሷን ፈታትና እሷም በቦታዋ ጅቡን አስራው ሄደች። ..."(አቶ ሼሎ ባላ፡ ጉርዶ ቀበሌ፣29/7/04 ዓ/ም)

በህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ በርካታ መሰናክሎች ይገጥማሉ። እነዚህ መሰናክሎች ሲገጥሙን ተስፋ በመቁረጥ ሁሉ ነገር እንዳበቃለት አድርጎ ከማ ሰብ ይልቅ በእርጋታ መፍትሄዎችን ብናስባቸው መፍትሄ የሌለው መሰናክል እንደሌለ እንረዳለን። ለዚህም ኤፌሪ ስንመለከት ሽለምጥማጧ በተያዘች ጊዜ ለማምለጥ ከመንፈራገጥ ይልቅ የተጠቀመች መፍትሄ ከዱላ እንድትድን አድርጓታል። በተመሳሳይ ሁኔታ በኤፌሪ 25 የሚተረከው የጦ የአዞ ታሪክ ጠጣዋ ሕይወቷን የሚያሳጣት አጣብቂኝ ውስጥ በገባች ጊዜ የተጠቀመች የማምለጫ መፍትሄ እንደታደጋት ያስረዳል።

በመሆኑም አደን ተወጥቶ መውጫው ቢጠፋ፣ ከብቶች ቢዘረፉ ሌላም ፈተና ቢገጥም ፈተናውን ማለፍ የሚያስችል መፍትሄ ማፈላለግ እንደሚገባ አልያ ግን በዝምታ መመልከት ውጤቱ ሽለምጥማጥና ጦጣ ዝም ቢሉ ከሚደርስባቸው አደጋ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጉዳት እንደሚገጥም ብሔረሰቡ አዘውትሮ በኤዔሪው ይመክራል።

ወደ ማያውቁት አከባቢ ሲኬድ ምን ማድረግ እንደሚገባ

የበና ብሔረሰብ አርብቶ አደር በመሆኑ የሚያረባቸው ከብቶቹ ሳይራቡ፣ ሳይጠሙ በተመቻቸ ሁኔታ ይረቡለት ዘንድ ለነሱ ተስማሚ ቦታ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር ይታያል። ታድያ በዚህ ሂደት አንዳንዴ የራስን ቀዬ ለቆ ራቅ ወዳለና ወደማያዉቁት አገር መሄድም ስላለ የችግሩን ጊዜ አሳልፈው ወደ ቀዬአቸው እስኪመለሱ በማስተዋል የተሞላ እንቅስቃሴ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ይህንንም አስተሳሰብ ለመገንባት ከሚተረኩ ኤዔሪዎች መካከል የቆቋና የጅግራዋ ታሪክ አንዱ ነው።

ኤዔራ- 26 አንድ ወቅት ላይ ቆቅና ጅግራ ዘር ለመውሰድ ይገናኛሉ። እናም ቆቅ ወደ ጅግራ ቤት ሄዳ ዘር እንድትሰጣት ትጠይቃታለች። ጅግራም የምትጠይቀውን ዘር እንደምትሰጣት፣ ነገር ግን አሁን ሳይሆን ዝናብ ሲመጣ ተመልሳ እንድትመጣ ነግራት ትሸኛታለች። ቆቅም በነገሩ ተስማምታ እየተመለሰች ሳለ መንገድ ላይ አንዲት ላም ሽንቷን ሽንታ ያጎረፈውን ጎርፍ አይታ "እንዴ! የተባለው ዝናብ ዘንቦ አይደለም እንዴ ይህ ጎርፍ የመጣው?" ብላ ወደ ጅግራዋ ቤት ተመልሳ ትሄዳለች። በራፍ ላይ ስትደርስ ከቤት ውስጥ ሆና የምትመለከታት ጅግራ "በራፋችን ላይ እግሩን አቅልቶ የመጣው ይሄ ምን ነገር ነው?" ብላ ስትጠይቅ ትሰማለች። ቆቋም መልሳ ጅግራዋን "አንቺ ጎባጣ አንቺ በመከርሸኝ መሠረት አይደል ዘሩን ለመውሰድ የመጣሁት?" ትላታለች። እቤት ውስጥ የነበረችው ጅግራም "እግረቀይዋ እግርሽን አቅልተሽ የምትመጭው ስለሀገሩ ምኑን አውቀሽ ነው?" ብላ መለሰች ይባላል።

(ወ/ሮ ኬሮ በላቸው፣ዲዚ አማ ቀበሌ፣23/7/04 ዓ/ም፣የካሴት ቁ.1/ለ)

የዚህ ተረት ፋይዳ የራስን አገር ለቆ ወደማያዉቁት አገር ሲሄዱ መደረግ ስላለበት ነገር ያስጨብጣል። በመጀመርያ ደረጃ ጅግራዋ ቆቋን "... ደግሞ አንቺ ስለዚህ አገር ምን ታውቂና ነው የምትናገሪው ..." እንዳለቻት ሁሉ ከለመድነውና ከኖርንበት ልማድና ባህል ወጥተን አዲስ አከባቢ ስንሄድ ወደ ተግባራችን ከመግባታች በፊት ስለአካባቢው አጠቃላይ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ ቀድሞ ማወቅ ተገቢ መሆኑንና ካልሆነ ግን ከማህበረሰቡ ልማድ ውጭ የሆነ ተግባር ከውን ግባችንን ሳናሳካ ልንቀር እንችላለንና ይህ እንዳይገጥመን ይተረካል።

በተለይ ደግሞ ዛሬም በናምች አካባቢያቸው በረሃ በመሆኑ በበጋ ወቅት ሳርና ውሃ ስለሚጠፋ ከብቶቻቸውን ይዘው በርቀና (አካባቢ በድርቅ ሲመታ ሳርና ውሃ ወዳለበት ወደ ሌላ አከባቢ ከብቶችን ይዞ መሄድ) ይላሉ። ሆኖም ግን ይህ ወቅት አልፎ ወደ ቀዬአቸው እስኪመለሱ በሄዱበት ቦታ ካሉ አካላት ጋር ተስማምተውና ያለምንም ግጭት በሰላም ወደ ቀዬአቸው ይመለሳሉ። ለዚህም በሄዱበት በማስተዋል እንዲንቀሳቀሱ በተለይ እናቶች የሚተርኩላቸው ተረኮች ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።

ተፈላጊ ግብ ላይ ለመድረስ

ኤዔራ- 27 በድሮ ጊዜ ዘወትር የሚጣሉ ባል እና ሚስት ነበሩ። ባልዬው ሁል ጊዜ ሲወጣ ሲገባ ሚስቱን በረባ ባልረባ ምክንያት ይደበድባት ነበር አሉ። እናም ድብደባው የበዛባት ሚስቱ የኑሮዋ ሁኔታ ግራ ቢገባት ሰፈሯ ወዳለች አሮጊት ሴት ቤት ሂዳ ችግሯን ሁሉ አንድ ባንድ ነገረቻት።... ይህን ጊዜ አሮጊቷ መልሳ "የጫካ አውሬ የሆነውን እና እጅግ አስፈሪውን አንበሳን ያክል እንስሳ ማላመድ እና ገራም ማድረግ ከቻልሽ የሰው ልጅ የሆነውን አንድ ባልሽን እንዴት መግራት አቃተሽ? በይ ወደቤትሽ ሂጅና አስቢበት።" ብላ ሸኘቻት ይባላል።

(ወ/ሮ ኬሮ በላቸው፤ ዲዚ አማ ቀበሌ፤ 23/7/04 ዓ/ም)

ከላይ የተተረከው የአሮጊቷ በብልሀት የተሞላ ምክርን የያዘው ኤዔሪ ሕይወታችንን የምንመራው በማስተዋል ከሆነ መፍትሄ የሌለው ነገር የለም። የችግሮች ሁሉ መፍትሄ ቁልፉ በእጃችን ነው። ከአንበሳ ጎፈር ፀጉር መንቀል እስኪቻል ድረስ የሰው ልጅ በመፍትሄዎች የተሞላ ስለሆነ ይህንን ማስተዋል ያስፈልጋል። የሚል መልእክት ያስተላልፋል። ኤሪ 28ትም ተመሳሳይ ጭብጥ ያለው ነው።

ኤዔሪ 28 አሥር ልጆች ያሉት አንድ ሰው ነበር። አንድ ቀን ታመመና በሽታው ልክፍት ነው ተብሎ ስለታሰበ የሰው ደም እንዲጠጣ ታዘዘ። በዚህን ጊዜ ልጆቹን ጠራቸውና የሰው ደም እንዲያመጡለት አዘዛቸው።... ለሁለተኛ ጊዜ ሳያገኙ ተመለሱ። ይህን ጊዜ አባትዬው ተናደደና ልጆቹ ን "በሉ ተሸከሙኝና ገበያ መ ሃል ውሰዱኝ" አላቸው።... ልጆቹም እንደታዘዙት ገበያው መሐል ላይ አስተኙት።... ይህን ጊዜ በሽተኛው ሰውዬ ልጆቹን ጠርቶ "አያችሁ! የሰው ደም የሚጠጣው በዘዴ ነው። ቀድማችሁ ቤት ድረስ አምጥታችሁልኝ ቢሆን ኖሮ እስካሁን እኔ ድኜ ነበር። በሉ አሁን ስጡኝ" ብሎ አላቸው ይባላል። (አቶ ቡራ ሼሎ፤ ቦሪ ቀበሌ፤ 17/7/04 ዓ/ም፤ የካሴት ቁ.18/ሀ)

በተጨማሪም ኤዔሪ 28 በሽተኛው አባት ከበሽታው የሚፈውሰው መድሃኒቱ የሰው ደም በመሆኑ ያንን ለማግኘት ልጆቹ ሲደክሙ ይታያሉ። ሆኖም ግን ሞኝነታቸውን የተረዳው አባት በምን ሁኔታ መድሃኒቱን ማግኘት እንደሚችሉ በተግባር ያስተምራቸዋል።

በመሆኑም ኤዔሪ 27 እና 28 የምንፈልገው ግብ ላይ ለመድረስ በርካታ ውጣ ውረዶች ከፊታችን እንደሚጠብቁንና እነዚህን ውጣ ውረዶች በጥበብ ከታገልናቸው የምንፈልጋቸው ግቦቻችንን ማሳካት እንችላለን፤ ይህም በማስተዋል መሆን አለበት። የሚሉ ብርታትን የሚያጎናጽፉ መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ።

- **ማስተማር እና ማዝናናት**

ብሔረሰቡ በእለት ተእለት ኑሮው ውስጥ አንዱ ከሌላው ጋር ሊኖረው የሚገባው የግንኙነት አግባብ በምን መልኩ መሆን እንዳለበት የሚያመለክቱ ተረኮች አሉት። ተረኮቹ ታናናሾች ለታላላቆቻቸው ሊኖራቸው ስለሚገባ ክብር፣ የወላጆችን ምክር ስለመስማት፣ በሌላ ሳኑ ደግሞ ታላላቆችም እኛ ብቻ ነን አዋቂዎች ታናናሾቻችን ምንም አያዉቁም ወይም ከእኛ የበለጠ ክህሎት የላቸውም ብለው ታናናሾችን እንዳይንቁ የሚተረኩ ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ተረኮች እስከዛሬ በብሔረሰቡ ውስጥ በዳበረ ሁኔታ ለሚታየው ታላላቆችን የማክበር፣ ታዛዥነትና ምክርን የመቀበል፣ የራስን አቅም አውቆ የመኖርና የመቻቻል ልማድ መጠንከር ጉልህ ሚና አላቸው።

ታናናሾችን አለመናቅና ታላላቆችን ማክበር

ኤዔሪ 29 ድሮ በአንድ ወቅት ፍየልና መገርገር ተፎካከሩ። ፍዬሉ መዥገሩን ንቆት ነበርና መዥገርዎ
ፍዬልን "አንተ ስትሮጥ እኔ ከእግርህ ስር ሳልጠፋ አንተ ጋር እኩል ካሮጥኩኝ እ
መዥገር አይደለሁም። እስኪ አንተ እሮጠህ እሮጠህ ከእግርህ ስር እየኝ፣ እኔ ከሌለሁ እ
መዥገር አይደለሁም!" ይለዋል። ከዚያ ለመሮጥ ሲዘጋጁ መዥገሩ የፍየሉ እግር ስ
ተጠግቶ ይቆማል። "ሩጫ እንጀምር!" ብለዉ መሮጥ ሲጀምሩ መዥገሩ ቶሎ ብሎ ፍየ
ላይ ይለጠፋል።... ፍዬሉም ብዙ ርቀት ሮጦ ሮጦ ሲደክም ቆም ብሎየት እንዳለ ለማየ
ዞር ሲል መዥገሩ "እኔን እንዳትረግጠኝ ካንተ እኩል እግርህ ስር ነኝ" ይለዋል። እና
እንዲህ አድርጎ ፍየሉን አሸነፈዉ።(አቶ ሽላይ በዶ፤የዲዚ አማ ቀበሌ ስራ አስኪያጅ፤3/7/0
ዓ/ም፤ የካሴት ቁ.17/ሀ)

ኤዔሪ 29 እና ኤዔሪ 30ን ስንመለከት ጅብ እና ፍዬል ትልቅነታቸውን ተመክተ
ትንንሽ ያሉዋቸውን እንቁራሪቷንና መዥገሯን መናቃቸውን ሆኖም በትንሽነታቸው የተናቁ

ግን ትልቅ ነን ባዮችን በብልሀት አሸናፊ የሆኑበትን መንገድ የሚያሳዩ ኤዜሪዎች ናቸው። ስለዚህ የማህበረሰቡ አካላት በእድሜ፣ በእውቀት፣ በሃብትና በመሳሰሉት "እኛ የተሻልን ነን፣ ከኛ ውጪ ማን አለ?" በሚል እንዳይኮፈሱ፣ ታናናሾቻቸውንም እንዳላዋቂ ቆጥረው እንዳይንቋቸውና ሀሳቦቻቸውም መደመጥ እንዳለበት መልዕክት ያስተላልፋሉ። በተመሳሳይም መልኩም ለታላላቆች ክብር መስጠት እንደሚገባ ያስተምራሉ፤ ኤሪ 31 ለዚህ ተጠቃሽ ነው።

ኤዜሪ 31 በድሮ ጊዜ ዘጠኝ ጅቦችና አንድ አንበሳ ለጦርነት ይሄዳሉ። ጦርነቱንም ተዋግተው ሲጨርሱ አሥር ከብቶችን ማርከው ይመለሳሉ። ... "እኔ አንድ ነኝ እናንተ ደግሞ ዘጠኝ ናችሁ። ስለዚህ ዘጠኝ ከብቶችን እኔ ብወስድ እናንተ ደግሞ ዘጠኝ ናችሁና አንድ ብትወስዱ አንድ ላይ አሥር ትሆናላችሁ፣ ስለዚህ እኛ እንደዚህ እኩል ተከፋፍለን እንሂድ ይላቸዋል።" ሀሳቡን የሰሙት ጅቦች በሀሳቡ ላይ ከተወያዩ በኋላ "ብንከራከር አንበሳ እኛን አይለቀንም" በሚል ሃሳቡን ተቀብለው አንዷን ከብት ብቻ ወስደው ወደ አባታቸው ይሄዳሉ። ..."(አቶ ጋርሾ ውካ፤አልዱባ ቀበሌ፤29/6/04 ዓ/ም)

በአጠቃላይ ብሔረሰቡ ለልጆቹና ለአከባቢው ወጣቶች በሆነ ነገር የሚበልጧቸውን ሰዎች ማክበር እንዳለባቸውና ከሚበልጧቸው ጋር ትግል መግጠም ሽንፈትንና ውርደትን ስለሚያስከትል ማሸነፍ አለመቻላቸውን ሲረዱ ግትር ከመሆን ይልቅ በዘዴ ማለፍ አስፈላጊ መሆኑን ለማስተማር ይህንንና መሰል ተረኮችን እንደሚነግሯቸው ስንመለከት የኤዜሪ ተረኮች ማህበረሰቡ ለገነባው የመከባበር ልማድ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ጉልህ መሆኑን እንገነዘባለን።

- **ምክርን መቀበልና ታዛዥነት**

ኤዜሪ 33- በድሮ ጊዜ አይጦች ድመት ሁል ጊዜ እነሱን እየበላች ስታስቸግር ከድመት ለማምለጥ መፍትሄ ለማግኘት እርስ በእርስ ስብሰባ ተጠራርተዉ ተቀመጡና ዉይይት ጀመሩ ተባለ። ድመት እንዳትበላቸዉ የሚያደርግ መፍትሔ ለማበጀት ብዙ ከተወያዩ በኋላ በስተመጨረሻ ላይ አንድ አይጥ "ድመት እኛን ለመብላት ስትመጣ ድምጽ ሰምተን እንድናመልጥ ለከብቶቻችን የምናስረዉን አይነት ቃጭል በአንገቷ ላይ እንሰር።" የሚል ሀሳብ አቀረበ። የቀረበውንም አዲስ ሀሳብ ያደመጡት አይጦች በሙሉ በአንድ ድምፅ ተስማምተው አፀደቁት። ወዲያውም ከመሀከላቸው አንድ ጥበቡ የተባለ ሽማግሌ አይጥ ተነሳና በውሳኔያችሁ ተስማምቻለሁ። ነገር ግን የተባለውን ቃጭል ለማሰር ድመትን ይዞ የሚያቀርብልን አንድ ኃይለኛና ጉልበታም አይጥ መምረጥ አለብን እናም ከመሀከላችን ሀይለኛ የሆነው ማነው? አሁን እንምረጥ" አላቸው። ነገር ግን ድመትን የሚይዝ አይጥ ይበላልና ይህንን ሀላፊነት ደፍሮ የሚቀበል ጠፋ። በዚህም ምክንያት ቃጭል ለማሰር የተደረገዉ ዉሳኔ ፈረሰ ይባላል። (አቶ ጊሎምባ ሳቤ፤ሞርገላ ቀበሌ፤14/7/04/ ዓ/ም)

በኤዴሪ 33 ላይ [illegible] ከሽማግሌው ሊሰሙ ወድያው ትክክለኛ አለመሆናቸውን አውቀው ሃሳባቸውን መቀየራቸው፣ መታዘዛቸውና ምክርን መቀበላቸው ከፊት ለፊታቸው ይጠብቃቸው ከነበረ አደጋ ሊታደጋቸው እናያለን። ስለሆነም የሽማግሌዎችን፣ የወላጆችንና የታላላቆችን ምክር መስማትና ታዛዥ መሆን ራስን ከአደጋ ብሎም አከባቢን ከመዓት ይጠብቃል የሚልን በተረት የተዋዛ መልእክት የማስተላለፍ ፋይዳ እንዳለው እንገነዘባለን።

ግልፅነትን ማስተማር

ኤዴሪ 34 "...ይህን ጊዜ የልጅቱ እናት ተደስታ ጓደኛዋን የቆነጠጠች መስሏት ሳታስበው አማቿን ቆነጠጠች። አማቿም ደንግጦ "ምነው እናቴ?" ብሎ ጠየቀ። ይህን ጊዜ ደንግጣ የምትለው ቢጠፋት "አይ! በኛ እኮ ቦታ በግ ነውር ስለሆነ አይበላም።" ብላ አለችው። ... ጓደኛዋ ስትበላ እሷ በአፏ ባመጣችው መዘዝ ሳትበላ ቀረች። ... እጇ ላይ ብዙ የአንባር ጌጣጌጥ ነበርና የፊላው ውሃ ከአንባሩ ጋር ሆኖ ሲያቃጥላት ደንግጣ በማውጣት እጇን ልብሷ ውስጥ ደበቀች። ... እጇ ተቃጥሎ ሥጋው ከአንባሩ ጋር ወልቆ አጥንቱ ብቻ ነበር የሚታየው ..." (ወ/ሮ ኬሮ በላቸው፤ ዲዚ አማ ቀበሌ፤ 3/7/04 ዓ/ም፤የካሴት ቁ.17/ለ)

ይህ ተረክ ሃሳብን በግልጽ ማቅረብ እየቻሉ በይሉኝታ ዝም ማለት ወይም መደበቅ የተለያዩ ጥቅሞችን የሚያሳጣ ከመሆኑም ባሻገር አስከፊ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ለማሳሰብ ከሚተረኩ ተረኮች መካከል አንዱ ነው። አማችዋ ቤት የሄደችው ሴት በክብር ስትጠየቅ ፍላጎትዋን ባለመግለፅዋና በመደበቅዋ የምትፈልገውን ነገር አጣች። በዚህም ሳታበቃ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሃሳብዋን ለማሳካት ስትል እጅዋን በቃጠሎ አጣች። ስለዚህ ከእንደዚህ አይነት ችግሮች ለመጠበቅ ግልፅነት አስፈላጊ ነው።

በግልፀኝነት ላይ በበናዎች ያለው ልምድ ሲታይ ትክክልም ይሁን የተሳሳተ ሃሳብን ያለምንም መሸማቀቅ፣ ይሉኝታና ፍርሃት በግልፅ መናገር የተለመደ ነው። ታድያ ሃሳቡ ትክክል ከሆነ የሚጠናከርበት የተሳሳተ ከሆነ ደግሞ ስህተቱ በተገቢው ይታረማል እንጂ በተሳሳቱ አላዋቂ አድርጎ መቁጠር አይታይም። ይህ ደግሞ ሰዎች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲያራምዱ ያነሳሳቸዋል። ይህንን እውነታ ማህበረሰቡ ውስጥ በነበርኩባቸው ጊዜያት በነበረው የመንግስትና አከባቢያዊ ስብሰባዎች እንዲሁም በባህላዊ የዳኝነት ስርአቱ ላይ በመመልከት ማረጋገጥ ችያለሁ።

በናዎች ሌባን ሌባ ፣ ጨዋን ጨዋ፣ በንፉን በንፉ በማለት ግለሰቡ ፊት ለፊት ቁሞ ባሉበት በግልፅ ይወያያሉ እንጂ ዞር ብሎ ማማት አልተለመደም። ምክንያቱም ትክክለኛውን ነገር ባይናገሩ በተረክ አርባ እንዳለችው አሮጊት የሚፈልጉትን አያገኙምና ነው። በዚህ ብቻ ሳያበቃ በትክክለኛው መንገድ በመሄድ ፍላጎትን ማሳካት እየተቻለ ሌላ የተሳሳተ መንገድ መከተል ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም የሚል አመለካከትን ለመገንባት እንደዚህ ባሉ ተረኮች ይማማራሉ።

- **ለጥቅም ብሎ የራስን ማንነት አሳልፎ መስጠት እንደማይገባ**

በበና ማህበረሰብ ዛሬም በጉልህ ከሚታዩ እሴቶቻቸው በራስ ማንነት መኩራት ተጠቃሽ ነው። ለጥናቴ በተዘዋወርኩባቸው ቀበሌያት ይህንን ለማረጋገጥ ችያለሁ። ስለአለባበሳቸው፣ ስለአመጋገባቸው፣ ስለአጨፋፈራቸው በአጠቃላይ ስላላቸው ባህላዊ እሴት ሲናገሩ በፍፁም መተማመንና ደስተኛ ሆነው ነው።

አስቀድሞ በናዎች የኔ የሚሏቸውን ማንነት በተረታ ጠንቅቀው እንዲያውቁ ተደርጓል። ማንነትን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ኖረውበት ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ ከእያንዳንዱ ግለሰብ ይጠበቃል። ታድያ ለገንዘብና ለሌሎችም ጥቅሞች ብሎ ማንነትን አሳልፎ መስጠት በብሔረሰቡ "ቀይስ" (ነውር) ከሆኑና በአፅንዖት ከሚወገዙ ተግባራት አንዱ ነው።

ብሔረሰቡ ለገነባው በራስ ባህልና ትውፊት መተማመን፤ ከተረታ በመቀጠል ኤዔሪዎች ጉልህ ድርሻ አላቸው።

ኤዔሪ 35 ቀበሮ ሁል ጊዜ ውሻ የሰው ልጅን ሰገራ ስትልስ ታያት ነበር። ይህ የውሻ የዘወትር ድርጊት ያስገረማት ቀበሮ አንድ ቀን ወደ ውሻ ጠጋ ብላ "ወዳጄ ውሻ ሁል ጊዜ የሰውን ሰገራ ስትልሺ አይሻለሁ። እናም ለምን ይህንን ታደርጊያለሽ?" ትላታለች። ውሻዋም "ምን ላድርግ ብለሽ ነው! ይህንን የማደርገው ወድጄ ሳይሆን ከሰው ጋር እኖር ብዬ ነው። ይህንን ባላደርግማ ኖሮ ምግብ አይሰጡኝም ነበር።" የሚል ምላሽ ትሰጣታለች። በውሻ ምላሽ የተገረመችው ቀበሮም መልሳ "ስሚ! እኔ ግን ከሰው ጋር ለመኖር ብዬ ሰገራ አልስም!" ብላት ሄደች ይባላል። (አቶ ላራ አልማ፤ ጉርዶ ቀበሌ፤28/6/04 ዓ/ም)

በዚህ ተረክ እንደ ውሻዋ ለጥቅም ብሎ የራስን ማንነት፣ ክብርን ማዋረድ ተገቢ እንዳልሆነ ተመልክቷል። ስለሆነም ከላይ ለገለጽኩት የማህበረሰቡ በራስ የመተማመን ባህሪ

መገንባት በማህበረሰቡ ውስጥ [illegible] አንችላለን::

- ስለ ታማኝነት (ቃልን ስለመጠበቅ)

ብሔረሰቡ እርስ በርስም ሆነ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያለው ግንኙነት በታማኝነት ላይ የተመሰረተ ከማታለል፣ ከሃሰት፣ ከስርቆሽና ከሌሎችም የብሔረሰቡን ማንነትን ከሚያጎድፉ ነገሮች የፀዳ ነው:: ይህንንም በተመለከተ ብዙኃኑ የማህበረሰቡ አባላት በተደጋጋሚ፡-

> እኛ በናዎች ማታለል፣ መስረቅ አናውቅም:: ልጆቻችንም ታማኞች እንዲሆኑ አድርገን ነው የምናሳድገው:: አንቺም እንደምታይው ከብቶቻችን እዚህ በየሜዳው ያድራሉ፣ ማንም አይነካቸውም:: እንደውም የከተማ ሰዎች የእነሱ አከባቢ ለእርባታ ስለማይመች ከእኛ ጋር ዝምድና እየፈጠሩ አንድና ሁለት የእርባታ ፍየልና ከብቶችን ገዝተው እኛ ጋር ያስቀምጣሉ:: እኛም ንብረታቸውን በታማኝነት ይዘን እናረባቸዋለን:: ታድያ አሁን ከእኛ የማይተናነስ የከብት ቁጥር ያላቸው የከተማ ሰዎች አሉ:: ይህን የሚያደርጉት ያለንን ታማኝነት ስላዩት ነው:: ሌላም ልንገርሽና አንዳንድ ጊዜ ከብቶቻችንን ከበርቀንቴ ይዘን ስንመለስ የኛ ያልሆኑ አንዳንድ ከብቶች ተቀላቅለው ወደ እኛ ቀዬ ይመጣሉ:: ማንም ታድያ የኔ ናቸው ብሎ በሃሰት አይወስዳቸውም:: እነዚህ ባለቤት የሌላቸው ከብቶች በሃላፊነት ለአንድ ግለሰብ ይሰጡና ይጠበቃሉ:: ትክክለኛው ባለቤት በማንኛውም ጊዜ ከመጣ ባለቤትነቱ ተረጋግጦ ይመለስለታል:: ባለቤት ሳይመጣ ግን ብዙ ዓመታት ካለፉ ከብቶችን ሸጠን ብሩን ለአከባቢያችን የልማት ስራ እናውለዋለን:: ይህም የኛ ማህበረሰብ ታማኝ ስለመሆኑ ሌላው ማረጋገጫ ነው::(በቀዬአቸው ስሂሂር በተደጋጋሚ ከሰማኋቸው የህብረተሰቡ ድምፆች)

ሲሉ ይደመጣሉ:: እናም ታማኝነትን አስመልክተው ከሚተርኳቸው ተረኮች፤

> ኤፄራ- 36 አንድ አንበሳና ሽለምጥማጥ አብረው ጦርነት ይሄዳሉ:: ከጦርነቱ መልስ አንዲት ላምና አንድ በሬ ዘርፈው ይመለሳሉ::... ሽለምጥማጥ ከሄደበት ሲመለስ አንበሳው "የኔ በሬ ወለደ" ይለዋል::... ቅኔው የገባቸው ዳኞችም "ልክ ነው! በሬ መውለድ አይችልምና ጥጃዋ ያንተ ናት::" ብለው ለሽለምጥማጥ ውሳኔ አስተላለፉ::..."(አቶ ቡራ ሼሎ፤ቦሪ ቀበሌ፤17/7/04 ዓ/ም፤ የካሴት ቁ.18/ሀ)

ማህበረሰቡ በዚህ "ኤፄሪ" ታማኝነትን ቢያጎድል እንኳ ያለአግባብ የራሱ ያደረገው ንብረት የባለቤቱ መሆኑ እንደማይቀር ይመክራል:: ስለዚህ ለንብረት፣ ለትዳር፣ ለሃላፊነት፣

ለወላጅ ታማኝ መሆን ምንጊዜም አድሎአዊ ላልሆነ ትክክለኛ ፍርድ መቆም እንዳለባቸውና ፍትኃዊነትን እንዲማሩበት ያደርጋል።

በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ለታማኝነት ወይም ቃልን ለመጠበቅ ልዩ ቦታ የሚሰጡት ጉዳይ ሲሆን በማህበረሰባዊ የአኗኗር ልምዱ በተግባር እያዋለው መሆኑ ከነሱ ገለፃ በተጨማሪ በቀዬአቸው ስሂሂር ለታማኝነታቸው መገለጫ ያሏቸውን ነገሮች (የከብቶችን ውጪ ማደር፣ የከተማ ሰዎችን ከብት ማርባት) መመልከት ችያለሁ። ታዲያ ለዚህ አስተሳሰብ መገንባት ከተረታ ቀጥሎ ያለውን ቦታ የሚይዘው "ኤዔሪ" ነው።

- **አካባቢንና ተፈጥሮን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት**

ብሔረሰቡ አካባቢውንና በዙርያው ያሉ ተፈጥሮአዊ በረከቶችን በማስተዋል ለሚያነሳቸው የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ሌላው የ"ኤዔሪ" ሩይዳ ነው።

በበና አካባቢ ከሚገኙ የተለያዩ አዕዋፍ ዝርያዎች ኪሎ በሚል መጠርያ የሚታወቀው ወፍ አንዱ ነው። በቆይታዬም ወፉን ለመመልከት ችያለሁ። ረጅም መንቁሩ ከሰውነቱ ገዝፎ የሚታየው ይህ ወፍ አንድም ቀን ምድር ላይ አርፎ ከወራጅም ይሁን ከኩሬ ብቻ መሬትን የነካ ውሃ አይጠጣም ይላሉ። ታድያ ውሃ ሲያስፈልገው የዝናብ ጠብታዎች መሬት ሳይደርሱ በአየር ላይ ሳሉ ነው የሚጠጣው። የዚህን ወፍ ድርጊት የተመለከቱ የአካባቢው ነዋሪዎች "ለምን ይህ ሆነ?" ብለው ለሚያነሱት ጥያቄ ምላሹ በኤዔሪ እንዲህ ይተረካል፤

ኤዔሪ 37 ድሮ እግዚአብሄር እና ወፍ ፉክክር ያዙ። "እናንተ ወፎች ላባችሁ ያምራል ስለዚህ ለእኔ ስጡኝ?" ብሎ እግዚአብሄር ሲጠይቃቸዉ ሁሉም ሰብስበዉ ሰጡት። "ላባችሁን ሰብስባችሁ የሰጣችሁኝ የእኔ ናችሁና እኔ የፈጠርኩትን ውሃ ጠጡ።" አላቸዉ። አንድ ኪሎ የሚባል ወፍ "ኤድያ!! እግዚአብሄር እኔን አንዴ ፈጥረሃል ላባዬንም አልሰጥህም። ከፈለክ እኔን የፈጠርከዉን ዉሃ ክልክለኝ" አለዉ። እንደዚህ ከሆነ "እኔም የፈጠርኩትን ዉሃ አልሰጥህም ሂድ" ብሎ አባረረዉ። ኪሎዉም "እግዚአብሄር አንተ የፈጠርከዉ ወራጁን የወንዝ ዉሃ ነዉና እሱን አልጠጣም። ዉሃ በጠማኝ ጊዜ ወደ ላይ ኪል...ኪል...ብዬ እጮህለሁ ዝናብም ሲመጣ የዝናብ ዉሃ ብቻ እጠጣለሁ።" አለዉ። ይህ ወፍ ወንዝ ወርዶ ዉሃ ዝቅ ብሎ አይጠጣም። ዝናብ በሚዘንብ ጊዜ አፉን ከፍቶ የዝናብ ዉሃ ብቻ ነዉ የሚጠጣዉ። እሱ ወፍ አሁንም ከዛፍ ላይ ይወጣና ክንፉን እያራገበና ወደ ሰማይ እያየ ይጮኻል። ዝናብም

ይመጣል" ብሎ እስካሁን ድረስ የዝናብ ዉሃ እየጠጣ ይኖራል። (አቶ አልዲ ቢሮ፤ዲዚ አማ ቀበሌ፤ 3/7/04 ዓ/ም፤የካሴት ቁ.17/ሀ)

ሲ የዱር እንስሳ መጠርያ ስም ነው። በመጠኗ ጥንቸልን የምታክለው ይህች የዱር እንስሳ ከሌሎች በተለዬ በጠጢን ዘወትር አንድ ቦታ ላይ ነው የምትጥለው። እናም "እንደሌሎች እንስሳት ለምን በጠጢን በደረሰችበት አትጥልም? አንድ ቦታ በጠጢን መበጣል ለምን ታጠራቅማለች?" በሚል ለሚነሱ ጥያቄዎች በኤዔሪ መልስ ይሰጣሉ፤

ኤዔሪ 38 ድሮ በአባቶቻችን ጊዜ ዝሆንና ሲ(ጥንቸል የምታክል የዱር እንስሳ ናት) ነበሩ። ሲ ትንሽ ትንሽ በጠጥ የምትጥል ሲሆን የዝሆን እበት ግን በጣም ትልቅ ነበረ። አንድ ዕለት የ ሲ ልጅ በዝሆኑ እበት ተያዘች (ሰጠመች)። ሲም "አሃ ዝሆን እበቱን አጠራቅሞ ጥሎ የእኔን ልጅ አስያዘ አይደል ቆይ እኔም በጠጤን አጠራቅሜ የእሱን ልጅ በማስያዝ ብድሬን እመልሳለሁ ብላ ፉክክር ጀመረች። "ዝሆን ይህንን እበት ስንት አመት ጥሎ ነዉ ያጠራቀመዉ?" ብላ በመገረምም እሷም በጠጢን አጠራቅማ የዝሆኑን ለማሳከል አንድ ቦታ ላይ መጣል ጀመረች። ዛሬ በጠጢን ጥላ አጠራቅማ ስትሄድ ዝሆኑ ረግጦ ጨፍልቆት ይሄዳል። "አይ ነገ ከነገ ወድያ ጥዬ አጠራቅማለሁ" ትልና እዚያዉ ቦታ ላይ ሄዳ ትጥላለች። ዝሆኑም ይረግጠዋል። እናም እስካሁን ድረስ "በጠጤን አጠራቅሜ የዝሆኑን ልጅ አንድ ቀን አስይዤ እገድላለሁ" ብላ እያሰበች ዛሬም ሲ አንድ ቦታ ላይ ነው በጠጢን የምትጥለዉ። (አቶ ሸላይ በዶ፤ ዲዚ አማ ቀበሌ፤ 3/7/04 ዓ/ም፤ የካሴት ቁ.17/ሀ)

በተጨማሪም ኤዔሪ 39፤ 40፤ 41፤ ያሉ ተረኮችን ስንመለከት ለዚህ ጠቀሜታ የሚተረኩ ሆነው እናገኛቸዋለን።

6. ማጠቃለያ

የበና ብሔረሰብ የራሱ የሆኑ የአኗኗር ስርዓት፣ ባህል፣ ወግ፣ ታሪክ፣ እምነትና ፍልስፍና ያሉት ሲሆን እነዚህንም በትውልዱ ውስጥ የሚቀርጽበት፣ የሚያጠናክርበትና ከዘመን ዘመን የሚያሸጋግርበት የበርካታ ዝርው ተረኮች ባለቤት ነው።

ይህም ጥናት በበና ብሔረሰብ ውስጥ የሚገኙ ዝርው ቃል ተረኮችን ክዋኔ እና ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ መፈተሽ እና ማሳየት የሚል አላማን ይዞ በመነሳት የተሰራ ነው። ብሔረሰቡ በተለያዩ የትረካ አውዶች የሚተርካቸው የተለያዩ ተረኮች ያሉት ሲሆን እነዚህን ተረኮቹን "ተረታ" እና ኤዔሪ" በሚል በሁለት እንደሚከፍላቸው "ተረታ" የሚላቸው እውነተኛ ታሪኮች ተብለው የሚተረኩና አልፎ አልፎም የአፈ-ታሪክነት ይዘት ያላቸው ሲሆኑ "ኤዔሪ" የተባሉት ደግሞ የፈጠራ ታሪክ ሆነው የተረት እና የሀተታ ተፈጥሮ ይዘት ያላቸው መሆናቸው ታውቋል።

ብሔረሰቡ ዝርው ተረኮችን በአብዛኛው የሚከውንባቸው ልዩ አውዶች ያሉት ሲሆን እነዚህም የቤት ውስጥ የጠዋትና ማታ፣ የጉዲል የምረቃ ስርዓት፣ የባህላዊ ዳኝነት ስፍራዎች፣ የበርቀንቴ፣ የቡኪ ስፍራዎች እና የጠጲ ሚጫሬ ስፍራዎች እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

በተረኮች ክዋኔ አውዳዊ ሁነት ውስጥም ለሚገኘው ታዳሚ፣ የሚተላለፈው መልዕክት እና የመስተንግዶ ሁኔታ እንደ አውዶቹ አይነት የሚወሰን መሆኑ፤ የከዋኙ የአከዋወን ሂደት እና የታዳሚው ተሳትፎን በተረኮቹ አይነትና ይዘት እንዲሁም የከዋኝ ማንነትና ችሎታ ላይ የሚወሰን መሆኑ በዝርዝር ቀርቧል።

የተረኮችን የአተራረክ ሂደት ስንመለከት የሚተረከው የተረክ አይነት "ተረታ" ከሆነ ሲጀምር "ድሮ አባቴ እንዲህ አለኝ" ፣ "ድሮ አባቴ ይህን አስተማረኝ" ፣ "ድሮ አባቴ ይህን አሳየኝ" በማለት ፤ ኤዔሪ ከሆነ ደግሞ "ኤና ኤና ጊዜ" (በድሮ ጊዜ) በማለት ይሆንና ሲጨርሱ ደግሞ "ተረታ" ከሆነ "ከአባቴ የተማርኩት የኔ ታሪክ ይሄ ነው" ወይም "ከአባቴ ያየሁት የኔ ታሪክ ይሄ ነው" ወይም "ከአባቴ የተነገረኝ የኔ ታሪክ ይሄ ነው" በሚል ሲሆን የ"ኤዔሪ" ደግሞ "እኔ ምለው ባጭሩ ይሄ ነው" በሚል የሚደመደም መሆኑ በግልጽ ታውቋል።

ዝርው ተረኮቹ የሚኖራቸውን ፋይዳ ጠቅለል አድርገን ስንመለከት ብሔረሰቡ የማንነቱ መገለጫ የሆኑ ባህላዊ ስርዓቶችንና እምነቶችን ጠቀሜታ በማጉላትና በማጠናከር ከዘመን ዘመን

ምግባርንና ግብረ-ገብነትን ማስተማር፣ አካባቢንና ተፈጥሮን መግለጽና ማዝናናት እንዲሁም ታሪክን በቃል ቀርሶ ለትውልድ ማስተላለፍ፤ በሚሉ በአምስት ዋና ዋና መሰረታዊ ፋይዳዎች ላይ የሚያጠነጥኑ ሁነው ተገኝተዋል።

ባጠቃላይ በጥናቱ ግኝትም የበና ብሔረሰብ የራሴ የሚላቸው የበርካታ ዝርው ተረኮች ባለቤት መሆኑ፤ በተጨማሪም እነዚህ ተረኮች ዛሬ የምናየውን የማህበረሰቡን ገፅታ ጥንታዊ ለዛውን ሳይለቅ ይዞ ለመቆየቱ የነበራቸው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን መረዳት ተችሏል። ስለሆነም በተረኮቹ ፋይዳ ላይ ከዚህ በተጨማሪ ጠለቅና ሰፋ ያለ ጥናት ቢደረግባቸው ለሃገር የልማት አቅጣጫ ጠቃሚ ፍንጭ ሊጠቁሙ ይችላሉ ብዬ አምናለሁ።

በመጨረሻም በነበረኝ የመስክ ቆይታ ጥናቱ በሚሸፍናቸው ቀበሌያትና በየግለሰቦች መኖርያ ቤት እዘዋወር ነበር። እናም በነዚህ የቆይታ ጊዜያት የማህበረሰቡ ኣባላት የኛነታችን መገለጫዎች ናቸው የሚሏቸውን ታሪኮች ለማሳወቅ እና ለትውልድ ለማስተላለፍ ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎትና ተነሳሽነት እጅግ አስደሳች ሁኖ አግኝቸዋለሁ። በተጨማሪም ጥቂት ቁጥር ያላቸው የተማሩ የማህበረሰቡ አባላት ማህበረሰባዊ ታሪካቸው እንዲጠናና እንዲታወቅ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ የሚጠየቁትን ተያያዥ ተግባራት ከመፈጸም በላይ በማንኛውም የስራም ሆነ የእረፍት ሰዓት አቅማቸው በቻለው መጠን የጥናቱን ሂደት ለመደገፍ ያላቸው ከፍተኛ ስሜት የሚያስደስትና የሚያበረታታ በመሆኑ በዚሁ ይቀጥል እላለሁ።

ሌላው ብሔረሰቡ አዘውትሮ በሚጠቀማቸው በርካታ ተረኮቹ አማካይነት ጠብቆ ዛሬም የሚፈጽማቸው ስርዓቶች ባለፀጋ በመሆኑ አንዳንዴም ዘመናዊውን አሰራር የሚያግዙ ልምዶችን የተካነ ሆኖ እናገኘዋለን። ስለዚህ መንግስትን ጨምሮ የተለያዩ አካላት በማህበረሰቡ ውስጥ ማከናወን የሚፈልጓቸውን የልማት ስራዎች በተሻለ ስኬት መፈጸም ይችሉ ዘንድ ከእቅዶቻቸው ጋር ግንኙነት ያላቸውን የማህበረሰቡን ልምድ መነሻ ቢያደርጉ መልካም ነው እላለሁ።

ለማ ንጋቱ፤ "በየም ብሔረሰብ ፆታ ተኮር ተረኮች የወንድና የሴት ምስል ትንተና"፤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999።

ማንያለው አባተ ባየህ፤ "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው"፤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999።

ምንዳ ገብሬ፤ "የጌዲኦ ልማዳዊ ሥርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው"፤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000።

አማረ ሞላ፤ "የሸክኾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና"፤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999።

ፈቃደ አዘዘ፤ *የስነቃል መምሪያ*፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮ ጥቁር ዓባይ አታሚዎች፣ 1991።

የብሔረሰቦች ምክር ቤት በባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም፤ *የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ኘሮፋይል*፤ ሐዋሳ፤ ፍቅረሠላም ማተሚያ ቤት፣ 2001ዓ.ም.።

ዩኒክ ኢትዮጵያ፤ ሰንላይት ሚዲያ ኮሚኒኬሽን እና የደቡብ ክልል ብሄረሰቦች ምክር ቤት፤ ቁጥር 1፣ ህዳር 2004 ዓ.ም።

የበና ፀማይ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት፤ "የበና ፀማይ ወረዳ አስተዳደር የአምስት አመት (2003-2007) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሰነድ"፤ ቀይ አፈር፤ ነሐሴ፣ 2003።

አልዱባ ኤስ.አይ.ኤም. ትርጉም ስራ ፕሮጀክት፤ *በንኛ አማርኛ እንጊልዘኛ መዝገበ ቃላት*፤ 2001ዓ.ም።

ዘሪሁን አስፋው፤ *የስነፅሁፍ መሰረታውያን*፤ አዲስ አበባ፤ አርትስቲክ ማተምያ ድርጅት፣ 1996ዓ.ም።

Abraham
Analysis". M.A. Thesis, Department of Foreign Languages and Literature, Addis Ababa University, 2000.

__.Oral Narratives as ideological weapon for subordinating women: The case of Jimma Oromo; Journal of African cultural studies. 2007

Bascom, William R. *The Forms of Folklore: Prose Narratives.* In Segal, Robert A.(Ed.) Anthropology, Folklore, and Myth. New York and London: University of Lancaster, Garland Publishing, 1996

__. "The Forms of Folklore: Prose Narrative". The Journal of American Folklore, Vol.78, No.307 (Jan.-Mar.1965), 3-20, American Folklore Society, http://www.jstor.org/stable/538099.

Bauman, Richard. *Story, performance, and Event: Contextual studies of Oral Narratives.* Cambridge University press, New York, 1986.

Bayileyegn Tasew. "Anyuaa Oral Prose Narratives: Ethnic Genres and Social Functions". M.A. Thesis, Department of Foreign Languages and Literature: Addis Ababa University, 1999.

Ben Amos, Dan. *Folklore in context.* South Asian publishers, New Delhi Madras, 1982.

Bender, ML *Language in Ethiopia* Oxford University Press, London 1976.

Dégh, Linda. "Oral Folklore: Oral Narratives." In Dorson, Richard M. (Ed.) *Folklore and Folklife: An Introduction.* Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Dorson, Richard M. (Ed.) *Folklore and Folk Life: An Introduction.* Chicago: The University of Chicago Press, 1972.

Dundes, Allen. *Essay in Folkloristic.* (1978)

Federal democratic republic of Ethiopia population census commission central statistical agency: The 2007 population and housing census of Ethiopia result for SNNPR. Part1 *statistical report on population size and characteristics:* Branna Printing Enterprise, August 2010 Addis Ababa.

Finnegan, [illegible] to Research Practices. New York: Thomson Publishing Company, 1992.

Oring, Elliot. *Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction.* Logan: Utah University Press, 1986.

Sahilu Kidane. "Borana Oromo Prose Narratives: A Contextual Study." M.A. Thesis, Department of Foreign Languages and Literature: Addis Ababa University, 1996.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions.* Logan: Utah State University Press, 2005.

Tesfaye Gebre Mariyam. "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Languages and Literature: Addis Ababa University, 1990.

Yihenew Jembere. "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam." M.A. Thesis, Department of Foreign Languages and Literature: Addis Ababa University, 1996.

1. የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

ተ.ቁ	ስም	እድሜ	ፆታ	[illegible]	አድራሻ	የሰጡት መረጃ
1	ግራዝማች አድነው ጋርሾ	90	ወ	የበና ብሔረሰብ 9ኛ ባላባት	ቦሪ ቀበሌ	ተረክና ሌሎች መረጃዎች
2	ቆጣ ሼሎ	55	ወ	የአገር ሽማግሌ	ቦሪ ቀበሌ	ተረክና ሌሎች መረጃዎች
3	ቡራ ሼሎ	57	ወ	የአገር ሽማግሌ	ቦሪ ቀበሌ	ተረክና ሌሎች መረጃዎች
4	ዲሶ ጋዲ	60	ወ	ደንብ ሰሪ የአገር ሽማግሌ	ቦሪ ቀበሌ(ቢዘንዳ)	ተረክና ሌሎች መረጃዎች
5	ጋርሾ ቡቃር	61	ወ	የአገር ሽማግሌ	ቦሪ ቀበሌ	ተረክና ሌሎች መረጃዎች
6	አርባ ቱርኬ	65	ወ	የአገር ሽማግሌ	ቦሪ ቀበሌ	ተረክና ሌሎች መረጃዎች
7	ጋርሾ ዉካ	71	ወ	የአገር ሽማግሌ	አልዱባ ቀበሌ	ተረክና ሌሎች መረጃዎች
8	ሳራ አይታ	57	ወ	የአልዱባ ቀበሌ ሊቀመንበር	አልዱባ ቀበሌ	ተረክና ሌሎች መረጃዎች
9	አሮምባ ጊልያር	65	ወ	የአገር ሽማግሌ	አልዱባ ቀበሌ	ተረክ
10	መሳቱ ማይሌ	49	ወ	አርብቶ አደር	አልዱባ ቀበሌ	ተረክ
11	ጪሾኮ ገሌ	61	ወ	አርብቶ አደር	አልዱባ ቀበሌ	ተረክ
12	መቆ ገማር	57	ወ	አርብቶ አደር	አልዱባ ቀበሌ	ተረክ
13	ሳራ አልማ	56	ወ	አርብቶ አደር	ጉርዶ ቀበሌ	ተረክ
14	መጋ ከምቤሌ	65	ወ	የጉርዶ ቀበሌ አመራር	ጉርዶ ቀበሌ	ተረክ
15	ሼሎ ባላ	71	ወ	የጉርዶ ቀበሌ ሊቀመንበር	ጉርዶ ቀበሌ	ተረክ
16	ኤኮ ኡሊ	69	ወ	የዲዚ ቀበሌ አፈጉባኤ	ዲዚአማ ቀበሌ	ተረክ
17	ሸላይ በዶ	53	ወ	የዲዚ ቀበሌ ሊቀመንበር	ዲዚአማ ቀበሌ	ተረክናሌሎች መረጃዎች
18	አልዲ ቢሮ	67	ወ	የአገር ሽማግሌ	ዲዚአማ ቀበሌ	ተረክ
19	ደምሴ በላቸው	55	ወ	የአገር ሽማግሌ	ዲዚአማ ቀበሌ	ተረክና ሌሎች መረጃዎች
20	ጪርሾ ኡሊ	53	ሴ	የቤት እመቤት	ዲዚአማ ቀበሌ	ተረክ
21	አሪ በላቸው	57	ወ	አርብቶ አደር	ዲዚአማ ቀበሌ	ተረክ

22	ጊሎን ጎ...					
23	በላቸው ቢቶ	68	ወ	አርብቶ አደር	ዲዚአማ ቀበሌ	ተረክ
24	ቡልኮ ጋርሾ	72	ወ	የአገር ሽማግሌ	ትሉንጎ ቀበሌ	ተረክ
25	ዱባር አይኬ	63	ወ	የአገር ሽማግሌ	ትሉንጎ ቀበሌ	ተረክ
26	ውካ ዶይማ	39	ወ	የቀበሌው አፈጉባኤ	ትሉንጎ ቀበሌ	ተረክ
27	ጋርሾ ጉጂ	48	ወ	የአገር ሽማግሌ	አልዱባ ቀበሌ	ተረክ
28	ሸላ ባርቂ	61	ወ	የአገር ሽማግሌ	አልዱባ ቀበሌ	ተረክ
29	ከቺ ኢንኮ	59	ሴ	የቤት እመቤት	አልዱባ ቀበሌ	ተረክ
30	በኒ ኪሎ	67	ወ	የአገር ሽማግሌ	አልዱባ ቀበሌ	ተረክ

2. በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት የተሳተፉ

ተ.ቁ	ስም	እድሜ	ፆታ	ስራ
1	አቶ ደሞ በዛብህ	32	ወ	የቀድሞ የበና ፀማይ ወረዳ አስተዳዳሪ
2	አቶ ጌቱ ጋርሾ	35	ወ	አልዱባ ኤስ አይ ኤም ትርጉም ስራ ፕሮጀክት ሰራተኛ
3	አቶ በርጊ በዛብህ	37	ወ	በዲዚአማ የበና ተወካይ ባላባት
4	አቶ ብዙነህ ከብቴ	82	ወ	የሃገር ሽማግሌ
5	አቶ ሳራ አይታ	57	ወ	የአልዱባ ቀበሌ ሊቀመንበር
6	ወ/ሮ ኬሮ በላቸው	55	ሴ	የቤት እመቤት
7	ወጣት አስናቀ ትርፌ	30	ወ	ተማሪ
8	አቶ አበባው ስዩም	32	ወ	የበና ፀማይ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ
9	አቶ ቆባ ሼሎ	55	ወ	አርብቶ አደር

3. በትርጉም ስራ የተባበሩ

ተ.ቁ	ስም	እድሜ	ፆታ	ስራ	ተሳትፎ
1	አንዱአለም ብዙነህ	29	ወ	አልዱባ ጤና ጣቢያ ነርስ	ከበንኛ ወደ አማርኛየትርጉም ስራ
2	አለኸኝ ዉባለህ	30	ወ	አልዱባ ጤና ጣቢያ ነርስ	ከበንኛ ወደ አማርኛ የትርጉም ስራ

ለመረጃ አቀባ

1. በበና ብሔረሰብ ባህል መሰረት ተረቶች ይነገራሉ ወይ?

2. በብሔረሰቡ ውስጥ ተረቶች ይነገሩ ከሆነ ተረቶቹ ምን ምን ይባላሉ?

3. ተረቶቹ በብሔረሰቡ ውስጥ መቼ እና የት ነው የሚነገሩት?

4. ብሔረሰቡ ተረቶችን መናገር መቼ ተጀመረ ብለው ያምናሉ?

5. ተረቶች እንዲነገሩ የሚያነሳሱ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

6. በህብረተሰቡ ውስጥ ተረቶቹን የሚናገሩ አካላት እነማን ናቸው?

7. ተረቶቹ ሲነገሩ የሚያደምጡ አካላት እነማን ናቸው? በምን ይወሰናል?

8. ህብረተሰቡ ተረኮቹን ሲተርክ በምን መልኩ ነው?

9. በትረካ ወቅት አድማጭ የሚኖረው ሚና ምንድን ነው?

10.በትረካ ወቅት አድማጭ ጣልቃ የሚገባበት ሁኔታ አለ ወይ?

11.በብሔረሰቡ ውስጥ ተረኮችን በመተረክ የሚተዳደር አካል አለወይ?

12.ተረኮቹ ሲተረኩስ የተለየ ነገር ይዘጋጃል (ምን የተለየ ዝግጅት ደረጋል)?

13.ብሔረሰቡ ተረቶችን ምን ተግባር አላቸው ብለው ያስባሉ?

14.ተረቶች ባይተረቱ ምን ለውጥ ያመጣል ብለው ያስባሉ?

15.ህብረተሰቡ ለተረቶቹ ያለው ቦታ ምን ያህል ነው?

ምዕራፍ 1

ተረታ 1-የአፃ ስርዓት አጀማመር

ጥንት በድሮ ጊዜ እኛ በናዎች ከከብት ላይ አንዘልም ነበር። እስከዚያ ድረስ ግን ሲፈፀም የነበረው ሥርዓት እንቧይ ደርድሮ አንገት ላይ በማጥለቅ በከብት ሥር በማለፍ ነበር የሚፈፀመው። በመሃል ግን አንድ ሀሳብ የኛ አያቶቻችን አሰቡ። ሃሳባቸዉም" ሌሎች ብዜረሰቦች ያገባሉ እኛም እናገባለን፣ ሌሎች ያጫሉ እኛም እንዲሁ እናደርጋለን፣ ሌሎች ኮይታ (ጥሎሽ) ይሰጣሉ እኛም እንሰጣለን እናም ከሌሎች ብዜረሰቦች የሚለየን ነገር ምን አለ? እኛ ከሌሎች የምንለይበት የራሳችን የሆነ የኛ የበኖች መለያ ሊኖረን ይገባል።" የሚል ነበር። ይህንን ሀሳባቸዉን ይዘዉ ለቢታና ለሀገር ሽማግሌዎች አቀረቡ በሀሳቡ የተስማሙት ቢታ" እኛ በኖች ከሌሎች እንለይ ዘንድ ማንኛዉም ወጣት የትዳር አቻዉን ከማጨቱና ከማግባቱ በፊት በከብት ጀርባ ላይ ይዝለል።" ብሎ ቢታው /የጎሳ መሪው/ በመጀመሪያ በከብት ጀርባ ላይ በመዝለል ደንቡን ከሠራ በኋላ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በከብት ጀርባ ላይ መዝለል ተጀመረ የኛ መለያም ሆነ። ይህንን ሳይፈጽም የሚያገባ ካለ ጋብቻዉ በኛ በበኖች ዘንድ ተቀባይነት የለዉም።

ተረታ 2- የማዝ ስርዓት አጀማመር

አፃን ስንጀምር ማዝ የዝያን ጊዜ የለም። ማዝን ያወጣው እሱ (ቢታው) ከዘለለ በኋላ የእሱ ልጅ ቱሶ የሚባለው ነው። የዚያን ሰዓት የዝላዩን ስርዓት ለማስፈጸም አረቻ (የጭሪ ወፍ) ተመረጠች። ምክንያቱም ወፏ ወተትና ከከብቶች ላይም መኛገር እየነቀለች የምትመገብ በመሆኗ ነው። እናም አንድ ሰው ወፏን ይዞ ከከብቶቹ ላይ አዘለላቸው። ከዚያም ንጉሱ "ይህች ወፍ እህል አትበላም ስለዚህ ይዟም ሰው እህል የማይበላ ማዝ ይሁን" ብሎ አለ። እናም ልጁ ሚስት አግኝቶ ደንብ እስከሚሰራ ድረስ እህል እንዳይበላ ተብሎ ተወሰነ። እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማዝ የሚሆነው ሰው የማዝነት ጊዜውን እስኪጨርስ ድረስ ወፏ ወተት እንደምትጠጣው ወተት፣ ወፏ መኛገር እንደምትበላው እሱም ሥጋ እየበላ እና በተጨማሪም ማር እየበላ ይኖራል። ከዚህ ውጭም ወፏ ዛፍ ላይ ሆና ሽንታን የማትሸና መሬት ላይ ቁጭ ብላ የምትሸና በመሆኗ ማዝም መሬት ላይ ቁጭ ብሎ ነው የሚሸናው። አዳሩም በቤቱ ውስጥ ሣይሆን በበረት ውስጥ ማደሪያ ሠርቶ ነው። የዚህም ምክንያት እቤት ውስጥ እህል ስለሚኖር ማዙ ድንገት ወደ ቤቱ ውስጥ ሲገባል ጃገረድ ወይም ማንኛዋም ሴት እህል ይዛ ስትወጣ ቢገናኙ እህሉም ይበላሻል፣ የልጁ ሆድም ያብጣል፣ ተነፋቶ ይታመማል። ስለዚህ ቢያንስ እስከ አንድ ዓመት ማለትም ልጃገረድ አግኝቶ እስኪያገባ ድረስ ማዝነቱን በዚህ መልኩ እየተገበረ ይኖራል። ምናልባት ወቅቱ ፀሐይ ሆኖ የዘለለ ከሆነ ደግሞ ወተት እንደልብ ስለማያገኝ ብዙ ጊዜ መቆየት አይፈልግም።

ተረጋ

አንድ ወቅት ላይ በናዎች "ኮኮብ መጥፎ ነገር እየተናገረች ነውና ሽሹ!" ተብለው ግማሹ ህዝብ ሸሽቶ ወደ አሪ ሀገር፣ የተወሰነው ደግሞ ወደ ካሮ ሀገረ ሸሽቶ ገብቶ ነበር። ከብዙ ጊዜ በኋላ ኮከቧ ወደ ቦታዋ ተመለሰችና ወደ ተለያዩ ሀገር የሸሹት ሰዎች መመለስ ጀመሩ። ወደ ካሮ ሸሽተው ከነበሩት አራት ወንዶች ብቻ ሲተርፉ፣ ወደ አሪ ከሸሹት ደግሞ አሥር ሴቶችና አንድ ወንድ ብቻ ነበር የተረፉት። ነገር ግን ሀገራቸው ላይ ቀርተው ከነበሩት አንድም ሰው የተረፈ አልነበረም። ኮከቧ ወደ ቦታዋ ተመልሳ ሀገሯ የተረጋጋች ስትሆን ወደ ካሮ ሸሽተው ከነበሩት የተረፉ አራቱ ወንዶች ወደ ሀገራቸው በመመለስ ጸጥ ላይ ሆነው እንጨት ሰብቀው እሳት በማውጣት ሁል ጊዜ ምሽት ላይ ያነዱ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ «ምናልባት ይህን እሳት የተመለከቱና የተረፉት ሴሎች የኛ ሰዎች ካሉ አቅጣጫችንን እየፈለጉ ይመጣሉ።» በሚል ሀሳብ ነበር።" ወደ አሪ ሀገር ሸሽተው ከነበሩትና ከተረፉት አሥራ አንድ ሰዎች መካከል የነበረው አንድ ወንድ ይህን እሳት ይመለከት ነበርና አንድ ቀን አብረውት ለነበሩ ሴቶች "በኋላ ማታ ላይ እናንተ ሴቶች ፍየል ፎክሩ!" ብሎ አለ። ፍዬል ፎክሩ ማለት በማህበረሰቡ ባህል በጭፈራ ሰዓት አንድ ሰው ለመፎከርያነት በሚመርጠው ፍዬል የቀንድ አቀማመጥ መፎከር ሲጀምር በዙሪያው ያሉ ሰዎች በዜማ እየተቀበሉ የሚያጅቡበት ባህላዊ ሥርዓት ነው። እናም ሰዓቱ ሲደርስ ተሰብስበው ጭፈራ ይጀመራል። ይህን ሰዓት ወንድየው ፉከራውን ይጀምራል። "ጉርቤ ጋር ያላችሁ የሚነገራችሁን ነገር ጆሮ ካላችሁ ስሙ፣ ጉርቤ ጋር ያላችሁ ልብ ካላችሁ የሆነ ነገር አስቡ፣ ጉርቤ ጋር ያላችሁ አይን ካላችሁ የሆነ ነገር እዩ /ተመልከቱ/፣ "እያለ ሲፎክር ሴቶችም ከሥር እያጨበጨቡ ያጅቡት ነበር። ጉርቤ በፉከራ አስመስሎ ይህንን መልዕክት ያስተላለፈበት ምክንያት በወቅቱ አስጠግተዋቸው የነበሩ አሪዎች ለመመለስ ማሰባቸውን ካወቁ እንዳይከለክሏቸውና እንዳያስቀሯቸው ከመስጋት የተነሳ ነበር። እናም ፉከራውንና ዘፈኑን የሰሙት አሪዎች እውነት ፉከራና ዘፈን ስለመሰላቸው፣ ቋንቋውንም ስለማያውቁ ይስቁ ነበር። ነገር ግን መልዕክቱ የገባቸው ወገኖቹ ዞር ብለው ወደሀገራቸው አቅጣጫ ቢመለከቱ እሳቱን በርቀት አዩ፤ ሊያነዱ የሚችሉትም ሰዎች እንደሆኑ አሰቡ። ጉርቤ "ፍየል ፎክሩ" ያላቸው ይህንን መልዕክት እየነገራቸው መሆኑ ገባቸውና በልባቸው ያዙ። ጭፈራውም ተጠናቆ ሠው ሁሉ ሲተኛ እኩለ ለሊት ላይ ተነስተው ጉዞ ጀመሩ።

ቀኑ ሲነጋ በረሀብና በችግር ምክንያት ተሰደው ወደ ሀገራቸው መጥተው የነበሩትን በናዎች ገዝተው ይኖሩ የነበሩት አሪዎች ያጡአቸዋል። ከዚያም ተከትለዋቸው ፍለጋ ቢሄዱም በናዎቹ ሀገራቸው ገብተው ነበርና ይመለሳሉ። ጠፍተው የመጡትም አሥራ አንዱ በናዎች የእሳቱን ምልክት እያዩ ተጉዘው ከካሮ ከመጡ ወገኖቻቸው ጋር ተቀላቀሉ። ሲገናኙም በችግር ምክንያት ብዙ ጊዜ ተለያይተው ቆይተው ነበርና ዘመድና ባዳ መለየት አስቸጋሪ ሆነባቸው። ይህን ጊዜ በአንድ ሀሳብ ተስማሙ። "ቀን ቀን ሁላችንም ዘመድ ነን። ማታ ማታ ሲሆን ግን ዝምድና የለንም ሁላችሁም ተያያዙ" በሚል ሀሳብ ተስማሙ። በዚህ መልኩም ኖሩ ሲኖሩ በሁለትና በሶስት ዓመት ተዋልደው በዙ ይባላል።

ተረታ 4- አንጀት አንባቢ

አባቴ ድሮ ልጅ በደንብ ስማ አለኝ፡፡ "ምን ማድረግ ትፈልጋለህ? አደን መሄድ ወይስ ጦርነት መግጠም? ጦርነት ለመግጠም ስትነሳ ማሸነፍ ወይስ መሸነፍህን አውቀህል? እንደዚህ አይነት ነገር ከማድርህ በፊት የምልህን በደንብ አዳምጥ፤ አንጀት አንብበው ሁሉን የሚያውቁ አሉና ቀድመህ ወደ እነሱ ሂድ፤ ጉዞህ ከንቱ እንዳይሆን ቀድመህ ጠይቅ፡፡ ውጤትህ ምን እንደሆነ ይነግሩሀል፤ ታድያ የሚሉህን ፈጽም፡፡ አትሂድ ካሉህ ቅር፤ ሂድ ካሉህ ደግሞ ሂድ፡፡ ይህን አልሰማ ብለህ ካዘዙህ ውጭ ከሆንክ ግን መጨረሻህ በሄድክበት መቅረት ነው የሚሆነው፡፡" አለኝ፡፡

ተረታ 5- ስለታማኝነት

ድሮ አባቴ "የሰዉ ገንዘብ አትመኝ" ይለኝ ነበር፡፡" ጫካ ሄደህ ቀፎ ስቀል፤ ከብቶችን ጠብቅ፤ ፍየሎችን ጠብቅ" ይለኝ ነበር፡፡ እኔም አባቴ በመከረኝ መሰረት ቃሉን አክብሬ ቀፎ እየሰቀልኩ እናቴንም እያከበርኩኝ ኖርኩኝ፡፡ አባቴንም ክፉ ነገር ብዬ አላሳዘንኩትም፡፡ ሲሞትም ቀበርኩት እናቴም ስትሞት በሰላም ቀበርኳት፡፡

ተረታ 6- ድህነትን ስለመጸየፍ

ድሮ አባቴ "የሰዉ እጅ እንዳታይ! ደሃ እንዳትባል! ደሃ ከምትባል የእኔ ልጅ ባትሆን ይሻላል ቀፎ ስቀል፤ ከብትና ፍየል አርባ" አለኝ፡፡

ተረታ 7- የልመና አስከፊነት

ድሮ አባቴ "ከብቶችህን በደንብ ካልጠበክ በጅቦች እንደሚበሉ ሁሉ በርትተህ ካልሰራህ አንተን ችግር ይበላሀል፡፡ የሰዉ እጅ ታያለህ! ለማኝም ትሆናልህ፡፡ ስለዚህ አንተ እንደዚህ ሆነህ እኔ አባትህ ከማዘንብህ በርትተህ ስራ! በላብህ እንጂ ሳትሰራ ከማንም ለምነህ እንዳታገኝ! ማንንም እንዳትለምን፡፡" ብሎኝ ነበር፡፡

ተረታ 8- ሽማግሌዎችን ስለማክበር

ድሮ አባቴ "አባትህንና እናትህን አክብር፤ ቢታን (የጎሳ መሪዉን) በክብር ትዛዙን ፈጽም፤ የሀገር ሽማግሌዎችንና ካንተ ትልቅ የሆኑትን አክብር፤ ይህንን ስታደርግ ከብቶችህና ቤተሰብህ ይባረካሉ፤ አከባቢህ ሰላም ይሆናል፤ ዝናብም ይዘንባል፤ ድርቅም አይነካህም፡፡ ይህን ባታደርግ ግን ትረገማለህ፤ ድርቅም ይሆናል፤ ከብቶችህ ያልቃሉ" ብሎኛል፡፡

ተረታ 9 - የቢታ እርግማን

ዛሬ የምንኖርባት ይህች ምድር ከመምጣታችን በፊት በሰዎች የተሞላች ነበር አሉ። ታድያ ልክ እንደ አሁኑ ቁጥራቸዉ ሲበዛ ለጎሳ መሪዉ አለመገዛትና ሽማግሌዎችን መናቅ በመጀመራቸዉ በቢታው ተረገሙ። ሙሉ በሙሉ ከምድርም ጠፉ። ከዚያ በኋላ ነዉ የተበታተነዉ ዘራችን ከየአቅጣጫዉ ተሰባስቦ እንደገና ዘራችን በምድር የሞላዉ።

ተረታ 10- የበና እና የሙርሲው ጦርነት

አንድ ወቅት ላይ በበና ምድር ላይ ትልቅ ሰው ነበር። ይህ ሰው አንድ ቀን ሰዎች እንደሰፈራ ተሰብስበው በነበረበት "አልበልታ" የሚባል አከባቢ ላይ ተኝቶ እያለ ልክ እንደ እግዚአብሄር መልዕክተኛ ሆና አንድ ወፍ ስታፏጭ ይሰማል። ከዚያም በጠዋት ተነስቶ ጥሩንባ እየነፋ ለሃገሩ ሰዎች "ዛሬ አንድም ሰው ከብቶችን ወደታች ወደማጎ አቅጣጫ እንዳይነዳ። ሁላችሁም ወደላይ ንዱ። አንድ እኔ ያየሁት ነገር አለ ዛሬ ጦርነት ይነሳል" ብሎ ይነግራቸዋል። በእሱቱም እሱን አዳምጠውት ከብቶቻቸውን ወደ ላይ የመለሱት ሰዎች ከብቶች ሲተርፉ እሱን ሳይሰሙ ከብቶቻቸውን ወደታች የነዱ ሰዎች ከብቶችና ከዚያን እለት ቀደም ብለው ተሻግረው የነበሩ ሰዎች ከብቶችም በሙርሲዎች ተዘረፉ። ወዲያውም ከሁለቱም ወገኖች የሆኑ አካላት በመሃከላቸው ካለ ወንዝ ዳር ይገናኛሉ። በወቅቱ ደግሞ በናዎች ከቀስት ውጭ ጦርም ሆነ ሌላ ምንም አይነት የጦር መሳርያ አልነበራቸውም። ሙርሲዎች ግን ጦርና ቀስት ነበራቸው። በናዎች በቀስት ሙርሲዎች ደግሞ በጦርና በቀስት ጦርነት ይጀምራሉ። ሲዋጉ ቆይተውም ከሙርሲዎች ወገን 5 ሰዎች ብቻ ሲቀሩ ጦርነቱ በቃን ብለው ተመለሱ።

በዚህ ሁኔታ የነበረው ጦርነት እንዳበቃ የተረፉት በናዎች የሞቱ ወገኖቸውን በጋራ በመሆን ቀበሯቸው ከዚያም ተሰብስበው ወደ ትንቢት ተናጋሪው ሰው በመምጣት ምን እናድርግ ብለው ጠየቁ ምክንያቱም በወቅቱ የተረፉት በናዎች በአብዛኛው ባሎቻቸው በጦርነቱ ምክንያት የሞቱባቸው አዲስ መሽራ የሆኑ ሴቶች ነበሩ። እናም "ምን ይሻላል?" ቢሉ ይህ ሰው በግ አረደና የሴቶቹን ሁሉ አይኖች እሰሩና ተገናኙ፤ ከዚያም ውለዱ አላቸው። ህዝቡም እሱ እንደመከራቸው አደረጉ። በዚያን ወቅትም ያረገዙ ሴቶች በሙሉ ወንዶች ልጆችን ወለዱ ይባላል።

ተረታ 11- የዘወትር አዳኙ

አንድ ወቅት ላይ ነው አሉ በየቀኑ ከቤቱ በወጣ ቁጥር አደን ውሎ ሲመለስ አውሬ ገድሎ የሚገባ ሰው ነበር። እናም በኛ በበና ማህበረሰብ ዘንድ ደግሞ አደን ማደን፣ አውሬ መግደል የጀግንነት ተግባር ተደርጎ ቢወሰድም አዘውትሮ መግደል ደግሞ በጥብቅ የሚወገዝ ተግባር ነው። ይህ በሆነበት የዚህ ሰው አዘውትሮ ማደን እና በገባ በወጣ ቁጥር መሳሪያ ማጮሁ ጥሩ እንዳይደለ በተደጋጋሚ የሚቀርቡት ሰዎች ይነግሩት ነበር። ነገር ግን ይህ ሰው የሰዎችን ተግሳፅ ወደ ጎን ትቶ በተግባሩ ይቀጥልበታል።

ታዲያ አንድ ቀን እንደለመደው ወደ ጫካ ሂዶ እያደነ እያለ ከርቀት ድኩላ ይመለከታል። እናም ድኩላውን ለመምታት ለኢላማ እንዲያመቸው ቦታ መርጦ እያነጣጠረ እያለ ከኋላው ባለ አቅጣጫ "የርያ" (አንተ ሰው) የሚል የጥሪ ድምፅ ይሰማል።

ወደ ኋላ ዞሮ ሲመለከት በአከባቢው አንድም ሰው ያጣል ። ከዚያም ወደ ኢላማው ተመልሶ እንደገና ሊያነጣጥር አሁንም ጥሪውን ይሰማል። ለሁለተኛ ጊዜ ዙሮ ሲመለከት ምንም ነገር የለም። እናም "የምን ሰው ነው የሚጠራኝ? ይሄ ሆነ ብሎ ድኩላውን ሊያስመልጠኝ ያሰበ መሆን አለበት።" ብሎ አስበና ወደ ኢላማው ይመለሳል። እናም ለሶስተኛ ጊዜ መሳሪያውን ሲያነጣጥር በተደጋጋሚ ጥሪውን ይሰማል። ነገር ግን ችላ ብሎ በመተኮስ የተመለከተውን ድኩላ ይመታዋል። ወድያውም ብድግ ብሎ ወደ ግዳዩ ሩጦ በመሄድ ደርሶ ቢመለከተው የገደለው ነገር የተመለከተውን ድኩላ ሳይሆን ከዚህ በፊት አይቶት የማያውቀውን የተለየ ፍጡር ሆኖ ያገኘዋል። ባጋጠመው ክስተትም እጅግ በመደንገጡ እሱም እዚያው ሞተ ይባላል።

ተረታ12- ባለ ሶስት ጡቷ ብቸኛዋ የበኖች የሴት ቢታ

እኔ ሶስት ጡት ያላት አያት ነበረችኝ። የተናገረችው ሁሉ ስለሚደርስ በእኛ ማህበረሰብ እሷ ያለችውን ችላ የሚል አልነበረም። እሷ አንድን ሰው ትሞታለህ ብላ ካለች ይህ ቃሏ በትክክል ይደርሳል። እሷ ያዘነችባቸውም ችግር ይደርስባቸዋል። እንደውም አንድ ሰውዬ ከሷ ጋር ተጣልቶ ስላዘነችበት ሳምንት እንኳን ሳይቆይ ሞቷል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሰዎችን አይታ መጨረሻቸውን ትናገር ነበር።

ተረታ 13- የበና ጀግና አይታ ታሪክ

ድሮ እናቴ የነገረችኝ የእኛ በኖች ሐመር ውስጥ ካሉ በሽዳዎች ጋር ጥሶኛ ነበሩ። በዚያን ሰዓት አይታ የሚባል የበና ጀግና ነበር። የበሽዳ ደግሞ ሱሚ የሚባል ጀግና ነበር። እናም በወቅቱ በሽዳዎች ከአልቲ (የበና ቀበሌ ናት) ሀገር የመጡ ሰዎችን ይጨርሱ ነበር። ከዚያ አይታ የሚባለው የበና ጀግና በሽዳ እየሄደ በአንድ ምሽት ብቻ እስከ አሥር ሰው ድረስ ይገድል ነበር። በዚያም ወቀት የበሽዳ እናቶች ልክ ህፃናትን አሁን "ጅብ መጣ! ጅብ መጣ!" ብለው እንደሚያስፈራሩት "አይታ መጣ! አይታ መጣ!" እየተባለ ልጆችን እያስፈራሩ ወደ ቤት ያስገቡ ነበር። አይታ ከዚህ ሦስት ሰዎችን አስከትሎ ወደ ጦርነት ቦታ ሄደ። የበሽዳው ጀግና እንደ ትናንት ሰው ገድሎ መጥቶ ፀጉሩን ሾርቴ ተቀብቶ ተቀምጦ ነበር። እናም የበናው አይታ የበሽዳው ወዳለበት ጫፈራ ቦታ ቀረብ ብሎ ይጠራውና "እኔ በሽዳ ነኝና አንተ ሰው የምትገድልበትን ቦታ ናና ምራኝ" አለው። እሱ በና ሆኖ አውቆ "እኔ በሽዳ ነኝ፣ ተነስ አንተ ጋር ሄጀ መግደል እፈልጋለው እና ምራኝ" ብሎ ይለዋል። የበሽዳው "እሺ! ተነስና እዚያ ጫካ ሄደን እናውራ" ብሎ ይለዋል። ከጭፈራው መሐል ወጥተው ወደ ጫካው ይገባሉ። ከዚያም ከበሽዳው በቀኝ በኩል ይቀመጣል። ጨቤ ታጥቆም ነበር። እናም የበናው ጀግና የበሽዳውን ጀግና "እኔን በና ሀገር እየመራህ

ውስደኝ::" ሲል የበሽዳው ጀግና "እኔም አንተን እመራሀለው ችግር የለም" ይለዋል:: ከዚያም "አንተ ሁለት በና ትገድላለህ?" ብሎ ሲጠይቀው የበሽዳው ጀግናም "እረ! እኔማ በጣም እገድላሁ" ሲለው የበናው ጀግና ጩቤውን አውጥቶ የበሽዳውን ወግቶ ይገድለዋል:: እንደገደለውም ትንሽ ወርድ ብሎ ይሄዳል:: በጊዜው ምንም መሣሪያ ብሎ ነገር የለም ጦር ብቻ ነበር ያለው:: እናም በጭፈራ ሰዓት ጦራቸውን ሰብስበው አንድ ቦታ ማስቀመጥ የተለመደ ስለነበር የበናው ጀግና የበሽዳ ሰዎች ተሰብስበው ሲጨፍሩ አይቶ ጦራቸውን ያስቀመጡበት ቦታ ሄዶ አንድም ጦር ሣይቀር ሰብስቦ ወሰደባቸው:: በመጀመሪያ ከሀገሩ ሲመጣ ተከትለውት የመጡ ሶስት ሰዎች ጫካ ውስጥ ተደብቀው ይጠብቁት ነበርና ወደ እነሱ ይሄዳል::

ለሰዎቹም "ይህንን ጦር ያዙ!" ብሎ ይሰጣቸዋል:: ወዲያውም ወደ በሽዳዎች ሰፈር ተመልሶ ይፎክር ጀመር:: ይህን ሰዓት ፋከራውን የሰሙት የበሽዳ ወንዶች ይደነግጣሉ:: ከዚያም ምንድን ነው? የምንሰማው ብለው ጦራቸውን ወዳስቀመጡበት ሩጠው ሲሄዱ ጦራቸውን በሙሉ ያጣሉ:: ከዚያም ዞር ብለው የራሳቸውን ጀግና" ሱሜ የታል? ሱሜ ጀግናው የታል?" ብለው ሲጠይቁ ከእነሱ ትንሽ እራቅ ብሎ ሙቶ ከመሬት ወድቆ ያገኙታል:: በባህላቸው መሠረትም ጀግና ወንዶች ከሌሎች የሚለዩበት እግርና እጃቸው ላይ የሚያስሩት ወርወራ /ቃጭል/ ከሱሜ ላይ ነበርና ዝቅ ብለው ቢመለከቱት ከእግሩም ሆነ ከእጁ ላይ ያለውን ወርወራ ያጡታል:: የበናው አይታም ወርወራውን ከእግርና እጁ ላይ ቆርጦ ወስዶታልና ሲያዩት ደንግጠው "ይህን ጀግና የገደለው ሰው እኛን ይምራል እንዴ? በዚያ ላይ ጦራችንም የለም እሱንም ወስዶታል::" ብለው ሩጠው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ::

ከተወሰኑ ቀናት በኋላም ኢቫንጋዲ ላይ በሽዳዎች ተሰብስበው እየጨፈሩ ሳለ የሚጨፍሩበት ቦታ ድረስ አይታ ይመጣል:: በእጁ ላይም ጦር ይዞ ነበርና በሽዳዎች ከሚጨፍሩበት ቦታ መሐል ላይ ሰክቶ ያቆማል:: ይህን ጊዜ በሽዳዎች ቆም ይሉና" ጦር እዚህ አከባቢ የለም እና ይህን ጦር ይዞ የመጣው ይህ ሰው ማን ነው? ከየት ነው የመጣው?" ብለው ይላሉ:: ይህን ሰዓት ከጭፈራው መሐል ያለች ልጃገረድ የአይታን ስም እየጠራ ዘፈን ትጀምራለች:: የበናና የበሽዳ ቋንቋ በተወሰነ መልኩ ይመሳሰላልና በሽዳዎች ያሉትን ሁሉ ይሰማ የነበረው አይታ ወደጭፈራው መሃል በመግባት በበሽዳ ቋንቋ "አይታ የሚባለው የቱ ነው? አይታ ዝሆን ነው? አንበሳ ነው? ወይስ አውራሪስ ነው? ስለዚህ አይታ ጋ እኔን ምሩኝ? እኔን ምሩኝ?" እያለ ጦሩን ይሰብቅ ነበር:: እናም አሁን ድረስ እኛ ጋ "የበና ጀግና አይታ እንደዚህ ነበር" እየተባለ ይነገርለታል::

ተረታ 14- ክብት እርባታና የጦር መሣሪያ መታጠቅ አጀማመር

አባቴ ድሮ ወጥመድ አጠማመድን ካሳየኝ በኋላ እኔም ማጥመዴን ቀጠልኩ። ነብርም በወጥመዴ ተይዞ ገደልኩ። ለአባቴ ስነግረዉም "እስካሁን ራሴ የሰራሁትን ጦር ይገፍ ነበር ያለሁት፤ አሁን ግን የነብሩን ቆዳ ሸጬ መሳርያ ገዝቼ አነግታለሁ (እታጠቃለሁ)" ብሎ ቆዳዉን በሸጠዉ ብር መሳርያ ገዛ። ለእኔም ጦሩን አወረሰኝ ለሁለተኛ ጊዜ በወጥመዴ ነብር ገደልን ይህን ጊዜ አባቴ "አሁን ቆዳዉን ሸጬ ለልጄ ክብቶች ነዉ የምገዛዉ" አለና ስድስት ክብቶች ገዝቶ ሰጠኝ። ሲሰጠኝም "እንግዲህ እነዚህን ክብቶች አርብተህ ሲበዙልህ በእነሱ መሳሪያ ግዛ" አለኝ። "ታናሽህም እንዲሁ ያደርጋል ልጅም ስትወልድ እኔ እንዳደረኩልህ አድርግ" አለኝ።

ተረታ 15 - ስለ አደን አጀማመርና አመጋገብ

ድሮ አባቴ አዉሬ ለመግደል ፈልጎ ጦር ሰራ በጦሩም እህል የሚበሉ ትንንሽ አዉሬዎችን መግደል ጀመረ። ቀጥሎም በገመድ ወጥመድ ሰራና ማጥመድ ጀመረ። አንድ ቀን ትንሽ አዉሬ በወጥመዱ ተያዘች ወድያዉ ጦሩን ሰጠኝና "ግደል!" አለኝ። አከታትሎም "ገደልክ ምንድነዉ የገደልከዉ?" ብሎ ጠየቀኝ ስሟን እኔ አላዉቅምና "ጃርት" ናት አለኝ።" መግፈፍ ትችላለህ?" አለኝ። አለመቻሌን ስነግረዉ ቢላዋ አንስቶ ከላይ ከላይ እየፋቀ ገፎ አሳየኝና ሲጨርስም ስጋ ነዉ እንዴ? አልኩት፤ ለመብላትም ፍቃደኛ አልነበርኩም። አባቴም "እኔ በልቻለሁ ልጄ አንተም ብላ አለኝ" እኔም ተቀቅሎ ነዉ ወይስ ጥሬዉን? ብዬ ስጠይቀዉ እንስራ አነሳና ቀቅሎ አሳየኝ። "ሲቀዘቅዝ ነዉ የሚበላዉ" ብሎ በሾርቃ (ከቅል ክፉይ የሚሰራ ባህላዊ እቃ) አቀዝቅዞ አበላኝ። በሌላ ጊዜ ሚዳቋ በወጥመድ ተይዛ ስለነበር በጦር ገደልኳትና በላናት። ቀጥሎ ዱኩላ ተያዘ እንዲሁ አደረግን። በመጨረሻም አባቴ" እስካሁን እኔ ባጠመድኩት ወጥመድ ስትገድልና ስትበላ ነበረ አሁን ግን ልጄ ተመልከት "አለኝና ወጥመድ አሰራርና የአጠማመዱን ዘዴ አሳየኝ።

ተረታ 16- ጀግንነት

ድሮ አባቶቻችን ለእኛ እንዲህ ብለው ይሉን ነበር። "ልጆች ማሌ ጋር ተጣልተናል፣ ከሙርሲም ጋር ተጣልተናል፣ አውሬም ገድለናል፣ እናንተ እንደዚህ ታደርጋላችሁ?" ብለው ሲሉን እኛም" አባቶቻችን እኛ መሣሪያ የለን በምን እንግደል?" ብለን እንላለን። እነሱም "እኛ ድሮ በጦር አይደል እንዴ ማሌንም ሙርሲንም የተዋጋነው? በጦር ሂዱ! ጦር ይዘን እኛ ሄደናል፣ ማጎ ድረስም ሂደናል" ይሉናል። እኛም መልሰን "በጦር ብንል አይሆንልንም፤ ጎሹ ሊወጋን ወደኛ ይመጣል፣ ከዚያም ሳንገድል ተመልሰን እንመጣለን።" እንላለን። ሌሎች ገድለው መጥተው ሲፎክሩ ሲሰሙ "እናንተ የሞታችሁ! እናንተ ምን ታደርጋላችሁ?" ይሉና መሣሪያ ለእኛ ይገዙልናል። ወደ ማጎም እንሄዳለን ቀጭኔ እንገድላለን። የቀጭኔ ጭራውን ይዘን መጥተን ስናሳያቸው ክብት ይሰጡናል። "ጎበዞች! አንበሶች! እናንተ ወደፊት እኛን ቀባሪ ናችሁ። በደንብ አድርጋችሁ ትቀብሩናላችሁ" ይሉናል።

ተረታ 17- የዛሬዋ ዲዚ አማ

የዲዚ አማ ቀበሌ ይህንን ስያሜ ከማግኘቷ በፊት "ዲዚሽሽ" በመባል ትታወቅ ነበር። ሽሽ ማለት ጥፋ፣ ተደበቅ ማለት በመሆኑ ግድያን ጨምሮ የተለያየ ጥፋት ያጠፉ ሰዎች እንደመሸሸጊያ ወይም ለመሸፈት የሚመርጧት ቦታ ስለነበረች ነው ስያሜዋን ዲዚሽሽ በሚል ያገኘችው። ለዘመናት በዚህ ስሟ ስትጠራ የነበረችው ይህች ቀበሌ ስም ከተግባር ጋር ይያያዛልና ነዋሪዎቿ አጥፍተው የሚሸፍቱባት ታሪኳ ቀርቶ ዛሬ የልማትና የሠላም መንገድን ስለያዘች ስሟ መቀየር አለበት በሚል የወረዳው ምክር ቤትና ህዝቡ በመስማማት ከ2003 ዓ.ም መጀመሪያዎቹ ጀምሮ ዲዚአማ የሚል ሲያሜ ሰጥተዋታል። አማ ማለት አበባ ማለት ነው።

ተረታ 18- ቢኛሬ

ድሮ አባቴ "ያደረኩትን ስማና አንተም በእኔ መንገድ ሂድ" አለኝ። "ሚስት አግባና ዘርህን ተካ እኔ እንዲሁ አድርጊያለሁና። ያላገቡ ሴቶችን ካገቡ ሴቶች ለመለየት ምልክት ይሆን ዘንድ አስሌ ወይም ዜር (የበና ሴቶች ፀጉራቸዉን የሚቀቡት ቀይ ከለር ያለው አፈር መጠሪያ ስም ነዉ) ፀጉራቸዉን ቀባቸዉ። ሚስቶችህ ከአንድ በላይ ከሆኑ የመጀመሪያ ሚስትህ ላይ ቢኛሬ (አንገት ላይ የሚታሰር ትልቅ ብረት ነዉ) እሰር፤ ለእሷም የመጀመሪያ ስለ መሆኗ ምልክትና መከበሪያዋ ነዉ።" አለኝ እኔም አደረኩ።

ተረታ 19- የጋሲ ጎሳ አመጣጥ

ጥንት የእኔ ቅድመ አያቶች አሁን ካለንበት ከዚህ የበና ሀገር ዉጭ ይኖሩ ነበር። በወቅቱ እነሱን ሲመራ የነበረዉ ንጉሳቸዉ በየዓመቱ ግብር ያስገብሯቸው ነበር። ግብሩ ደግሞ እህል ወይም ከብት ሳይሆን ሰዉ ነበር። ግብሩ ዞሮ ዞሮ አንደኛዉ አመት ላይ እኛ ቤተሰብ ላይ ደረሰ ማለትም የጥንት አያት ቅደመ አያቴ የአመቱን ግብር ሰዉ እንዲያቀርብ ተጠየቀ ያኔ የነበረዉ የቤተሰቡ ቁጥር 4 ልጆች ከእሱና ከሚስቱ ጋር 6 ብቻ ነበሩ።

ይህ መልዕክት ከንጉሱ የደረሰዉ አያቴ አንድ ሀሳብ አሰበና ተገበረዉ። ሀሳቡም "በማሳዬ ላይ ዘር ብዘራ ዘር ስለ ዘራ የትም አይሄድም ብለዉ ያስባሉ ስለዚህ ደቦ (ስራን በህብረት የመስራት ዘዴ) ልጥራ" ብሎ የአካባቢውን ህዝብ በሙሉ ደቦ ጠራ ዘሩም ተዘራ። ዘርቶ ሲጨርስም በሰዎች ፊት በንጋታዉ ከልጆቹ መሀል አንዱን ግብር እንደሚሰጥ ቃል ገብቶ ለንጉሱ መልዕክት ላከ። ህዝቡም ወደየቤቱ ተበተነ። ቀኑ መምሸት ሲጀምር የቀጣዩ ቀን ፀሐይ ከመዉጣቷ በፊት ልጁን ከግብር ለማዳን የወሰነዉ ጥንት አያታችን ዝግጅቱን በፍጥነት አጠናቆ አራቱ ልጆቹን ሚስቱንና እራሱን ይዞ በድምሩ ስድስት ቤተሰቡ ጋር ሌሊቱን ፀሀይ ከመዉጣቷ በፊት ያንን አከባቢ ለቀዉ ተሰደዱ። እዚህ አሁን ካለንበት ስፍራ መጥተዉ ሰፈሩም። እየተባዛንም ለዚህ በቃን አሁን ዉሩሪ፣ ሻባ፣ ስሌ (የቀበሌያት ስም ነዉ) በቃ በአራቱም የበና ምድር ላይ ተሰራጭተን እንገኛለን።

ተረታ 20- የቢታ አመጣጥ

ድሮ የአኔ አባት የመጣዉ አሪ ሀገር ዉስጥ ባኮ ተብሎ ከሚጠራ ቦታ ነዉ። ሲመጣም ትንሽ ቆዳ ብልቱ ላይ ታጥቆ ነበር። ብልቱም አልተገረዘም። መጥቶ ከዚህ ከፔንቴ ተራራ ስር ከአንድ ዛፍ ስር ቁጭ አለ። እዚህ የነበሩ ሰዎችም ምን አንደሚሰራ ጠየቁት። እሱም "ስለ ከብቶች፣ ስለ ዝናብ እግዚአብሄርን እለምናለሁ አላቸዉ" ሰዎቹም ስለማንነቱ በደንብ ለማወቅ በማ አምጥተዉ አረዱና አንጀቱን ማንበብ ጀመሩ። ከአንጀቱም እግዚአብሄር የባረከዉና ከእነሱ ጋር ቢሆን ሀገራቱም ትባረካለች የሚል አነበቡና እንደዚህ አሉት፤ "በባህላችን መሰረት ተገርዘህ ዝለልና ከእኛ ጋር ተጋብተህ ኑር" አሉት። እሱም "በኛ ዘር ደም አይፈስም ነዉር ነዉ። ስለዚህ አልገረዝም" አላቸዉ። (ይህ ጎሳ ገታ የሚባለዉ የንጉስ ጎሳ ሲሆን አሁንም ድረስ አይገረዙም) እነሱም እሺ ብለዉ ሳይገረዝ ከብት እንዲዘል አደረጉትና ዘለለ። ቀጥለዉም "አንተ ከእኛ ጋር ኑር፣ አንተን ለእኛ እግዚአብሄር ልኳልና ለእኛ ንጉስ ሁን። ሌላ ሰዉ አንሾምም" አሉት። እሱም እሺ ብሎ ረሃብ፣ ድርቅ ከቀየዉ እንዲጠፋ፣ ዝናብ እንዲዘንብ፣ ከብቶችና ሰዉ ደህና እንዲሆኑ በርጆን (እግዚአብሄርን) ይለምን ነበር። እሱ ሲሞትም ለመጀመሪያ ወንድ ልጁ ንግስናዉን አወረሰው። በዚህ መልኩ እሱም አዉርሶ እንዲሞት አዘዘዉ። እናም ንጉስ የሚሆነዉ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ነዉ በዚህ አካኋን ንግስናችን እየተወራረሰ መጥቶ። ዛሬ ላይ እኔ ዘጠነኛ የበና ቢታ ስሆን ስሞትም እንዲያስተዳድር ለመጀመሪያ ወንድ ልጄ ለቆጻ አድነው ንግስናዬን አወርሻለሁ።

ተረታ 21- ባለ ሦስት ቀለማቱ ልጅ

ሻባ (ከበና ቀበሌያት አንዷ ናት) በሚባል መንደር አርመምባ የሚባል ሰዉ ነበር። ሚስቱ ከእናታ ልጅ ጋር ዝሙት ሰርታ ጸንሳ ልጅ ወለደች። መጀመሪያ እነዚህ ሁለት ዘመዳሞች ዝሙት ይሰራሉ ብሎ የጠረጠረ አልነበረም። በኋላ ግን ልጁ ሲታይ ልክ እንደ ፎቶ ከባሏ ዉጭ ዝሙት ካደረገችዉ ዘመዷ ጋር በመመሳሰሉ ሰዎች መጠርጠርና ዉስጥ ለዉስጥ ማንሾካሾክ ጀመሩ። በተጨማሪም ልጁ ደረቱ፣ ጀርባዉ፣ የብብቱ ስር ሲታይ እንደ ባንዲራ ቀይ፣ ሰማያዊ፣ ቢጫና የተለያዩ ቀለማት ሰዉነቱ ላይ ነበሩት። ይህ ደግሞ የሰዎችን ጥርጣሬና ሹክሹክታ የበለጠ ያጠናከረ ሆነ።

የአከባቢው ሰዎችም "እኛ የቆዳዉ ቀለም የተቀየረና ቡራቡሬ ሆኖ ሲወለድ የምናዉቀዉ ከብትና ፍየል ነዉ። የሰዉም ተጀመረ እንዴ? እስቲ ምንጊ ብለን ከምናጠፋዉ መጨረሻዉን ይደግና እንየዉ።" ብለዉ ፊቀዱና መከታተል ጀመሩ። ልጁ በተወለደ በአንደኛዉ አመት በዚያች ቀበሌ ዙርያ ያሉት ሌሎች አካባቢዎች ዝናብ ሲዘንብ በዚያች ቀበሌ ጠብ ሳይል አለፈ። ሁለተኛዉና ሶስተኛዉ አመትም ያለ ዝናብ ቀጠለ። የአከባቢዉ አዋቂዎች ስለ ዝናብ ተጠየቁ፣ እነሱም ጫማቸዉን ጥለው (ከከብት ቆዳ በስሉ ለዚህ ተግባር ሲባል የሚሰራ ጫማ ነዉ) ከዘመዳሞች የተወለደው ህጻን ከቀበሌዉ እስካልወጣ ድረስ መቼም ዝናብ እንደማይዘንብ ተናገሩ። ህጻኑም አቅራቢያዉ ወዳለዉ ወደዚህ አልዱባ ቀበሌ ወንጌልን ወደ ሚከታተሉና ክሪስቲያን ወደ ሆኑ ዘመዶቹ ተላከ።

እዚህ መጥቶ አንድ ዓመት እንደቆየ አልዱባ ዝናብ ጠፋ። ህዝቡም ጉዳዩ አስጨንቆት ሲጠይቅ ከሻባ ቀበሌ ሰዎች "እናንተጋ ዝናብ የጠፋዉ ከዘመዳሞች የተወለደ ልጅ ስለገባ ነዉ። የ እኛን እዳ ተሸክማችኋል" የሚል መልዕክት ደረሳቸዉ። የአልዱባ ህዝብም ተሰብስቦ በጉዳዩ መክሮበት" ከዚህ ባህልና አስተሳሰብ ዉጭ ወደ ሆነ ቦታና ብሄረሰብ እንላከዉ።" ብለዉ ወደ አሪ ሀገር ላኩት ከዚያ ጀምሮ የዝናቡ ሁኔታ ተስተካከለ።

ተረታ 22- የ"ጎሪ" ስርዓት

"ድሮ አባቴ አንድ ነገር አስተማረኝ "ልጅ ወልደህ ስድስት ወር ሲሞላዉ ከእናቱ ጡት ውጪ ሌላ እህል ከመቅመሱ በፊት ደንብ የሚሰራ ሰው ጠርተህ ደንብ አሰራለትና እህል አቅምሰው፣ ይህ የኛ ደንብ ነው። ካልሆነ ግን ልጁ በስብሶ ሳይፈለፈል እነደቀረ እንቁላል ነው፤ ሰው አይደለም። ደንቡን በወቅቱ ለማድረግ ባትችል እንኳ እህል ሲደርስ ጠብቀህ ደንቡን አሰራለት፤ አለበለዝያ ክብትም አይዝለል" ብሎ አለኝ። እና በኛ ሃገር ሰው ሁሉ ይህንን ደንብ በግዴታ መፈፀም አለበት።

ተርታ 23- የቃቆ ወንዝና የበና ድንበር አፈጣጠር

ድሮ ቢታ ዛሬ ወዳለበት የበና ምድር ከመምጣታቸዉ በፊት የአሪ ህዝቦች ጋር ባኮ ተብሎ የሚጠራ ተራራማ ሀገር ላይ ይኖሩ ነበር። ታድያ ተራራማ አገራቸዉ ላይ ሆነዉ ቁልቁል ሲመለከቱ በርቀት የኛን ሀገር በዛፍ ተሸፍኖ አዩት። ለታላቅ ወንድማቸዉም "ከርቀት የማየዉ ያ ምድር መልካም ምድር ይመስለኛል እና አይቸዉ ልመለስ።" ብለዉ ነግረዋቸዉ ወደዚህ መጡ። በመንገድ ሲመጡ በንብ መንጋ ታጅበዉ ስለነበር ያየ ሁሉ" ተአምር! ተአምር!" እያለ ፔንቴ ተራራ ስር አረፉ።

ባረፉበት ቦታም በርጆን (አምላክን) ሲለምኑ ይታዩ ነበር። ይህንን ተግባራቸዉን እና የንቡን ሁኔታ በማየት የእኛ ሰዎች በባህላችን መሰረት ክብት አዘልለው፣ አጋብተውና ቢታ አደርገዉ ሸመው ከኛ ጋር እንዲኖር በመፈለጋቸው ሀሳባቸውን አቀረቡለት። እሱ ግን "የእናንተን ሀሳብ እቀበላለዉ። ነገር ግን ወንድሜን እመለሳለዉ ብዬ ስለመጣሁ በዚሁ ብቀር ያገሪንበኛል ይጨነቃልም። ስለዚህ ለሱ ነግሬዉ ተመልሼ ከናንተ ጋር ልኑር" የሚል መልስ ሰጣቸው። የእኛ ሰዎች ግን እንዲሄድባቸው ስላልፈለጉ መመለሱም ስላጠራጠራቸው ወንድምዬዉ ለሱ እንኳን እንቢ ቢለዉ እኛ በልመና አስጨንቀን እሺ እንዲል እናደርጋለን በማለት በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው ሽማግሌዎችና ህዝቡ አጅበዉት ጉዞ ወደ ወንድምየዉ ሀገር በእግር ጀመሩ።

እየተጓዙም ሳለ ለካስ የታናሽ ወንድሙ እመለሳለዉ ብሎ መጥፋት ያስጨነቀዉ ታላቅ ወንድም ሰዎችን አስክትሎ ወንድሙን ፍለጋ እየመጣ ነበርና ቃቆ ተብሎ የሚጠራ ወንዝ ላይ ተገናኙ። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ታላቅየዉ ታናሹ የቆየበትን ምክንያት ጠየቀዉ። ታናሹም "ለማየት የመጣሁት ምድር እጅግ መልካም ምድር ነዉ። ህዝቡም ከነሱ ጋር እኖር ዘንድ ጠየቀኝ። አንተን ማስፈቀድ ስላለብኝ

ይህንን ላማክርህ ወዳንተ ስመጣ ተገናኘን። ይህም ህዝብ የተከተለኝ ያንተን ፍቃድ ለመቀበል ነዉ" አለዉ። በሁኔታዉ እጅግ የተገረመዉ ታላቅ ወንድምም "በእዉነት ይህ ሁሉ ህዝብ እኔን ለማስፈቀድ ከመጣማ የሚደንቅ ነዉ። ከዛሬ ጀምሮ ከእነሱ ጋር እንድትኖር ፈቅጀልሀለሁ። ከዚህ በኋላ ከዚህ ወንዝ ወደታች ያለዉን አንተ አስተዳድር፣ ከዚህ ወደ ላይ ያለዉ ደግሞ የእኔ ነዉ" ብሎት ተለያዩ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የቃቆ ወንዝ እስካሁን ድረስ ከአሪ ብሄረሰብ ጋር የሚለየን ድንበር ሆኗል።

ኤፄሪ 24- የዝሆንና የሽለምጥማጥ ታሪክ

ከዕለታት አንድ ቀን ዝሆን ማር ተሸክሞ ወደ ገበያ ተነሳ። በመንገድ ሲሄድ ከአንድ ሽለምጥማጥ ጋር ተገናኘ "አንተ ዝሆን ሆይ! እኔን ደክሞኛል ተሸከመኝ?" አለችዉ። ዝሆኑም "እኔ ማር ተሸክሜአለዉ" አላት። "እባክህ እኔን ተሸከመኝ?" ብላ ለመነችዉ። "እሺ" ብሏት ከማሩ አጠገብ ሽለምጥማጧን ተሸክሞ ወደ ገበያ ጉዞዉን ቀጠለ። ሽለምጥማጧም ማሩን መብላት ጀመረች፤ ማሩ ማለቁን ስታይ "እኔን አዉርደኝ ቦታዬ ላይ ደርሻለሁ" አለችዉ። ዝሆኑም አዉርዷት ማሩን ሲያይ ቅሉ (የማሩ መያዣ ነዉ) ባዶ ሆኖ አገኘዉ። "ማሩን እንዴት አድርገሽ ጨረሽ?" ብሎ ጠየቃትና ወድያዉ ይዞ አሰራት አርጩሜም ሰብሮ ሊገርፋት ሲል ሽለምጥማጧ ፈጥና "ይህ አርጩሜ ስለማያሳምም በሱ አትምታኝ፤ ይልቅስ በበረሃ አርጩሜ ምታኝ" አለችዉ።

ዝሆኑም አርጩሜ ለመስበር በረሃ ወረደ። ሽለምጥማጧ የታሰረችዉ ቦታ ጅብ መጣ። ጅቡም" ለምን ታሰርሽ?" አላት። "ጮማ ስጋ ብይ ተብዬ እምቢ በማለቴ ነዉ የታሰርኩት" አለችዉ። ጅቡም "እባክሽን ባንቺ ቦታ እኔ ልታሰር?" ብሎ ለመናት። "እንዲህ ከሆነ እኔን ፍታኝና አንትን ልሰርህ" አለችዉ። በሀሳቡም ስለተስማሙ ጅቡ ሽለምጥማጧን ፈታትና እሷ ጅቡን አስራዉ ሄደች። ዝሆንም አርጩሜዉን ከበረሃ ይዞ ሲመጣ ጅቡ በችኮላ እንዳየዉ "እኔ እበላለዉ! እኔ እበላለዉ!" ሲል የሰማዉ ዝሆን ቅድም ማሬን ተበላ አሁን ደግሞ እኔን ብሎ ደብድቦ ገደለዉ ይባላል።

ኤፄሪ 25- ጦጣና አዞ

አንድ ነገር እንደዚህ ሆነ ብለው ይናገራሉ። አንድ ጦጣ ከወንዝ ዳር ካለ የሾላ ዛፍ ላይ ሆኖ የዛፉን ፍሬ ሲበላ ከወንዙ ውስጥ ያለች አዞ ከሾላው ፍሬ እንዲጥልላት ትለምነዋለች። ጦጣውም "አንቺ ዛፍ ላይ መውጣት የማትችይ እንዳአንቺ አይነቱ ደግሞ ይህን አይነት ፍሬ ይበላል እንዴ?" ብሎ ይናገራታል። አዞዋም "እባክህ ጣልልኝ" ብላ ደጋግማ ትለምነዋለች። ጦጣውም" የእውነት ልስጥሽ እንዴ?" አለቻት። አዞዋም "ስጠኝ" ብላ መለሰችላት። ይህን ጊዜ ጦጣው ከሾላው ሁለት ፍሬ ጣለላት። አዞዋም ሁለቱን ፍሬ ከወሰደች በኋላ "አሁንም ትንሽ ትንሽ እየመጣህ ስጠኝ" አለችው። ከዚያም ጦጣው ትንሽ ትንሽ እያወረደ ይሰጣት ጀመር። ጦጣው "እኔ እያወረድኩ ፍሬውን ትንሽ ትንሽ ላንቺ ስሰጥሽ አንቺ ለእኔ ምን ትሰጪኛለሽ?" ሲላት አዞዋም" አንተ ወደ እኔ፣ ከወረድክ እኔ እሰጥሀለው" ብላ ትለዋለች።

60
23
37

ጦጣውም መልሶ "ውሃ ውስጥ ብወድቅስ ውሃው እኔን አይበላኝም ወይ? "ብሎ ጠየቃት። አዞዋም" አይ! አይበላህም። አንተ እኔን የሾላውን ፍሬ እያወረድክ እንዳበላኸኝ እኔም አንተን በጀርባዬ ተሸክሜ ሄጀ የኛን ምግብ አበላሀለው" አለችው። ጦጣውም "እንዴት አድርገሽ ይዘሸኝ ትሄጃለሽ?" ብሎ ጠየቃት። አዞዋም "አንተ የእኔ ጀርባ ላይ ትቀመጣለህ፣ ከዝያም እኔ እየዋኘው ወደ ቤቴ ወስድህና ምርጥ ምርጥ ምግብ አበላሀለው" አለችው። ጦጣውም "አሃ! እውነትሽን ነው?" ቢል አዞዋም" እውነቴን ነው፤ በመጀመሪያ ግን እሱ ላይ ያሉትን ፍሬዎች በሙሉ አውርድና ለልጆቼ ቤት እንወስዳለን። ከዚያም እቤት የኔን ምግብ ላንተ እሰጥሀለሁ" አለችው። ጦጣውም የቀሩትን ፍሬዎች ለቅሞ ወደ አዞዋ መጣና "እሽ እንዴት ልሁን?" ብሎ ሲጠይቅ አዞዋ ጀርባዋን ሰጠችውና "ዝለልና ጀርባዬ ላይ ውጣ" አለችው። ጦጣውም እንደታዘዘው ዘሎ የአዞዋ ጀርባ ላይ ወጣ። አዞዋም "በቃ አሁን ሀይቁን ተሻግረን ቤቴ እንሄድና ለልጆቼ ፍሬውን ካበላሁ በኋላ የኔን ምግብ ደግሞ አንተ በልተህ ስትጨርስ እንደአሁኑ በጀርባዬ ተሸክሜ አምጥቼ ከቦታህ ላይ እመልስኃለሁ" አለችው። ጦጣውም አዞዋ ያለችውን በማመኑ ከአዞዋ ጋር ወደቤቷ ተጓዘ። ቤቷም እንደደረሰች ጦጣውን አውርዳ ከአንድ ጥግ ካስቀመጠች በኋላ የሾላውን ፍሬ ለልጆቿ ሰጠች። ከዚያም ጮክ ብላ ባሏን "የትነው ያለኸው?" ስትል ተጣራች። የአዞዋ ባልም" ጥሪዋን ሰምቶ ነበርና እኔ እዚህ ታች ምናምን ባገኝ ብዬ አጥምጄ ቁጭ ብያለሁ" አላት። አዞዋም "እኔ አሪፍ ምግብ አምጥቼ አዘጋጅቻለውና ቶሎና" አለችው። ደግማም "በጣም አሪፍ ምግብ አምጥቻለውና ፍጠን" አለች። ይህን ጊዜ የአዞዋ ባልም እየሮጠ መጣ። እናም ወደ እሷ ቀርቦ" የታለ አምጥቻለው ያልሽው ምግብ?" አላት። አዞዋም ይሄው በሴት ዘዴ ላንተ ያመጣሁት ምርጥ ምግብ ብላ ጦጣውን አሳየችው። ጦጣውም ከተቀመጠበት ወዲያው ተነሳና "እሺ! አንቺ እኔን ለባልሽ ምርጥ ምግብ ማዘጋጀትሽ ጥሩ ነው ነገር ግን ነገ ለልጆችሽ የሾላ ፍሬ እያወረደ ማን ይስጥሻል? ስለዚህ ቤት ሄጀ ለቤተሰቦቼ የሾላ ፍሬ እያወረዳችሁ ለአዞ ልጆች ስጡ። ብዬ መናገር አለብኝ እነሱ እንኳን እንበ ቢሏችሁና ድንገት ብትራቡ ምን ልትሆኑ ነው ዛሬስ እኔን በላችሁ ስለዚህ እኔን ከመብላታችሁ በፊት ዛፍ ላይ እንዴት እንደሚወጣና ፍሬው ደግሞ እንዴት እንደሚቀጠፍ ላስተምራችሁ አለ። አዞዋም እውነት መስሏት ተነሳችና "እውነትህን ነው? ዛፍ ላይ መውጣት ታስተምረኛለህ?" ብላ ጠየቀችው ጦጣውም አዎ ዛፍ ላይ እንዴት በቀላሉ ልትወጪ እንደምትችይ በሚገባ አሰተምርሻለው።" ይላታል። ይህን ጊዜ አዞዋም ወደ ባልዋ ዞራ "ጥሩ! አንተ እዚህ ቁጭ በል። እኔ ሄጄ ዛፍ ላይ እንዴት መውጣት እንደሚቻል እማርና መልሼ አመጣዋለው።" ብላ ትነሳለች። ከዚያም ጦጣውን በጀርባዋ ላይ አድርጋ ዛፉ ስር ስትደርስ ጦጣው ከጀርባዋ ዘሎ ዛፉ ላይ ይወጣል። አዞዋም" አንተ ጦጣ ምነው ዛፍ ላይ መውጣት አስተምርሻለው ብለህ አልነበር? "ብላ ስትለው ጦጣው በ'እንዴት" ሂጂ ደካማ! ለዚያውም አንቺ ነሽ ዛፍ ላይ መውጣት የምትማሪው? ደግሞስ እንዳንቺ አይነቱን ጅል ነው እኔ ዛፍ ላይ መውጣት የማስተምረው? በይ አንቺም እድሜልክሽን በውሃ ውስጥ ኑሪ። እኔም ዛፌ ላይ ሆኜ እያራሁብሽ ኖራለሁ።" ብሎ አለ ይባላል።

ኤፄሪ 26- ቆቅና ጅግራ

አንድ ወቅት ላይ ቆቅና ጅግራ ዘር ለመውሰድ ይገናኛሉ። እናም ቆቅ ወደ ጅግራ ቤት ሄዳ ዘር እንድትሰጣት ትጠይቃታለች። ጅግራም የምትጠይቀውን ዘር እንደምትሰጣት፤ ነገር ግን አሁን ሳይሆን ዝናብ ሲመጣ ተመልሳ እንድትመጣ ነግራት ትሸኛታለች። ቆቅም በነገሩ ተስማምታ እየተመለሰች ሳለ መንገድ ላይ አንዲት ላም ሽንቷን ሸንታ ያጎረፈውን ጎርፍ አይታ "እንዴ! የተባለው ዝናብ ዘንቦ አይደለም እንዴ ይህ ጎርፍ የመጣው?" ብላ ወደ ጅግራዋ ቤት ተመልሳ ትሄዳለች። በራፍ ላይ ስትደርስ ከቤት ውስጥ ሆና የምትመለከታት ጅግራ "እንዴ! በራፋችን ላይ እግሩን አቅልቶ የመጣው ይሄ ምን ነገር ነው?" ብላ ስትጠይቅ ትሰማለች። ቆቋም መልሳ ጅግራዋን "አንቺ ጎባጣ አንቺ በመከርሸኝ መሠረት አይደል ዘሩን ለመውሰድ የመጣሁት?" ትላታለች። እቤት ውስጥ የነበረችው ጅግራም "እግረ ቀይዋ! እግርሽን አቅልተሽ የምትመጭው ስለ ሀገሩ ምኑን አውቀሽ ነው?" ብላ አለች ይባላል።

ኤፄሪ 27- የአሮጊቷ ምክር

በድሮ ጊዜ ዘወትር የሚጣሉ ባል እና ሚስት ነበሩ። ባልዬው ሁል ጊዜ ሲወጣ ሲገባ ሚስቱን በረባ ባልረባ ምክንያት ይደበድባት ነበር አሉ። እናም ድብደባው የበዛባት ሚስቱ የኑሮዋ ሁኔታ ግራ ቢገባት ሰፈሯ ወዳለች አሮጊት ሴት ቤት ሄዳ ችግሯን ሁሉ አንድ ባንድ ነገረቻት። "ባሌ ወጥቶ ገብቶ ይደበድበኛል፣ ከእለት እለትም ዱላው በዛብኝ። ስለዚህ ምን ይበጀኛል? ምን ትመክሪኛለሽ?" ስትል ጠየቀቻት። አሮጊቷም ሴት የሴትዬዋን ችግር ሁሉ አንድ ባንድ ከሰማች በኋላ "ችግርሽ በጣም ቀላል ነው። ምን ማድረግ እንዳለብሽ እነግርሻለሁ፤ ከዚያ በፊት ግን አንድ የምትፈፅሚው ነገር አለ። እሱን ስትፈፅሚ ብቻ ነው የምነግርሽ" ትላታለች። የሰውዬው ሚስትም ችግሯን የምትፈታላት ከሆነ የምታዛትን ነገር ሁሉ ልትፈፅም ቃል ትገባለች። አሮጊቷም የሴትዬዋን ቃል ከተቀበለች በኋላ "እንግዲህ እኔ የማዝሽ ነገር ቢኖር ከአንበሳ ጎፈር ላይ አንድ ዘለላ ፀጉር ነቅለሽ እንድታመጪልኝ ነው። ያን ካመጣሽልኝ ለቤትሽ ችግር መፍትሄ የሚሆነውን ሁሉ እነግርሻለሁ።" ትላታለች።

ችግርተኛዋ ሴትም ከባሏ ጋር ያለውን ችግር ለመፍታት የሚሆናትን መፍትሄ ለማግኘት አሮጊቷ ያዘዘቻትን ነገር እንዴት መፈፀም እንዳለባት ማሰብ ጀመረች። ትዕዛዙም እጅግ ከባድ እና ፈታኝ ሆነባት። ነገር ግን በእሷ ላይ ካለ ችግር አይበልጥም ብላ በማሰብ እንዴት ማድረግ እንዳለባት መፍትሄ መፈለግ ጀመረች። አንበሳ ማግኘት የምትችልበትን አከባቢም አፈላልጋ ካወቀች በኋላ አንድ በግ አሳረደች፣ ከበጉ ላይም ከፊት እግሩ አንዱን ይዛ አንበሳው ወደሚገኝበት አከባቢ ሄደች። አንድ አንበሳም ከሩቅ ስታይ እሱ አስኪመለከታት ድረስ ጠብቃ የበጉን አንድ እግር አስቀምጣ ወደ ቤቷ ተመለሰች። በንጋታውም በተመሳሳይ ሰዓት የበጉን ሌላ እግር ይዛ የትናንቱ ቦታ ላይ መጣች። እንዳጋጣሚ አንበሳውም ነበርና ወደእሷ ዙሮ ሲመለከታት አሁንም ያመጣችውን የበግ ስጋ አስቀምጣ ተመለሰች።

በሶስተኛው ቀን አሁንም ከበጉ አንድ እግር ከተወሰነ ስጋ ጋር ይዛ አንበሳውን ወደምታገኝበት ጫካ ሄደች። አንበሳውም በተከታታይ ቀናት ስጋ በማግኘቱ በቦታው ላይ ይጠብቅ ነበርና ስታገኘው እንደሌላው ቀን በሩቁ አስቀምጣ ከመሄድ ይልቅ ቀረብ ብላ እንዲለምዳት ለማድረግ አሰበችና ወደ አንበሳው ተጠግታ ከፊቱ አስቀመጠችለት። እናም አስኪበላ ድረስ ቁማ ስትመለከት ቆይታ ወደቤቷ ተመለሰች። ስትመለስም አንበሳው እየለመዳት መምጣቱን እያሰበች ነበርና በንጋታውም የመጨረሻውን ስጋ ይዛ ስትሄድ ግን ፀጉሩን ለመውሰድ ወሰነች። እንዳሰበችው በአራተኛው ቀን የበጉን የመጨረሻ እግር ይዛ ወደ አንበሳው መኖርያ ስፍራ ስትሄድ እንደጠበቀችው አንበሳውን የተለመደው ስፍራ ላይ ሲጠብቃት ስላገኘችው ስጋውን ሰጥታ እየበላ እያለ ፀጉሩን በመደባበስ አንድ ፀጉር ነቅላ ለመውሰድ ቻለች። ሴትየዋም የአንበሳውን ፀጉር እንደያዘች በቀጥታ ወደ አሮጊቷ ቤት ትሄዳለች። እንደደረሰችም ለአሮጊቷ የታዘዘችውን የአንበሳ ፀጉር እንዳመጣች ትነግራታለች። አሮጊቷም እንዴት ልታገኝ እንደቻለች ትጠይቃታለች። ሴትዬዋም የተጠቀመችውን ብልሃት በዝርዝር ትነግራታለች። ይህን ጊዜ አሮጊቷ መልሳ "የጫካ አውሬ የሆነውን እና እጅግ አስፈሪ የሆነውን አንበሳን ያክል እንስሳ ማላመድ እና ገራም ማድረግ ከቻልሽ የሰው ልጅ የሆነውን አንድ ባልሽን እንዴት መግራት አቃተሽ? በይ ወደቤትሽ ሂጅና አስቢበት።" ብላ ሸኘቻት ይባላል።

ኤፄሪ 28- በሽተኛው አባት

አሥር ልጆች ያሉት አንድ ሰው ነበር። አንድ ቀን ታመመና በሽታው ልክፍት ነው ተብሎ ስለታሰበ የሰው ደም እንዲጠጣ ታዘዘ። በዚህን ጊዜ ልጆቹን ጠራቸውና የሰው ደም እንዲያመጡለት አዘዛቸው። ልጆቹም ፍለጋ ወጥተው ምንም ነገር ሳያገኙ ባዶአቸውን ተመለሱ። አባትዬውም ያዘዛቸውን እንዳመጡ ቢጠይቃቸው እንዳላመጡ ነገሩት። መልሶ ለሁለተኛ ጊዜ ላካቸው። ለሁለተኛ ጊዜ ሳያገኙ ተመለሱ። ይህን ጊዜ አባትዬው ተናደደና ልጆቹን "በሉ ተሸከሙኝና ገበያ መሃል ውሰዱኝ" አላቸው። ልጆቹም እንደታዘዙት ወደ ገበያ ሲወስዱት ገበያው መሀል ላይ እንዲያስተኙት አዘዛቸው። ልጆቹም እንደታዘዙት ገበያው መሐል ላይ አስተኙት። ይህን ጊዜ ገባይተኛው ሁሉ ልጆቹን "ምን ሆናችኋል? በሽተኛውን ሰው እንዴት ገበያው መሐል ታስተኙታላችሁ? ወደ ዳር አውጡት" ቢሉ በሽተኛው ሰውዩ "በፍፁም እኔ እዚህ ነው የምተኛው" አለ። አንድ ሰው ፍየል እየነዳ መጥቶ በሽተኛው አጠገብ ቆመ። ከበሽተኛው ሌላ ጎን ላይ ደግሞ ጤፍ ዘርግቶ የሚሸጥ ሰው አለ። በሌላ ጎኑም ሸክላ ምጣድ የያዘም ነበር። ከበሽተኛው አጠገብ ያሉ ሰዎች ፍየሉን "ከበሽተኛው አጠገብ ዞር አድርግ!" ብለው ፍየሉን ገፉት። ይህን ጊዜ ጤፍ የሚሸጠው ሰውዬም ወዲያውኑ "የኔንም ጤፍ ያበላሻልና ከዚህ ዞር አድርግ!" ብሎ ፍየሉን ወደጎን ገፋበት። ፍየሉም ሲገፋ የባለ ሸክላው ምጣድ ላይ ይወጣበትና ምጣዱን ይሰብርበታል። የምጣዱ ባለቤትና የፍየሉ ባለቤት ይጣሉና ድብድብ ይጀምራሉ። የምጣዱ ባለቤት በጣም ተናዶ ስለነበር የፍየሉን ባለቤት እጅግ በጣም ደብድቦት ከበሽተኛው አጠገብ ይጥለዋል። ይህን ጊዜ በሽተኛው ሰውዬ ልጆቹን

ጠርቶ "እያችሁ! የሰው ደም የሚጠጣው በዘዴ ነው። ቀድማችሁ ቤት ድረስ አምጥታችሁልኝ ቢሆን ኖሮ እስካሁን እኔ ድኜ ነበር። እና አሁን ለኔም ስጡኝ ለናንተም ጠጡ" ብሎ አላቸው ይባላል።

ኤፄሪ 29- የፍየልና መዥገር ፉክክር

ድሮ በአንድ ወቅት ፍየልና መዥገር ተፎካከሩ። መዥገርም ፍየልን "አንተ ስትሮጥ እኔ ከእግርህ ስር ሳልጠፋ አንተ ጋር እኩል ካሮጥኩኝ እኔ መዥገር አይደለሁም። እስኪ አንተ እሮጠህ እሮጠህ ከእግርህ ስር እየኝ፣ እኔ ከሌለሁ እኔ መዥገር አይደለሁም!" ይለዋል። ከዚያ ለመሮጥ ሲዘጋጁ መዥገሩ የፍየሉ እግር ስር ተጠግቶ ይቆማል። "ሩጫ እንጀምር!" ብለዉ መሮጥ ሲጀምሩ መዥገሩ ቶሎ ብሎ ፍየሉ ላይ ይለጠፋል። ብዙ ርቀት ሮጠዉ ሲቆሙ ወድያወኑ መዥገሩ ወርዶ "እኔ አጠግብህ ከእግርህ ስር ነኝ ያለሁት እናም እንዳትረግጠኝ" ይለዋል። ፍየሉም "እንዴት ተቀደምኩኝ? እስኪ አሁን እኩል ተረከዝ ለተረከዝ ቆመን ሩጫዉን እንጀምር" ይለዋል። መዥገሩም አጠገቡ ተጥግቶ "እንጀምር" ይልና ወድያዉ ፍየሉ ላይ ይለጠፋል። ፍየሉም ብዙ ርቀት ሮጦ ሮጦ ሲደክም ቆም ብሎ የት እንዳለ ለማየት ዞር ሲል መዥገሩ "እኔን እንዳትረግጠኝ እኔ ካንተ እኩል ከእግርህ ስር ነኝ" ይለዋል። እናም እንዲህ አድርጎ ፍየሉን አሸነፈዉ።

ኤፄሪ 30- ጅብን እሮጦ ያሸነፈው እንቁራሪት

አንድ ቀን ወንዝ ዳር ወዳለ እንቁራሪት ጅብ ይመጣና "አንተ እንቁራሪት እኔን በሩጫ ታሸንፋለህ?" ብሎ ይጠይቃል። እንቁራሪቱም "አሸንፋለሁ!" ይለዋል። ጅቡም "በል ከሶስት ቀን በኋላ ስለምንወዳደር ተዘጋጅ!" ብሎት በቀጠሮ ይለያያሉ። እንቁራሪቱም የቀጠሮው ቀን እሲኪደርስ ድረስ በወንዝ ውስጥ ያሉትን ጓደኞቹን አሰባስበና ምክር ሰጣቸው። "ከሶስት ቀን በኋላ ከጅብ ጋር ውድድር ስላለን የዝያን ቀን እናንተ ተበታትናችሁ ጅቡ በደረሰበት ‹አው!› እያለ ድምጽ ሲያሰማ ከፊት ያለ እንቁራሪት ‹ቁዋ!› በማለት የመልስ ድምጽ አሰሙ።።" ብሎ መከራቸውና ተለየዩ። በሶስተኛውም ቀን በቀጠሮው ጅብ ወደ እንቁራሪት ዘንድ ይመጣና "አንተ እንቁራሪት የቀጠሮ ቀናችን ዛሬ አይደል?" ብሎ ይጠይቀዋል። እንቁራሪቱም "ልክ ነህ! ዛሬ ነው ቀጠሮአችን" ይለዋል። ጅቡም "በል እንግዲህ አንተ በአባትህ ባህል መሠረት በወንዙ ውስጥ ለውስጥ እሩጥ፣ እኔም በአባቴ ባህል መሠረት ዳር ዳር እሮጣለሁ" ይለዋል። እንቁራሪቱም ይስማማና እሩጫውን ይጀምራሉ። ጅብም ትንሽ ይሮጥና ቆሞ "አው! አው!" ብሎ ሲጮኽ ከፊት ለፊቱ እንቁራሪት "ቋዋ! ቋዋ" የሚል ድመጽ ያሰማል። እንዲህማ አይሆንም ብሎ ጅቡ ፍጥነት ጨምሮ ትንሽ እንደሮጠ ቆሞ "አው!" ብሎ ሲጮኽ ከፊት ለፊቱ እንቁራሪት "ቋዋ!" የሚል ድምጽ ያሰማል። ጅብ በዚህን ጊዜ በጣም ይናደድና "እቁራሪት እኔን ካሸነፈችማ እዚህ ምድር ላይ ምኑን ኖርኩት?" ብሎ እንደገና ፍጥነቱን በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ ብዙ ከሮጠ በኋላ ቆሞ "አው!" ሲል አሁንም ከፊት ለፊቱ "ቋዋ!" የሚል የእንቁራሪት ድምጽ ይሰማል። ይህን ጊዜ ጅቡ እጅግ በጣም

ይናደድና ባለ በሌለ ኃይሉ ሲሮጥ ከፊት ለፊቱ ገደል ነበርና ሳያይ ከገደል ውስጥ ገብቶ ተሰባብሮ ሞተ ይባላል።

ኤፄሪ 31- የጅብና አንበሳ ዘረፋ

በድሮ ጊዜ ዘጠኝ ጅቦችና አንድ አንበሳ ለጦርነት ይሄዳሉ። ጦርነቱንም ተዋግተው ሲጨርሱ አሥር ከብቶችን ማርከው ይመለሳሉ። ሲመለሱ አንበሳ አንድ ነገር አሰበ ሃሳቡም "እኔ አንድ ነኝ እነሱ ዘጠኝ ናቸው፤ ዘርፈን የመጣናቸው ከብቶች ደግሞ አሥር ናቸው። ስለዚህ ዘጠኙን ከብቶች ለራሴ ከወሰድኩ ከእኔ ጋር አሥር ይሆናሉ፣ እነሱ ደግሞ ዘጠኝ ስለሆኑ አንድ ቢወስዱ አሥር ይሆናሉ። እናም እንደዚህ አድርገን መካፈል አለብን "ብሎ አሰበና በመንገድ ላይ ሳሉ ጅቦችን እንደዚህ ይላቸዋል።" እኔ አንድ ነኝ እናንተ ደግሞ ዘጠኝ ናችሁ። ስለዚህ ዘጠኝ ከብቶችን እኔ ብወስድ እናንተ ደግሞ ዘጠኝ ናችሁና አንድ ብትወስዱ አንድ ላይ አሥር ትሆናላችሁ፣ ስለዚህ እኛ እንደዚህ እኩል ተከፋፍለን እንሂድ ይላቸዋል። "ሀሳቡን የሰሙት ጅቦች በሀሳቡ ላይ ከተወያዩ በኋላ" ብንከራከር አንበሳ እኛን አይለቀንም " በሚል ሃሳ ቡን ተቀብለ ው አንዲን ከብት ብቻ ወ ስደው ወ ደ አባታቸ ው ይሄዳሉ፡ : እንደደረሱም አባታቸው "ልጆቼ ጦርነቱ ተሳካላችሁ እንዴ?" ብሎ ይጠይቃቸዋል። ልጆቹም "አባባ ጦርነቱ ለኛ በጣም ተሳክቷል እኛም አሥር ከብቶችን ማርከን ይዘን መጥተን ነበር። ነገር ግን አንበሳ ዘጠኙን ወስዶ አንዱን ለኛ ተወልን። እኛ ደግሞ ይኸው የተሰጠንን ይዘን መጥተናል።" አሉ። ይህን ጊዜ የዘጠኙ ጅቦች አባት "እንዴ! እኔ ወንድ ልጅ አልወለድኩም? እንዴት ዘጠኝ ከብት ለሱ ሰጥታችሁ ለራሳችሁ አንድ ከብት ብቻ ይዛችሁ ትመጣላችሁ?" ብሎ ይቆጣቸውና በንዴት "እስቲ እሱ ያለበትን ቦታ ለእኔ አሳዩኝ?" ይላቸዋል። ልጆቹም ፈርተው "አይ! አባዬ በኋላ አንበሳ እኛን አይለቀንምና ይህ ነገር ይቅርብን።" ይሉታል። አባታቸውም "በፍጽም! ተነሱ እኔን ምሩኝ" ይላቸዋል። ልጆቹም እሺ ብለው አንበሳው ወዳለበት ቦታ ይጓዛሉ። አባታቸው በእጁ ከሩቅ እየጠቆማቸው" እዚያ ጋ ሣር ይታያችዋል? ከእሱ ወዴት ነው? "ይላቸዋል። ልጆቹም" አባታችን! ያ የምታየው ሣር እውነተኛ ሣር አይደለም የአንበሣው ጎፈሬ ነው" ይሉታል። ከዚያ "እሺ" ብሏቸው ይጓዛሉ። ትንሽ እንደሄዱ አሁንም የጅቦቹ አባት በእጁ እሩቅ እየጠቆመ "እዚያ ጋ እሳት ይታያችኋል? ከእሱ እሳት ወዴት በኩል ነው?" ብሎ ይጠይቃቸዋል። ይህን ጊዜም ልጆቹ "አባታችን ያ የምታየው እሣት አይደለም የእሱ አይን ነው" ይሉታል። ከዚያም እየተጓዙ አንበሳው ጋ ይደርሳሉ። ተመልሰው መምጣታቸውን አንበሳው ሲመለከት "እንዴ እናንተ ለምን ተመልሳችሁ ወደዚህ መጣችሁ?" ብሎ ይጠይቃቸዋል። ይህን ጊዜ የዘጠኙ ጅቦች አባት ጠጋ ብሎ "እኛ ድሮ አመድ ውስጥ እየተንከባለልን አመድ ነው የምንበላው፣ አሁን ደግሞ ልጆች እኔ ላይ ከብት ይዘውብኝ ሲመጡ ይኼ እኮ ለአንበሳ የሚገባ ነው! አንድም ቢሆን እንኳ ለምን ወደዚህ ይዛችሁ መጣችሁ? ሁሉንም ለሱ መስጠት ነበረባችሁ። ብዬ ተቆጥቻቸው ይህን የቀረውን በሬ ላንተ ለማድረስ ነው የመጣሁት።" ብሎ የቀረችውን አንድ ከብት ለአንበሳ ሰጥቶ ከልጆቹ ጋር ባዶ እጁን ተመልሶ ሄደ ይባላል።

ኤዜሪ 32- እርጉዟ ጦጣ

ድሮ አንበሳና ሸለምጥማጥ አብረው ይኖሩ ነበረ። አንድ ቀን አንበሳ ፀሐይ ለመሞቅ እግሩን ወደ ላይ ሰቅሎ ቡጭበት ሸለምጥማጥ ተመልክቶት "አጎቴ ሞታል! ኑና ተመልከቱ" እያለ እንሰሳቱን ይጠራቸዋል። እነሱም መጥተው እውነት መስሏቸው ተሰብስበው እየጨፍሩ ሳለ መጨረሻ ላይ አንድ እርጉዝ ጦጣ ትመጣለች። እርጉዟ ጦጣ ግን ወሬው እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ቀስ ብላ በጣቷ የአንበሳውን ቂጥ ነካ ብታደርገው የአንበሳው ቂጥ ወደ ውስጥ ጭምቅ ሲል ትመለከታለች። ሁኔታው ግራ ስለገባትም የባሏን ስም "ዞቦር ቃሮ" ብላ ተጣርታ "የሞተ ነገር ቂጡን ጭምቅ ያደርጋል እንዴ?" ብላ ትጠይቀዋለች። ባሏም ሚስቱ ያለችውን ሰምቶ ባለማመን "የእርጉዝ ውሸታም አየሁ" ብሎ ይሳለቅባታል። ነገር ግን እርጉዟ ጦጣ ያየችውን አይታለችና "አሃ! እንዲያ ከሆነ በሉ እናንተ ጨፍሩ" ብላ ትታቸው ሄደች። ይህን ጊዜ አንበሳው የሞተ መስሎ ሁሉን ነገር ይከታተል ነበርና ድንገት ተነስቶ በዙሪያው ያሉትን በሙሉ ደብድቦ ገደላቸው። ያቺ እርጉዝ ጦጣ ግን ትታቸው በመሄዷ ከሞት ተረፈች ይባላል።

ኤዜሪ 33- የአይጦች ስብሰባ

በድሮ ጊዜ አይጦች ድመት ሁል ጊዜ እነሱን እየበላች ስታስቸግር ከድመት ለማምለጥ መፍትሄ ለማግኘት እርስ በእርስ ስብሰባ ተጠራርተዉ ተቀመጡና ዉይይት ጀመሩ ተባለ። ድመት እንዳትበላቸዉ የሚያደርግ መፍትሔ ለማበጀት ብዙ ከተወያዩ በኋላ በስተመጨረሻ ላይ አንድ አይጥ "ድመት እኛን ለመብላት ስትመጣ ድምጽ ሰምተን እንድናመልጥ ለከብቶቻችን የምናሰረዉን አይነት ቃጭል በአንገቷ ላይ እንሰር።" የሚል ሀሳብ አቀረበ። የቀረበውንም አዲስ ሀሳብ ያደመጡት አይጦች በሙሉ በአንድ ድምፅ ተስማምተው አዐደቁት። ወዲያውም ከመሀከላቸው አንድ ጥበቡ የተባለ ሽማግሌ አይጥ ተነሳና በውሳኔያችሁ ተስማምቻለሁ። ነገር ግን የተባለውን ቃጭል ለማሰር ድመትን ይዞ የሚያቀርብልን አንድ ኃይለኛና ጉልበታም አይጥ መምረጥ አለብን እናም ከመሀከላችን ሀይለኛ የሆነው ማነው? አሁን እንምረጥ" አላቸው። ነገር ግን ድመትን የሚይዝ አይጥ ይበላልና ይህንን ሀላፊነት ደፍሮ የሚቀበል ጠፋ። በዚህም ምክንያት ቃጭል ለማሰር የተደረገዉ ዉሳኔ ፈረሰ ይባላል።

ኤዜሪ 34- አማቿ ቤት ሄዳ እጇን የተቃጠለችው ሴት

አንዲት ሴትዮዋ ጓደኛዋን ይዛ ወደ አማቿ ቤት ትሄዳለች እንደደረሱም ልጃቸው ሾፎሮ አፍልታ እየጠጡ ሲጫወቱ ምሽት ላይ ባለየው መጣ ወዲያውም ወደሴቶቹ ቀርቦ አጠገባቸው ተቀመጠና ሰላም አላቸው። ለተወሰነ ሰዓትም ሲያወራቸው ቆይቶ ትንሽ ልጅ ጠራና "ሂድና ያንን ቦቃ በግ ይዘህ ና!" ብሎ አዘዘው። ይህን ጊዜ የልጅቱ እናት ተደስታ ጓደኛዋን የቆነጠጠች መስሏት ሳታስበው አማቿን ቆነጠጠች። አማቿም ደንግጦ "ምነው እናቴ?" ብሎ ጠየቀ። ይህን ጊዜ ደንግጣ የምትለው ቢጠፋት"

አይ! በኛ እኮ ቦታ በግ ነውር ስለሆነ አይበላም። "ብላ አለችው። ይህን ጊዜ ሰውዬው" ታዲያ አንዴ በጉ ስለታረደ አንቺ ካልበላሽ አብራሽ የመጣችው አትበላም ወይ?" ብሎ ጠየቃት። "እሷ ትበላለች" ብላ መለሰች።

ከዚያ ሥጋው ተሠርቶ ለጓደኛዋ ተሰጣት። ጓደኛዋ ስትበላ እሷ በአፏ ባመጣችው ጉድ ሳትበላ ቀረች። የቀረውንም ሥጋ እንዲበስል ምድጃ ላይ ጥደው ተኙ። በጨለማ ሰው ሳያያት ተነስታ ከተጣደው ሥጋ አውጥታ ልትበላ ፈለገችና ወደ ተጣደው ሥጋ ውስጥ አንድ እጇን ጭምር አደረገች። እጇ ላይ ብዙ የአናባር ጌጣጌጥ ነበርና የፈላው ውሃ ከአንባሩ ጋር ሆኖ ሲያቃጥላት ደንግጣ በማውጣት እጇን ልብሷ ውስጥ ደበቀች ። በንጋታውም ሾ ፎሮ ተፈልቶ ሲሰጣት ቀኝ እጇ ን ደብ ቃ በሌላኛ ው ስትወ ስድ የተመለከተቻት ልጇ "እናቴ በቀኝሽ ተቀበይኝ እንጂ በግራሽ ለምን ትቀበይኛለሽ?" ብላ ብትላት ቀኝ እጇን አውጥታ አሳየቻት። እጇ ተቃጥሎ ሥጋው ከአንባሩ ጋር ወልቆ አጥንቱ ብቻ ነበር የሚታየው እና ልጅቷ ደንግጣ "ምን ሆነሽ ነው? እናቴ" ብትላት "የተጣደው ሥጋ ውሃ ጨርሶ ሲያር ውሃ ለመጨመር ሄጄ ነው እንደዚህ የሆንኩት።" ብላ አለች። ልጅቱም የተጣደውን ሥጋ አውርዳ ስታይ የእናትየው የእጇ ሥጋና አንባሩ እንዳለ ሥጋው ውስጥ አገኘችው ይባላል።

ኤፄሪ 35- ውሻና ቀበሮ

በድሮ ጊዜ አንድ ሰውዬ ጋር የምትኖር መልከመልካም ውሻ ነበረች። ቀበሮ ሁል ጊዜ ይህች ውሻ የሰውን ልጅ ሰገራ ስትልስ ታያት ነበር። የውሻዋ ይህ የዘወትር ድርጊት ያስገረማት ቀበሮ አንድ ቀን ወደ ውሻ ጠጋ ብላ "ወዳጄ ውሻ ሁል ጊዜ የሰውን ሰገራ ስትልሽ አይሻለሁ። ይህንን ለምን ታደርጊያለሽ?" ትላታለች። ውሺትም "ምን ላድርግ ብለሽ ነው! ይህንን የማደርገው ወድጀ ሳይሆን ከሰው ጋር እኖር ብዬ ነው። ይህንን ባላደርግ ኖሮ ምግብ አይሰጡኝም ነበር።" የሚል ምላሽ ትሰጣታለች። በውሻዋ ምላሽ የተገረመችው ቀበሮም መልሳ "ስሚ እኔ ግን ከሰው ጋር ለመኖር ብዬ ሰገራ አልስም።" ብላት ሄደች ይባላል።

ኤፄሪ 36- የአንበሳና የሸለምጥማጥ ችሎት

አንድ አንበሳና ሸለምጥማጥ አብረው ጦርነት ይሄዳሉ። ከጦርነቱ መልስ አንዲት ላምና አንድ በሬ ዘርፈው ይመለሳሉ። ከተመለሱም በኋላ ላሚቷን ለሸለምጥማጡ፣ በሬውን ደግሞ ለአንበሳው አድርገው ይካፈላሉ። ከዚያም የሸልምጥማጡ ላም ታረግዝና ትወልዳለች። ላሚቷ በምትወልድ ሰዓት ሸለምጥማጥ አልነበረምና አንበሳው ከላሚቷ ቂጥ ላይ ደም ወስዶ የራሱ በሬ ቂጥ ላይ ይቀባል። ከዚያም ሸለምጥማጥ ከሄደበት ሲመለስ አንበሳው "የኔ በሬ ወለደ" ይለዋል። ይህን ጊዜ ሸለምጥማጥ በልቡ "በሬ እንዴት ይወልዳል?" ብሎ ያስብና አንበሳውን "የአንተ ይሆን የኔ ላም የወለደችው እውነቱን ለማወቅ ሰዎች ይዳኙን?" የሚል ሀሳብ አቀረበ። ከዚያም ለሰዎች ጉዳዩ ተነግሯቸው በቀጠሮው ቀን ለመዳኘት

ቁጭ ብለው ሲጠብቁ ሽለምጥማጥ በሰዓቱ ሳይመጣ ይቀራል። አንበሳው "ለምን ቶሎ አትዳኙንም?" ብሎ ጥያቄ ያቀርባል። ለፍርድ የተቀመጡት ሰዎች "ባለጉዳዩና እኛንም የጠራን ሽለምጥማጥ ነው። እኛ እሱ ሳይመጣ እንዴት እንወያያለን?" ይሉታል። ይህን ጊዜ ያረፈደው ሽለምጥማጥ በዳኝነቱ ቦታ ይደርሳል። ህዝቡም "ምን ሆነህ ነው ይህን ያህል ሰዓት ያረፈድከው?" ብለው ይጠይቁታል። ሽለምጥማጥም "የቆየሁት ከባድ ችግር ገጥሞኝ ነው፤ ችግሬም እኔ ወደዚህ እየመጣሁ ሳለ መሬት ተሰንጥቃ ስለፋ ቆይቼ ስጨርስ እንደገና ሰማይ ተሰነጠቀ፣ አሁን ደግሞ ሰማዩን ሰፍቼ ጨረስኩ ብዬ ዞር ስል ወንዙ በእሳት ተያይዞ አየሁት" ይህን ጊዜ አንበሳው "እንዴ! ይህ ነገር እንዴት ነው? ከመቼ ጀምሮ ነው ውሃ በእሳት የሚያያዘው?" ብሎ ጠየቀ። ሽለምጥማጥም "ከመቼ ጀምሮ ነው በራስ መውለድ የጀመረው?" ሲል መልሶ ጥያቄ አቀረበ። ቅኔው የገባቸው ዳኞችም "ልክ ነው! በራ መውለድ አይችልምና ጥጃዋ ያንተ ናት።" ብለው ውሳኔ አስተላለፉ። አንበሳውንም "በነገሩ አታምንም?" ብለው ቢጠይቁት ምንም ሳያንገራግር በቀላሉ ውሳኔውን አምኖ ተቀበሎ ጥጃዋን ለሽለምጥማጡ መለሰ ይባላል።

ኤዔሪ 37- የኪሎ ወፍ ወራጅ ዉሀ ለምን አይጠጣም

ድሮ እግዚአብሄር እና ወፍ ፉክክር ያዙ። "እናንተ ወፎች ላባችሁ ያምራል ስለዚህ ለእኔ ስጡኝ?" ብሎ እግዚአብሄር ሲጠይቃቸዉ ሁሉም ሰብስበዉ ሰጡት። "ላባችሁን ሰብስባችሁ የሰጣችሁኝ የእኔ ናችሁና እኔ የፈጠርኩትን ውሃ ጠጡ።" አላቸዉ። አንድ ኪሎ የሚባል ወፍ "ኤድያ!! እግዚአብሄር እኔን አንዴ ፈጥረሃል ላባዬንም አልሰጥህም። ከፈለክ እኔን የፈጠርከዉን ዉሃ ከልክለኝ" አለዉ። እንደዚህ ከሆነ "እኔም የፈጠርኩትን ዉሃ አልሰጥህም ሂድ" ብሎ አባረረዉ። ኪሎዉም "እግዚአብሄር አንተ የፈጠርከዉ ወራጁን የወንዝ ዉሃ ነዉና እሱን አልጠጣም። ዉሃ በጠማኝ ጊዜ ወደ ላይ ኪል...ኪል... ብዬ ጮሀለሁ ዝናብም ሲመጣ የዝናብ ዉሃ ብቻ እጠጣለሁ።" አለዉ። ይህ ወፍ ወንዝ ወርዶ ዉሃ ዝቅ ብሎ አይጠጣም። ዝናብ በሚዘንብ ጊዜ አፉን ከፍቶ የዝናብ ዉሃ ብቻ ነዉ የሚጠጣዉ። እሱ ወፍ አሁንም ከዛፍ ላይ ይወጣና ክንፉን እያራገበና ወደ ሰማይ እያየ ይጮኻል። ዝናብም ይመጣል የዝናብ ዉሃ የጠጣል። በበጋ ወራት ዉሃ የሚባል ነገር አይቀምስም። እግዚአብሄር ድሮ "እኔን ላባህን ከልክለሀልና እኔ የፈጠርኩትን ወራጅ ዉሃ አትጠጣም።" ብሎት እስካሁን ድረስ የዝናብ ዉሃ እየጠጣ ይኖራል።

ኤዔሪ 38- ሲ በጠጢን ለምን አንድ ቦታ ትጥላለች

ድሮ በአባቶቻችን ጊዜ ዝሆንና ሲ (ጥንቸል የምታክል የዱር እንስሳ ናት) ነበሩ። ሲ ትንሽ ትንሽ በጣጥ የምትጥል ሲሆን የዝሆን እበት ግን በጣም ትልቅ ነበረ። አንድ ዕለት የሲ ልጅ በዝሆኑ እበት ተያዘች (ሰጠመች)። ሲም "አሃ ዝሆን እበቱን አጠራቅሞ ጥሎ የእኔን ልጅ አስያዘ አይደል ቆይ እኔም በጠጤን አጠራቅሜ የእሱን ልጅ በማስያዝ ብድሬን እመልሳለሁ ብላ ፉክክር ጀመረች። "ዝሆን ይህንን እበት ስንት አመት ጥሎ ነዉ ያጠራቀመዉ?" ብላ በመገረምም አሷም በጠጢን አጠራቅማ የዝሆኑን ለማሳከል አንድ ቦታ ላይ መጣል ጀመረች። ዛሬ በጠጢን ጥላ አጠራቅማ ስትሄድ ዝሆኑ ረግጦ ጨፍልቆት

ይሄዳል። "አይ ነገ ከነገወድያ ጥዬ አጠራቅማለሁ" ትልና እዚያዉ ቦታ ላይ ሄዳ ትጥላለች። ዝሆኑም ይረግጠዋል። እናም እስካሁን ድረስ "በጠጤን አጠራቅሜ የዝሆኑን ልጅ አንድ ቀን አስይዤ እገድላለሁ" ብላ እያሰበች ዛሬም ሲ አንድ ቦታ ላይ ነው በጠጧን የምትጥለዉ።

ኤዔሪ 39- የመኖ ወፍና ንብ

ድሮ ንብ ጫካ ውስጥ ካለ ዛፍ ግንድ ውስጥ መኖር ትጀምራለች። በቆይታም ግንዱ እጭ ይይዛል። እጩን በያዘ ጊዜ አንድ እለት ላይ አንድ ሰውዬ ንቧ ባለችበት ጫካ አከባቢ እየተጓዘ እያለ "መኖ" የምትባል ወፍ ሰውየውን በጩኸቷ እየመራች ንቧ ወዳለችበት ዛፍ ድረስ ይዛው መጥታ ዛፉን ታሳየዋለች። ሰውየውም ዛፉን ቆርጦ በመጣል እጩን ጥሎ ማሩን መብላት ይጀምራል። ወፏም እጩንና ሰውየው መጦ የጣለውን ሰፈፍ መብላት ትጀምራለች። ይህን ጊዜ ምን ቧ "አንቺ የኔን ልጆች ለምን ትበያለሽ?" ብላ ወፏን ስትጠይቃት ወፏም መልሳ "እንደዚህ ካልሸማ ከዛሬ ጀምሮ እድሜ ልክሽን ሰዎችን እየመራሁ እያመጣሁ ያንችን ልጅ አስበላለሁ" ብላ አለች። ከዝያን ጊዜ ጀምሮ ወፏ በጫካ ውስጥ ያለን ማር ለሰዎች መርታ እያሳየች ትኖራለች ይባላል። እናም በረሃማ በሆነ አከባቢ እና ደን ባለበት አከባቢ የሚኖሩ ወይም አዘውትረው የሚሄዱ ሰዎች ወፏንና የምታሰማውን ድምፅ ለይተው ስለሚያውቁ የወፏን ድምፅ ሲሰሙና እሷን ሲያዩ ተከትለዋት ይሄዳሉ። እናም "ቁዋ" ይባላል። የጫካ ማር ነው።

ኤዔሪ 40- ዝሆን ዉሃ ለምን ጭሮ ይጠጣል

አንድ ዝሆንና አንድ ትልቅ እንቁራሪት ነበሩ። በጋ በሆነ አንድ ወቅት ላይ እንቁራሪቱ በመንገድ ላይ ካለ ጉድጓድ ዉስጥ ተቀምጦ ነበር። ዝሆኑም ውሃ ፍለጋ በዚያ መንገድ ሲመጣ እንቁራሪቱን ይመለከተዋል። ከዝያም "ምነዉ መንገድ ላይ ቆመሃልሳ?" ብሎ ይጠይቀዋል። እንቁራሪቱም "እኔ መንገድ ላይ ብቆምስ አንተ ምን አስጨነቀህ?" ብሎ በትዕቢት መልስ ይሰጠዋል። ይህን ግዜ ዝሆኑም "ውሃ ፍለጋ እየሄድኩ ነዉና ውሃ በየት በኩል እንዳለ አይተህ እንደሆነ ልጠይቅህ ብዬ ነዉ?" ይለዋል። እንቁራሪቱም "እኔ ላንተ ውሃ ፈላጊ ነኝ እንዴ?" የሚል መልስ ሲሰጠዉ ዝሆኑ በጣም ስለተናደደ ይሰድበዋል። እንቁራሪቱም "ለምን ትሰድበኛለህ?" ብሎ ይጠይቃል። ዝሆንም "ሂድ! ምን ታመጣለህ?" በሚል መሰዳደብ ይጀምራሉ። ወዲያውም እንቁራሪቱ "ቆይ ለመሆኑ አንተ እኔን የምትሰድበኝ ትልቅ ስለሆንክ ነዉ?" ሲል ይጠይቃል። ዝሆኑም" ታድያስ! ከፊለክ ደግሞ ላይህ ላይ ልዉጣና ላሳይህ? "ብሎ በትእቢት ሲመጣ እንቁራሪቱም እልክ ስለያዘው አንገቱን መዞ ከጉድጓድ ዉስጥ ይወጣል። ይህን ጊዜ ዝሆኑ" ይህ አዉሬ መሬት ዉስጥ ሆኖ አንገቱ ብቻ ይህንን ካክለ ሙሉ አካሉን ቢያወጣማ ጨረሰኝ!" በማለት ሮጦ ይሄዳል። እንቁራሪቱም "አሁን ብትሮጥ ያመለጥክ መስሎሀል? አለቅህም!" ይለዋል። ከዚያ በኋላ ዝሆኑ መንገድ ቀይሮ በሌላ መንገድ በመሄድ ወንዝ አከባቢ ደረሰ። እንደደረሰ ወንዙ አጠገብ ዝናብ ዘንቦ የተጠራቀመ ውሃ ይመለከታል። ኩንቢውንም ከቶ መጠጣት ይጀምራል ነገር ግን መንገድ

ላይ ተጣልቶት የነበረው እንቁራሪት ዝሆኑ ሳያየው ኑሮ በሳን መጥቶ ውሀ ውስጥ ገብቶ እየጠበቀው ነበርና ቀስ ብሎ ወደ ኩንቢው ዉስጥ ይገባል። ከዚያ ዝሆኑ ኩንቢዉን ብድግ ሲያደርግ እንቁራሪቱ ኩንቢዉ ዉስጥ ሆኖ "እኔ እኮ ካንተ ጋር እዚህ ነኝ" ይለዋል። ዝሆኑም ደንግጦ ኩንቢዉን ብያወናጭፍ፣ ብያወናጭፍ ማስወጣት ያቅተዋል። ከዝያም ዝሆኑ ወደ ትልቅ ድንጋይ ተጠግቶ ኩንቢዉን ማጋጨት ጀመረ። ነገር ግን እንቁራሪቱን ሊያስወጣው ስላልቻለ እየደጋገመ በማጋጨቱ ኩንቢዉ ተበጣጥሶ ሞተ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ዝሆን አንድ ቦታ የተኛ (የረጋ) ውሃን አይጠጣም። ወራጅ ውሃ ወይም አሸዋ ቆፍሮ ነዉ ውሃ የሚጠጣዉ ይባላል።

ኤፄሪ 41- መብረቅ ብዙውን ጊዜ ገበሎ ያለበትን ድንጋይ ወይም ዛፍ ለምን ይመታል?

በድሮ ጊዜ መብረቅ አንድ በግ ይጠፋበትና ቆቅ አይታ እንደሆነ ለመጠየቅ ወደ ቆቅ ይሄዳል። ቆቅንም "አንቺ ቆቅ! አንድ በግ ጠፍቶብኝ ነበር እና አይተሽው ይሆን?" ብሎ ይጠይቃታል። ቆቋም "አቶ መብረቅ እኔ በግ የሚባል ነገር አላየሁም። ምናልባት ኮካ የሚባል ወፍ አለ፣ አፉም እግሩም ቀይ ሆኖ ደም የጠጣ ይመስላል፣ ምናልባት እሱ አይቶት ከሆነ ብትጠይቀው ጥሩ ነው። "ትለዋለች። መብረቁም ወደ ኮካ ሂዶ "አንተ ኮካ! እኔ በግ ጠፍቶብኝ ነበር እና አንተ ደግሞ አፍህ ደም የጠጣ ነው የሚመስለው እና አይተኸው ይሆን?" ብሎ ይጠይቀዋል። ወፉም "እኔ ይህ ተፈጥሮዬ ነው። ከፈለክ ናና ፍቀህ ተመልከት" ብሎ እያሳየው "ምናልባት ጅግራ ከሁለት ልጆቿ ጋር እንጨት ለቅማ ስትሄድ አይቻታለሁና እስቲ ጠይቃት" ብሎ ይልከዋል።

መብረቁም በኮካው ጥቆማ መሰረት ወደ ጅግራ ሂዶ "ጅግራ! እኔ በግ ጠፍቶብኝ ነበር፣ አንቺ ደግሞ ከልጆችሽ ጋር እንጨት ለቅመሽ ስትሄጂ ነበር አሉ። እና እንጨቱ ለምንድነው? በጌን አይተሽ ይሆን?" ብሎ ይጠይቃል። ጅግራም "አይ አቶ መብረቅ! የእኔ ጀርባ ከጥንት ጀምሮ እግዜር የፈጠረው እንጂ እንጨት አይደለም። ገበሎ ግን እዚያ ድንጋይ ላይ አንገቱን ሞራ ተቀብቶ ተኝቶ ነበር እስቲ ምናልባት እሱን ጠይቀው።" ትለዋለች።

መብረቅም ወደ ገበሎው ሂዶ "ገበሎ! እኔ በግ ጠፍቶብኝ ነበር እና አንተ አይተህ ይሆን? ካላየህ አንገትህን ከየት ተቀባህ?" ብሎ ይጠይቀዋል። ገበሎም በንዴት "ምን አገባህ? እኔ ያንተን በግ ጠባቂ ነኝ እንዴ?" ብሎ ዘሎ የተሰነጠቀው ድንጋይ ውስጥ ይገባል። መብረቁም ገበሎው የገባበትን ድንጋይ በንዴት ይመታዋል። እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መብረቅ የሚመታው ገበሎ ያለበትን ቦታ ነው ይባላል።

ኤፄሪ 42- የጫቂ /የቡዳ/ አመጣጥ

በድሮ ጊዜ የሰዉ ልጆች በምድር ላይ በዝተዉ ነበር። ከዚያም የተነሳ እርስ በርስ ጦርነት ጀመሩ። በጦርነቱም ብዙ ሰዎች በመሞታቸዉ አከባቢዉን እሬሳ ሞላዉ። አከባቢዉ በከፍተኛ ሁኔታ ሸተተ (ገማ)፣ ሽታዉም ከአከባቢዉ ርቀዉ ያሉትን አራዊቶች ጠራቸዉ። ከመጡት አራዊቶችም መሀል

ነብሮች ነበሩ። ነብሮችም የሞቱትን ሰዎች እራሳ በልተዉ ሲጨርሱ በህይወት ያሉትን መብላት ጀመሩ። ከጦርነቱ የተረፉ ጥቂት ሰዎችን ነብሮቹ እያሳደዱ ሲበሏቸዉ በአቅራቢያቸዉ ወደ ሚገኝ ተራራ ላይ ወጥተዉ በዋሻ ዉስጥ ተደብቀዉ መኖር ጀመሩ። እዚያም ሳሉ ሽኮኮ እያደኑ በመብላት ቀናትን ገፉ። እየቆዩ ስሄዱ ግን የሚበሉትን ነገር በማጣታቸዉ በከፍተኛ ሁኔታ ተራቡ። ከዋሻቸዉም እንዳይወጡ ነብርን ፈሩ። በዋሻቸዉ አቅራቢያ ያሉትን ሽኮኮዎች በልተዉ ጨረሱ። በመጨረሻም ምንም አማራጭ ስላልነበራቸዉ ህይወታቸዉን ለማቆየት ሲሉ አንዱ ሰዉ ሌላዉን ሰዉ መብላት ጀመረ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጫቂ /ቡዳ/ የሚል ስያሜ ተሰጣቸዉ።

ኤፄሪ 43- ዉሻ ከሰዉ ጋር እንዴት መኖር እንደጀመረ

በድሮ ጊዜ ዉሻና ተኩላ አንድ ላይ ይኖራሉ ይባላል። እናም አንድ ቀን ዉሻዉ ሲጮህ ተኩላዉ "አንተ ዉሻ እባክህን አትጩህ! አንተ ስትጮህ ከርከሮ ከሰማ እኛን መጥቶ ይጨርስናል።" ብሎ ይናግረዋል። ከዚያ ዉሻ ያንን ይሰማና "እንዴ ከተኩላም ለካ ከርከሮ በጣም ሃይለኛ አዉሬ እንደሆነ አሁን ተረዳሁ። ስለዚህ ከተኩላ ጋር አልኖርም ከከርከሮ ጋር ብኖር ይሻለኛል።" ይልና ወደ ከርከሮዎች ጋ ሄዶ አብሮ መኖር ይጀምራል። እዚያም ከርከሮ ጋር አብሮ እየኖረ እንደ ልማዱ ለሊት ለሊት መጮሁን ይጀምራል። ሲጮህ የሰማው ከርከሮም አንድ ቀን "እባክህን አንተ ዉሻ አትጩህ! እንተ የምትጮኸዉን ነብር ቢሰማ መጥቶ እኛን ይጨርሰናል። ስለዚህ እባክህ አትጩህ!" ይለዋል። ዉሻውም ይህን ይሰማና "እንዴ ከከርከሮም ለካ ነብር በሀይል ይበልጣል። ስለዚህ እኔ ከከርከሮ ጋር ከምኖር ከነብር ጋር ይሻለኛል "ብሎ ወደ ነብር ሄደ። ሄዶም ከነብር ጋር አብሮ ተስማምተዉ መኖር ይጀምራሉ። እየኖረም ላለ አንድ ቀን ሲመሽ ውሻው እንደልማዱ መጮህ ይጀምራል። ሲጮህ ነብሩ ይነሳና "እባክህን አንተ ዉሻ ለምን ትጮኃለህ? አንተ የምትጮኸዉን ድምጽ ሰዉ ቢሰማ መጥቶ እኛን ይገድለናል። ስለዚህ እባክህን አትጩኽ" ብሎ ይነግረዋል። ከዚያ በኋላ ዉሻም እንደገና "ከነብርም የሰዉ ሀይል ይበልጣል እንዴ? ሰዉ ለካ ከሁሉ የበላይ ነዉ! ስለዚህ እኔ ከነብር ጋርም አልኖርም ከሰዉ ጋር እኖራለሁ።" ብሎ ወደ ሰዉ ይሄዳል። ከሰዉ ጋርም አብሮ እየኖረ እንደልማዱ አሁንም ቀኑ ሲመሽ መጮኽ ይጀምራል። ጩኸቱን የሰማው ሰዉየዉም "አንተ ዉሻ ምን ፈልገህ ነዉ የምትጮኸዉ? ዝም በል! ዝም ባትል ግን እደበድብኃለሁ" ብሎ ይለዋል። ከዝያ በኋላ ዉሻ "አሃ! ከሁሉ ነገር የሚበልጥ ለካ ሰዉ ነዉ። ስለዚህ ከዚህ በኋላ እኔ ከሰዉ ጋር አብሬ እኖራለሁ እንጂ ከማንም ጋር አልኖርም።" ብሎ ከሰዉ ጋር መኖር ጀመረ ይባላል።

ኤፄሪ 44- የሸለምጥማጥ፣ የጉሬዛ፣ የዝንጀሮ፣ የጦጣና የጥንቸል እርሻ

ድሮ እነዚህ አምስቱ እንስሳት አብረው እየኖሩ ትልቅ እርሻ አርሰው ዳጉሳ ዘሩ። የዘሩትም ዳጉሳ ሲበስል "እንግዲህ ይሄን ዳጉሣ የምንጨምርበት ትልቅ ጎተራ እንስራ። ጎተራውንም ለመሥራት የቆቦ ባላ ሁላችን ቆርጠን ይዘን መምጣት አለበን።" ብለው ይስማማሉ። ተስማምተውም አብረው የቆቦ ባላ

ቆርጠው አምጥተው ጎተራውን ይሠራሉ። ሠርተው ከጨረሱ በኋላ ጎተራውን በዳጉሳ ሞልተው "እንግዲህ ሁላችን የዘር ጊዜ ሲመጣ አብረን መጥተን ይህን ጎተራ ከፍተን ለዘር የሚሆነንን ነገር ከዚህ እንወስዳለን።" ብለው ይመካከሩና በሩን በደንብ ዘግተው መርገው ይሄዳሉ። ብልጡ ሽለምጥማጥ ግን ከጎተራው ትንሽ ራቅ ብሎ ጉድጓድ ይቆፍርና ውስጥ ለውስጥ በቀጥታ የቆቦው ባላ ሥር ይደርሳል። ከዚያም የቆቦው ባላ ውስጡ ክፍት ስለሆነ ውስጥ ለውስጥ ወደ ጎተራው ገብቶ ያንን ዳጉሳ እየበላ ዓመቱን ሙሉ ውስጥ ይቀመጣል።

ዓመቱ አልቆ የዘር ጊዜው በመድረሱ ቀድሞ በገባበት ቀዳዳ ይወጣና ጓደኞቹን ይሰበስባል። ከዚያም ለጓደኞቹ "እንግዲህ ከኛ መሐከል ትልቁና ሃለቃችን የሆነችው ዝንጀሮ ናትና ዝንጀሮ ለኛ የጎተራውን በር ትክፈት። "ይላል ሽለምጥማጥ። ከዚያም ዝንጀሮዋ ወደ ጎተራው በመሄድ የጎተራውን በር ስትከፍት ያስቀመጡት ዳጉሳ ተበልቶ አልቆ ገለባው ብቻ ነው የቀረው። ምንም ፍሬ የለውም ነበር። በዚህን ጊዜ እርስ በርስ ጥርጣሬ ጀመሩ። ብልጡ ሽለምጥማጥ ይነሳና" እስቲ ሁላችንም ወደ ሰማይ እየተመለከትን አራችንን እንራ። ከዚያ ዳጉሳውን የበላው አካል ይታወቃል። "የሚል ሀሳብ ያቀርባል። ሁሉም ሀሳቡን ተቀብለው አራቸውን ወደ ሰማይ አንጋጠው ሲያሩ ዝንጀሮዋ እርጉዝ ነበረችና ሽለምጥማጡ ወደሷ ተጠግቶ በማራት የራሱ ዳጉሳ ያለበትን አር ከሷ አር ጋር ለውጦ ያስቀምጣል። ከዚያም እንዲፈተሽ በተመካከሩት መሠረት አራቸው ሲፈተሽ ዳጉሳው ያለበት የእርጉዟ ዝንጀሮ ሆኖ ይገኛል። በዚህን ጊዜ ሁሉም ተናደው ዝንጀሮዋን ደብድበው ይገሏታል።

ከዚያም "አሁን የዘር ጊዜ ነው የተመነጠረውን ማሳ ዝናብ ሣይመጣ አሁን ላይ ማቃጠል አለብን።" ብለው ይመካከሩና ይሄዳሉ። ከዚያ ብልጡ ሽለምጥማጥ ይነሳና "ጦጥና ጉሬዛ በባሕላችሁ መሠረት ማሳ ውስጥ ካለው ዛፍ ላይ ውጡና እሳቱን ጠብቁ፣ ጥንቸልም በባሕልሽ መሠረት መኖርያሽ ሣር ነውና ከማሳ ውስጥ ካለው ሣር ውስጥ ገብተሽ ጠብቂ፣ እኔም በአባቴ ባህል መሠረት መኖሪያዬ ጉድጓድ ውስጥ ነውና እዚያ ገብቼ እጠብቃለው። ከዚያ ማሳው ተቃጥሎ ሲያልቅ ከያለንበት ተሰባስበን አንዳንድ ነገሮችን እንሰራለን" ይላል። በዚህም ጊዜ ሌሎችም በሀሳቡ ተስማምተው ጦጣና ጉሬዛ እርሻ ውስጥ ካለው ዛፍ ላይ ይወጣሉ፣ ጥንቸልም እዚያው ከእርሻ ውስጥ ካለ ሣር ውስጥ ትገባለች። ሽለምጥማጥ እሳቱን አንስቶ የእርሻውን ዙሪያ ካያያዘ በኋላ ኩይሳው ላይ ካለ ጉድጓድ ውስጥ ይገባል። በእርሻው ዙሪያ የተቀጣጠለው እሳትም በሐይል በመንደዱ እርሻ ውስጥ ያሉት እነጦጦ፣ ጉሬዛና ጥንቸል ከእሳቱ መውጣት ስላልቻሉ እዚያው ተቃጥለው ሞቱ። ከዚያም ከጥቂት ሰዓት በኋላ ሽለምጥማጥ ከጉድጓዱ ወጥቶ ቢያይ ጓደኞቹ ሁሉ ተቃጥለው ሞተው ይመለከታል። ይህን ጊዜ ሽለምጥማጥ "ከዚህ በኃላ ምን ታመጣላችሁ! ዳጉሳችሁን በልቼ የጨረስኩት እኔ ነኝ።" ይልና ቀድሞ ሲበላ የተረፈውን ዳጉሳ ለመብላት ወደ ጎተራው ሄደ ይባላል።

ኤፄሪ 45- አንበሳና ሽለምጥማጥ

ነገሩ እንዲህ ነው፣ ድሮ ሽለምጥማጥ አንበሳ ጋር ከብት ያረቡ ነበር። ሽለምጥማጥም አንበሳን አራኮ /አጎቴ/ ብሎ ይጠራው ነበር። አንድ ቀን "አራኮ የኔና ያንተ እናቶቻችን እያስቸገሩን ነውና ደብድበን እገሚደላቸው" አለው። አንበሳውም "እውነት እንግደላቸው?" ብሎ ሲጠይቅ "አዎ!" አለው። አንበሳውም "እሺ! አንተም ያንተን እናት ደብድበህ ግደል፣ እኔም የኔን እናት ደብድቤ እገላለሁ።" ብሎት ቤት እንደደረሰ እናቱን ደብድቦ ገደለ። ሽለምጥማጡ ግን እናትዬውን እየደበደበ መሆኑን በማስመሰል "ኡ...ኡ...ኡ.... ገደለኝ.....ገደለኝ...." እያለች እንድትጮኽ ለእናቱ ነግሯት ቆዳ ሲደበድብ ቆየና እናቱን በቀፎ አድሮ ጎሾላ የሚባል ዛፍ ላይ ሰቀላት። እናቱን ደብድቦ የገደለ ለማስመሰልም ፍየል አርዶ ቦታው ላይ ደም አፈሰሰ። አንበሳው ግን የእውነት እናቱን ገድሎ ጫካ ጣላት። ጥቂት ቀን እንደቆዩ ሽለምጥማጥ "አራኮ እናቶቻችንን ገደልን። ድረቅም እኛ ጋ እየመጣ ነውና ከብቶችን ተነስና እንጠብቅ" አለው። አንበሳውም "አይ! አንተ ከብቶችን ይዘህ ሂድና ጠብቅ!" አለውና ከብቶችን ይዞ ሄደ። እናትየውም ማታ ማታ ከሾላው ዛፍ ላይ ፍሬ ለቅማ ትጠብቀው ነበር። ከብቶችን እየጠበቀ በዛፉ ሥር የሚያልፍ ያስመስልና ዛፉ አጠገብ ሲደርስ "እማዬ! ጣይልኝ፣ እማዬ! ጣይልኝ" ሲላት እሷ ፍሬውን ስትጥልለት ይበላ ነበር። ፍሬውንም በልቶ ጠግቦ ወደ አጎቱ ይመለሳል። አጎቱም "አንተ ሽለምጥማጥ ሆድህ በጣም ጠግቧል። ከብቶች ግን ወተት የላቸውም አንተ ምን በልተህ ነው ሆድህ የተነፋው?" ይለዋል። እሱም "አጎቴ ደግሞ ከብቶች ሣር ሲግጡ እኔም ስግጥ፣ ውሃ ሲጠጡ አብሬ ስጣጣ፣ አፈር ሲበሉ አብሬ ስበላ ስለዋልኩ ነው የጠገብኩት" አለው። አንበሳውም "እንዲህ ከሆነ ዛሬ እኔ ነኝ የምጠብቀው።" ብሎ ከብቶችን ይዞ ይሄዳል። ከብቶች ሣር ሲግጡ እሱም ለመጋጥ ሲሞክር፣ አፈር ሲበሉ እሱም ሲሞክር፣ አልሆንለት ብሎት ይውላል። ሽለምጥማጡ ግን እናቱ ጋ ሄዶ ተደብቆ በልቶ ይመጣ ነበር። አንድ ቀን አንበሳው "ነገሩን ማጣራት አለብኝ።" ብሎ ሽለምጥማጡን አስቀድሞ ቀስ ብሎ ኮኗላው ይከታተለው ጀመር። ይህን ጊዜ እናቱን "እናቴ! ጣይልኝ" ብሎ ጠይቆ ሲበላ አዬው። እሱ አመሻሹ ላይ ከብቶችን ለማስገባት ሲሄድ አንበሳው እንደሱ "እናቴ! ጣይልኝ" ብሎ የጣለችለትን በልቶ ከጠገበ በኋላ የሽለምጥማጡን እናት ገድሎ መጣ። ጠዋት ሽለምጥማጡ የእናቱን መሞት ያይና ከብቶችን ይዞ እንደ ተመለሰ ቁጭ ብሎ ያለቅሳል። አንበሳው ለምን እንደሚያለቅስ ደጋግሞ ቢጠይቀውም መልስ አልሰጥ ይላል።

በበነጋው ሽለምጥማጡ ከብቶችን ለጥበቃ ይዞ ሄዶ ጥላሸትና አመድ ቀላቅሎ ከብቶችን መቀባት ጀመረ። ግማሹን ጎሽ፣ ግማሹን የሜዳ አህያ፣ እያስመሰለ የተለያዩ እንስሳት አስመስሎ ቀባቸው። እንደጨረሰም ወደ ቤት ሮጦ ሄዶ "አራኮ! ያለውን የአራዊት አይነት ብታይ! ፍጠን" ብሎ ነግሮ ይዞት መጣ። ሽለምጥማጡ ሥጋ ልብላ ቢል አጎቱ እንደማይሰበላው ስላወቀ አሰበና "አራኮ አሁን እንዲህ አድርግ፣ እያንዳንዱን ለመለየት አትሞክር። እየለየሁ እገድላለው ስትል ያዩና ያመልጣሉ። ስለዚህ ሁሉን ግደላቸው" አለው። አንበሳው እንደተባለው እንዳይለዩት ብሎ ሁሉን በፍጥነት ገድሎ ጨረሳቸው።

ከዚያም ከገደላቸው መካከል አንዷን እንዲያይ ሲነግረው ላሙ ሆና አገኛት። ሽለምጥማጡም በፍጥነት ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ እየዘፈነ ነበር። አጎቱም "ከዚህ እንዴት ገባህ" ሲለው "ሁለት ጊዜ ከምታየው ትልቅ ድንጋይ ጋር በቂጥህ ስትጋጭ አንተም ትገባለህ" አለው። አንበሳውም እየተንደረደረ ሁለት ጊዜ ተጋጨ። እሱም ክራር እየደረደረ

የአጎቴ ቂጥ፣

የአጎቴ ቂጥ፣... እያለ ይዘፍን ነበር።

በመጨረሻም አንበሳው ከመጋጨቱ ብዛት ሞተ። እሱ ሁሉንም ሰብስቦ ወደ ጉድጓዱ አስገባ። ጅብም እሳት ለመጫር መጥታ ነበርና የአጥንት ስብርባሪ ሰጥቷት " አራኮ ከመጣ ይገድልሻልና ቶሎ ሂጂ!" ብሎ ሸኛት። የአጥንቱ ስብርባሪ የጣማት ጅብ ሁለተኛ ጊዜ መጣች። "አራኮ ካየሽ ይገድልሻል ብዬ እየነገርኩሽ?" ብሏት የአጥንት ስብርባሪ ሰጥቷት መጋጥ ስትጀምር ሳታየው ቀስ ብሎ የአጎቱን እራሳ ጭራ ከጅቧ ጭራ ጋር ያስራል። እንደጨረሰም "ስነግርሽ አልሰማ ብለሽ አጎቴ መጣ" አላት። ዞር ስትል ጭራውን በመመልከቷ በድንጋጤ መሮጥ ጀመረች። ሮጣ፣ ሮጣ ዞር ስትል አሁንም ይከተላት ነበር። በዚህ መልኩ በድንጋጤ ስትሮጥ ገደል ገብታ እሷም ሞተች። በብልጠቱ ሽለምጥማጥ ሁሉን ነገር የራሱ አደረገ።

ኤፄሪ 46- ሁለቱ ሴት ልጆች

ድሮ ሁለት ሚስቶች ያሉት አንድ ሰው ነበር። አንደኛዋ ሚስቱ ሁለት ሴቶች ልጆች ሲኖሯት አንደኛዋ ሚስቱ ግን አንድ ልጅ ብቻ ነበራት። የሁለቱ ሴቶች ልጆች እናት የሆነችው አንደኛዋ ሚስቱ ሞተች። አንድ ልጅ ብቻ የነበራት ሚስቱ ደግሞ እነዚህን ሴቶች ልጆች አትወዳቸውም ነበር። አንድ ቀን እናታቸው የሞተችባቸው ሴቶች ልጆች ዲሞክ የሚባል የዛፍ ቅጠል ቀቅለው የሴትዬዋን አንድ ልጅ ያበሉታል። የሴትዬዋም አንድ ልጅ ይሞታል። በዚህ መክንያትም ሴትዬዋ ልጆቹን ጭራሽ ትጠላቸዋለች። ዘወትር አባታቸው እያለ ትደበድባቸው ታሰቃያቸውም ነበር። ይህንን መንገላታታቸውን የተመለከተው አባትም አንድ ቀን "አይኔ እያዬ ልጆቼ እንዲህ ከሚሰቃዩ ሩቅ አገር ወስጄ አስቀምጣቸዋለሁ።" ይልና የልጆቹን ልብስ፣ ለቀለብ ሚሆናቸውን ዱቄት፣ የተዘጋጀ ምግብና ልጆቹን ይዞ ሩቅ ሀገር ይሄዳል።

እየተጓዙም እያለ ቀኑ መሽቶባቸው ዛፎች ባሉበት ጫካ ውስጥ ገብተው ይተኛሉ። አባትየው ልጆቹን በቀኝና በግራ አድርጎ እሱ መሃል ላይ ይተኛል። ለሊት ላይ የልጆቹ አባት ልጆቹ ሳይነቁ ከመሃላቸው ቀስ ብሎ ተነስቶ በምትኩ የዛፍ ግንድ አጋድሞ ትቷቸው ጠፍቶ ወደ ቤቱ ይመለሳል። እሱ እንደሄደም ትንሽ ቆይቶ ጅብ ሲጮህ ትንሽዋ ትነቃና አባቷ ወዳለበት ብትዳብስ አባቷ እንዳታለላቸው ትረዳለች። ይህን ጊዜ ከታላቋ ይልቅ ብልጥ ነበረችና ታላቋን ቀስቅሳ አባታቸው እንደሌለ ትነግራታልች። ቀኑ

እስኪነጋ ድረስም ወደ ራሷ አስጠግታ ታስቀምጣታለች። ቀኑ ሲነጋም በአካባቢያቸው ቅርብ ርቀት ላይ ወዳለ ተራራ ላይ ይወጣሉ። ተራራው ላይም ዋሻ አግኝተው ገብተው ይቀመጣሉ። በዋሻው ውስጥም ጥቂት እንደቆዩ ውስጡ የአንበሳ ልጅ እንዳለ ይመለከታሉ። ትንሽ ቆይቶም የትንሹ አንበሳ እናትና አባት እደን ሄደው ከነበሩበት አጋዘን ገድለው ሲመለሱ ሴቷ አንበሳ በዋሻው ውስጥ ሰዎች እንዳሉ ትመለከታለች። ወደ ባሏም ዘወር ብላ ሰዎቹ ልጇን ለመግደል የመጡ እንደሆነ በቁጣ ትነግረዋለች።

ወንዱ አንበሳም ልጆቹን ተመለክቶ እንዳትነካቸው እንቢ ብትል ግን እሱም የሷን ልጅ እንደሚገድልባት ነግሮ ያስጠነቅቃታል። ከዚያም ካመጡት የአጋዘን ስጋ አንድ እግር ለልጆቹ ይሰጧቸዋል። ልጆቹም ስጋውን ተቀብለው ከዋሻው ራቅ ወዳለ ቦታ ይሄዳሉ። እዚያም ስጋውን እየበሉ ሲኖሩ ከተራራው በታች ካለ ሜዳ ላይ የደረሰ ሰብል ይመለከታሉ። ትንሽ ቆይቶም የእሳት ጭስ ይመለከቱና በአካባቢው ሰው አንዳለ ይነጋገራሉ።

ታናሽዬውም ብልጥ ስለሆነች ታላቅዬውን እዚሁ ያሉበት እንድትቀመጥና እሷ ቀስ ብላ ሄዳ ልታጣራ ፈለገች። ቀስ ብላም ዱካ ሳታሰማ ውደቤቱ አጠገብ እንደ ደረሰች ቤቱ የጭራቅ ቤት መሆኑን አረጋገጠች። እና ወደ ቤቱ ስትመለከት በራፉ ላይ አንድ አህያ ታስሮና ቤቱ ባዶ ሁኖ ትመለከታለች። ከዚያም ለአህያው ሰርዶ አጭዳ ሰጥታው በቀጥታ ወደቤቱ ውስጥ ትገባለች። ውስጥ ያገኘችውን ወተት፣ የተዘጋጀ ምግብ፣ እና ቅቤ ገልብጣ ይዛ ወደ እህቷ ትመለሳለች። ከእህቷ ጋርም ያንን ምግብ ለተወሰነ ቀን በልተው እንደጨረሱ ታላቅዬው "ዛሬ እኔ ነኝ ሂጄ ከጭራቁ ቤት ምግብ ይገፍ የምመጣው" ብላ ትነሳለች። ይህን ጊዜ ታናሽየው የጭራቁ ቤት ውስጥ ዝም ብላ እንዳትገባ፣ እንደደረሰች በራፉ ላይ አንድ አህያ ታስሮ እንደምታገኝና ለአህያውም የተወሰነ ሰርዶ አጭዳ መስጠት እንዳለባት፣ ከዚያ ወደ ቤት ውስጥ መግባት እንዳለባት ትነግራታለች። ታላቅዬው እህቷ ያለቻትን ነገር ሰምታ ወደ ጭራቁ ቤት ትሄዳለች። እንደደረሰችም ግቢው ውስጥ በያይነቱ የበሰሉ የዛፍ ፍሬዎችን ትመለከታለች። እነዚህንም እየተመለከተች እህቷ ያስጠነቀቀቻትን እረስታ ለአህያው ሳትሰጥ ዝም ብላ ወደ ቤት ውስጥ ትገባለች። ገና ወደ ውስጥ ከመግባቷ በራፉ ላይ ታስሮ የነበረው አህያ ይጮሃል።

ጭራቁ ከብቶቹን በጠዋት ሊያሰማራ ወደ ጫካ ሂዶ ነበርና የአህያውን ጩኸት እንደሰማ በፍጥነት ወደቤቱ ይመለሳል። ቤቱ እንደደረሰም "ማን ነው እዚህ ያለው?" ብሎ ጠየቀ። ይህን ጊዜ ቤት ውስጥ የነበረችው ሴቷ ልጅ በሩጫ ወጥታ ማምለጥ ስለማትችል በፍጥነት እቤቱ ውስጥ ያገኘችው ትልቅ እንስራ ውስጥ ገብታ ትደበቃለች። ጭራቁም ወደ ቤቱ ውስጥ ገቡቶ ሲፈልጋት እንስራ ውስጥ ተደብቃ እንዳለች ያገኛታል። "እቺማ አሪፍ ናት" ብሎ የእንስራውን አፍ ግጥም አድርጎ አስሮ ምድጃ ላይ ጥዷት እንጨት ሊያመጣ መጥረቢያ ይዞ ይሄዳል። ታናሽዬውም እህቷን ካሁን አሁን ትመጣለች ብላ ብትጠብቅ ስትቆይባት "እህቴ ምን ሁና ይሆን? ተበላች ወይ?" ብላ ተነስታ ወደ ጭራቁ ቤት ትሔዳለች። እንደደረሰችም ጭረቁ አለመኖሩን አረጋግጣ ለአህያው ሳር አጭዳ ትሰጥና ወደ ቤቱ ውስጥ

ትገባለች። እህቷንም ፊልጋ ብታጣት ትጣራለች። ይህን ጊዜም እህትዬው እንስራው ውስጥ ሁና "አቤት!" ስትላት ከእንስራው እህቷን አውጥታ በምትኩ ድንጋይ ሰብስባ እንስራው ውስጥ ጨምራ እህቷን ይዛ ወደ ሚኖሩበት ትመለሳለች። ጭራቁ ከሄደበት ቆርጦ ያመጣውን እንጨት ምድጃ ላይ ጥዶት በሄደው እንስራ ስር አንድዶ እየዘፈነ ከጎኑ ቁጭ አለ። እሳቱም ሲነድበት እንስራው ውስጥ የነበረው ድንጋይ መፈንዳት ጀመረ። አንዱ ሲፈነዳ "አይኗ ፈነዳ" ሌላ ሲደግም "ልቧ ፈነዳ" እያለ ሲደሰት ቆይቶ አንደኛው ድንጋይ ሲፈነዳ እንስራውን ሰብሮ ልቡን ብሎ ይገድለዋል።

ሁለቱ ሴቶች ተደብቀው ከሚኖሩበት ቦታ ላይ ሁነው ሲመለከቱ በሁለተኛውና በሶስተኛው ቀን በጭራቁ ቤት አጠገብ ላይ በነበረው የደረሰ ሰብል ወፎች እንደልብ ሲያርፉበትና ሲነሱ፣ ላሞች ያለማቋረጥ ሲጮሁ ይመለከቱና ጭራቁ መሞቱን ተጠራጥረው ቀሥ እያሉ ወደ ቤቱ ይጠጋሉ። ተደብቀውም ቤቱ ውስጥ ሲመለከቱ ብዛት ያላቸው ዝንቦችን ሲርመሰመሱ ይመለከታሉ። ከዚያ መሞቱን አረጋግጠው ወደ ቤቱ ውስጥ ይገቡና የጭራቁን ሬሳ ጎትተው አውጥተው ወደ ገደል ጥለው የጭራቁን ከብቶች ሁሉ የራሳቸው አድርገው መኖር ይጀምራሉ።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ከብት ሊለውጡ የፈለጉ ሁለት ወንዶች እነሱ ወዳሉበት ቤት ይመጣሉ። ሴቶቹም ተቀብለዋቸው ካስተናገዷቸው በኋላ የመጡበትን ጠይቀዋቸው ሲረዱ እነሱን አግብተው እዚሁ እንዲኖሩ ይጠይቋቸዋል። ወንዶቹም ሃሳባቸውን ተቀብለዋቸው ሴቶቹን አግብተውና ሃብታቸውን በጋራ እየተጠቀሙ መኖር ይጀምራሉ። እየኖሩም ሳለ የልጆቹ አባት ልጆቹ በህይወት መኖራቸውን አጠያይቆ እንዳወቀ ያሉበት ቦታ ድረስ አፈላልጎ ይመጣል። ሴቶቹም አባታቸውን በሰላም ተቀብለው ለአስር ቀናት ያህል በእንክብካቤ ካስተናገዱት በኋላ በአስራ አንደኛው ቀን አውጥተውት ሰው የሚበላ አውሬ ጠርተው አስበሉት ይባላል።

ኤፄሪ 47- የውሻና የጅብ ንግግር

ውሻ አንድ ዕለት በሰፈር ውስጥ ሲዞር አንድ ሰው ያገኘውና በድንጋይ ይመታዋል። ይህን ጊዜ ውሻው ይጮኃል። የውሻውን ጩኸት የሰማው ጅብም ወደ ውሻው ለመድረስ እየሮጠ ሲመጣ ከውሻው ጋር መንገድ ላይ ይገናኛሉ። በዚህን ጊዜ ጅቡ ውሻውን "ቅድም ምን ሆነህ ነው ስትጮኽ የሰማውህ?" ብሎ ይጠይቀዋል። ውሻው ሲመልስም "አንድም አይነት አውሬ በመንገድ ላይ እንዳይገኝ ተብሎ ነው።" ብሎ መልሰ ሰጠው ይባላል።

ኤፄሪ 48- የመሲናዋ ፍየል ሌቦች

አንዲት መሲና የሆነች ፍየል የነበረችው ሰው ነበር። የሰውየው መሲና ፍየል ዘወትር የምትተኛው ከሰውየው መኖርያ ቤት በረንዳ ላይ ነው። እናም ጠግባ ስትተኛ ሁል ጊዜም "እ! እ! እ!" የሚል ድምጽ ታሰማለች። ታዲያ አንድ ቀን እቺን መሲና ፍዬል ለመስረቅ ሁለት ሌቦች ወደ ሰውዬው ቤት ይመጡና

እንደኛው ሌባ ጓደኛውን "አንተ ሂድና የሰውዬው በራፍ ላይ ተኝተህ እንደ ፍየሏ እ! እ! እ! በል። እኔ ቀስ ብዬ ፍየሏን ይዤ እወጣለሁ" ይለዋል።

እንደተመካከሩት አንደኛው ሌባ የሰውየው በራፍ ላይ ተኝቶ "እ! እንደ ፍየሏ"፣ "እ! እንደ ፍየሏ"፣ "እ! እንደ ፍየሏ" እያለ ተኝቶ ሳለ ጓደኛው ፍየሏን ይዞ ይወጣል። ነገር ግን የፍየሏ ባለቤት ያልተለመደ ድምጽ ሰምቶ ይነቃና "እንዴ ይሄ ነገር ምንድ ነው? እ! እንደ ፍየሏ እያለ የሚል?" ብሎ ከቤቱ ወጥቶ ቢመለከት በራፉ ላይ ጥቅልል ብሎ የተኛ ሰው ይመለከትና እንዳያመልጠው ዘሎ የሰውየውን ወገብ ጥርቅም አድርጎ ይይዘዋል። ወገቡን የተያዘው ሌባም ጓደኛውን ጠርቶ "ተያዝኩ!" ይለዋል። ጓደኛውም መልሶ "ምንህን ነው የያዘው?" ሲለው ጓደኛውም "ወገቤን ነው! ወገቤን ነው!" ብሎ ይመልሳል። ጓደኛውም መልሶ "ወገብህን ከያዘ ግድ የለም ታመልጣለህ። ይልቅስ ጣቱን በምራቅ አድርጎ አፍንጫህን እንዳይዝ ከልክለው! አፍንጫህን ከልክለው!" ብሎ ሲለው የፍየሏ ባለቤት እውነት መስሎት እጁ ላይ ምራቅ ተፍቶ የሌባውን አፍንጫ ቢይዘው ሌባው አምልጦት ሮጠ ይባላል።

ኤዬሪ 49- አዳኙን የበላችው ጭራቅ (አንድ)

በድሮ ጊዜ ሁለት አዳኝ ሰዎች ነበሩ። ከዕለታት አንድ ቀን አውሬ ለመግደለ ወደ ጫካ ሄደው ሲመካከሩ አንደኛው "ጓደኛዬ አንተ በዚህ በኩል ሂድ! እኔ በእዚኛው እሄዳለው። በሄድክበት አጋጥሞህ አውሬ ከገደልክ ለእኔም ልክ ትስጠኝ። እኔም ደግሞ እንደ አጋጣሚ ከገደልኩ ምልክት አሰጥሀለሁ" ብሎ ይናገራል። ከዚያም በዚህ ተስማምተው ተለያይተው በተለያየ አቅጣጫ ስሄዱ አንደኛው ጥቂት እንደ ተጓዘ ጭራቅ ታገኘውና ከነቀስቱ ትውጠዋለች። አንደኛው ግን አደኑን ቀጥሎ እያለ ዲፊር ሳያገኝና ይገድላል። ቅድም ከጓደኛው ጋር ሲለያዩ በተስማሙት ምክር መሠረት ምልክት ይሰጣል። ጓደኛውን የበላችሁ ጭራቅ "አቤት!" እያለች ወደሱ ትመጣ ጀመር። እሱም ይጣራል። እሷም "አቤት!" እያለች ወደሱ ትቀርባለች። አሁንም ደግሞ ምልክት ሲያደርግ ጭራቋ "አቤት!" ብላ ከኋላው ብቅ ትላለች። አዳኙም "እኔ ጓደኛዬን የጠራሁ መስሎኝ ለካስ የጠራሁት ሌላ ነገር ነው" ብሎ ይደነግጣል። በዚህን ጊዜ ጭራቋ ወደሱ ትጠጋለች። አዷኙም "ነይ ወደ እኔ ተጠጊና ይህን አውሬ አርደን አብረን እንብላ። "ብሎ በያዘው ቢላዋ አውሬውን ሲገፍ እሷ በእጇ ብቻ የአውሬውን እግሮች በቀላሉ መገነጣጠል ጀመረች። በተመለከተው ነገር አዳኙ በጣም ይደነግጣል። ቀጥሎም ሥጋውን ጠብሶ ለመብላት እሳት ሊያቀጣጥል ሲዘጋጅ ጭራቋ "አንተ ምን ልታደርግ ነው?" ብላ ጠየቀችው። አዳኙም "እኔ እሳት አቀጣጥዬ ሥጋውን ጠብሼ ልበላ ፈልጌ ነው" ይላታል። ጭራቋም "ሣሮችንና እንጨቶችን አንድ ላይ ሰብስበህ አድርግ!" ትለዋለች። እሱም በታዘዘው መሠረት ገና እንጨቱን ሲሰበስብ ጭራቋ "አህ!" ብላ ከአፏ እሳት በማውጣት እሳቱን አቀጣጠለች። እሱ ደረቅ እንጨት እየሰበሰበ ሲጨምር ገና ያልደረቀውን ጭስ ጭስ የሚለውን ስጋ እያነሳች መብላትና መዋጥ፣ መብላትና መዋጥ ጀመረች።

አዳኙም ለራሱ ትንሽ ስጋ ወስዶ በደረቁ ጠብሶ ለመብላት ገና እየጠበሰ እያለ እሷ ጠግባ ኖሮ አለፍ ብሎ ካለ ዛፍ ስር ሂዳ ቁጭ ብላ ታንቀላፋለች። አዳኙም ስጋውን ጠብሶ ከጨረሰ በኋላ ወደ እሷ ቀርቦ "እንብላ" ይላታል። ጭራቋም "እኔ በቃኝ ጠግቤአለሁ! አንተ ብላ" ትለዋለች። አዳኙም ስጋውን በልቶ እንደጨረሰ ለጭራቋ ጥያቄ ያቀርብላታል። "ከዚህ በኋላ እኔ ምንድን ነው የሚሻለኝ? ምን ማድረግ አለብኝ?" ይላታል። ጭራቋም "አንተ ከዚህ ሩቅ ወዳለ ተራራ ሂድና ተራራው ላይ ወጥተህ ወደኋላ ስትመለስ አዋራ እያነሳ የሚመጣ አውሎ ንፋስ ካየህ እኔ ነኝ።" ትለዋለች። አዳኙም ከእሷ ተለይቶ እየሮጠ ሲሄድ አንድ ወንዝ ያገኛል። እንደ ደረሰም ውሃውን ጭሮ ከጠጣ በኋላ "ይህች ጓደኛዬን የበላች ጭራቅ ከዚህ በኋላ እኔንም ካገኘች አትምረኝምና ነፍሴን ላትርፍ።" ብሎ ከወንዙ አጠገብ ካለ ትልቅ ሾላ ዛፍ ላይ ቀስቱን እንደያዘ ጫፍ ድረስ ይወጣና ይቀመጣል። ከዚያ ጭራቋ እየሮጠች ተከትላው መጥታ ወንዙ አጠገብ ስትደርስ ዝቅ ብላ ዱካውን ታያለች። ወደ የትኛው አቅጣጫ እንደሄደ ለማወቅ ብትፈልግ ዱካው የጠፋባታል። ከዝያ ተስፋ ቆርጣ ውሃ ልትጠጣ ዝቅ ስትል በውሃው ውስጥ ከዛፍ ጫፍ ላይ የተቀመጠ ሰው ሰል ታያለች። ቀና ብላ ስታይ አዳኙን ከሾላው ዛፍ ጫፍ ተቀምጦ ትመለከታለች። በሁኔታው ተናዳ የዛፉን ቅርንጫፎች እየገነጠለች ወደ ላይ ለመውጣት ስትሞክር አለሆንላት ይላል። አዳኙም ተስፋ ቆርጦ በያዘው ቀስት እየደጋገመ ይመታት ነበር። በመጨረሻ ላይ ግን አንድ ቀስት ብቻ በእጁ ላይ ስለቀረ በቀረችው አንድ ቀስት እንደ ምንም ብሎ ዓይኗ ላይ አነጣጥሮ ይመታትና ትወድቃለች። እንደ ወደቀችም "እኔ ቶሎ አልሞትምና ሞታለች ብለህ ከዛፉ ላይ ቶሎ እንዳትወርድ፤ የኔን መሞት የምታረጋግጠው ከትንሽ ቆይታ በኋላ ቁራዎች መጥተው ዓይኔን ከበሉ፣ በቂጤና በአፌ አከባቢ ዝንቦች መጥተዉ ከተቀመጡ፣ እኔ በትክክል ሞቻለውና ወርደህ ሆዴን ቀደህ ተመልከት።" ብላ ትናገራለች። ቆይቶ ጭራቋ እንዳለችው ቁራዎች "ቋ....ቋ...ቋ..." እያሉ መጥተው አይኗን አውጥተው በሉ። ዝንቦችም "ቦም...ቦም...ቦም..." እያሉ መጥተው በአፍና ቂጧ ላይ አረፉ። ይህን ጊዜ አዳኙ ከነበረበት ዛፍ ወርዶ እንደታዘዘው የጭራቋን ሆድ ቀዶ ሲመለከት ድሮ የበላቻት ሴት ልጅ፣ ለአደን ወጥተው እያለ የጠፋው ጓደኛው ከነቀስቱና ሌሎችም ብዙ ነገሮች ተመልክቶ ሲጨርስ ቆዳዋን ገፈፈና ወደ ሰፈሩ ወሰደ። ሲደርስም የሰፈሩን ሰዎች ጠርቶ "እስኪ ኑና እኔ የገደልኩትን አውሬ ተመልከቱ! እናም ምን እንደሆነ ንገሩኝ?" ብሎ ሰዎችን ጠርቶ አሳየ ይባላል።

ሌሬ 50- አዳኙን የበላችው ጭራቅ (ሁለት)

በድሮ ጊዜ ሁለት ሰዎች ለአደን ጫካ ይሄዳሉ። በሄዱበትም አንደኛው ጭራቅ ይገድልና አርዶ ቆዳውን ገፎ ይዞ ይመጣል። በግቢው ውስጥም ቆዳው እንዲደርቅ ወጥሮ ፀሐይ ላይ ያደርገዋል። ሰውዬው ላራት ልጆች አሉት። እና ልጆቹ በተወጠረው ቆዳ ላይ ቁጭ ሲሉ ቆዳው ከነልጆቹ ወደላይ ብድግ ይልና ልጆቹን "ወደ ሰማይ ይዣችሁ እሄዳለሁ" እያለ ይላቸው ነበር። ልጆቹም ወደ አባታቸው ሄደው ይነግሩታል አባታቸውም በሉ ንቀሉና አምጡት ይላቸዋል። ልጆቹም እንደታዘዙት የጭራቁን ቆዳ ለማምጣት በላዩ ላይ ወጥተው እንጨቱን እየነቀሉ እያለ ቆዳው ብድግ ብሎ አራቱንም ልጆች እንደያዘ

ወደ ሰማይ ሄደ። ብዙ ርቀት ወደላይ ይሏቸው ከሄደ በኋላ ልጆቹን የት ቦታ ላይ ቢጥላቸው እንደሚፈልጉ ለእያንዳንዳቸው ጥያቄ ያቀርብላቸዋል። ከልጆቹም አንደኛው "የአባቴ ቤት ጣርያ ላይ ጣለኝ " ይላል። ሌላኛው ደግሞ "የአባቴ ከላድማው በሬ ላይ ጣለኝ" ሲል ሦስተኛው ልጅ ደግሞ "የአባቴ በር ላይ ጣለኝ" ይላል። የመጨረሻውና አራተኛው ልጅ ደግሞ "ገደል ውስጥ ጣለኝ" ሲል የፈለገውን ቦታ ይገልፃል። የጭራቁ ቆዳም ልጆቹን እንደየፍላጎታቸው ባሉበት ቦታ ይጥላቸዋል። ሶስቱ ልጆች ወደ አባታቸው ቤት ወድያው ሲደርሱ አንደኛው ወደገደል የተጣለው አንደኛው ልጅ ግን ከገደሉ ውስጥ መውጣት ባለመቻሉ እዝያው እንዳለ አንድ ቁራ ይመጣል። ልጁም ለአባቱ ሂዶ እሱ ገደል ውስጥ መኖሩን እንዲነግረው ይልከዋል። ቁራዉም ወደ ልጁ አባት ሂዶ አንድ ልጁ ገደል ውስጥ እንዳለ ይናገራል። የልጁ አባት ግን ቁራውን ያባርረዋል። ቁራውም ወደ ልጁ ተመልሶ አባትዬው እንዳባረረው ይነግረዋል። ትንሽ ቆይቶም አንድ በግ ከገደሉ አፍ ላይ ያለን ማጋዶ (ጨው አፈር) ለመላስ ይመጣል። ከጉድጓዱ አፍ ተጠግቶ አፈሩን እየላሰ እያለ ልጁ እንደምንም ብሎ እግሩን ይዞ ያወርደውና አርዶ ስጋውን ዘልዝሎ እየተመገበ መዋል ይጀምራል። ከአንድ ቀን በኋላም የበጉን ስጋ የተመለከተ አንድ ጉራዛ ወደ ልጁ ይመጣል። ከስጋው ጮማ ላይም ትንሽ ቆርጦ እንዲሰጠው ይለምነዋል። ልጁም የጠየቀውን ጮማ እንደሚሰጠው ነገር ግን በቅድምያ የእሱን ገደል ውስጥ መሆን ለአባቱ ቤት ድረስ ሂዶ እንዲነግርለት ትእዛዝ ይሰጠዋል። ጉራዛውም ትእዛዙን ተቀብሎ ወደ ልጁ አባት ቤት ሂዶ ሁኔታውን ቢናገር እሱም እንደቀደመው ቁራ ተባሮ ይመለሳል። ከሱ በኋላ ደግሞ ጭልፊት ይመጣል። ጭልፊቱም እንደሌሎቹ ተልኮ የልጁን ገደል ውስጥ መኖር ለአባትዬው ሊነግር በመሄድ እሱም በድንጋይ ተባሮ እንደመጣ ይነግረዋል። ይህን ጊዜ ልጁ ወደአባቱ መልዕክት መላኩ እንደማያዋጣው በማመን ያገኘንና ጭልፊቱን ሊያወጣው እንደሚችል ይጠይቀዋል። ጭልፊቱም ፈቃደኛ በመሆን ልጁን ከገደሉ ውስጥ ጎትቶ ካወጣ በኋላ መርቶ ወደ አባቱ ቤት በማድረስ ለአባቱ አስረከበው ይባላል።

ኤዄሪ 51- የራሱን ሀገር ትቶ ወደ ሰው ሀገር የሄደ ሰው ታሪክ

አንድ ሰው ነበር። ይህም ሰውዬ በሀገሩ ያሉ ሰዎች እየታመሙ ሲሞቱ፣ እየታመሙ ሲሞቱ በተደጋጋሚ ሲመለከት አንድ ቀን "ሰዎች ወደ ማይታመሙበትና ወደ ማይሞቱበት ሀገር እሄዳለው።" ብሎ ተወልዶ ያደገበትን የትውልድ ሀገር ትቶ ወደ ሌላ ሀገር ይሄዳል። በሄደበት ሀገር ደግሞ ሰዎች ታመው ሲሞቱ ጭራሽ አይቀበሩም። ሬሳውን ጎትተው ሜዳ ላይ ይጥሉታል። ይህንን ሲመለከት "ወይኔ በእኛ ሀገር ሰው ሲሞት ሰዎች ተሰብስበው ወስደው በክብር ይቀብሩታል። ከዚህ ሀገርስ የራሴ ሀገር ይሻለኛል።" ብሎ አሰበ ይባላል።

ኤዔሪ 52- ሁለቱ ሌቦች

በድሮ ጊዜ አንድ ሰውዬ ፍዬልና ማር ተሸክሞ ወደ ገበያ ሲሄድ ሁለት ሌቦች በመንገድ ያዩታል። እነዚህ ሁለት ሰዎች ይመካከሩና አንደኛው ወደ ጫካ ገብቶ ቁጭ ሲል ሌላኛው አይነ-ስውር መስሎ በመንገድ ዳር ቁጭ ይላል። መንገደኛው ማሩንና ፍዬሉን እንደያዘ ወደ አይነ-ስውሩ ጠጋ ብሎ "አንተ ሰውዬ! እዚህ መንገድ ዳር ምን ትሠራለህ?" ብሎ ይጠይቀዋል። አይነ-ስውር መስሎ የተቀመጠው ሌባም "እኔ አይኔ ስለማያይ ወደ ገበያ መሄድ ፈልጌ የሚመራኝ ሰው አጥቼ ነው።" ብሎ ይመልሳል። መንገደኛውም "ታዲያ እኔ በአንድ እጄ ፍዬል እየጎተትኩ፣ በሌላው ማር ተሸክሜ እየሄድኩ ነው፤ እና እንዴት ልረዳህ እችላለው?" ይለዋል። አይነ-ስውር የመሰለው ሌባም "ጥሩ! እንዲህ ከሆነ ፍዬሉን የእኔ አንድ እጅ ላይ እሠር ። ቀጥሎ ያ ለውን ገ መድም አንተ ያገና እንጓዝ" ይለዋል። ሰውየውም እንደተመከረው የሰውዬውን ሀሳብ ተቀብሎ የፍዬሉን ገመድ በአይነ ስውሩ ሰው እጅ ላይ አሥሮ፤ ጫፉን ደግሞ እሱ ራሱ ይዞ ጉዞ ይጀምራሉ። በጫካ ውስጥ ተደብቆ የነበረው ሌባም ይወጣና ቀስ ብሎ አይነ-ስውር መስሎ ፍዬሉን ከያዘው ሌባ እጅ ፍዬሉን ፈቶ ወደ ጫካው ይዞት ይገባል። ከዚያ ትንሽ እንደተጓዙም አይነ-ስውር የመሰለው ሌባ ከፊቱ ያለውን ገበሬ "ቆይ እስቲ አንዴ ቆም በል! ቅድም እጄ ላይ አሥረኸው የነበረው ፍዬል ሲጎትተኝ ይታወቀኝ ነበር። አሁን ግን ቀለለኝሳ? አንዴ አይልኝ" ብሎ ይለዋል። ባለ ፍዬሉም እንዳተባለው ዞር ብሎ ወደኋላው ቢመለከት እውነትም ያስከተለውን ፍዬል ያጣዋል። "እንዴ! ፍዬሉ ወዴት ቀረ? በጠሰ እንዴ?" ብሎ ቢጠይቅ ሌባው "ቅድም እዚያ ታች ሲታገለኝ ነበር ይለዋል። ገበሬውም ደንግጦ ማሩን እንደተሸከመ ወደኋላ ሊመለስ ሲል እኔ እንግዲህ እዚህ ቁጭ ብዬ ልጠብቅህ ማሩንም ተሸክመኽ ከምትደክም አጠገቤ አስቀምጠህ አይነ-ስውር ነኝ ወዴት እሄዳለሁ ብለህ? ይልቅስ እርቆ ሳይጠፋ ቶሎ ፈልገው ይለዋል። ገበሬውም እውነት መስሎት ማሩን ጥሎ ፍዬሉን ፍለጋ ሲሄድ አይነ-ስውር የመሰለው ሌባ ብድግ ብሎ ማሩን ተሸክሞ ይጠፋል። ሰውዬው ፍዬሉን ፈልጎ፣ ፈልጎ አጥቶ ሲመለስ መንገድ ላይ ትቶት የሄደውን ማርም ሆነ አይነ-ስውሩን ያጣቸዋል። በሁኔታውም እጅግ አዝኖና ተበሳጭቶ ባዶ እጁን ወደ ቤቱ ይመለሳል። ሌቦቹ ግን በዚህ ሳያበቁ እንደለመዱት ሌላ ሀገር ሄደው ዛፍ ላይ ከተሰቀለ ቀፎ ማር ሲሰርቁ ባለቤቱ በመድረሱ ከዛፉ ላይ በፍጥነት ወርደው ለማምለጥ ሲጣደፉ ከዛፉ ወድቀው ሞቱ ይባላል።

ኤዔሪ 53- ሁለቱ ወንድማማቾች

በድሮ ጊዜ ሁለት ወንድ ልጆች የነበሩት አንድ ሰው ነበር። ታናሽየው ሀብታም ሲሆን ታላቅየው ደሀ ነበር። አንድ ወቅት ታላቅየው ታመመና ታናሽ ወንድሙን ጠርቶ "አንድ ዶሮ ስጠኝ" ብሎ ለመነው። ታናሹም "ሂድና ሚስቴን ጠይቃት፣ እኔ ስለምነግራት ትሰጥሀለች" ይለውና በጎን ወደ ሚስቱ ሄደ "ታላቁ በኋላ መጥቶ ዶሮ ቢጠይቅሽ እንዳትሰጪው" ብሏት ወጥቶ ይሄዳል። ታላቅየውም እንደተባለው ወደ ባለፀጋው ታናሽ ወንድሙ ሚስት ሄዶ ዶሮውን ቢጠይቃት ሚስትየው "እሱኮ ለእኔ የነገረኝ

ወንድሜ መጥቶ ዶሮ ቢጠይቅሽ እንዳትሰጪው ብሎ ነው ያለኝ" ትለዋለች። በሁኔታው የተናደደው የባለፀጋው ታላቅ ወንድም ወደቤቱ ይመለስና "ወንድሜን ባለፀጋ አድርጎ ፈጥሮ እኔን ደሀ ያደረገኝን እግዚአብሔር መግደል አለብኝ" ብሎ ይወስንና ከቤቱ ጦር ይዞ ይወጣል። በመንገድ ላይም እግዚአብሔር በለው ተመስሎ ያገኘውና "አንተ ሰውዬ ወዴት ነው የምትሄደው?" ብሎ ይጠይቀዋል። መንገደኛውም "እኔን ደሀ አድርጎ የፈጠረኝን እግዜር ልገለው እየሄድኩ ነው" ብሎ ይመልሳል። ሰውየውም "እግዚአብሔርን ለምንድነው የምትገለው?" ብሎ ደግሞ ይጠይቃል። ደሀው መንገደኛ "እኔን ደሀ አድርጎ ፈጥሮ ታናሼን ለምን ሀብታም አደረገ? እና ለዚህ ነው ልገድለው ያሰብኩት" ብሎ ይመልሳል። ሰውየውም "አሃ ለዚህ ነው" ብሎ መንገዱን ይቀጥላል። ደሀው ሰው አሁንም የተንዘ እያለ እግዜር እንደገና በሌላ ሰው ተመስሎ አሁንም ከመንገድ ላይ ያገኘዋል። እናም መንገደኛውን "አንተ ሰውዬ ወዴት እየሄድክ ነው?" ብሎ ይጠይቀዋል። ደሀው መንገደኛ ዳግም እግዜር እሱን ደሀ ታናሽ ወንድሙን ሀብታም አድርጎ ስለፈጠረ ልገድለው እየሄደ መሆኑን ይናገራል። ነገር ግን እግዜር አራሱን እያናገረው መሆኑን አያውቅም ነበር።

እግዚአብሔርም በሁለተኛው ዙር ሰውዬውን እንዲህ ይለዋል "አሃ በዚህ ምክንያት እግዜርን ልትገድል እየሄድክ ነው?" ይለውና መልሶ "በል አሁን በምትሄድበት አቅጣጫ ይህን ከፊትህ ያለውን ተራራ እንዳለፍክ ከተራራው ጀርባ ዛፍ ላይ ቁጭ ያለ አሞራ ታገኛለህ፤ እዛም ስትደርስ አሞራው ከሚጮህበት ዛፍ ሥር ሁለት ሳጥኖች ታገኛለህ" ብሎት ይሄዳል። ደሀው መንገደኛ መንገዱን ይዞ ሲንዝ ከተራራው ጀርባ ላይ "ቁር! ቁር! ቁር!" እያለ የሚጮህ አሞራ ይመለከታል። ከዚያም "አሃ ቅድም የተባልኩበት ቦታ ደረስኩ "ይልና ከዛፉ ሥር የተነገረውን ሁለት የተቆለፉ ሳጥኖች ያገኛል። ጥላ ቦታ ፈልጎ ተቀመጠና ሁለቱን ሳጥኖች ሲያነሳ አንደኛው እጅግ በጣም ይከብደዋል፤ አንደኛው ሳጥን ግን ቀላል ነበር። በጣም የከበደውን ሳጥን ከፍቶ ቢመለከት በሣጥኑ መሉ ብር ነበር። ሌላኛው ቀለል የሚለውን ቢከፍት በምድር ላይ ያሉ አራዊቶች፣ አእዋፍ፣ አናብስት፣.... ወዘተ የዱር አራዊቶች እየሮጡ እየሮጡ ወጡ። ልክ በዚያው ቅጽበት ደግሞ በምድር ያሉ አራዊቶችን ቋንቋ በመሉ ቻለ።

ከቦታውም ተነስቶ ብሩን ይዞ በመሄድ ፍዬልና ከብት በብዛት በመግዛት ልክ እንደወንድምየው በጣም ባለፀጋ ሆነ። አንድ ቀን መንገድ ለመሄድ ልብሱን ለባብሶ ሲወጣ ሚስቱ ተመለከተችና አብዝታ ሳቀችበት። ባልዋም ዞር ብሎ ሚስቱን እየተመለከታት "ምነው በእኔ ነው ወይ የምትስቂው? ምን የሚያስቅ ነገር አገኘሽ?" ይላታል። ቀጥሎም "አንቺ እኔ ላይ እየሳቅሽ ከምትኖሪ እኔ ራሴን አጠፋለሁ! በዚች ምድር ላይ አልኖርም" ይላል። ራሱን ለማጥፋት ሲልም በሬ አርዶ ድግስ ደግሶ ጎረቤቶችን ሁሉ ይጠራል። ቤቱ የሚያሳድገው አንድ ውሻ ለድግሱ ከታረደው በሬ የተራረፈውን ሲመገብ የተመለከተ የጎረቤት የሆነ ሌላ ውሻ ይመጣል። ይህን ጊዜ የቤቱ ውሻ የጎረቤቱን ውሻ "የኔ ጌታ ዛሬ ራሱን ሊያጠፋ ነው ይህን የደገሰው፤ እናም እኔ ከዚህ በኋላ ሥጋ አላገኝም። አንተ ግን ጌታ ስላለህ ነገም ከነገወዲያም ሥጋ ታገኛለህና የኔን ሥጋ አትቀራመት" ብሎ ይለዋል። የጎረቤቱም ውሻ "ለምንድነው ጌታ ራሱን

የሚያጠፋው?" ብሎ ቢጠይቀው የቤቱ ውሻም በሚስቱ ምክንያት እንደሆነ ይነግረዋል። የጎረቤቱ ውሻ "ታዲያ ራሱን ከሚያጠፋ ለምን ሚስቱን አያባርርም?" ብሎ ይጠይቃል። የቤቱ ባለቤትም በምድር ላይ ያሉ እንሳስትን ቋንቋ ሁሉ እንዲሰማ የታደለ ነበርና የሁለቱን ውሾች ምልልስ በደንብ ያዳምጥ ነበር። እናም የጎረቤቱን ውሻ ንግግር ሲሰማ "አሃ! ለካስ መፍታትም አለ!" ብሎ ከራሱ ጋር ሲነጋገር ሰንቱ ደርሶ ነበርና ለድግሱ የተጠሩ እንግዶች ሙሉ በሙሉ ስለመጡ ሀሳቡን ይቀይርና ራሱን ለማጥፋት ያዘጋጀውን ድግስ ቀይሮ "ዛሬ የጠራኋችሁ ከሚስቴ ጋር ልለያይ በመሆኑ ነው" በማለት ይነግራቸዋል። ድግሶ እንደተናቀቀም ከሀብቱ ግማሽ በግማሽ ለሚስቱ አካፍሎ ሚስቱን በህዝብ ፊት ፈታት። እናም የውሻን ቋንቋን በመስማቱ እራሱን ከሞት አድኖ ሚስቱን ብቻ ፈታ። በመሆኑም ድሮ አባቶቻችን ጋብቻ ሲፈርስ ባልና ሚስት ንብረት የሚካፈሉት ከዚያን ጊዜ የተጀመረ እንደሆነ ይናገራሉ።

ኤፄሪ 54- ጥበበኛው ባል

ሌሰኛ ሚስት የነበረችው አንድ ሰው ነበረ ይባላል። ይህ ሰው ብዙ ጓደኞች ያሉት ሲሆን ሚስቱ ከሰ እየተደበቀች ከነዚህ ጓደኞቹ ጋር እንደምትውል ብዙን ጊዜ ይሰማ ነበር። በዚህ ሁኔታዋ የተበሳጨው ባል ይህን ባህሪዋን ትተዋለች ብሎ ብዙ ነገሮችን ቢሞክርም ልትተው አልቻለችም። ለሷ ብሎ ደግሞ ከሚወዳቸው ጓደኞቹ መጣላትን አልፈለገም። ስለዚህ ሚስቱን ይዞ ራቅ ወዳለ ሀገር ሄዶ መኖር እንዳለበት ይወስናል። እናም ወደ ቤቱ ሄዶ ሚስቱን "ተነሽ እቃችንን ሰብስቢና ወደ ሌላ ሀገር እኔዳለን" ይላታል። ሚስቱ ግራ ተጋብታ "ለምንድነው የምንሄደው?" ብላ ብትጠይቅ "ተነሽ ካልኩሽ ተነሽ ነው፣ በቃ ሌላ ሀገር ሄደን መኖር አለብን።" ይላትና እሷም እቃቸውን ይዛ ጉዞ ይጀምራሉ። ብዙ ከተጓዙ በኋላ አንድ ሌላ ሀገር ይደርሳሉ። እቃቸውን አንድ ቦታ አራግፈው ኑሮ ይጀምራሉ። እየኖሩ ሳለ የሚስቱ አመል /ፀባይ/ ያማረረው ባል ለሚስቱ እንዲህ ይላል "ስማ አንቺ! እዚህ ሀገር ያሉ ወንዶች ብልታቸው ሁለት ነው። እና ተጠንቀቂ!" ይላታል። ከዚያም ወደ ውጭ ወጥቶ ሰዎች ተሰብስበው ጠጅ የሚጠጡበት ቤት ገብቶ ለብቻው ቁጭ ይላል። ውስጥ የነበሩ ሰዎች "ማነህ አንተ? ከየት ሀገር ነው የመጣኸው? ለምንስ መጣህ?" እያሉ ሲጠይቁት እሱም "እኔ ከሩቅ ሀገር ነው የመጣሁት፣ የመጣሁበትም ምክንያት ባለቤቴ በአከባቢያችን ያሉ ብዙ ወንዶችን ብልት እየቆረጠች ስላስቸገረች በዚህ ምክንያት ሰዎች አባረውን ከሀገራችን አስወጥተውን ነው። ብሎ መልስ ይሰጥና ከጠጅ ቤቱ ወጥቶ ይሄዳል። ይህን የሰሙ ሰዎችም በውስጣቸው ይዘው ቀስ እያሉ ሴትየዋን ይግባቧታል። በዚህ መሐከል አንድ ሰውዬ ባሏ ያወራው ነገር እውነት መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይፈልጋል። እናም ቀስ ብሎ ሴትየዋን ከተግባባ በኋላ ይዟት ይተኛል። ይህን ጊዜ ሴትየዋ ባሏ ገና እዚህ ሀገር ስትገባ የነገራት ነገር እውነት ይሁን ውሸት ለማረጋገጥ ስለፈለገች ግንኙነት እያደረገ እያለ መሐል ላይ ሁለተኛው ብልት የቱጋ እንዳለ ለማረጋገጥ ቀስ ብላ እጇን ሰዳ ስትዳብስ ጊዜ መጀመሪያ በልቡ ጥርጣሬ የነበረው ሰውዬም "እኔም መቆረጤ ነው!" በሚል በድንጋጤ ዘሎ ከላይዋ ይነሳና ልብሱን ይዞ ይሮጣል። ከዚያም "የሴትየዋ ባል ያወራው ታሪክ እውነት ነው" ብሎ ለሌሎች ሰዎች በመናገሩና ወሬውም ለብዙ ሰው በመዳረሱ

ከዚያም ቀን ጀምሮ ሴትየዋን ፈልጎ የሚቀርብ ወንድ ጠፋ። ባሏም በፈጠረው ዘዴ ከሀሳብ ተገላግሎ መኖር ጀመረ ይባላል።

ኤዤሪ 55- ባለ ውሸማዋ ሚስት

አንድ ወቅት አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ተጋብተው ይኖሩ ነበር። አብረው ሲኖሩ አንድ ልጅ ይወልዳሉ። ሴትዬዋ ግን በጎን ውሸማ ትይዛለች። አንድ ቀን እቤቷ ውስጥ ጉድጓድ ትቆፍራለች፣ በእንስራም ንፍሮ ትጥዳለች። ንፍሮውም ሲበስል ከነእንስራው ጉድጓድ ውስጥ ትጨምረውና በላዩ ላይ ቆዳ ታነጥፋለች። ልጇንም እዚያ ቆዳ ላይ ታስተኛዋለች። ከዚያም ባልዋ መጥቶ ሾፎሮ ሊጠጣ ከልጁ አጠገብ ቁጭ ይላል። በእንሥራ የተቀቀለው ንፍሮ ከጉድጓዱ ውስጥ "ቦቅ! ቦቅ! ቦቅ!" ሲል ይሰማ ነበርና ለባልዋ "አንተ ሰውዬ የልጃችን ሆድ ሲጮኽ ትሰማለህ?" ትለዋለች። ባልዬውም "ታዲያ ይሄ ምን ነገር ነው? እስቲ ጫማ ጣይ ቤት ሂጂ" አላት ሚስትየውም "በቃ! እስቲ እኔ እሄዳለው" ብላ ሄዳ ጫማ አስጥላ መጣች። ለባልዋም "እቤት ውስጥ ያለችው ትልቋ መሲና ላም ናት ልጁን ያሳመመችው። ኩላሊቷም አንድ ስለሆነ ትታረድ ብሎ ጫማው ተናግሯል" ብላ ትነግረዋለች። ባልዬውም "እሺ ልጄ ከሚሞት እኔ ላሚቷን አርዳለሁ" አላተና ላሚቷን አረዳት። ቆዳዋን ገፈፈ፣ ሆድቃዋን እያወጣ እያለ ሚስትዬው ተደብቃ ወደ ጥጃዎች ቤት ትገባና ጥጆችን ትለቃለች። የተለቀቁት ጥጆችም ወደ እናቶቻቸው ሥር እሮጠው ሲገቡ ሴትዬዋ በጎን ወደ ባልዋ ትሄድና "እንዴ! በሽተኛው ልጄ ምን ሊጠጣ ነው? ጥጆች ሁሉ እየጠቡ ነው። ሩጥና ሄደህ ጥጆችን መልስ!" ትለዋለች። ባልየውም እውነት መስሎት ወደ ጥጆቹ ሩጦ ሲሄድ እሷ በጎን ሄዳ የታረደችውን ላም አንድ ኩላሊት አውጥታ ወደ ጫካ ትጥላለች። ከዚያም ባልዋ ሲመለስ "እስቲ ቶሎ ቶሎ በልና ኩላሊቷን አውጥተን እንይ" ትለዋለች። ባልየውም የላሚቷን ኩላሊት ሲፈትሽ እውነትም አንድ ሆኖ ብቻ ያገኘዋል። ይህን ጊዜ "ወይ ጉድ! እቺ ላም ባትታረድ ኖሮ ይህን ጊዜ ልጄ ሞቶ ነበር አይደል?" ብሎ አለ። ሴትየዋም የፈለገችው ተሳክቶላት ጥሩ ጥሩ የሆነውን ሥጋ ለውሸማዋ አብልታ ጨረሰች ይባላል። ለውሸማዋም ስትል የማይሆን ነገር አደረገች ይባላል።

ኤዤሪ 56- የአንድ በግና ፈረስ ታሪክ

በግና ፈረስ አንድ ቀን ሰርዶ ለመጋጥ አብረዉ ወደ መስክ ሄዱ። ከቦታዉ እንደደረሱም ዝቅ ብለው መጋጥ ጀመሩ። በግዋ ቶሎ ጠገብች ፈረሱ ግን ጭራሽ አልጠገበም ነበር። በግዋ ፈጥና መንገድ ላይ ወጥታ ፈረሱን ከፍ ባለ ድምፅ መጥራት ጀመረች። ፈረሱ ግን ሰርዶዉን ዝም ብሎ ይግጥ ነበር። ስሙንም እየጠራች መወትወቷን ቀጠለች። ፈረሱም "ትንሽ ቆይኝ! እቺን ሰብስቤ ልጨርስ" አላት። ትንሽ ቆይታም ደግማ ተጣራች። "ቆይኝ የሰበሰብኩትን ልጉረስ "እያላት ሳይጨርስ የጅብ ጨኽት ሰሙ።

በግዋም ቀድማ ተዘጋጅታ ስለነበር የጅቡን ጩኽት እንደሰማች ሮጣ ወደቤቷ ሄደች። ፈረሱ ግን የሆዱ ነገር አላስችል ብሎት እዝያዉ እየጋጠ ነበር። ጅቡ አጠገቡ ደርሶ ኖሮ "ማንን ነዉ እዚህ የማየዉ?" ብሎ ጠየቀ። ፈረሱም "እኔ ነኝ ጌታዬ!" ብሎ መለሰ። "እባክህ እርቦኛል ምን ላድርግ?" ብሎ ጠየቀዉ ጅቡ። ፈረሱም "አብረን ሳር እንጋጥ" አለዉ። ጅቡም ተቆጥቶ "እኔ ሳር ስግጥ የት አየኸኝ! ይልቅ ትንሽ ርሃቤን ማስታገሻ እንዲሆነኝ አፍንጫህን ልንከስ።" አለዉ። ፈረሱም ስለፈራ "ሳታሳምመኝና ሳታበዛ ንከሰኝ" ብሎ ፈቀደለት።

ጅቡም ተቻኩሎ መሉ የፈረሱን ፊት መቦጨቅ ጀመረ። ፈረሱም በሁኔታዉ ተደናግጦ እየጮኸና እየተደናበረ ሮጠ። ጅቡም "ቆይ! ቆይ! ተረጋጋ መድኃኒቱ ከእኔ ዘንድ ስላለ ነዉ ፊትህን የቦጨኩት። ይልቅስ ተመለስና መድኃኒቱን ልጨምርልህ።" አለዉ። በጅቡ ንግግር የተታለለዉ ፈረስ እዉነት መስሎት ሲመለስ መሉ ለመሉ በልቶት ጨረሰዉ።

ኤዜሪ 57- የአንድ ኃይለኛ አንበሳ ታሪክ

በድሮ ጊዜ አንድ አንበሳ አውሬዎች ሁሉ በሚመላለሱበት መንገድ ላይ ተኝቶ አውሬዎችን ይጠብቅ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን በዚሁ መንገድ ላይ አንድ ጅብ ይመጣል። አንበሳውም ቆጣ ብሎ "አንተ ጅብ! ከየት ነው ምትመጣው?" ብሎ ይጠይቀዋል። ጅቡም በጣም እየፈራ "የሚበላ ነገር ስፈልግ ውዬ አጥቼ ደክሞኝ ወደ ቤት እየተመለስኩ ነው" አለ። አንበሳው "ስማ! ያንተ ባላባት ማን ነው?" ብሎ ጠየቀው። ጅቡም "እንዴ ጌታዬ! ካንተ በላይ ባላባት ወይም ንጉስ አላውቅም። እኔ የማውቀው አንተን ብቻ ነው።" ብሎ ይመልሳል። አንበሳውም "በል ሂድ! ከፊቴ ጥፋ!" ብሎ ያባርረዋል። አንበሳው እዚያው እያለ አንዲት አህያና አንድ በሬ በዚያው መንገድ ይመጣሉ። እንደደረሱም አንበሳው ብድግ ብሎ "አንቺ አህያ! አንቺና ይህ በሬ ወዴት ነው የምትሄዱት? የናንተስ ንጉስ ማን ነው?" ብሎ ይጠይቃቸዋል። በሬውም "ከአንተ በላይ እኛ ሌላ ንጉስ እንዳለ አናውቅም። አንተ ብቻ ነህ" ይለዋል። ከዚያም አንበሳው "በሉ ቶሎ ከአይኔ ጥፉ" ብሎ ያባርራቸዋል። እነሱም እንደ ሄዱ አንሳው ·እዚያው እያለ በዚያው መንገድ አንድ ዝሆን ትመጣለች። አንበሳውም "አንቺ ዝሆን ከየት ነው የምትመጭው? ደግሞስ ያንቺ ንጉስ ማን ነው?" ብሎ ይጠይቃል። ዝሆኗም ቀረብ ብላ "ከየት ነው የምትመጭው ብሎ ለመጠየቅ አንተ ማን ነህ?" ብላ በኩምቢዋ ሰብስብ አድርጋ ወደ ላይ ታነሳውና ወደ መሬት ትጥለዋለች። ቀጥላም አንድ እግሯን ብድግ አድርጋ ጀርባው ላይ ታስቀምጣለች። ይህን ጊዜ አንበሳው እየተንቀጠቀጠ ልመና ይጀምራል "እባክሽ አትግደይኝ? እባክሽ! እባክሽ!" እያለ ሲለምን ዝሆኗ "ሁለተኛ እንዲህ አይነት ነገር ታሳይና?" ብላ ጥላው ትሄዳለች። በዚህን ጊዜ አንበሳው "አሃ! ለካስ ለጌታም ጌታ አለው?" ብሎ ሁል ጊዜ በድፍረት ይተኛበት የነበረውን መንገድ ጥሎ ሌላ ቦታ ሄደ ይባላል።

ኤፄሪ 58- የዝንጆሮ ጭፈራ

አንድ ሰው ዝንጆሮ አገር እርሻ አረሰ። ሰውዬው ማሳውን ዝንጆሮ እንዳይበላ አንድ ዋሺ የሚባል ውሻ አሳደገ። እንደገናም አንድ ቀስት ገዛ። ከዚያ በኋላ በደንብ አርሶ ስለነበር ማሳው ውስጥ ብዙ እህልም በሰለ። እህሉ እንደበሰለም ዝንጆሮዎች መጡበት። ዝንጆሮዎችንም በቀስት መታቸው። አስር ዝንጆሮዎችንም ገደለ። እነሱን ሲገድል ያዩት የቀሩት ተመልሰው ሄዱ። በሌላ ቀን የቀሩት ዝንጆሮዎች እህሉን ሊበሉ መጡ። እንደገናም ሰውዬው ዋሼ የሚባለውን ውሻውን ላከባቸው። ዋሼም ሂዶ ሀያ ዝንጆሮዎችን ገደለ።

ይህን ጊዜ የቀሩት ዝንጆሮዎች ለክስ አያታቸው ጋር ዳገት ላይ ወዳለ ዋሻ ሄዱ። ሄደውም ከሰሱ። ከዚያ ሁለት መንደር ዝንጆሮዎች ተላኩ። ያንደኛው መንደር ዝንጆሮዎች ስም "ጴሪፔን" ሲሆን የሌላኛው መንደር ደግሞ "ውሽሎን" ይባሉ ነበር። ዝንጆሮዎቹ ወደ እርሻው ሂደው ሊበሉ አጥሩ ጋር ሲደርሱ ሃይለኛ ዝናብ ዘነበ። ዝናቡ ሲዘንብም ሰውዬው፣ ውሻውና ቀስቱ እቤት ውስጥ ነበሩ። ዝንጆሮዎቹም እህሉን በልተው እንደጨረሱ ከማሳው ወጥተው ጉቶ ላይ በመሆን፡-

"ያንተ ውሻ ዋሼ በዝናቡ ወዴት ገብቶ ነበር፣ ያንተ ቀስት በዝናቡ ወዴት ገብተው ነበር፣ የገደልካቸው ያኚ ዝንጆሮዎች እህልህን በልተው ወደ ጫካ ገቡ።" እያሉ መዝፈን ጀመሩ ይባላል።

ኤፄሪ 59- ተንኮለኛው አማች

በድሮ ጊዜ ባሏ ትታት አማቿ ጋር የምትኖር ሴት ነበረች። አንድ ቀን የአማቿ ጥጆች ይሞታሉ። ይህን ጊዜ አማችየው እሷ እንድትበላ ሥጋውን ይዞላት ይመጣል። እሷም በጥጆቹ መሞት ማጽናናት ሲገባት ደስ ብሏት "ጎሽ የኔ ልጅ! አሁንም ለኔ ይዘህ ና እሺ?" አለችው። አማችየውም "እሺ! ነገ ይገፍልሽ እመጣለሁ" አላት። ከዝያም በንጋታው አርጃኖ ከነነፍሱ ይዞ በጨርቅ ጠቅልሎ ሥጋ አስመሰሎ ይዞላት መጣ። እሷም "የኔ ልጅ መጣህ እንዴ? እኔ ላነተ ሾፍሮ አፍልቻለውና ወደቤት ግባ" አለችው። አማችየውም "ይኸው እናቴ! ይገፍልሽ መጥቻለው" አላት። ከዚያም "እቺ ሞታ ያመጣውልሽ ላሜ ጋር ናት። (ጋር ማለት አንድ በና ከብት ሲዘል ደንብ የሚሰራበት ሴት ጊደር መጠርያ ነው) ስለሆነም ለእኔ ነውር ናትና አልበላትም፤ እኔ ሾፍሮውን ጠጥቼ ከሄድኩ በኋላ አንቺ ፍቻትና ብይ። አሁን ግን ሻራ /ቆጥ/ ላይ አስቀምጭ" ብሎ ሰጣትና "ከመፍታትሽ በፊት ግን በሩን በደንብ መዝጋትሽን አረጋግጪ" አላት። ከዚያም ሾፍሮውን ጠጥቶ ወጥቶ የሄደ መስሎ ከጓሮ ተደበቀ። ወዲያውም እሱ እንደወጣ የሄደ መስሏት እየተጣደፈች በራፉን ዘጋች። እሱ ተደብቆ ይመለከታት ነበር። በሩን እንደዘጋችም የተሰጣትን መፍታት ጀመረች፣ ከዚያም አርጃኖው በህይወት ነበረና እሷን መቧጨር ጀመረ። ይህን ጊዜ "ወይኔ! የኔ ልጅ! ይህች ያንተ ምን አይነት ጋር ናት?" ብላ አለች ይባላል።

ኤዔሪ 60- የሴት ትንሽ የለውም

በልጅነታ ለባል የተሰጠች አንዲት ልጅ ነበረች። በባህሉ መሰረትም ልጅቱ የባሏ አባት ቤት ሄዳ ማደግ ስላለባት አባታ "ልጄ እኔ አንቺን ለባል ሰጥቼሻለሁና ሂጂ" ብሎ ወደ ባሏ አባት ቤት ይልካታል። ልጅታም የባሏ አባት ለእሷ አያት እንደሆነ ተደርጎ በባህሉ መሠረት ይታሰባልና ከአያታ ጋር መኖር ትጀምራለች። ሁለት ወር ያህል እንደቆየችም ባሏ ቤት መግባት ፈልጋ አያታን "ባሌ ቤት ልሂድ?" ብላ ትጠይቀዋለች። የባሏ አባትም አይሆንም ይሏታል። ይህን ጊዜ ልጅት ከአያታ መኝታ ራስጌ ላይ አሯን ታራለች። አያታ ከስራ ተመልሶ ቤቱ ገብቶ ቁጭ እንዳለ ቤቱ ይሸተውና "ምንድነው የሚሸተኝ?" ብሎ ይጠይቃታል። ልጅቱም አሯን እንዳራችና ግን ትንሽ እንደሆነች ትናገራለች። ይህንን ሲሰማ የልጁ አባት "እንዴ የእር ትንሽ አለው እንዴ?" ብሎ ቢጠይቅ ልጅቱም መልሳ "አሃ! የሴትስ ትንሽ አለው እንዴ?" በማለት ጥያቄውን በጥያቄ ብትመልስ አባትዬው ነገሩ ገብቶት ልጅታን ወደ ባሏ ቤት ሸኛት ይባላል።

ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የኔ ስራ መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም ንዋይ ጌታሁን ውድነህ

ፊርማ _____

የማስረከቢያ ቀን 7-1-05